ከበአሉ ግርማ

# ከአድማስ ባሻገር

# ክፍል አንድ

## ፩

ቤቱን የዝምታ አዘቅት ውጦታል ። ከዚያ ዝምታ በዝምታ የሚመነጨው የሙዚቃ ቃና መጨረሻ የለውም ። ነፍስን በሀሴት ሊያወራጭ አእምሮን ኮርኩሮ ሀሳብን በስልት ሊያስደንስ ይችላል ።

አበራ ወርቁ፣ በዚያ መጨረሻ በሌለው ዝምታ ተውጦ ሙሉ የሌሊት ልብሱን ለብሶ እንደልማዱ የጣት ጥፍሩን በጥርሱ እየከረከመ ወዲህና ወዲያ በመንጐራደድ ለገላው ያሞቀው ውሀ ወደ ገንዳው እስኪወርድለት ድረስ የወት ሮው ባልሆነ ትእግስት ይጠባበቃል ።

ቧንቧው እንፋሎት ብቻ ስለሚተፋ ወደገንዳው የሚ ወርደው ውሀ ዝናብ ዘንቦ ካባራ በኋላ ከሰንበሌጥ ላይ ኮለል ኮለል እያለ እንደሚወርድ ጠፈጠፍ ስልት እየጠበቀ አንድ ሁንድ ይንጠባጠባል ።

«ትኩስ የህይወት ጠብታ፣ ትኩስ፤ ወፍራም የህይወት ጡብታ» የሚል ሀሳብ ላንዳፍታ አእምሮው ውስጥ እንደ

መብረቅ ብልጭ ብሎ መልስ ድርግም አለ ። የአበራ አእምሮ ካንድ ሀሳብ ወደሌላ ሀሳብ ስለሚጋልብ አንድ ነገር በተለይ ወስዶ እስከ መጨረሻው ድረስ ሊያስብበት አይችልም ፤ ለዚህ ነበር ባለቅኔ ፤ ወይም ደራሲ ፤ ወይም ሰአሊ የመሆን ተስፋውን ውስጡ ቀብሮ ያስቀረው ። ነፍሱ ግን ራቧን ባንድ ነገር ለመግለጥ ዘለአለም እንደዋተተች ፤ እንደቃተተች ትኖራለች ። አእምሮው ወዲያና ወዲህ እንደሚባክን ስለሚያውቅ አዘውትሮ ፤ «ሀሳብ መጨረሻ የለውም ፤ ቁም ነገሩ መኖር ነው ፤ የኑሮን ጣእም ማወቅ ፤ ሀሳብ የፈጠረው ግብ ካልደረሰ ውጤቱ ያው ነው ፤ ምሬትና ብስጭት ። እምን ፤ ሌላ ምናለና!» ይላል ።

አንድ ትልቅ ወፍራም ጥቁር ዝንብ ከየት መጣ ሳይባል እንግዳ ቤት ገብቶ ጥዝዝ — እያለ እንዴ ከኮርኒሱ ጋር ፤ አብዛኛውን ጊዜ ከመስኮቱ መስተዋት ጋር ፤ እንዳንዴ ደግሞ ከተንጠለጠሉት ባለአራት ጡት መብራቶች ጋር እየተጋጨ ከፍሉን ውጦት የነበረውን ከባድ ዝምታ ባንዳፍታ አደፈረሰው ። የዝምታው ሙዚቃ ስልቱን አጣ ። አበራ መንጉራደዱን ትቶ ዝንቡን ለመግደል ይሯሯጥ ጀመር ። የጢት ካቦርቱን አውልቆ ፤ ዝንቡ መስኮትና ኮርኒሱ ላይ ሲያርፍ ለመግደል አንድ ሁለት ጊዜ ከሞከረ በኋላ ጥዝዝ … እያለ ሂዶ መብራቱ ላይ በማረፉ የሚያደርገው ነገር ጠፍቶት ወደላይ እንጋጦ ለጥቂት ጊዜ ተመለከተውና ተስፋ እንደመቁረጥ ብሎ ራሱን ነቀነቀ ። «እህ !» አለና ሂዶ መስኮቱን ከፍቶ ይጠብቀው ጀመር ። እሱም እንዳሰበው ፤ ዝንቡም በበኩሉ ይጠብቅ የነበረውን መውጫ ቀዳዳ

ያገኘ ይመስል ጥግዝዝ ... እያለ ሹልክ ብሎ ወጣ ። ከውጭ የሚመጣው ሁካታ ተወርውሮ ጆሮውን መታው ። የመኪና ጋጋታ ፣ ጡሩምባ ፣ የበጎች ጩኸትና የሰዎች ድምጽ ባንድ ነት ሲሰማ የአማኑኤል ሆስፒታል አብዶች ተሰብስበው ያቋቋሙት የሙዚቃ ጓድ ይመስል ጆሮ ይጠልዛል ። ቶሎ መስኮቱን ዘጋ ። «እኔ ግን መውጫ ቀዳዳ የለኝም !» አለ ዝንቡን አስታውሶ ።

አበራ ለጊዜው የሚኖርበት ሰፈር በየበአላቱ ቀን የበግ ገበያ ሆኖ ይውላል ። የሚኖረው በመስፍን ሀረር መንገድ ከሾላው በላይ ተስፋዬ ቀጂላ ቤት ፊትለፊት ሲሆን ፣ ይሄኛው ቤት በአምስት አመት ውስጥ ዘጠነኛ ቤቱ መሆን ነው ። ከወንድሙ ምክር መሀል አበራ ልብ ውስጥ በመጠኑ የሚገባው የቤት መስራት ጉዳይ ነው ። አበራ ወርቁ ቤት አጠገብ ወይም ፊትለፊት የሚባልበት ጊዜ ይመጣ ይሆን ? ጊዜው ሩቅ መስሎ ታየው ።

ለመጀመሪያ ጊዜ በኩራት አይን የቤቱን እቃ አንድ ባንድ ይመለከት ገባ ። ውጭ የደመቀ የጸሀይ ብርሀን ቢኖርም የዝምታው አዘቅትና ጽላሎት በስውር መንገድ ተዋህደው የእንግዳ ቤቱን ብርሀን ደብዛዛ አድርገውታል ። በብርሀን አይን የሚያሞቀው የምንጣፉና የሶፋዎቹ ደማቅ ቀይ ቀለም አሁን የረጋ ደም መስሏል ። ወርቅማ ሆነው በጥቁር ጥለት ያጌጡት የመስኮት መጋረጃዎች በብርሀን ያላቸውን ድምቀት አጥተው ፈዝዘዋል ። ከውጭ ወደ ውስጥ ሲገቡ በስተቀኝ ካለው ግድግዳ ላይ የተሰቀለው በህብረ ቀለማት ስለቀለማት የተሰራው ስእል ብርሀን በማጣቱ የቀረው ውበት ጠፍቷል ። ትኩር ብሎ ተመለከተው ። ፍዝዝ

ብሎ በተመሰጠ አእምሮ አየው ። ስእሉን ሳይሆን በስእሉ ውስጥ አልፎ የሚመለከተው ራሱን ነበር ። በከንቱ ያሳለፈውን ህይወቱን ነበር—ያሳለፈውንና ወደፊትም ቢሆን ሊያገኘው የሚችለው መስሎት የማይታየውን ህይወት ፣ «ማን ነኝ ? ምንስ ነኝ ? እቃ ። ለዚያውም ዋጋ የሌለው የበሰበሰ እቃ ። እቃ ሆኜ እንድቀር ያደረገኝ ማነው ፤ እኔው ራሴ ? ወይስ ያፈራኝ ህብረተ ሰብ ? ወይስ አልፈው የመጣሁት የትምህርት አቋም ? የምን የትምህርት አቋም ፤ የአቋሙ አላማስ ምን ይሆን ? ሳይ ሳዩን የሸምጥ ለማስጋለብ ፤ ለምን አላማ ! የትምህርት አላማው እያንዳንዱ ሰው ራሱን ፣ ማንነቱን ፣ የተፈጥሮ ችሎታውን እንዲያውቅ ማድረግ ነበር ። እኔ ግን ማንነኝ ?» እያለ ፤ አይኖቹን ስእሉ ላይ ተክሎ ሲያስብ ፍዝዝ ብሎ ቀርቶ ነበር ። ደንዝዞ ነበር ።

በስተግራ ያለው ግድግዳ ጽላሎቱን እሳርፎበት ተንጣሎ የሚታየው ራዲዮ ግራም የሬሳ ሳጥን መሰለ ። ሱዛን ሮስ የተባለችው የሰላም ጓድ ልኡካን ባልደረባ ህይወቱ ውስጥ በድንገት ለጥቂት ወራት ባትገባ ኖሮ አበራ ይህን ራዲዮ ግራም ለመግዛት ሀሳብ አልነበረውም ። ነገር ግን ፣ ከገዛ ላይቀር የሚገዛው ነገር ሁሉ ከባድና ዋጋ ያለው መሆን አለበት ። «የምቀጥ[illegible]ው ለነገ የሚሆነኝ መሆኑን ወይም አለመሆኑን በርግጥ ስለማላውቅ ለምን ርካሽ ነገር እገዛለሁ ? በርግጥ የማውቀው ዛሬን ብቻ ነው ፣» በማለት ሁል ጊዜ ውድ እቃዎችን ይገዛል ። ቤቱ ርካሽ እቃ አይገኝም ።

ሱዛን ሮስ ፣ «ብልጫ ያለውን ነገር የሚመርጡ ወንዶች ደስ ይሉኛል ፣ ምክንያቱም ለውድና ለከፍተኛ ነገሮች የሚ

ጣጣሩ ወንዶች ሲያጋጥሙኝ እኔ በበራቤ ያለኝ አስተያየት ውሀ እንዳገኘ ጽጌረዳ ይለመልማል ፡» እያለች ደጋግማ ትነግረው ነበር ። ሆኖም አልጋ ውስጥ ገብታ ያለሙዚቃ መንቀሳቀስ ፈጽሞ እንደማትችል አስታወሰ ። ያለሙዚቃ ሰውነቷ አይፍታታም ። ያለሙዚቃ ፍቅር ሰጥታ ፍቅር መውሰድ ጨርሶ አይሆንላትም ። ከስንት ማግባባት በኋላ ቤቱ የወሰዳትን ወንድ አስቀድማ የምትሰጠው ምርጫ ፤ «ሙዚቃ ስጠኝና ፍቅር ልስጥህ ፡» የሚል ነበር ። ታዲያ ፤ አበራ ቤቱ ባመጣት ምሽት እንደዚያ ያለውን ምርጫ ስታቀርብለት አላመናትም ። ውርጭ ውስጥ እንዳደረ ብረት የሚቀዘቅዘውን ጭኗን እየደባበሰ ፤ ረጅም ጠጉሯ ስር ውስጥ እንደዝሆን ጥርስ የነጣውን ማጅራቷን እንደ በጥፍሩ እየቧጠጠ ፤ እንደ በጥርሱ እየነከሰ ፤ ከንፈሯን አሁንም አሁንም እየሳመ ፤ ካሁን አሁን ተሸነፈችልኝ በማለት ልቡ ድው ድው ፤ የደም ስሮቹ ትር ትር እያሉ ሲጠብቅ ከላዩዋ ላይ ገፍትራው ተነሳች ።

የታጠፈውን ቀሚሷን እያስተካከለች ፤ «ሙዚቃ ስጠኝ ነው የምልህ! » አለችው በቁጣ ቃል ፤ ሲቃ በያዘው ድምጽ ። ጉንጮቿ ላይ የነበረው ደም ቁልቁል ወረደ ። ባንዳፍታ ጸሀይ ያልነካው በሽተኛ ይመስል ገረጣች ። ከሩቅ ሲመለከቱት ነጭ ፤ ከቅርብ ሲያዩት ሽሮ የሚመስለውን ጥርሷን ታፋጭ ጀመር ።

«ስለግዜር ብለሽ አሁን ሙዚቃ ምን ያደርግልሻል ! ልባችንን እንድ ብናደርገው እኛው ራሳችን ውብ ሙዚቃ ልንፈጥር እንችላለን --- የተፈጥሮ ዳንኪራ እየረገጥን ፡» አለችው ፤ በረጅሙ ሚሶውር ነህ ፤ ለማየት አትችልም! » አለችው ፤ በረጅሙ

ተንፍሳ ። ረጅም ጠጉሯን በሁለት እጆቿ ጭምድድ አድርጋ ይዛለች ። እጆቿ ላይ ያሉት የደም ስሮች እንደሽምጥ አጥ ተገትረዋል ። እና ከቀሉት ትናንሽ ውብ አይኖቿ እንባ እየፈለቀ የገረጡትን ጉንጮቿን ያርሰው ነበር ።

«ምን! »

«ያለሙዚቃ አይሆንልኝም ፤ ፍጹም አይሆንልኝም ፤ ፍቅሬን ለወንድ አሳልፌ ከመስጠቴ በፊት ነፍሴ ወደ ሙዚቃ አለም መግባት አለባት ። ከዚያ በኋላ ነጻነት ይሰማኛል ፤ ውስጤ እንደጸጌረዳ እምቡጥ ይከፈታል ፤ ለመስጠትም ሆነ ለመቀበል ዝግጁ እሆናለሁ ። »

«እሱን ተይው ! ፍቅርሽን ለመስጠት ነፍስሽን አስቀድመሽ ለሙዚቃ መለወጥ የምትፈልጊው ለጥቂቶች ብቻ ነው ? ወይስ ከብጤዎችሽም ጋር እንዲሁ ነሽ ?»

«አበራ ፤ ለምን እንዲህ ትላለህ? ለቀለም ደንታ እንደሌለኝ እዚህ መምጣቴ ሊያረጋግጥልህ አይችልም ?»

አበራ ጊዜ አላጠፋም ። በሚቀጥለው ቀን ሄዶ ራዲዮ ገራም ገዛ። ከዚያ በኋላ ሱዛን የየሙዚቃውን ስልት በማለት፤ በስሜት እስኪተለየችው ቀን ድረስ ትጠብቅ ነበር ። ጸሀይ እንዳየች የጸጌረዳ እምቡጥ ወከክ ፤ ትርክክ ትልለት ነበር ።

ከዚው ተርከ ፤ ከሱዛን ዘንድ ትናንት የደረሰው ካርድ «መልካም ፋሲካ ፤ ስኳር ወለላዬ ፤ የትም ብሆን አብረን የሰማናቸው ጥኡም ሙዚቃዎች ትዝ ይሉኛል ። የማዝነው ችን አብረን ባናዳምጥ በጥቂት ጊዜ ውስጥ ብዙ ሙዚቃዎ ነው ። ሆኖም ቅሬታ የለኝም ፤ እያንዳንዷ ደቂቃ ትዝ ትለ

ኛለች » የሚል ነበር ። ራዲዮ ግራሙ ላይ አስቀምጦታል ። ጫሳቱ እልፍ ረመጥ ፤ ረመጡ በርዶ አመድ የሆነ ትዝታ ነው » ሲል አሰበና የቤት ካቦርታውን ትከሻው ላይ ጣል አድርጎ ወደ መታጠቢያ ቤት ሄደ ።

መታጠቢያ ቤቱን ያጥለቀለቀው እንፋሎት ያፍናል ። የፊት መስተዋቱም ፤ የመስኮት መስተዋቱም ፤ ግድግዳውን ያለበሱት ነጭ ሸክላዎችም በሙሉ በላብ ደፍቀው ወርዝ ተዋል ። ገንዳው ውስጥ የወረደው ውሀ ግን ይህን ያህል አይፋጅም ። እንደፍላጎቱ ቢሆን ውሀው መፋጀት አለ በት ። አበራ ገላውን አሽቶ ለመታጠብ ስለሚሰንፍ ገንዳው ውስጥ በጀርባው ተንጋሎ መቀቀልን ይወዳል ። በተለይ የጀርባው ነገር ጭንቁ ነው ። ጀርባውን አሽቶ የሚታጠብ በት ዘዴ ሲገባው አልቻለም ። ለሌላ ሳይሆን ለዚህ ብቻ ሚስት ቢያገኝ አይጠላም ።

የሌሊት ልብሱን አውልቆ እርቃን ስጋውን አንድ ሁለት ጊዜ ከተንጐራደደ በኋላ በእንፋሎት ወርዝቶ የቤት ጭጋግ የመሰለውን የፊት መስተዋት በፎጣው ወለወለና ላንዳፍታ ፊቱን ተመለከተ ። የቀይ ዳማ ቢሆንም ጸሀይ ያልመታው ፊቱ ገርጥቷል ። የአበራ መልክ ቁንጅና ትላ ልቅ አይኖቹ ላይ ነው ። ትርችም ያሉት ቅንድቦቹ ከኮሌ ናቸው ወጣ ወጣ ላሉት አይኖቹ ልዩ ውበት ይለግሷቸዋል ። ሽፋሎቹ በምላጭ የተስተካከሉ ይመስላሉ ። በራው በመ ጠን ገለጥ ባያደርገው ኖር የግንባሩ ግጠር ጉልቶ በታየ ነበር ። አፍንጫው ስልክክ ብሎ ወርዶ ቀዳዳዎቹ በመጠን ሰፋ ሰፋ ያሉ ናቸው ።

መቀስ አንስቶ ካፍንጫው ውስጥ እንደ ራዲዮ አንቴና ረዘም ብለው የወጡትን አንዳንድ ጠጉር ከርክሞ ሲያበቃ፣ አፉን በመክፈት ምላሱን ወደ ውስጥ ቀልሶ ፤ ተዋጊ በሬ ይመስል ያንገት ስሮቹ እስኪያብጡ ድረስ ወደታች አቀርቅሮ ፤ የታችኛዎቹ ጥርሶቹን ከውስጥ በኩል ሲጃራ ምን ያህል እንዳበለዛቸው ተመለከተ ። የዛገ ቆርቆሮ መስለዋል ። ሽንት እንዳሸተተ በግ ስስ ከንፈሮቹን ብልጥጥ አድርጎ ተመለከተ ። ጥርሶቹ እንደወተት ባይነጡም ጸአዳ ናቸው ።

ጢሙ አድጎ እንደሆነ ለማየት በሁለት እጆቹ ጉንጮቹን ከታች ወደላይ መላልሶ ደባበሰ ። ጢሙ አላደገም ፣ ጉንጮቹ እንደህጻን ልጅ ገላ ለስልሰዋል ። ብብቶቹ ውስጥና ጉያው መካከል ያለው ጠጉር ግን እንደባህታዊ ጠጉር አድጎ ተገማምዷል ። የእግሩ ጥፍሮች አድገው ገሚሶቹ ተጣጥፈው ገሚሶቹ ደግሞ ተሰባብረዋል ። ሱዛን የብብቱንና የጉያውን ጠጉርም ሆነ የእግር ጥፍሮቹን በየጊዜው ታስተካክልለት ነበር ። እርሱ ለራሱ ሊያደርግ የማይችለውን ስታደርግለት ልዩ ደስታ ይሰማት ነበር ።

«ወንዶችን ማሞላቀቅ ደስ ይለኛል ። እንዳንተ ያሉ የእግር ጥፍራቸውን መቁረጥና የብብት ጠጉራቸውን መላጨት የማይችሉ ሳገኝ ደግሞ የበለጠ ደስታ ይሰማኛል » የምትለው ሁሉ ትዝ አለውና፤ «ምንነው አሁን በተገኘች!» ብሎ በመመኘት ገንዳው ውስጥ ገብቶ በጀርባው እንደ ልማዱ ተንጋለለ ።

የገንዳው ርዝመት ለአበራ መካከለኛ ቁመት ይህን ያህል አስቸጋሪ ሆኖ አልተገኘም ። የሲጋራትን ነገር እርግፍ

አድርጎ የተወው ከሰባት አመት በፊት ካዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ እንደወጣ ቢሆንም ፣ የትከሻው ስፋት ፣ የወገቡ ቅጥነትና የዳሌው ስልክክ ማለት ከስፖርት አለም ተለይቶ የኖረ ሰው አያስመስሉትም ።

ሰውነቱን በስንፍና ለማሸት ሲሞክር ደረቱ ላይ በቀኝ በኩል ያለውን ለሀያ አምስት አመታት አብሮት የኖረውን ትልቅ ጠባሳ ነካ ። ትርንጉ ትዝ አለችው ። በነፍስ ትኖር ይሆን ፣ ሞታ ይሆን ፣ አያውቅም ። የሚያውቀው አንድ ነገር ብቻ ነው ።

እድሜዋ ከእርሱ እድሜ ገፋ ያለ ነበር ። ፊቷ እንደ ውድቅት ጨለማ ጠቁር በወዝ የተንጨፈጨፈ ነበር ። ጠጉሯ እንጉጉ ባንድ የሚቀጠር ፣ ፍርጥምጥም ያለች ጉጭማ ነበረች ። እናቱ ወይዘሮ ባፈና ሞልቶት ቡና ለመጠጣት የግል ሲኒአቸውን ይዘው መንደር ሲሄዱ ፣ ትርንጉ አበራን ትጠራውና መደብ ላይ ተጋድማ ፣ «ና እንጫወት» ትለው ነበር ።

«ምን አይነት ጨዋታ?»

«ና ምን ቸገረህ ፣ እኔ አሳይሀለሁ ።»

ታጫውተዋለች። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ከጨዋታው የሚያገኘው ደስታ እየጣመው ስለሄደ የእናቱን ከቤት መውጣት በናፍቆት ይጠባበቅ ነበር ። እንዲያውም አንዳንዴ ትርንጉ ስራ ይዛ አላጫውትህም ስትለው ምርር እያለ ያለቅስ ነበር ። በተለይ ከባይበዳኝ ጋር ስትዳራ ያየ እንደሆነ ትንሿ ልቡ እርር ፣ ድብን ትል ነበር ። ቆየት ብለው እሱን አስወጥተው በር ሲዘጉበትማ አይጣል — ትርጉሙን ለይቶ የማያውቀው

ስሜት በስራ አካላቱ እየተሰራጨ ያብከነክነው ነበር… ያብሰለስለው ነበር ።

ታዲያ አንድ ቀን ጧት እናቱ ቡና ለመጠጣት ከቤት እንደ ወጡ አበራና ትርንጎ መደብ ላይ ወጥተው ጨዋታቸውን ቀጠሉ ። ወይዘሮ ባፈና እንደ ከቤት ከወጡ በየቤቱ ቡና እክትመው ቤት እስኪመለሱ ድረስ ዋላው ቤት ስር ከትት እንደሚል ያውቃሉ ። ነገር ግን ፤ ያን ቀን ለካ ሰኔእቸውን ረስተው ሄደው ኖሮ ወዲያውን ተመልሰው መጥተው የአጥረ ግቢውን በር «ትርንጎ ፤ ትርንጎ» እያሉ ሲያንኳኩ ፤ ትርንጎ ድንግጣ እንደ ከላዬዋ ላይ ስትወረው ረው ጊዜ ሽንኩርት ለመክተፍ ያስቀመጠችው ቢላዋ ላይ ሄዶ በደረቱ ወደቀ ። ጠባሳው እብርት ይኖራል—ግቡታ ወሻ ሆኖ ። አሁን የት ትሆን ?

የትርንጎ ትዝታና የውሀው ሙቀት ሰውነቱን አሻና ንቶት ኖሮ ፍትወት አደረበት ። አበራ አንድ ስሜት ካደረበት ያንን ስሜት ሳያረካ ለመቆየት አይችልም…ከዚያ በኋላ ራሱን እየጠላ አይኖቹን ከድኖ ከሀሊናው ጋር ሲሟገት የመታጠቢያው ቤት በር ተንኳኳ ።

«ማንነው !» ሲል ጠየቀ ፤ በጕረና ድምጽ ። አድርበት የነበረው ምትሀት ከመቅጽበት አለፈ ። በፍትወት ስሜት እብጦ የነበረው ሰውነቱ ባንዳፍታ ሙሽሽ አለ ።

«ከእቁባቶችህ አንዷ መስዬህ ደንገጥክ እንዴ ?» ሲል ውጭ የቆመው ሰው መልሶ ጠየቀው ። ከፍ ዝቅም ሳይል እንድ አቅጣጫ ይዞ የሚሄድ ፤ ለአበራ ጆር እንግዳ ያልሆነ ወፍራም ድምጽ ነበር ።

«ሀይሉ ፤ አንተ ነህ ? ከእቁባቶቹ አሁን አንዷ ብትገኝ ከሰማይ እንደወረደችልኝ መና እቆጥራት ነበር ፤ ሸረ ለመሆን ትናንት ማታ ምን ጉድጓድ ውጦህ ነበር ?» ገንዳው ውስጥ ያለው ውሀ ይንቦራጨቃል ። አበራ ቶሎ ለመውጣት የተጣደፈ ይመስላል ።

«ለስውጥ ያህል ትናንት ከሸርሙጣ ጋር አላደርኩም ፤ ጠረናቸው እየሰለቸኝ ሄዷል ። ካንዷት የጣሊያን ገረድ ጋር ነበር ያደርኩት ። ይገረምሀና የፍቅር ሙያ ባለቅኔ ናት ለማለት ይቻላል ፤» አለ ሀይለማርያም ካሳ በተለመደው ግልጽ አንደበቱ ። ስለራሱ የሚደብቀው ነገር የለም ። ስለሰው ሲናገርም ፊትለፊት ነው ። ታዲያ የሚያውቁት ኢትዮጵያውያን ከሩቅ ይሸሹታል ። ሌሎች ባጋጣሚ ምክንያት የተዋወቁት ደግሞ ይህ ሰው እብድ ነው እንዴ ፤ በማለት ይዘባበቱበታል ። ከቂል የሚቆጥሩትም አሉ ። ጥቂቶች ናቸው ሀይለማርያም ግልጽ ሰው መሆኑን በማወቅ የሚያደንቁት ።

አበራ ከውስጥ ገላውን የሚታጠብበትን ውሀ እያንቦራጨቀ ፤«ብለህ ብለህ ገረድ ተራ ገባህ ?» ሲል ተሳለቀበት ።

«አጉል ሀሊያ ባይታከልበት ኖሮ አንድ ወንድ ካንዲት አመቤት ሆነ ከደንገጡር የሚያገኘው ደስታ ልዩነት ባል ኖረው ነበር ፤ የሚለውን አባባል አታውቅም ? ለማንኛውም ነገር በገንዘብ አላመጣኋትም ፤ የመጣችው ለመደሰትና ለማስደሰት ብቻ ነበር ። አልቻልኳትም ። ድካምና እንቅልፍ ተደምረው ስለተሸነፍኩ ይቅርታ እንድታደርግልኝ ለመንኳት ። እየተንሰፈሰፈች ስታለቅስ አደረች ። ጧት ስትሄድ ምን አለችኝ መሰለህ ?»

«ምን አለችህ?»

«ብስብስ የወንድ አልጫ ብላኝ ወጣች ። ሁለተኛ የምትመጣ አይመስለኝም ። ሴት አውላ ባለመሆኔ አዝናለሁ ። ሆኖም ወርቅ ነበረች ።»

«አንተን የሚያጋጥሙህ ሁሉ ወርቅ ናቸው ። ለምን ማእድን ሚኒስቴር ስራ አትጠይቅም? ብዙ ወርቅ ታስገኝላቸው ነበር ፤» በማለት አፌዘበት ። ሀይለማርያም አብሮ ያደራትን ሴት ሁሉ «ወርቅ ነበረች» እያለ ማሞገስ ያዘወትራል ። «ቃላትን የሚጠመዝዙ ሰዎች እንደሚያስጠሉኝ ነግሬህ ነበር፤ የአእምሮ መሀንነት ምልክት ነው ። እንግዳ ቤት እጠብቅሀለሁ ፤» ብሎት ሄደ ። ከላይ ከባድ ጭነት የተሸከመ ሰው ይመስል ሀይለማርያም ሲሄድ በተረከዙ መሬቱን ይምርዳል ። በዚህ የተነሳ ሙሉ ተረከዝ ያለው አንድም ጫማ የለውም ። የሚያደርጋቸው ጫማዎች ሁሉ ከኋላ ስለሚንጋደዱ ባንድ በኩል ጥርሱ የረገፈበት ሰካራም ሰው ይመስላሉ ። አበራ ሀይለማርያምን አንድ ነገር ለምኖት አልፈጽምም ብሎት ሲያስቸግረው ፤ «እንግዲህ እንደጫማህ መጣመም አትጀምር» ይለዋል ።

ሀይለማርያም ብርሀን የሌለበት ቤት ደስ ስለማይለው እንግዳ ቤት ውስጥ የነበሩትን መብራቶች ሁሉ አብርቷል ። ግድግዳው ላይ ያለው ስእልም ሆነ ምንጣፉ ፤ ሶፋዎቹና የመስኮት መጋረጃዎቹ በብርሀን አማካይነት ህያው ሆነዋል ። መብራቶቹ የእርሱንም ሁኔታ ጭምር አጉልተው ያሳያሉ ።

ጽልመት የመሰለው ጠጉሩ አድጎ ጐፍሯል ፤ የሶስት ወይም የአራት ቀን እድሜ ያለው ጺሙ ጉንጮቹና አራት

ማእዘን አገጩ ላይ ሲታይ እጥንት ላይ የሚተራመስ ጉንዳን ይመስላል ። ጢይም ፊቱ ላይ ስጋ አይታይም ። ጉንጮቹ ላይ ያሉት አጥንቶች እንደ አለት ቆመው ሰው ላይ ያፈጣሉ ።

ድፍጥጥ ብሎ ወርዶ ቀዳዳዎቹ ሰፋፊ የሆኑትን አፍንጫውን እንደወናፍ ከፍ ዝቅ እያደረገ ፣ ወፍራም ከንፈሮቹን ገጥሞ ፣ ከማንበብ ብዛት የተንሳ ደከነመው የቀሉትን መነከለኛ አይኖቹን ውልብ ውልብ እያደረገ ያነብባል ። መጽሀፍ ከእጁ ወይም ከኪሱ አይገኝም ማለት ዘበት ነው ። ከመጽሀፍ ጋር አብሮ ውሎ አድሮ አብሮ ከአንቅልፉ ይነሳል ።

የተጋጠሙትን ከንፈሮቹን ላንዳፍታ የሚያላቅቃቸው ሲጃራ ሲምግ ብቻ ነው ። ከፍንጫው እየተኸረመለመለ የሚወጣው ጢስ መሬት ይዞ የሚሳብ የክረምት ጉም ይመስላል ። በቀኝ እጁ መጽሀፍ ይዞ እንደሆን ፣ ከግራ እጁ የተቀጣጠለ ሲጃራ ይታጣል ብሎ የሚወራረድ የለም ። «የተቀጣጠለ ሲጃራ ፣ የተዘረጋ መጽሀፍና አንድ ብርጭቆ ውስኪ የልብ ጓደኞቼ ናቸው ፣ ከነርሱ ጋር ስሆን እዝናናለሁ ፤ » ይላል አዘውትሮ ። ሶስቱንም ይዟል ። ተዝናንቷል ።

የሚያነብበው ጎር ቪዳል ስለቄሳር ጁሊያን የጻፈውን ታሪካዊ ልብ ወለድ መጽሀፍ ነው ። መጽሀፉን አንብቦ ለመጨረስ ምንም አልቀረውም ። ከመጽሀፉ ላይ ቀና አለ ። አንገቱ ረጅም ነው ። ማንቁርቱ ብርኩማ መስላ ትታያለች ። በረጅሙ ተንፈሰና አሊቃ ጣቱን ለማቃጠል የደረሰችውን ሲጃራ ልምጥጥ አድርጎ ከሳባት በኋላ መኮስተሪያው ላይ አወደማት ። የደካከሙትን አይኖቹን እምሀበ አልቦ ላይ አሳርፎ ፣ «ጁሊያን ክርስቲያንነትን ከአለም ገጽ አጥፍቶ

የማሪኮችንና የሮማውያንን በብዙሀን አማልክት ላይ የተመሰረተ ስልጣኔ እንደገና ለማጽጽም ያደረገው ታላቅ ጥረት ቢሳካለት ኖሮ — » በማለት ስፊ የሀሳብ ጉዳና ከመጀመሩ ፣ ከውጭ ወደ እንግዳ ቤት የሚያስገባው በር ተንኳኳ ። ሀይለማርያም የሚጠላው ነገር ቢኖር ሀሳቡን የሚገታ ደንቃራ ሲመጣበት በመሆኑ የአበራ ታላቅ ወንድም ፣ አቶ አባተ ወርቁ ሲገቡ በፈገግታ አልተቀበላቸውም ።

«አበራ የለም እንዴ?» ብለው ኮሰተር ባለ ድምጽ ጠየቁት ። ጉሪጥ አይኖቻቸው ያረፉት በውስኪው ብርጭቆ ላይ ነው ። እድሜ ባያበልዛቸውና ቅንድቦቻቸው ባይረግፉ አይኖቻቸው የአበራን ውብ አይኖች ይመስላሉ ። የኑሮ ትግል ባያከስላቸው እንደ ወንድማቸው የተዩ ፃማ ናቸው ። ከቦርጫቸው ይሆን ወይም ካለባበሳቸው እጭር መስለው ይታያሉ ። የለበሱት ከታች ካኪ ሱሪ ፣ ከላይ ጥቁር የሱፍ ኮት ነው ። በዚያ ላይ ቀጭን በጥቁር ጥለት የታጠረች ኩታ ደርበዋል ። ነጭ ኩታዋና ጥቁር ጥለቱ ፣ ሽበት ጣል ጣል ካለበት ጠጉራቸው ጋር ባንድነት ሲታዩ አንድ አይነት ህብረቀለም ይፈጥራሉ ። ፊታቸው ላይ ጉልተው በሚታዩት መስመሮች ላይ ከእድሜ የቀሰሙት እውቀት ተጽፎ ይነበባል ፣ እንደ አበራ ፊት ወጣትነት ብቻ ያበበበት ባዶ ፊት አይደለም ። እነዚያ መስመሮችና እነዚያ እሳታቸው ጠፍቶ ረመጣቸው ብቻ የቀረው አይኖች ስላሳለፉት ደስታም ሆነ ሀዘን በዝምታ ያንጐራጉራሉ ።

ሀይለማርያም ትኩር ብሎ ፊትለፊት ሰው የመመልከት ልማድ አለው ። ሰው ፊት ላይ ባልጭ ጽርግም የሚለው

ፈገግታ፣ ከውስጥ መንጭቶ ወጥቶ የሚነበበው ሀዘንና ደስታ፣ ዘመን እያለፈ ሲሄድ ተጽፈው የሚቀሩት መስመሮች እንደ ጥሩ መጽሀፍ ያስደስቱታል። አንዳንድ ጊዜ የሰዎችን ፊት ትኩር ብሎ በተመሰጠ አእምሮ ሲመለከት የሚሉትን ሳይሰማ የሚቀርበት ጊዜ አለ። ባገኙት ቁጥር በቁጣ ደማቸው የሚለወጥበት ምክንያት ሊገባው አልቻለም።

አቶ አባተ፣ «አበራ የለም እንዴ?» ብለው ሲጠይቁት በሙሉ ልቡ አልሰማቸውም ነበር። አበራ መታጠቢያ ቤት መሆኑን ነገራቸውና ውስኪ ቀድቶ ሰጣቸው። ኩታቸውን ትከሻቸው ላይ አስተካክለው ተዝናንተው ተቀመጡ።

ዝምታ ቤቱን ዋጠው። የአቶ አባተ ዝምታ ይሁን ወይም የአየሩ ቅዝቃዜ፣ ሀይለማርያም ብርድ ተሰማው። ረጃጅም ቅልጥሞቹን ሰብስቦ እንደ ገበሬ ዝንጀሮ እጆቹ ከጉልበት በታች የሚውሉትን እጆቹን አጣምሮ ቁጭ ካለበት ሶፋ ላይ ተመቻችቶ ተቀመጠ። ሀይለማርያም የሚለውን ነገር ለመፈለግ የአእምሮውን ጓዳ ሲፈትሽ፣ አቶ አባተ ውስኪአቸውን ፉት ብለው ካጣጣሙ በኋላ ቀድመውት፣ «ከአበራ ጋር ከተዋወቃችሁ ስንት ዘመን ይሆናል?» ብለው ጐሪጥ አይናቸውን ጣራው ላይ አሳርፈው ኮስተር ባለ ድምጽ ጠየቁት።

ዱብ እዳ ነበር። ለምን ይህን ጥያቄ እንዳቀረቡለት፣ ወይም ጥያቄው ምን አቅጣጫ እንደሚይዝ ባይገባውም፣ ዘመኑን ለማስታወስ ሲያሰላስል፣ አበራ ከዚህ ቀደም፣ «ወንድሜ በኔና ባንተ ጓደኝነት በጣም ይቀናል፣ አጥፊው አንተ ነህ ብሎ ስለሚያምን ሁለተኛ አንተን እንዳላይህ ባገኘኝ ቁጥር ይመክረኛል፣» ብሎ የነገረው ትዝ አለው። ጠይም፣

ረጅም ፊቱ ላይ ፈገግታ ብልጭ አለ ። አምስቱንም ጣቶቹን የጐፈረ ጠጉሩ ውስጥ ከትቶ ወደኋላ ካበጠረ በኋላ ሲጃራ አውጥቶ አቀጣጠለ ። ጉሮሮውን አሳላና ፣ «በግምት ሀያ አመት ይሆናል ፣» አላቸው ።

ግምቱ ትክክል ነበር ። በአስፋው ወሰን ትምህርት ቤት ለአምስት አመት ፣ በጀኔራል ዊንጌት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለአራት አመት ፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ እንደገና ለአራት አመት ፣ በካሊፎርኒያ ዩኒቨርሲቲ ለሁለት አመት አብረው ቆይተዋል ። ይህን ዘመን ሁሉ ክፍል ጐን ለጐን ነበር የሚቀመጡት ፣ የሚያጠኑት ባንድ ላይ ነበር ። የሚበሉትና የሚውሉት አብረው ነበር ። በዚህ የተነሳ አንዱ ያመጣትን ወዳጅ ሌላው ሲወስድ «አንተ ሌባ» ከመባባል በስተቀር መቀያየምና ቂም መያዝ በመካከላቸው ተፈጥሮ አያውቅም ። በተለይ አሜሪካን ሀገር ካሊፎርኒያ በነበሩበት ወቅት አበራ ለራሱ እንደምንም አግባብቶ ያመጣትን ቤት አሳልፎ ለሀይለማርያም ይሰጥ ነበር ፣ ምክንያቱም ሀይለማርያም ሴቶችን የሚያግባባበት ዘዴ የለውም ። ከነሱ ጋር ሲሆን ምላሱ ይተሳሰርና የሚያደርገው ነገር መላ ቅጡ ይጠፋዋል ።

ሳክራሜንቶ ከምትባል ከተማ ሄደው ካንዲት ጥቁር አሜሪካን ጋር ያሳለፉትን ሌሊት እንኳን ሳይቀር አስታወሰ ። ጊዜው ደግሞ እንዴት ይከንፋል ! ሁለቱም በፖለቲካ ትምህርት ተመርቀው ካሜሪካ ሀገር ከተመለሱ አን ካን አምስት አመት አልፏቸዋል ።

ሀይለማርያም ፣ አቶ አባተን ካወቃቸው ብዙ ዘመን ሆኖታል ። አስፋው ወሰን ትምህርት ቤትም ፣ ጀኔራል

ዊንጌትም ፣ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅም በነበረበት ዘመን ከአበራ ጋር እየተመላለሰ ብዙ ጊዜ ቤታቸው ተጋብዟል ። ቤታቸው በሄደ ቁጥር አዲስ ሚስት አግብተው ስለሚያገኛቸው ይገርመው ነበር ። እንደሰማው ከሆነ ካባታቸው የወረሱትን ርስት ሸጠው የጨረሱት ለጥሎሽና ለድግስ ነው ። ካለልጃገረድ ደግሞ አያገቡም ። የእርጅናቸውን መጠን የሚለኩበት ዘዴ ሳይሆን አይቀርም ።

«ታዲያ ጓደኝነት ለመቼ ነው፣ ሌላው ቀርቶ ራሱን እንዲችል በምክር ብትረዳው ምናለበት፣ ስምንት መቶ ብር ደሞዝ እየበላ የሚኖረው በኪራይ ቤት ነው ። እኔ ቤት ሰርቼ ራሴን ችዬ የምኖረው በሁለት መቶ ብር ደሞዝ ነው ። በዚሁ አቅም ወላጅ እናታችንን የምረዳው እኔ ነኝ ፣ አበራ እንደሆን ዞር ብሎ እንኳን አያያትም ። ይህ እንኳን ቀርቶ ራሱን ቢችልና ሰው ቢሆን ግድ የለኝም … ችኩል ነው ፣ በጣም ችኩል ነው ። ካንድ ስራ ላይ አይረጋም ፣ ምክር ሲሰጡት እሺ ብሎ አይቀበልም ፣ በችሎታው የሚያደንቀው የለም ። ያጣው ትእግስት ብቻ ነው ። ትእግስት ይኑርህ ብዬ ብመክረው ምን እንዳለኝ ታውቃለህ?

«ምን አለዎት? »

«ትእግስት ይኑርህ ብሎ ምክር አይገባኝም ፣ የረጋ ውሀ ይገማል ፣ ይበሰብሳል ፣» ብሎኝ ተቆጥቶ ሄደ ። ትእግስት ቢኖረው የቀሩት ጓደኞቹ በእድገት መቼ አልፈውት ይሄዱ ነበር ። ስንቶቹ ቅርስ አኑረው ፣ ሚስት አግብተው ፣ ልጅ ወልደው ፣ ዘመዶቻቸውን እየረዱ ፣ ባመት በአል እየጠየቁ ፣ በወላጅና በዘመድ ምርቃት እየለመለሙ ይኖራሉ ።

እንሱን ሳይ እቀናለሁ ። ብትመክረው ምናለበት? » በማለት ራሳቸውን በሀዘን ነቅንቀው በረጅሙ ተነፈሱ ።

ሀይለማርያም ፈገግ ብሉ ባፍንጫው የሲጃራ ጢስ እየለቀቀ ፤ «ከወንድም ምክር ሌላ ምን የተሻለ ነገር ይመጣል ብለው ነው? » አላቸው ። የተናገረውን በጥብቅ ያሰባበት አይመስልም ። አቶ አባተ የሚሉትን በግማሽ ልቡ ነበር የሚያዳምጠው ። ሙሉ ልቡ ያረፈው ፊታቸው ላይ በሚመላለሱ ን ስሜቶች ላይ ነበር ።

«ካንድ ማህጸን የወጣን አይመስለኝም ፤ አያውቀኝም ፤ አላውቀውም ። ካንድ ማህጸን እንዳልወጣን ሰዎች ተራርቀናል ። በመካከላችን የተፈጠረው ጋኔን ምን እንደሆን አይገባኝም ። አባታችን ሲሞቱ የተውልንን መሬት ጠላት እንዳይቀማን ጧት ማታ እየተሟገትኩና ፤ ሲቸገረው ፤ ያባቱ እጥንት እየወቀሰኝ ፤ ያባቴ ሎሌዎች እየታዘቡኝ ፤ መሬቱን ቀርጿ እየሸጥኩ ያስተማርኩት እኔ ነበርኩ ። ወንድምነቱን ቢንቅ እንዴት የዋልኩለትን ውለታ ሊረሳ ይችላል ? ለዚህ ያደረሰው ማን ሆነና ነው ? ይህም ይቅር ፤ ለሱ ይብላኝ እንጂ የኔን ውለታና ልፋት እግዜር ይቆጥርልኛል ። የማዝነው የወላድ መሀን ለሆንችው እናቱ ነው ፤» አሉና ሲያበቁ ፤ በመጨረሻ ከውስጥ በፈለቀ ወፍራም ድምጽ ፤ «እንደም ብሆን እግዜር ለወንድምና ለልጅ አላደለኝም ፤ ወንድሜም ልጄም እሱ ነበር ። ፈጣሪዬን ምን እንደበደልኩት አላውቅም ፤ ሀይማኖቴን ጠብቄ ጧት ማታ እማልደዋለሁ ፤ መሆን እድርጉ እንዴት በዚህ ላይ የወንድም ባላ ይሰጠኛል ?» በማለት ደፍርሰው ደም በለበሱት አይኖቻቸው ሀይለማርያምን ለመጀመሪያ ጊዜ ትኩር ብለው ተመለከቱት ። አይኖቻቸው

ተጋው ። ቀጠሉና ፣ «ከኔ ይልቅ አንተ ስለምትቀርበው ብትመክረው ጥሩ ነበር ። ከኔ ወንድምነት ያንተ ጓደኛ ነት እንደሚበልጥበት አውቃለሁ — መቼስ ምን ይሆናል ። ትዳር ቢይዝ ሰው ይሆን ነበር ፣ ችኩልነቱም ምናልባት ሳይቀዘቅዝ አይቀርም ። ለኔም ቢሆን በሱ አማካይነት ያባቴ ዝርያ መቀጠሉን አይቼ ብሞት ትንሽ ነገር አይ ደለም ፤» አሉት ።

ሀይለማርያም እንደልማዱ አምስት ጣቱን የጉፈረው ጠጉሩ ውስጥ ጨምሮ ትንሽ ካሰበ በኋላ ፣ «አንድ ሰው ራሱን ችሎ ወገኖቹን ለመርዳት አስቀድሞ ማንነቱን ማወቅ አለ በት ። ማንነቱን ፍለጋ ላይ ያለ ሰው ራሱን ወዳድ መስሎ ሊታይ ይችላል ። ይህም በመሆኑ ለራሱም ደስታ አጥቶ ፣ የስጋ ዘመዶቹንም ያበሳጫል ። እንዲህ ያለው ሰው ማንነ ቱን አውቆ የተቀሰቀሰው መንፈሱ እስኪረጋጋ ድረስ ቢተ ውት የተሻለ ሳይሆን አይቀርም ። አጉል ምክር ከሰድብ ይቆጥረዋልና … » በማለት የጀመረውን ሀሳብ በመጠኑ ገልጾ ዝርዝር ጉዳይ ውስጥ ሊገባ ሲቃጣ ፣ አቶ አባተ አቋረጡትና ፣ «የምትለው ነገር አይገባኝም ። ማንነቱን እንዴት አያውቅም ! የጀግናው የፊታውራሪ ወርቁ ባንት ይርጉ ልጅ ነው ። ዘራቸው እንደወርቅ የጠራ ፣ በለጋስነ ታቸውና በሀይማኖታቸው ጽኑነት ሀገር ያወቃቸው ታላቅ ሰው ነበሩ ። ማንነቱን አያውቅም ብሎ ነገር አይገባኝም ። ማንነታቸው ጠፍቶ እንዳይቀርኮ ነው ትዳር ይዞ ፍሬ እን ዲያገኝ የምጥረው ። በወንድሜና ብኔ መሀል የተፈጠረው ጋኔን እንዲያውም አንተ ሳትሆን አትቀርም ! » በማለት ፊታቸው ላይ የተጻፉት መስመሮች ነፍስ ዘርተው መደ

ንፉት እንደጀመሩ ፣ አበራ በቀኝ እጁ ጠጉሩን ወደ ኋላ እየዳመጠ መጣ ። ነጭ ሸሚዝና የሚያብለጨልጭ ጥቁር ሱሪ ለብሷል ። ቀይ ሆኖ ጥቁር ፣ ከብ ነጥቦች ጣል ጣል ያሉበት ፣ ገና ያልታሰረ ክራቫት ትከሻው ላይ ይታያል ።

አቶ አባተ ከተቀመጡበት ሶፋ ላይ ሆነው በንዴት እየተንቆራጠጡ ደጋግመው ፣ «ወቸ ጉድ ! ኧረ የፈረሰኛው ጊዮርጊስ ያለህ ! ጆሮ ምን ያስማል ! ወቸ ጉድ ! አጉል ምክር ከስድብ ይቆጠራል ይበለኝ !» እያሉ ሲያጉረመርሙ፣ አበራና ሀይለማርያም ተያይተው ፈገግታ ተለዋወጡ ።

ሁለቱ ስለሱ ያወሩ እንደነበረ አበራ ገብቶታል ፣ ስለምን ያወሩ እንደነበረም ባይሰማቸውም ያውቃል ። አቶ አባተ አበራን የሚያውቅ ሰው ባገኙ ቁጥር ለወንድማቸው የዋሉለትን ውለታ አንድ ባንድ ከዘረዘሩ በኋላ እግረ መንገዳ ቸውን መሀንነታቸውን ገልጸው ምከሩልኝ ሳይሉ አያልፉም።

እድሜአቸው ከሀምሳ አመት በላይ ይሆናል ። ልጅ ወልደው ለመሳምና ያባታቸው ዝርያ እንዲቀጥል ለማድ ረግ የነበራቸው ተስፋ አመት አልፎ ዘመን ሲተካ እየሞተ ስለሚሄድ ፣ ከሶስት አመታት በፊት ጀምረው ሙሉ ተስፋ ናቸውን የጣሉት በአበራ ላይ ነው ። የአበራ ግድየለሽነት እየሆነባቸው ይሄዳል ፣ መንፈሳቸው ይረበሻል ፣ ከመሬት ተነስተው ቁጡ ይሆናሉ ። ፉታ የሚያገኙት የመጠጥ ብርጭቆ ሲጨብጡ ብቻ ስለሆነ ዘወትር ሳይጠጡ ቤት አይገቡም ።

አበራ የወንድሙን ብርጭቆ ሞላና ለራሱም ውስኪ ቀድቶ ሲጃራውን አቀጣጥሎ ቁጭ አለ ። ሀይለማርያም

ከትከሻው ላይ ከባድ ጭነት የወረደለት ሰው ይመስል በረጅሙ ተንፍሶ ተዝናና ። አቶ አባተ ለወንድማቸው ሲነግሩት የፈለጉት ነገር እንዳለ ስለገባው ልሂድ ልቆይ እያለ ከራሱ ጋር ሲሟገት ፤ አቶ አባተ ወደ አበራ ዞረው ፤ «የመጣሁት ነገ ፋሲካ መሆኑን ላስታውስህ ነበር ፤ እናንተ እንደ ሆን ረስታችሁታል ። ቤተ ክርስቲያን ፤ ጾም ፤ ጸሎት ፤ ንስሀ የሚባል ነገር በናንተ ዘንድ ቀርቷል ። ዘመድ መጠየቅና ምክር መስማት ነውራችሁ ነው ። ይህ ሁሉ ግዝት ነው ። ከምን ላይ እንደበቀላችሁ እግዜር ይወቅ ፤ ልባችሁን የሞላው ትእቢት ብቻ ነው ... አዬ ትምህርት ! አዬ የኛ አዋቂ ዎች ! » ብለው ስሜታቸው እየገነፈለ ሂዶ ስድብ ላይ ከመድረሳቸው በፊት ፤ አበራ አቋረጣቸውና ፤ «ነገ ፋሲካ መሆኑን አውቃለሁ ። እናታችንን እንድንጠይቅ ከፈለግህ ነገ በሰባት ሰአት መጥቼ ልውሰድህ ፤ » አላቸው ።

«በፋሲካ እለት እናት ቤት እንዴት ባዶ እጅ ይኬ ዳል ? እኔ በግ እሰናድቻለሁ ፤ » አሉት ።
«እኔም በግ እንዳልወስድላት የበግ ሳት አገላብጨ መግዛት አልችልም ። ነጋዴዎቹም ቢሆኑ ገና ሲያዩኝ በዋጋ ይሸቅ ቡኛል ። መጠጥ እወስድላታለሁ ፤ » ከማለቱ እምና አንድ የበግ ነጋዴ እንዴት እንዳበሳጨው ትዝ አለው ።

«ይህ በግ ዋጋው ስንት ነው?»
«[illegible] ብር።»
«[illegible]ኛውስ?»
«[illegible] ብር ።»
«[illegible]ታቸው ከምን ላይ ነው ?»

«ምግንታቸው ላይ።»
«ቀልቡን ተወውና እርግጡን ተናገር ።»
«ጠበድበት ባውንድ አይነቅበም።»
«ሌንዴ ! ምን መጣ ?»
«ፋሲካ ።»
«በዛሬ እለት በሬ መግዛት አይቀልም እንዴ ?»
«ታዲያ በግ ተራ ለምን መጡ !»

ከዚያ ሁሉ ጣጣና የራስ ምታት በኋላ የተገዛው በግ ዳለቻ ባለመሆኑ ፤ ቤት ከመግባቱ በፊት ወይዘሮ ባፈና ፤ «እረ የተከልዩ ያለህ ! ምኑን አመጣህብኝ !» በማለት ወዲያውኑ በርካሽ ዋጋ መልሰው ሸጡት ። ውቃቢአቸው ጥቁር በግ አይወድም ። ይሁንና ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ውጪ በወጡ ቁጥር ጃንጥላ ይዛ የምትከተላቸው ጥቁር ሴት ልጅ ከኋላቸው ካጡ ውቃቢ የራቃቸው ይመስላቸዋል ። «ጥላ ቢስ… ቀትረ ቀላል የሆንኩ ይመስለኛል …» ይላሉ ዘመኑን እያረገሙ — የጥንቱን እያስታወሱ ።

## ፪

አቶ አባተ ወስኪውን ደጋግመው ከቀዱ ቆይተዋል ። ጸሀዩዋ የእለት ምቷን ለምመት ቁልቁል ወርዳ እድማስ ላይ የእሳት ፍም መስላ በመተኛቷ ደጃፍ መጠለም ጀምሯል ። ጉምጮቹ በእሳት የጋዩ ይመስላሉ ። ንፋስ ስስልስ በመስኮት

የሚታዩት ባህርዛፎች አይወዛወዙም ። ህይወት ያላቸው አይመስሉም ። አረንጓዴ ቀለማቸው ወደ ጥቁረት ሲለወጥ ምንም አልቀረውም ።

የጸሀዪዋ ቁልቁል መውረድ እንግዳ ቤቱ ውስጥ ላሉት የኤሌክትሪክ መብራቶች ድምቀት ሰጥቶ ነፍስ ዘርቶባቸዋል ። እንግዳ ቤቱ በሲጃራ ጢስ ታፍኗል ።

«እንደማማህ መጠመሙን ተወውና ገነት ሆቴል ሄደን ብናመሽ ይሻላል ። በዛሬ ሌሊት ክርስቶስ ከመቃብር ሲነሳ ተኝቼ ላንብብ ማለት መናፍቅ ያስኛል ። ሀጢአት ነው ። ለውግዘት የሚያበቃ ሀጢአት ነው ፤ » አለው አበራ ። አብረው እንዲሄዱ ሀይለማርያምን ሲለምነው አራተኛው ጊዜ መሆኑ ነበር ። አበራ በሚያብለጨልጭ ጥቁር ልብስና ተወልውሎ በሚያንጸባርቅ ጥቁር ማማ ተሸሞንሙኗል ። የነጭ ሸሚዙ ኮሌታ እንደውብ ጥርስ ከሩቅ ይጣራል ። ቀይ ሆኖ ጥቁር ክብ ነጥቦች ያሉበት ክራቫቱና ተመሳሳይ የደረት መሀረቡ በግሩም አኳሆን ከልብሱ ጋር ተዋህደዋል ።

ሀይለማርያም ከሚያነብበው መጽሀፍ ላይ ቀና ብሎ ጉሮሮውን አሳላና ፤ «አሁን ገነት ሆቴል እንሂድ ብለህ ባት ጨቀጭቀኝ ምናለበት ? ጥሩምባ ሲያናፉ ለመስማት ነው ፣ ወይስ ጭፈራ ለማየት ? አይን ከማስቀየምና ጆሮ ከማስ ጠለዝ ሌላ ትርፉ ምንድንነው ? ከሄድኩ ላይቀር የሚያስ ደስት የሰው ፊት የማይበት ቦታ ብሄድ ደስ ይለኛል… ለነፍስ ምግብ የሚሆን…» አለና አፉን እንደጉማሬ ከፍቶ አዛጋ ። መጽሀፋንና ሲጃራውን እንደያዘ ረጃጅም እጆቹን ወደላይ ዘርግቶ ተንጠራራ ።

«ለነፍስ ምግብ የሚሆን እንደማያጋጥምህ አስቀድመህ እንዴት ልታውቅ ትችላለህ? መጽሀፉም ቢሆን እሹ ታገኛላችሁ ፤ በር ምቱ ይከፈትላችኋል ነው ያለው ። ይልቅ እንሂድ ፤ ከመሄዳችን በፊት ግን ልብስህን መለወጥ አለብህ — ዛሬ እንኳን !»

የሀይለማርያም ቡናማ ኮትና ሱሪ ተጨማደዋል ። ለሶስትና ላራት ቀኖች፤ቀንም ሆነ ሌሊት ተለይተውት የሚያውቁ አይመስሉም ። ካንዱ በኩል ያለው የሸሚዙ ኮሌታ ወደላይ ተቀልሶ ከጆሮ ግንዱ ጋር ይሟገታል ። ከእርጅናው የተነሳ ቀለሙ የደበዘዘው ቀይ ከራቫት ወደጐን አዘንብሏል ። ሽምቀቆው ተፈትቶ የሚያውቅ አይመስልም ። የለበሰውን ልብስም ሆነ ያደረገውን ጫማ ከሸሚዙና ከእግር ሹራቡ በስተቀር ፤ የሚለውጠው ምናልባት በሶስት ወር አንድ ጊዜ ቢሆን ነው ። ልብሱን በለወጠበት እለት ቅንቅን እንደ ያዘው ሰው ሰውነቱ ሲወረጭ ይውላል ፤ ቀኑ ሁሉ ይቀፈዋል ። «እንሂድ ካልክ ተነስ ። መቼም አንተ ፈቃድህ ካልሞላ እንደህጻን ልጅ ሰው አትለቅም ። ለልብሴ እንደሆን የጠላኝ ከፊቴ ዞር ሲል ይችላል ፤» አለና ተነስቶ ቆመ ።

ጨለማው አይን ያዝ ማድረግ ጀምሮአል ። ባህርዛፎቹ ከሩቅ ሲታዩ አየር ላይ የተንሳፈፈ ጥላ ይመስላሉ ። እንደውቅያኖስ ባህር በተንጣለለው ሰማይላይ የብር ሰባሪ መስላ በባህርዛፎች መካከል የምትታየው ጨረቃ ከእንቅልፉ ነቅቶ እንደሚያዛጋ ህጻን ትማርካለች ። ቀዝቃዛ የሆነውና ድምቀት ያለው ፈገግታዋ ልብ ያሞቃል ። ጥቁር ብርድልብስ የመሰለ ጉም ውስጥ ስትገባ የአበራ ልብ አብሮአት ሰመጠ ።

«ጨረቃዋ !»
«ጨረቃዋ ምን ሆነች !»
«የጨረቃ ውበት አይገርምህም ፣ ድምቀት ከትዝታዜ ጋር… ልዩ ምትሀት አለው…… ድምቀቷና ትዝታዜዋ እየሳበኝ አንዳንዴ ፈዝዤ የምቀርበት ጊዜ አለ……»

«የስአሊ ስሜትክን እየማረከችው ይሆናል ። ተፈጥሮ ሁልጊዜ ስአሊዎችን እንደማረከች ነው ፣ ግን እንደ ሸር ሙጣ ምስጢሯን አታካፍላቸውም ።»

«ዱሮ ቀረ ፣ ጊዜው አልፏል ። ራሴን በምፈልገው መን ገድ ለመግለጽ ሳልችል የህይወትን ጉዳና አቋርጬ እን ደምሄድ አንዳንዴ ትዝ ሲለኝ መፈጠሬን እጠላለሁ ። የታ ፈነችው ነፍሴ ውስጤ ስትቃትት ይሰማኛል ፣ » አለና ሀሳቡን ከአእምሮው ውስጥ አራግፎ ለማውጣት ያህል ራሱን ነቀነቀ ።

የቀን ሙያተኞች የቆርቆሮ አገልግሎታቸውን ይዘው ወደ የቤታቸው ይሮጣሉ ። በዝግታ የሚሄድ ሰው አይታይም ። ከመርሀ ቤቱ ቡና ቤት አጠገብ ወደታችና ከሾላው ወደ ላይ የሚመጡት ቁጥር የሌላቸው በጐች መንገዱ ላይ ይተራመሳሉ ።

በዚያ ጨለማ ገና የበግ ላት ደባብሰው ለመግዛት የሚጣደፉም ነበሩ ።

ከያንዳንዱ ቤት የሚመነጨው የቅመም መአዛና የሚ ነጠር ቅቤ ቀዝቃዛውን አየር መመረዝ ጀምሯል — ብዙ መሰዋእት የሚደረግበት ሌሊት ነው ። የህይወት እርምጃ ፍጥነቱን ጨምሯል ። አበራና ሀይለማርያም የፍጥነቱን ስልት ለመጠበቅ ተነሳሱ ።

## ፫

የብርጭቆውና የጠርሙሱ ቻቻታ ፤ የጡሩምባው የብርጭቆውና የጠርሙሱ ቻቻታ ፤ የጡሩምባው እሉኡታ ፤ የህዝቡ ጋጋታና ግፊያ ፤ ከመጠጥ ሽታና ጉም ከመሰለው የሲጃራ ጪስ ጋር ተደባልቀው የገነት ሆቴ ልን የዳንስ አዳራሽ ምድራዊ ገሀነም አስመስለውታል ።

የሴቶቹ ጉትቻ ፤ ሀብል ፤ የደረትና የጠጉር ጌጣጌጦች እንዲሁም ያንዳንድ ወንዶች ሸሚዝ እጀታ ቁልፎች ፤ የሻማ ዎቹን ብርሀን እየወሰዱ መልሰው ይወረውራሉ ። ሁሉም የሚተነፍሰው በዳንሱ አዳራሽ ውስጥ የሚጋጨውን ትኩስ አየር ነው ። ወበቁም ሆነ በሴቶች ሽቶና በወንዶች ላብ የተመረዘው ትኩስ አየር እንደእሳት ወላፈን ከሩቅ የሰው ፊት ይገርፋል ። ወላፈኑ የሚሰማው አዲስ ለመጡት እንጂ እዚያው የቆዩትን ተዋህዷቸዋል ።

የመጠጥ ሀይል ይሉኝታቸውን የገፈፋቸው ፤ ወይም እው ቀው ለመታየት አንዳንድ ሴቶች ሲያስካኩ ፤ አንዳንድ ወን ዶች የደም ስሮቻቸውን አግተርትረው ሙዚቃው እንዲዶ ንምላቸው ድምጻቸውን ከጣራው በላይ አሳልፈው ሲጮሁ ፤ የጡሩምባው እሉኡታና የታምቡሩ እሩምታ ላንቃው እስኪ ሰነጠቅ ከሚጮኸው ድምጻዊ ተማዋች ጋር ሲወዳደሩ ፤ አንዱ ሌላው የሚለውን ለመስማት ዘበት ከመሆኑም ሌላ ፤

የተወሳሰበው የህይወት ድር አንድ ትልቅ ትኩስ ነኮርኳር ሆኖአል ። በዚህ ነኮርኳር ውስጥ ውሳጣዊ ሀኬትና ምኔት ቦታ አልነበራቸውም ፤ ነገ ትርጉም አልነበረውም ። ዛሬ በትኩስ የህይወት አየር ተሞልቶ አብጦአል ።

«ከዚህ የበለጠ ምን የነፍስ ምግብ አለ ?» ሲል አበራ ሀይለማርያምን ጠየቀው ። ወጣት ፊቱ ላይ አንድ አይነት ሀሴት ይጫወታል ። የጣት ጥፍሮቹን በጥርሱ መከርከም ጀምሯል ። ሀይለማርያም እንኳን ወፍራም ፈገግታ አሳየ ። ፈገግ ሲል የሀዘን ብርድልብስ ለብሶ የሚታየው ረጅም ፊቱ ህይወት ያገኛል ።

ያልተያዘ ጠረጴዛ እንዳለ በደካከሙት አይኖቹ እያማ ተረ ሲፈልግ ትንሽ ከቆየ በኋላ ትከሻውን ነቅንቆ «ባዶ ጠረጴዛ ቢገኝ ምሽቱ የተሻለ ይሆን ነበር ...» ከማለቱ አንድ ወንድና ሴት የተቀመጡበትን ጠረጴዛ በድንገት ለቀው ወደበር ሲያመሩ ተመለከተ ። መጀመሪያ በርሳዋን እንጠልጥላ የተነሳችው ሴቷ ነበረች ። ወንድዬው እሷን ይዞ ሊያስቀምጣት ሲሞክር በንዴት መንጭቃው እየተንደ ረደረች ወደበሩ ስታመራ ወንድዬው እየሮጠ ተከተላት ።

አይኖቿ እሳት ጉርሰዋል ። ከንፈሮቿ ብርድ እንደ ያዘው ሰው ይንቀጠቀጣሉ ። «ሁሉ አማረሽን ገቢያ አታ ውጪት» ስትል ሀይለማርያም ሰማትና የጸባቸው መነሻ ገባው ።

እጇዋን ለማስለቀቅ ስትመነጭቀው ጠረጴዛቸው ላይ የነበረው መጠጥ ሁሉ በመደፋቱ ሲወጡ ብዙ ሰው ሳያያ ቸው አልቀረም ። ውጭ ወጥተው ቢታረቁም እንኳ ይሉኝታ

አይመልሳቸውም ። የቀረው ጠረጴዛ በሙሉ በህዝበ ክርስ ቲያን ተይዟል ። መፈናፈኛ ቦታ የለም ።

አበራና ሀይለማርያም ተያዩና ሂደው ጠረጴዛውን ያዙ ። እኩለ ሌሊት ሆኗል ። ክርስቶስ ከመቃብር የሚነሳበት ጊዜ በመሆኑ ሙዚቃውም ሆነ ዳንኪራው እጅግ ደርቷል ። የሲጃራ ጢስ ጪርስ መጠጡ እንደውሀ ይንቆረቆራል ። የዳንስ አዳራሹን አፍኖታል ።

የሁሉም አይን በመጠጥ፣በጢስና በወበቅ ሀይል ቀልቶ ደም ከመምሰሉም በላይ ፣ የወንዶቹ ደም ስሮች ተገትረው ማበጥ ጀምረዋል ። ስንት ብር የፈሰሰበት የሴቶቹ ጠጉር በላብ ተጨማዶ እንዳልነበረ ለመሆን ምንም አልቀረውም ።

የሻማው መብራት ተወርውሮ አበራ ፊትና ሸሚዙ ላይ ልዩ ልዩ ጥላ እየፈጠረ ይጫወታል ። ሁለቱም ክንዶ ቻቸውን ጠረጴዛው ላይ አስደግፈው በተመሰጠ መንፈስ አፍ ለአፍ ገጥመው ያወራሉ ። መካከላቸው በጣም ያልጉ ደለ የውስኪ ጠርሙስ ቆሟል ።

«አበራ ስንት ጊዜ ልንገርህ! አሁንም በድጋሚ እነግርሀለሁ። አንተም ብትሆን እኔ የፖለቲካ ሰዎች አይደለንም ። ይህን አንተ ከኔ የበለጠ ታውቃለህ ። ጊዜአችንና ህይወታችንን ነው የምናባክነው — በከንቱ ።»

«አውቃለሁ ሀይሌ ፣ ህይወት የትሳሳተ መንገድ ላይ አው ጥታ ጥላናለች ... ግን ምን ይሁን ?»

«የጣለችን ህይወት አይደለችም ፣ እኛው ነን ራሳችንን የጣልነው ። ፊቴን መስተዋት ውስጥ ስመለከተው ጉልቶ ሚታየኝ ፍርሀቱና ወኔ ቢስነቱ ነው ፣ ሌላ ነገር አይታ

የማም ። በምግባራችን የራሳችንን ደህንነት ልንፈጥር እንችላለን ። ይህን ለማድረግ አስቀድመን በትንሹ መሞት ያሻናል … በልጅነት ወላጆች ጫንቃ ላይ ፤ ከዚያም በኋላ ለትምህርትም ሆነ ለሥራ መንግሥት ትከሻ ላይ ተንጠልጥለን እስከመቼ ድረስ ! እስካሁን ድረስ ከመውሰድ በስተቀር መልሰን የተካነው ምን ነገር አለ ? ምንም ! ምንም !»

«ምን ልናደርግ እንችላለን ብለህ ነው ? ይልቅ እንጠጣ !»

«ከህይወት ጽዋ እስካሁን እሬት ስንጠጣ ቆይተናል ። አቅጣጫችንን መለወጥ ያለብን አሁን ነው ። በራሳችን ላይ ከመዝመት የበለጠ ንቅናቄ (ሬቮሉሽን) የለም ። የህይወቴ ምክንያት ድርሰት ነው ፤ ያንተም የስእል ሙያ ነው ። ታውቀዋለህ ፤ አውቀዋለሁ ። የህይወት ጥሬያቸውን አውቀው ነፍሳቸውን ባላቸው ችሎታ የሚገልጹ ሰዎች አማልክት ናቸው ፤ ሸክም አይደሉም ፤ መኻንገር አይደሉም ፤ አማልክት ናቸው …እና የሰው መጨረሻ አላማው ራሱ አምላክ ለመሆን ነው ፤ ጽድቅና ገነት የዚህ ምሳሌ ናቸው …ሃይማኖት የሚሉት ፈሊጥ መጥቶ ከመቃብር ባሻገር ባያደርጋቸው ኖሮ! »

«ግን ምን ልናደርግ እንችላለን ነው የምልህ ! ጊዜው አልፎአል ። እስካሁን ድረስ ለራሴ እንግዳ ሆኖ የኖረው የህይወቴ ጥሬ የተዳፈነ እሳት መሆን አለበት ። እንደገና ጀማሪ ለመሆን አልችልም ። ጊዜው አልፎአል ።»

«ጊዜው አላለፈም ። የህይወትህን ጥሬ ካወቅህ ዘንድ ባንድ ቀን እንኳን ራስህን ብትገልጽ ይበቃል …እና

ጥሪውንና አላማውን የማያውቅ ሰው ሆኖ ብዙ ዘመን ከመኖር ባንድ ቀን አምላክ መሆን ይበልጣል ። ጣይ ምህ መጥተው ባይበጠብጡኝ ኖር ቅድም ቤትህ የመ ጣሁት ምን ልናደርግ እንደምንችል ልነግርህ ነበር ። በማለት ህይወትን መንጋጋው መሀል ጨምሮ ያላመጣ ይመስል አፉን አጣጣመ ። የደከከሙት አይኖቹ ነፍስ ዘሩ ፤ አፍንጫውን ነፍቶ ትኩስ አየር ወደ ውስጥ ሳበ ። ራቱ በላ ደፍቷል ።

«ይልቅ እንጠጣ……ለጤናችን…»

ሀይለማርያም የተጉነጨውን ውስኪ አጣጥሞ ሲያበ ወደፊት ምን ለማድረግ እንደሚችሉ ሲነግረው ሲቃጣ ፤ ወይስ «ጽዋችሁን የምታነሱት ለራሳችሁ ጤንነት ነው ! ለክርስቶስ ከሙታን መነሳት ? » የሚል ስለታም ድምጽ ሰማ ። ከጣራው አልፎ ያለቅጥ የሚያናፋው ጡሩምባ ፤ በወለሉ ላይ የሚቀልጠው ዳንኪራ ፤ የብርጭቆውና የጠር ሙሱ ቻቻታ ፤ ሁሉሉቱም ከሩቅ እንጂ ከቅርብ አይሰሙ ነበር ። ልቦናቸው በሀሳባቸው ተመስጦ ነበር ። ሁለቱም ደንብረው ቀና አሉ ። ገድሉ በዛብህ ነበር ።

«ፈቃዳችሁ ቢሆን……» አለና ከመጥረቢያ መሳይ ረጅም ራቱ ላይ የማይለየውን እንደቀለሀ ባዶ የሆነ ፈገግታ እያሳየ ወንበር ስቦ ቁጭ አለ ። ጥርሶቹ እንደአጠና እጥር ችርችም ብለው ነጣጭ በመሆናቸው ከንፈሮቹን አይከድ ኑም ።

ለስ ከንፈሮቹ ፤ የማንባቱን ውሀ ልክ ይዞ የወረደው እፍንጫው ፤ ሰዉን እንደሽንኩርት የሚልጡት ዐይኖቹ ልብ

ናቹ ከመጥረቢያ መሳይ ፊቷ ጋር ባንድነት እንደጕራዴ ያሽሟጥጣሉ ።

ሀይለማርያም የጕን እያየው ፣ «ከኛ የምትፈልገው አንድ ነገር መኖር አለበት እንጂ እኛን ብለህ እንዳልመጣህ ይገባኛል ፣ ምን ኖሯል ?» ሲል እንደማንጓጠጥ አድርጐ ጠየቀው ። አንድ ነገር ለመጀመር ስንሳ ለምን እንከን አያጣኝም ? የሚል ጥያቄ ሀይለማርያም ፊት ላይ ጕልቶ ይታያል ።

«አንተኮ ስትናገር መቸም ለነገ አትልም ፤» አለውና እንደ ወበሬ የሾለውን የራስ ቅሉን በቁጭት ነቀነቀ ።

«ታዲያስ ጃል ፤» አለ ሀይለማርያም ፣ ቀጠለና ፣ «ሰዎኑን እነማንን አጋጨህ ?»

ገድሉ ባንዳንድ አካባቢ «ማኪያቬሊ» የሚል ቅጽል ስም አግኝቷል ። ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ በነበረበት ዘመን የወል ስሙ «ካርኒጂ» ነበር ። ስስ ከንፈሮቹን እንደወትሮው እሞጠሞጠና ፣ «ሰዉን ማጋጨትኮ ራሱ አንድ ትልቅ ሙያ ነው ። ማንም ከመሬት ተነስቶ ሊያደርገው አይችልም ። የያንዳንዱን ሰው መሰረተ ባህርይ መርምሮ የማወቅን ችሎታ ይጠይቃል … እና የጥቂቶች ተሰጥኦ ነው …» ከማለቱ ፣ ሀይለማርያም አቋረጠውና ፣ «በዚህ ተሰጥኦ ነዋ እንዶቀስት ወደላይ የተወረወርከው ?» አለው ። ጕቶ ላይ ግን ባሯን እንደምታከ ላም ጕንበስ ቀና እያለ ጠረጴዛው ላይ ያስደገፈውን እጁን ሳያነቃንቅ ባምስት ጣቶቹ ጠጉሩን ማበጠር ጀምሯል ።

«መቼም አፍህ ለከት የለውም ፣ ቢኖረውና ትንሽ ይሉኝታን ብታውቅ እንተም ወደላይ የመወርወር እድል

ይገጥምህ ነበር ። የሚሰማህንና የምታስበውን ሁሉ እንደ ንፍጥ አውጥተህ መዘርፈጥ ብልግና አይመስልህም ? ከባህላችን ውጭ ነው ።»

«ይገባኛል ፤» አለ ሀይለማርያም፤«እኔም ከዚህ አይነቱ ባህል ውጭ ነኝ ። የማስበውንና የሚሰማኝን ከመግለጥ ልቆጠብ አልችልም ። ይህን ለማድረግ ደግሞ ወኔ ያስፈልጋል ።»

ገድሉ ትእግስቱን ሊጨርስ ምንም አልቀረውም ፤ ነገር ግን ከመጥረቢያ መሳይ ፊቱ ላይ የማይለየው ፈገግታ አልጠፋም ። አፉ ይናገር እንጂ አይኖቹ ሌላ ቦታ ሄደዋል ፤ የወዳጅነት ጭውውት የያዙ ለማስመሰል ፈገግታውን ፊቱ ላይ እያሰፋው ይሄድ ነበር ። አበራ በአይኑ የገድሉን አይኖች ተከተለ ። ወደ ጠረጴዛቸው የመጣበት ምክንያት ገባው ፤

«ቅድም ስለተናገርኩት ተስጥኦ እንደገና ካነሳህ ላይቀር ልንገርህ ፤ ከምትኖርበት የፈጠራ አለም እንድትወጣ ምናልባት ይረዳህ ይሆናል ። እናንተ የምትኖሩት ከአድማስ ባሻገር ነው ። በዚህ አለም፤ አንዱ የሌላው መሰላል ነው... እና ላይ ለመድረስ የሚችሉት ልዩ ተሰጥኦ እንዲኖራቸው ያስፈልጋል ... እንደኔ ... እንዳንተ ያሉት ሌትና ማታ ሀሊና ! ሀሊና ! እያሉ በመጮህ ራሳቸውን የሚያታልሉት ግን እርካብ ሆነው ነው የሚቀሩት ። ጥንትም እንዲህ ነበር ። አሁንም ተፈጥሮ ህጓን አልለወጠችም ፤» ብሎት ፈገግታውን እያሳየ ተነሳ ። ገና ትናንት ኮከብ እንደጫነ ምክትል መቶ አለቃ ትከሻውን ወደፊት አስቀድሞ ሲውዘዘግ ረጅም፤ ቀጭን ቁመናው እየተጠማዘዘ የወጣ የማረቆ ቃሪያ

ይመስላል ። ገድሉ ሲሄድም ፤ ሲቀመጥም ፤ ሲናገርም የሰውን አይን ወደሱ ለመሳብ ፤ መኖሩን ለማስታወቅ ከመሞከር ወርሶ የሚቦዝንበት ጊዜ የለም ። በየሰርጉ ቤትም ሆነ በየግብዣው ስሙ እንዲጠራ ብቻ መኪናውን ወስዶ ያለቦታ ያቆማል ። ህዝብ በተሰበሰበበት ፤ በተለይ የድምጽ ማጉያ መሳሪያ ካለ ፤ ምክንያት ፈልጉ ስሙን ከነማእረጉ ማስጠራት አለበት ።

«ምንነው እንዲህ ጨከንክበት?» አለው አበራ ፤ በግማሽ ልብ ። ትላልቅ አይኖቹ ሌላ ቦታ ሂደው ተተክለዋል ። ከተተከሉበት ነቅሎ ወደ ሀይለማርያም ሲመልሳቸው አልቻለም ። በአይኖቹ የተራቆተውን ደረቷን ፤ ረጅም አንገቷን ፤ ክብ ትከሻዋን ፤ የጽጌረዳ እምቡጥ የመሰለውን ከንፈሯን ይዳስሳል ።

ለጠረጴዛው ጉኗን ሰጥታ እግሮቿን አነባብራ ተቀምጣለች ። ክንዷን ጠረጴዛው ላይ አስደግፋ መዳፏ ላይ ጋደም ብላለች ። አውራ ጣቷ ክብ አገጯ ስር ገብቶ በሌባ ጣቷ ጉንጯን እንደማከክ እያለች ትተክዛለች — ሀሳብ የያዘው ወይም የተገረመ ሰው ይመስል ።

ጥቁር ፤ የሚያብለጨልጭ ቀሚሷ የሻማውን መብራት ሲስብ ፤ እንደ አልማዝ የሚያበራው ጉትቻዋ መልሶ ይወረውረዋል ። በተለይ የወርቅ ቀለም ካለው ነጠላ ጫማዋ ውስጥ ለብቻው ሾልኮ ወጥቶ የሚታየው አውራ ጣቷ የባለጌ ጓደኛ ምላስ ይመስል ሰው ላይ ያሾፋል ፤ ይቀልዳል ። እሷ ስታየው አበራ ያቀረቅራል ። እሷ ዞር ስትል ያያታል ። አንዳንዴም አይኖቻቸው ይጋጫሉ ። ሲጋጩ ሁለቱም

ከመቅጽበት ዞር ይላሉ ፣ ይጋጫሉ ፣ ይመለሳሉ ። ትንፋልጭታ ፣ ትልቅ ብልጭታ ።

ይህ ሁሉ ሲሆን ሀይለማርያም ልብ አላደረገም ነበር ። እቀርቅሮ ገድሉ የተናገረውን ነገር ያሰላስል ነበር ። ነገሮውን አሳላና ፣ «…ልጨክንኩበትም ። የምጨክነው በራሴ ላይ ነው እንጂ በሰው ላይ አይደለም ። መጥረቢያን መጥረቢያ ማለት ጭካኔ ሊሆን አይችልም ። ዝም ከማለት የቀለለ ነገር የለም ። የሚያስቸግረው የሚያስቡትንና የሚያምኑበትን ሳይፈሩ መናገር ነው ። እና ለኔም ሆነ ለማንም ከዚህ የበለጠ ፍትህ ላደርግ አልችልም ። ግን የገድሉ ነገር ይገርማል ፣ የስልጣን ነገር ናላው ውስጥ ገብቶ አሳብዶታል ፣ እውር ሆኗል ።» አለ ፣ እያዘነ ፣ እየተከዘ ።

«መቼም…ምናልባት እሱ ከደረሰበት ባለመድረሳችን ቀንተን ይሆናል ። ቢሆንም ተሰጥኦውን አውቆ ስራ ላይ በማዋሉ ከኛ ሳይሻል አይቀርም ።»

«እንዲህ ያለውን ተሰጥኦ አልከው ? እኔ እሱን ብሆን ሀሊናዬ እንደ እባጩንሬ ይኮሰኩሰኝ ነበር …» በማለት ቅድም ገድሉ ከመምጣቱ በፊት የጀመረውን ሁለቱን የሚመለከት ሀሳብ ሊያመጣ ቢቃጣው ፣ «ዳኙ አንተ እሱ አይደለህም !» ብሎት ፣ አበራ ፣ የተቀመጠበት ወንበር የወረረው ይመስል ፣ እንደወስፈንጥር በሮ ሄደ ። ሀይለማርያም አልገረመውም—አበራን ያውቀዋልና ። አሁን መደረግ ያለበት ነገር ቅድሚያ ማግኘት አለበት ። «ዋጋ ያለው እጅ ውስጥ ያለ ጊዜ ነው…ነገ ነገ ነው…እና በሁለቱ መካከል ያለው ድልድይ አያስተማምንም ።» በአይኖቹ ተከተለው ።

እሷ ቀድማው እሱ እየተከተላት የዳንስ ወለሉ ላይ ከተሰበሰበው ህዝብ መሀል ገብተው ጠፉ ። የሲጃራ ጉም አዳራሹን እንደጭጋግ አፍኖታል ። አየር በማጣት ሳይውለበለቡ ከሚነዱት ሻማዎች የሚመጣ ብርሀን በስተቀር ሌላ የለም። ለለውጥ ያህል ሙዚቀኞቹ አምባሰል የሚባለውን ዘፈን እንደ መስከረም ምንጭ ማንቆርቆር ጀምረዋል ።

ከፊትለፊቱ ያለችው ሻማ እንባዋ ወርዶ ወርዶ እግሯ ስር ረግቷል ። ነድዳ እየሟሸሸች... ነድዳ ነድዳ እያነሰች እስከታልቅ ድረስ አልጠበቃትም ። አጠፋት ። የመጨረሻ ትንፋሿ አፍንጫው ውስጥ ገባ ። ለምን እንደሆነ አላወቀም ። አበራን ትቶ ስለ ገድሉ ያሰላስል ጀመር ፣ እያወጣ ፣ እያወረደ ፣ እያስታወሰ ።

እነሱ ዘንድ ለምን እንደመጣ አውቋል ፣ አበራ ለዳንስ የወሰዳትን ሴት ከቅርብ ሆኖ ለማየት ነበር ። ከዚህ በፊት የማይተዋወቁ መስለው አልታዩትም ። ነገር ግን፣ስታየው ለምን ጀርባዋን ሰጠችው ? የሱ ነገር ሳይሆን የሷ ጀርባ ነበር እሱን ያባረረው ። በሰፈሩት ቁና መሰፈር አይቀርም እንደሚባለው ዋጋውን አግኝቷል ። እሱስ ቢሆን ኮሌጅ ያኔ ተማሪ በነበረበት ዘመን በችግር እየማቀቀች ፣ ትምህርቱን ሲጨርስ አልፎለት ያሳልፍልኛል በማለት በተስፋ ስትጠብቀው የኖረችውን የልጃገረድ ሚስቱን ድግሪ ባገኘ በሳምንቱ አይንሽን አልይ ብሎ ጀርባውን ሰጥቷት የለም ? አሁን ሴትኛ አዳሪ ሁና ቀርታለች ፣ ያልታደለች ! «አንዱ የሌላው መሰላል ነው ፣ ጥንትም እንዲህ ነበር ፣ አሁንም ተፈጥሮ ህግን አልለወጠችም ።»

አበራ የሚወዛወዘው የሙዚቃውን ሳይሆን የሷን ስልት እየተከተለ ነው ። ተስፋ አሳሳጣችውም፤ በመካከላቸው ንፋስ እንኳን የሚያስገባ ቦታ የለም ። ነገር ግን ከራሱ ሰውነት ግለት በስተቀር የሷ አይሰማውም ። እንደ በረዶ ቀዝቅዛለች ። እቅፍ የማይሞላውን ወገቧን ጭምቅ፤ ጥብብ፤ እምቅ አድርጎ ያዘ፤ ግድ አልነበራትም ። እቅፉ ውስጥ ብትሆንም እንደእውነቱ ከሆነ ግን በጣም ሩቅ ዋለች ። የሷ ቅዝቃዜ ሳይሆን የሱ ትኩሳት አበሳጨው ። ቅዝቃዜዋ የሚያሟሽሸው መስሎት ተሰማው ። ቅርብ ሆና ሩቅ፤ ቢሆንም ስልቷን ይከተላል ። ምን አይነት ቀዝቃዛ የህይወት ስልት !

አንዱ ዘፈን አልቆ ሌላው ቀጠለ፤ ሌላ ዘፈን፤ ሌላ ስልት... ትዝታ ። ለሶስተኛ ጊዜ፤ «ስምሽን ብትነግሪኝ ምናለበት ?» አላት እየተለማመጠ ።

እሷም ለሶስተኛ ጊዜ፤ «ስሜ ምን ያደርግልሀል ? ይልቅ እንደንስ!» አለችው፤ የሙዚቃ ቃና ባለው ድምጽ፤ እያሾፈች ። ሲሰሟት የምትዘፍን እንጂ የምትናገር አይመስልም ። ድምጿ ስልት እየጠበቀ ይነሳና ይወድቃል— እንደ ባህር ሞገድ ።

አበራ ወገቧን ሸርቦ እንደያዘ ዳንሱን ትቶ ቆሞ ነበር ። በዚያ ጨለማ ውስጥ ትላልቅ አይኖቿ እንደፈርጥ ይንቦገቦጋሉ — ለመሳብ ። ሆኖም የውበት ድባብ የምትባል አይደለችም ። ግን ታስደነግጣለች ። ጎንባሯ አጭር ሆኖ በመጠኑ ስልክክ ብሎ የወረደው አፍንጫዋ ስር ሲደርስ ወደላይ ይገለበጣል — ሰጨ ላይ ለማረፍ ። ከንፈሮቿ ሲፈነዱ

የደረሰ የጽጌረዳ እምቡጥ ይመስል አብጠው ይታያሉ— ለማጓጓት ። ዳንሱን ቀጠሉ…

አበራ ለጥቂት ጊዜ ስልቷን በታላቅ ትእግስት ሲጠብቅ ቆየና በድንገት ሳታስበው፣«ከነስምሽ ገደል ልትገቢ ትችያለሽ !» ብሏት ወለሉ ላይ እንደ ቆመች ትቷት ሊሄድ ሲል እጁን ይዛ አስቀረችው ፤ አልተንቀሳቀሰም ።

እጅዋ ሲንቀጠቀጥ ይሰማዋል ። በጨለማ ካፎቴ እንደተመዘዘ ጐራዴ ጥርሶቿ ብልጭ አሉ ። አይኖቿ በዚያ ጨለማ እንደቀለጠ ብር ሲንከባለሉ ይታዩታል ። የደረቱን ከንፈሮቿን በመላስ አለሰለሰችና ፣ «ማንም ወንድ ሉሲትን ተራምዷት ሊሄድ አይችልም !» አለችው ፣ የቀድሞውን ስልት ባጣ ድምጽ ።

«አንቺ ማነሽና !»
«ሉሲት ታደሰ ።»

«ታዲያ ምን ይሁን ?» ብሏት እጁን ለማስለቀቅ ሲል ፣ ጠበቅ አድርጋ ያዘችው ። እንዴት እንደተረዳው ባያውቅም በዋዛ እንደማትለቀው አያያዟ ነገረው ። ለማምለጥ እንደገና አልሞከረም ። ሳይታወቀው ይዟት ይደንስ ጀመር ፣ ስልቷን እየጠበቀ ። ንቅናቄዋ እየሳበው— እየተጠጋት— ወገቧን እየሸረበ— በሚያልበው እጁ ።

«እንኳን አንተና ማንም ሱሪ የታጠቀ ወንድ ሜዳ ላይ ጥሎኝ ሊሄድ አይችልም !» ለመጀመሪያ ጊዜ የልቧን ትርታ ሰማ ። እጅዋና ጉንጩ ደም መርጨት ጀምረዋል ። ትንፋሿ በንዴት እየጤሰ ጆሮ ግንዱን ለበለበው ።

«ኤ ማን መስዬሽ ነው !»

«አንተ ማን እንደሆንክ አውቃለሁ ፤ ስላንተ ብዙ ነገር ሰምቻለሁ ። መጀመሪያ ትምህርት ሚኒስቴር ፤ ከዚያ ቀጥሎ ዩኒቨርስቲ ፤ ከዚያም በኋላ ማስታወቂያ ሚኒስቴር ፤ አሁን ደግሞ የምትሰራው አገር ግዛት ሚኒስቴር ውስጥ ነው ፤ አይደለም ? የሰናይት አደራ አሲቃ አይደለህም ? ስላንተ ብዙ ነገር አጫውታኛለች ።»

«ምን ብላ ?»

«ሴቶች ላይ ኩራትና ትእቢት ታበዛለህ ። በእምብርክክ መጥተው እስኪለምኑህ ድረስ ዞር ብለህ አታያቸውም አሉ ። ሰናይት ብቻ ሳትሆን በየመስሪያ ቤቱ የሚያውቁህ ሴቶች ሁሉ ነግረውኛል ። ማወቅ ያለብህ እኔም እንዳንተ ኩሩ መሆኔን ነው ።»

ድምጿ የቀድሞ ስልቱን አገኘ ። ቅርብ ሁና ሩቅ ቦታ የሄደች መምሰል ጀምራለች ። ቅዝቃዜ ሰውነቷን ወርሶ ነበር ።

«አንችም እንደኔ ከሆንሽ ልንቋቋም አንችልም ።» ካላት በኋላ ፤ ቅዝቃዜዋንና ርቀቷን እያስታወሰ ፤ የሰውነቱ ላብ ፤ የእጁ ላብ ፤ እየበሳጨው ፤ «ሆኖም አንቺ እንዳልሺው እኔ በከንቱ ኩራት አላምንም ። የማምነው ሰጥቶ በመቀበል ነው ፤» አላት ። ወደሳንባው የሚስበው ትኩስ አየር ከረጅም አንገቷ ስር የሚመጣውን የሽቶ መአዛ ያዘለ ነው ። ድንገተኛ የሰውነት ስቃይ ተሰማው…ፋታ የማይሰጥ ስቃይ … በፍጥነት መብረድ ያለበት ስቃይ ።

«ሰጥቶ መቀበል» ብላ ፈገግ እንዳለች ቶሎ ስቃዩን ሊያስተዋው ለማለት ተጣደፈ ። እሷ ግን ማዳመጥ ትታ ነበር ። ፊቷ ወደ እሱ ዞሮ ነበር ፤ ግን አታየውም ነበር ።

አበራ መጥቶ ፣ «ዉስኪውን ምን ወረሰው ነከህ ?» ሲለው ሀይለማርያም የተከናነበውን የሀሳብ ቡሉኮ ከራሱ ላይ አንስቶ ፣ ከእንቅልፉ እንደነቃ ሰው እንደመባነን ብሎ ፣ «ብቸኝነቴን አጠብኩበት ፣» አለውና ወፍራም ፈገግታ አሳየው ። የደካከሙት አይኖቹ የባሰውኑ ደክመዋል ፣ ቀልተዋል ። የኤሌክትሪክ ብርሀን አይኖቹን እየወጋ ስላስቸገረው ማየት ተስኖታል ።

አበራ እንደቆመ አንድ ብርጭቆ ዉስኪ ባንድ ትንፋሽ ወለጠና ፣ «እንሂድ ፣» አለው ። አንድ አይነት ጣር ራቱ ላይ ይነበባል ።

«ይገባኛል ። ስቃይ ይዞሀል ፣ መተንፈስ አለብህ ። አይደለም ?» እያለ የዉስኪውን ጠርሙስ ይዞ ተነሳ ። አበራ እንደመገረም ብሎ ባይኑ ስላንጓጠጠው ፣ «ጓደኛዬን ጥዬ አልሄድም ፣ ጠርሙሷ አብራኝ መምጣት አለባት ፣» አለው ።

«እንደፈለክዉ ፣ ብቻ ቶሎ እንሂድ !» ሀይለማርያም የዉስኪውን ጠርሙስ ባንድ እጁ ደረቱ ላይ ይዞ ፣ ሌላውን እጁን ኪሱ ከትቶ ፣ ትከሻው ላይ ከባድ ሸክም እንደያዘ ሰው እየተጎተተ ሲሄድ ፣ አንዳንድ ሰዎች ዘወር እያሉ ይመለከቱት ነበር ።

የመጡት በአበራ መኪና ነበር ። የሀይለማርያም ጥቁር አፔል መኪና አበራ ቤት ቀርታለች ። ከመኪርኪሷ የተነሳ በምሽት አታስተማምንም ።

አበራ እየታገለ በስንት መከራ መኪናውን ካቆመበት ስፍራ አወጣና በረጅም መብራት ወለገውን እየቀደዱ

በአዲሱ ቄራ መንገድ ወደላይ ወጥተው ሜክሲኮ አደባባይን ወደግራ ትተው ፤ የመኪናቸውን አፍንጫ ወደሰሜን በመደገን ወደ ቸርቺል ጎዳና አመሩ ። ከፍት የሆነው ሰፊው መንገድና በጥፊ የሚማታው ቀዝቃዛ አየር በጆሯቸው መታደስ ጀምረዋል ።

ጨረቃዋ ጉም ውስጥ ገብታ ተደብቃለች ። ከዋክብት ጌጣቸውን የነፈጉት ጥቁር ሰማይ በከባድ ዝምታ ተውጦ ተንጣሏል ።

ከዋቢ ሸበሌ ሆቴል የሚመነጨው ሙዚቃ ወደ መንገድ ይጎርፍ ነበር ። ደጅ ተደርድረው የሚታዩት መኪናዎች ቁጥር ግንት ሆቴል ደጅ ከነበሩት አያንስም ።

የአበራ መኪና የቸርቺል ጎዳናን አቀበት መያያዝ ስትጀምር አንዴ አጓራችና እንደቀስት መወርወር ጀመረች ።

አልፎ አልፎ አንዳንድ ሰካራሞች ወዲህና ወዲያ እየተላጉ ሲሄዱ ይታያሉ ። የቸርቺል ጎዳናን አቀበት ጨርሰው ወደ ካኒንግሀም መንገድ ሲታጠፉ ሲሉ ፤ አንዱ የመብራት ምሰሶ ተደግፎ ጉንበስ ቀና እያለ ሲያስመልሰ ተመለከቱና ሁለቱም አዘኑ ። ያ ምሰሶውን ተደግፎ እንደዚያ ሲታወክ ፤ ጓደኛው ወደ ግንብ ዞሮ ፊኛውን እያሰሰ ያፏጭ ነበር ።

ያዲስ አበባ እምብርት ሁና የቆየችው ፒያሳ በውሾች ተወርራለች ። ወደ አጼ ምኒልክ አደባባይ ሲያመሩ ከቅዳሴ የሚመለሱ ምእመናን ነጣጣ ጋቢና ቡሉኮ ተከናንበው ሲጓዙ አልፎ አልፎ ይታያሉ ። ሁኔታው ለአበራ

አስቂኙ የህይወት ድራማ መሰሉ ሰለታየው ወይ. ሀይለማርያም ዞር ብሎ ፣ «አያስገርምህም ?» አለው ።

«ምን ?»

«በኛና በነዚህ ሰዎች መካከል ያለው ልዩነት ... አስቂኙ የሆነው ድራማ አይታይህም ?»

«ልዩነታችን ይገባኛል ፣ ድራማው ግን አልታየኝም ። እነሱም መንፈሳቸውን እኛም መንፈሳችንን አድሰን መመለሳችን ነው ። የነሱ ከኛ መሻሉን በማያጠራጥር መንገድ ሊነግርህ የሚችል የለም ። ይህን ለግብረ ገብ አስተማሪዎች እንተውና ይልቅ ስለአላማችን እንወያይ ……»

«እእ…አሁን አይደለም ፣ ኋላ ፣ አሁን የቅድሚ ልጅ የቀሰቀሰችብኝን ስሜት ከውስጤ ማውጣት አለብኝ ፣ ስቃይ እርግዤ መቆየት እንደማልችል እያወቅህ ምንነው ?» አበራ የመስፍን ሀረርን መንገድ ለቆ ግራውን በመያዝ ወደ. ዮሀንስ ቤተ ክርስቲያን በሚወስደው ቁልቁለት ትንሽ እንደተጓዘ እንደገና ወደ. ግራ ታጥፎ ወደ ገዳም ሰፈር ገባ ። የውሀ ልኩ ከፍ ያለ ባለ አራት ደጃፍ ዛኒጋባ ቤት ስር መኪናውን ወስዶ ሲያቆም ፣ ማን እንደመጣ ለማየት ወይም ለመታየት ቤተኛ አዳሪዎች ቀያይ መጋረጃዎቹን እየገለጡ ከየደጃፉ ብቅ ብቅ አሉ ፣ እየሳቁ ። «አንቱ ዛሬ ደግሞ ጨሰኪ. ይዘው መዞር ጀመሩ እንዴ ?» አለች ከመካከላቸው አንዷ ፣ ድምጿ ጨለማውንና ጸጥታውን ቀደደው ።

የዶሮ ወጥ ሽታ ያካባቢውን አየር አውዶታል ። ሀይለማርያም ረሀብ ተሰማው ። ባዘቦቱ ቀን በየሰፈሩ እፍ

ንጣ የሚወጋው የባህር ዛፍ ማገዶ ጢስ በትመምና በቅቤ ተደምስሶ ጨርሶ ጠፍቶአል ። አፍንጫ የሚወጋ ሌላ ነገር ቢኖር ከየቤቶቹ ቤት የሚመጣው የእጣንና የከርቤ ጢስ ነው ።

አበራ ጭር ያለውን ቤት መርጦ ወደ ውስጥ ዘው ሲል ሀይለማርያም የዉስኪውን ጠርሙስ እንጠልጥሎ ተከትሎት ገባ ።

አበራ እንዳሰበው ከአራት ሴቶች ሌላ ማንም አልነበረም ። በቀይ መብራት አንዷን ከሌላዋ መለየት አስቸጋሪ ነበር ። ሁለቱ ያገር ልብስ ፣ የተቀሩት ደግሞ አጫጭር ፣ ሰውነት ላይ ልክክ የሚሉ ቀሚሶች ለብሰዋል ። አበራ ፣ ዳሌዋ ሰፋ ብሎ የታየችውንና ሲገባ እንደሌሎቹ ወከክ ያላለችለትን ቤት መርጦ ፣ «ተማደርዳሪ ጦም አዳሪ...» እያለ እጅዋን ይዞ እየጐተታት ወደ ውስጥ ገባ ። ሌሎቹ በቅናት አይን ቆዳዋን ገፈፏት ። የቀሩት ሶስት ሴቶች ሀይለማርያምን ከበው ይዘው ፣ «ጋሼ ፣ አንቱ...ምን እንጋበዝ ታዲያ ?» ይሉት ጀመር ......

«አሁን ልትነግረኝ ትችላለህ ፣ ከራሴ ጋር እርቅ አድርጌ አለሁ ፣» አለው በነጭ መሀረብ ጉንጮቹንና ግንባሩን እየጠረገ ። የተቀባችው ሽቶ የተስማማው አይመስልም ። የተሸበረው ሆዱ ኮስተር እንዲልለት ዉስኪ አዘዘ ።

ወለሉ ላይ ቄጠማ ተነስንሷል ። ስታይ አይናቸው ፣ ሸፍኗቸው ልብ ባያደርገው ነበር እንጂ ቅድምም ነበር ። ሴቶቹ ፣ ባንኮኒው ኋላ ቆማ ሲጃራ ከምታጨሰው በስተቀር ፣ የሸማኔ መወርወሪያ ይመስል ወዲህና ወዲያ ይሯሯጣሉ ። አንድ ዝግጅት ይዘዋል ።

«በል ንገረኝኮ ፣ ለመስማት ዝግጁ ነኝ ፣» በማለት ደጋግሞ ወተወተው ። ሀይለማርያም ውሀ እንደምትጠጣ ዶሮ ወደላይ አንጋጦ አፉ ውስጥ የነበረውን የሲጃራ ጢስ ክብ ክብ በማድረግ ወደጣራው ከላካቸው በኋላ መለስ በማለት አበራን ትኩር ብሎ ተመለከተው ። ፊትለፊት ተያዩ ። የሀይለማርያም ፊት ፈገግ አለ ።

«ስራህን ለቀህ ሙሉ ጊዜህን የስእል ስራ ላይ እንድታውል እፈልጋለሁ ፣ ስራህን እንድትለቅ የምገፋፋህ ሁለት ነገር እጣምረህ ለመስራት እንደማትችል ስለማውቅ ነው ። ብትፈልግ ልታደርገው ትችላለህ ። ግን አትችልም ። ሰነፍ ነህ ። ሁለት ፣ ሶስት ስራዎች ባንድነት ሲያጋጥሙህ ፣ የስራዎቹን ብዛት ምክንያት በማድረግ አንዱንም ሳትሰራ ቁጭ እንደምትል አውቃለሁ ። ነጻ ከሆንክ ምክንያት ሊኖርህ አይችልም ፣» ሲል ከውስጥ በመነጨና ትእዛዝ በተመላበት ድምጽ ነገረው ።

አበራ ደነገጠ ። ግራ ገባው ። ሳቅ አለ ። ኮስተር አለ ። ሲጃራውን ጉልቅ አደረገ ። ዉስኪውን ጨለጠና ፣ «ምን እየበላሁ? የሶስት ሺህ ዘመን ስልጣኔ ቢኖረንም ቅሉ ፣ የማንኛውም ጥበብ ባለሙያዎች የሚበለጽጉበት ሁብረተሰብ ውስጥ አይደለንም ። ምን እየበላሁ» ሲል ጠየቀው ።

«ስለሱ አታስብ ። የኔ ደመወዝ ለሁለታችን ይበቃል ። እርግጥ ነው ፣ እንዳሁኑ በምቾት ልንኖር አንችልም ይሆናል ። ቅንጦትን መሰናበት ይኖርብናል ። የመንግሥት ስራ ፣ የመንግሥት ደሞዝ ፣ የመንግሥት መኪና ፣ አበል ፣ ልዩ ወጭ ፣ ዳረጐት ፣ ዋስትና ያለው ስራ...ያለድካም ዋጋ

ይቀርብናል ። ቅድም እንዳልኩት ማንነታችንን ለማወቅ ትንሽ መሞት ያስፈልገናል ። የሚገርመው ነገር ፍልስፍናችንም ሆነ ፍርሀታችን ፤ ደስታና ሀዘናችን ከሆድ ርቆ አይሄድም ።»

«እሱስ እሺ ። አንተስ?»

«ስለኔ አታስብ ። እየሰራሁ ለመጻፍ እችላለሁ ። ትንሽ እንቅልፍ ይበቃኛል ። አንተ ግን ሰአሊ ለመሆን ሙሉ ጊዜ ያስፈልግሀል ። ይህን ላንተም ሆነ ለኔ ስትል ማድረግ አለብህ ፤ ያንተ ቆራጥነት ለኔ ብርታት ሊሆነኝ ይችላል ።»

«ያልሆነልን እንደሆንስ ?»

«አሁንም ቢሆን አይረባም እየተባልክ መታማትህ እንደ ሆን አልቀረልህም ። ግን ቁምነገሩ እሱ አይደለም ። ሙከራችን ይበቃል ። ከልጅነት ጀምረህ እስካሁን ድረስ ከሰው ትከሻ ወርደህ አታውቅም ። ፍርሀትህ ይገባኛል ። ድህነትና ችግር ምን እንደሆኑ አታውቅም ...... አልቀመስከውም ።

«አንተ ቀምሰሀል ?»

«አዎን ፤ ችግር ፤ ረሀብና ሲቃይ ምን እንደሆኑ አውቃለሁ ። አባቴ የመንደር አድርተኞች ለፋፊ ነበር ። እሱ ደህና በነበረበት ጊዜ በቀን አንዴ እንኳ ቢሆን እንጀራ በዶኬ እንቀምስ ነበር ። ታሞ አልጋ ላይ ከዋለ በኋላ ግን ጥሬ እንኳ ካቅሙ ያርብን ነበር ። በሽታው ሳይሆን ችጋር በመጨረሻ ገደለው ። እናቴ ጸሎት ታደርግ ነበር ፤ የሰማት አምላክ አልነበረም ። እናቴ ቅጠል እየጠረገችና በየሰዉ ቤት እንጀራ እየጋገረች ስንኖር እሷም ያልጋ ቁራኛ ሆነች ። እዩኛት በማገዶ ጢስ ሟሽሸው ጠቆ ። ጸሎት አደረግሁ ፤ የሰማኝ አምላክ አልነበረም ። ርቧት አህል ባይኗ አየሁ

ሞተች ። ከሰማይ የወረደልኝ መና እጦት እረሀብ ፣ ስቃይና ብቸኝነት ብቻ ነበር— በሰባት አመቴ ። ያኔ ነው እግዜር ቢኖርም ባይኖርም በሰው ጣጣ እንደማይገባ ትንሿ ልቤ ያወቀችው ። ከጐረቤታችን አንዱ ሰው ረድቶኝ አስቶው ወሰን ትምህርት ቤት አዳሪ ባልሆን ኖሮ እኔም እንደወላጆቼ ችጋር ይገድለኝ ነበር ። ችግርና ብቸኝነት ምን እንደሆኑ አውቃለሁ ።» አለ የደካከሙትን አይኖቹን እምህበ አልቦ ላይ አሳርፎ በአግን ጢስ የተበከለውን አየር ወደ ውስጥ በረጅሙ እየሳበ ።

አበራ ጥፍሩን በጥርሱ እየከረከመ በሀሳብ ይዋልል ነበር ።

«አንድ ቀን ስለችግርና ስለብቸኝነት ውብ የሆነ ድርሰት እንደምትጽፍ ተስፋ አለኝ ።» አለው ። ሀይለማርያም ላይ በደረሰው ሁሉ ልቡ ተነክቶ ነበር ። ባንድ በኩል ያደረበት ሀሳብ ይህን ዘመን ሁሉ አብረን ስንኖር ለምን እስካሁን ድረስ ስለ ልጅነት ሀይወቱ ሳይነግረኝ ቀረ ፣ የሚል ነበር ።

«ስለችግርና ስለብቸኝነት ለመዝፈን ፍላጐት የለኝም ። ማጻፍ የምፈልገው ስለ አለም ውበትና ስለሰው ተፈጥሮ መሰረታዊ ጥሩነት ፣ እንዲሁም ሰው በራሱ የራሱን ደህንነት እንዳያገኝ ስለሚያደናቅፉት ሁኔታዎችና አካባቢዎች ነው ። በዚህ ውጥን ውስጥ ችግርና ብቸኝነት አነስተኛውን ስፍራ ይዘው ይገኛሉ ።»

እጣን በገል ቀርቦ ይጤሳል ። ጢሱ ቀጥ ብሎ ወደ ግራው ይንሰራራል ። ቡና በጀበና ቀርቧል ። ከጀበናው

ጢሱ ቱግ ቱግ እያለ ይደነፋል ። ሶስቱም ሴቶች ከጓዳ ተከታትለው ወጡ ። ከመካከላቸው አንዷ የያዘችውን መሶብ አምጥታ ሀይለማርያምና አበራ ፊት አኖረች ፤

አራቱም ሴቶች ቀረቡ ። ከባንኮኒው ኋላ ቆሞ የነበረ ችው ሴት ፤ «ብሉ እንጂ አብረን እንፈስክ ፤ እንኳን ወመ ሉጋሙን ፈታላችሁ ፤» አለቻቸው ።

ህዝበ ክርስቲያን አብረው ቀረሱ ፤ ፋሲካም ሆነ ፤

## ፩

«የበግ ቆዳ ያለው ? ጠርሙስ ያለው? የፍግ ቆዳ ያለው?» አንዱ ሲያልፍ ሌላው ይተካል ። ያንዱን ድምጽ ከሌላው ለይቶ ለማወቅ አይቻልም ። ተመሳሳይ የሆነ ከጉሮሮ የሚ ይወርድ የጉረና ድምጽ ነበር ። አበራ ግን በእንቅልፍ ልቡ የበር ኳኳታ ይሰማው ነበር ።

«የበግ ቆዳ ያለው ? ጠርሙስ ፤ ጠሳ ያለው ?» በህልሙ የእንጀራ አባቱ አስከሬን መጥቶ ፤ «አንተ ወስላታ ተነስተህ በሩን አትከፍትም !» እያለ ይጮህበት ነበር ። አበራ ከእን ቅልፉ ነቃ... «የበግ ቆዳ ያለው?...» ሲራገም ምንም አል ቀረውም ፤ የሰአቱ መርፌድ እርግማኑን አስረሳው ።

ሰውነቱ ዝሏል ። የራስ ምታት ይዞ ይፈልጠዋል ።
ከንፈሮቹ በዉስኪና በሲጃራ ብዛት ተቃጥለው የተጠበሰ
ጉበት መስለዋል ። እንቅልፍ ያልጠገቡት አይኖቹ ቀልተው
አብጠዋል ። በእንቅልፍ ልቡ አንድ ነገር ሲሰማ ሁልጊዜ
ስለእንጀራ አባቱ ያልማል ።

በመነሳትና በመተኛት መካከል እየዋለለ ፣ በመሄድና
በመቅረት መካከል ነፍሱ እየተሟገተች ፣ የውዱን ሳይሆን
የግዱን ተነሳ ። አበራን የሚያስቸግረው ነገር ቢኖር ካል
ጋው መላቀቅ ሳይሆን አይቀርም ። ለመኝታው ልዩ ፍቅር
አለው ።

ይህ ፍቅር በአእምሮው ውስጥ የተጸነሰው ገና በልጅ
ነቱ ነበር ። የራሱ የሆነ ሰፊ ፣ የሚሞቅ መኝታ እንዲኖረው
ይመኝ ነበር ። አንዲት ሰሴንና ካሊም ጣል ያለባት ፣ የምት
ቁረቁር መደብ ላይ ተጋድሞ እንቅልፍ እያንገላጀጀው ፣
ሽልብ ሲያደርገው ብንን እያለ ፣ የእንጀራ አባቱ መጠጥ
ቤት አምሽተው ሲገቡ በር ለመክፈት በሚጠባበቅበት
ጊዜ ፣ ትንሿ ልቡ የማይቆረቆርና የማይበርድ መኝታ ኖሮኝ ፣
ነጻነት አግኝቼ ፣ እፎይ ብዬ በተኛሁ እያለች ዘወትር ማታ
ማታ ትመኝ ነበር ። ምኞቷ በከንቱ አልቀረም ። ሰፊ የሚ
ሞቅ የሞዝቮልድ አልጋ አግኝታለች ። መንበረ ሰላም
ይለዋል ።

ለሶስት አመት ያህል አብራው የኖረችው ገረድ ፣
የልብ አውቃ ነች ። የሚፈልገውን ከመጠየቁ በፊት እስ
ቀድማ ታቀርባለች ። አንድ ጠርሙስ አምቦ ውሀ ፣ ሁለት
አስፕሪንና አንድ ወፍራም ፣ ጥቁር ቡና ከጠጣ በኋላ ሉሲት

ታደሰ የሰጠችው የስልክ ቁጥርና አድራሻዋ ትዝ አሉት ፣
እምሳሏ ፊቱ መጥቶ ተደቀነበት ። ቀዝቃዛ እጇዋ ውክ
ከጋለ ሰውነቱ ወርዶ የቀለጠውን ላብ አስታወሰ ። ዉኒኪ
እንተና......ግንም ሜዳ ላይ ጥሎኝ ሊሄድ አይችልም ፤
ላንዳፍታ የገድሉ በዛብህ ከርሳም አይኖች እንዴ እሴቱ
ተጣብቀውባት ቀዝቃዛ ውበቷን ሲመጥጡ ታዩት ።
ግንኙነታቸው ምን ይሆን ?

ሀሳቡ ወደ ሀይለማርያም ዞረ ። የገባለት ቃል መቁ
እንደመብረቅ መታው ። ክብደቱ ስር ትክሻው ሲሰምጥ
ተሰማውና በረጅሙ ተነፈሰ ። ሁለት ወር!... ከዚያ በኋላ
ስራውን ትቶ ጊዜውን በሰአል ሙያ ላይ ማዋል አለበት ።
በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ የመኪናውን እዳ ክፍሉ መጨረ
አለበት ። የራዲዮ ግራሙን እዳ እንደሆን ትናንት የመጨ
ረሻውን ክፍያ በማድረግ ተገላግሏል ።

የእጁ መዳፍ ላይ የተጻፉትን ሰንበሮች እንደሚያነብ
ሰው ሁለቱንም እጆቹን በማጠጋጋት ለጥቂት ጊዜ ተመለ
ከቶ ሲያበቃ ፤ ደሙ ተቆጥቶ ስሮቹ እስኪያብጡ ድረስ
ቡጢ ጨበጠና ወደሰማይ አንጋጠጠ ። ሀይለማርያም በመጨ
ረሻ የተናገራቸው ቃላት ጆሮ ግንዱ ውስጥ አስተጋቡ ፤
ዐቅሎ ብትጀምር የተሻለ ነው ፤ ከዚህ ቀደም ከንዱ መ
ሪያ ቤት ወደሌላ እያልክ እንዳበደች ውሻ ስትከለፈፍ
የኖርከው ለምን ይመስልሀል ? ችሎታ አለው ፤ ግን ም
ያደርጋል ፤ አንድ ቦታ ረግቶ መስራት አይችልም ከመሀል
ሌላ ምን አተረፍክ ? ከራስህ ሮጠህ ልታመልጥ አትችልም ፤
መቼም ቢሆን ......እና ፤ እንዲሁ ከቀጠልክ አንድ ቀ

ወሽመጥህ ይቆረጥና የት እንደሆነ የምታርፈው ታውቃለህ ? አማኑኤል !»

አማኑኤል ? ሲሄድ የተነሳውም እዚያ ነበር ። እናቱ ወይዘሮ ባፌና ሞልቶት የሚኖሩት ሰባተኛ ወረዳ አማኑኤል ቤተ ክርስቲያን አካባቢ ነው ።

እስካሁን ድረስ ወንድሙ ትእግስታቸውን ጨርሰው ይሆናል ። ተጣድፎ ከቤት ሲወጣ በእንቅልፍ እጦትና በመጠጥ የበዙትን አይኖቹን ጠራራ ጸሀይ ያስርሀራሂ መታቸው ።

እንዳሰበው ወንድሙና ባለቤታቸው ወይዘሮ እልፍነሽ ተሰማ ሲጠብቁት ውለው ተስፋ በመቁረጥ መንገዱን በእግር መያያዝ ሲጀምሩ ደረሰባቸው ። ነጭ ሙክት ፤ አንድ ወረንገሎ ኩሊ አሸክመው ከሚኖሩበት ከአባ ኮራን ሰፈር ወጥተው ደጃዝማች ነሲቡ መንገድ ሲደርሱ ምንም አልቆራቸውም ። በቢስ ኩባንያ አድርጎ ባይመጣ ኖሮ ሊያገኛቸው ባልቻለም ነበር ።

«ምንነው አበርዱ !» አለችው ፤ እልፍነሽ በተለመደው እንጀባራቂ ፈገግታዋና በለሰለሰ አንደበቷ ። የለበሰችው ያገር ልብስ ትንቡሽቡሽ አድርጓት ግርማ ሞገስ ጨምሮላታል ። ወንድሙ ከግልምጫ ሌላ ምንም አላሉትም ።

«መጠጥ የምገዛበት ሱቅ አጥቼ ስፈልግ ነው ጊዜ የፈጀሁት ፤» አላት የፈገግታዋን አጸፋ እየመለሰ ። አቶ አባተ ካገቧቸው... አምስት... ሰድስት... ሚስቶች ሁሉ አበራ እልፍነሽን ይወዷታል ። እግዜር ልጅ ቢሰጣት ምናለበት !

ፈገግታዋ እንደጧት ጸሀይ ደምቋል ። ልዝብ እንደሆነች ግልጽነቷ ደስ ይሉታል ። አጢያየሟ ፤ የቂመቷ እጥር

ምጥን ማለትና እጭር ሆኖ ጉርድርድ ያለው አሻንጉሊት ፊቷ ላይ የሚተራመሰው ደም፤ ሰው ላይ ልዩ ምትሀት ያሳድራሉ ። የሉሊት ፈገግታ ግን…አዎን፤እንደጨረቃ ብርሀን ደማቅ ሆኖ የሚበርድ የራሱ የሆነ ምትሀት አለው ።

አቶ አባተ ፤ «እናንተን ያመነ ጉም የዘገነ…» እያሉ በማጉረምረም መኪናው ላይ ወጥተው ተሳፈሩ ። ኩሊው አበራን ከእግር እስከራሱ እንዳይሞት እንዳይሽር አድርጐ ገላመጠው ። ሀያ አምስት ሳንቲም ወረወረለት ።

በጉጇም በረንዳ ወደ ላይ ወጥተው ቀኛቸውን በመያዝ ለጥቂት ጊዜ እንደተጓዙ ፤ የልዑል መኰንንን ትምህርት ቤትና የቀድሞ የቅዱስ ጳውሎስን ሆስፒታል አልፈው ወደ ግራ በመታጠፍ ወደ ሰባተኛ አመሩ ። ከዚያም ወደ አማኑኤል ቤተ ክርስቲያን የሚወስደውንና ዘለአለም እንደተጠገነ የሚኖረውን መንገድ ይዘው ቁልቁለቱን እንደወረዱ ቀና ውን መንገድ ለቀው ወደግራ ታጠፉ ።

በመጡበት መንገድ ሁሉ ጃኖ የለበሰ መሶብና ገንቦ አሸክመው ፤ ወይም ነጭ ፤ አብዛኛውን ጊዜ ቀይ ጨርቅ ባል ያለበት ድፎ ዳቦ የያዘ ሰፌድ አሸክመው ፤ ወይም በወረቀት የተጠቀለለ መጠጥ አንጠልጥለው ፤ ወይም እንደየዘመዶቻቸው ውቃቢ ዳለቻ ፤ ቡሀ ፤ ነጭ ፤ ድፍን ጥቁር በግ እስጐትተው የአከፋይ ለማድረስ የሚሄዱ ብዙ ሰዎች ይታዩ ነበር ።

የመጡበት መንገድ ሁሉ እንደሌላው ጊዜ ፊታቸው ተለይቶ በማይታወቅ ፤ እንደጉንዳን በሚተራመሱ ህዝብ ፤ በዚያ ህዝብ መሀል እንደጥይት በሚበሩ ሴይቼንቶዎችና ኦሎ ቢባል መንገድ በማይለቁ ከባድ የጭነት መኪናዎች

ባለማየቱ ፤ አበራ ፤ ጭንቅ አልያዘውም ነበር ። በዝተው የሚ
ታዩት የበግ ቆዳ ነጋዴዎች ብቻ ነበሩ ።

ለለውጥ ያህል ሁሉም የለበሰው የክት ልብስ ቢሆ
ንም ፤ አበራ የለበሰው ጥቁር እጅጉርድ ሸሚዝና የተኳሸች
ጥቁር ሱሪ ብቻ ነው ። አውደ አመት መሆኑን የዘንጋ አስ
መስሎታል ።

በህጻንነቱ ዘመን ፤ «እማማ ቡና ደርሷልና ኑ ትላለች፤»
እያለ መልእክት በማድረስ ሲሯሯጥ ያደገባት መንደር ከፊቱ
ብቅ አለች ።

ጥንት ፤ በሰፈሩ የነበሩት ቤቶች ተራርቀው የቆሙ
ነበሩ ። እያንዳንዱ ቤት የራሱ የሆነ ትምክህትና ኩራት
ነበረው ። አሁን ግን እንደሰንሰለት ተያይዘዋል ። ያንዱ
ቤት ግድግዳ ለሌላው ድጋፍ ሲሆን…ካንዱ ቤት የሚመነ
ጨው ጢስ ሌላውን ሲያሞቅ… ለክፉም ሆነ ለደግ በች
ግር ገመድ ተቆራኝተው የቆሙ ይመስላሉ ።

የእናቱ ቤት ግን ብቻውን እንደቆመ አለ ። ኮባዎቹና
ጥዶቹ አርጅተው ወርካ መስለዋል ። ስቀላ ቤቱ እንዳለ
ቢሆንም የተቀባው ቀለም ምን አይነት እንደሆነ ለማወቅ
ያዳግታል ።

በህጻንነቱ ፤ ሸርተቴ ሲጫወትባት የነበረችው ኮረብታ
አሁንም አለች ። እናቱ ቤት ፊትለፊት ያለችው መስክ
ስፋቷ ቀንሶ ታየው ። አጠና ሻጮች ስፍረውባታል ። የህ
ጻንነቱ አለም ። ኳሊፎርኒያ በነበረበት ጊዜ እነዚህ ሁሉ በእ
ዩን ህሊናው እየዞሩ እንዴት ይናፍቁት ነበር !

ግንባሩን ቋጥሮና ሀሞቱን ኮስተር አድርጐ በየቦታው
ጉች ጉች ብለው የሚታዩትን የልጆች አይነ ምድር እየዘለለ

ሲሄድ ፤ እናቴ ፤ ጐረቤት ሁሉ እንዲሰማቸው ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ፤ «ማን አባቱ ነው ይህን ዶሮ አጥሬ ስር የጣለው ! ዘረቢስ ሁሉ ...» እያሉ የስድብ ዶፍ ሲያወርዱ ሰማቸው ፤ አልተለወጡም ። ቢያንስ በቀን አንድ ጊዜ መንደረተኞቹ ላይ መሮህ አለባቸው ። በሳቸው ዘንድ ሁሉም «ዘረቢስ» ነው ።

ወይዘሮ ባፈና ባፋቸው ቢናገሩም ብቻቸውን እህል አይቀምሱም ። የጣሳ ቤት ቤተኛ አዳሪዎች የሚልሱትን አጥተው ሲቸገሩ የሚመጡት እርሳቸው ዘንድ ነው ። በሰፈሩ እማማ የማይላቸው የለም ። መሮህ ሲጀምሩ መንደርተኞቹ ፤ «እንግዲህ ጀመሩ ፤» ብለው ወደየቤታቸው ከመግባት በስተቀር አይናገሯቸውም ። ታዲያ ዝምታቸው የባሰውኑ ያበሳጫቸዋል ። ውሀ አስመጥተው «የተከልፉን» ስም በመጥራት ዶሮው ላይ ካፈሰሱ በኋላ ፤ ልጆቻቸውን አስከትለው ፤ «ተመስገን ፤ ለዚሁም ተመስገን ፤ እሰይ እንኳን መጣችሁ ፤» እያሉ ወደቤት ገቡ ።

ቤቱ ውስጥ የነበሩት በርጩማዎች ፤ አግዳሚ ወንበርና ፤ በስተግራ በኩል ጥግ የነበረችው መደብ አሁንም አሉ ። አልተለወጡም ። እድሜአቸው ከአበራ እድሜ ይበልጥ እንጂ አያንስም ።

ወይዘሮ ባፈና ደፋ ደፋ ማለት ጀምረዋል ። እየፎከሩ ፤ እየደነፉ የሚቀርበው ወጣቸው አበራን ትዝ አለውና ምራቁን ዋጠ ። አርፈው ለመቀመጥ ቢፈልጉም የሰንበቱ ነገር ፤ የእድሩ ጣጣ ፤ የልቅሶውና የማስተዛዘኑ ፈሊጥ ፤ ጧትና ማታ ቤተ ክርስቲያን የመሳሙ ጉዳይ ጊዜ አይሰጣቸውም ፤ አርፈው መቀመጥ አይችሉም ።

ባሻር ቁመታቸው ደፋ ደፋ እያሉ ፣ «የዘንድሮስ መከ
ረም አይበለው ። የኔን ተከልዬ ለሰው አይሰጠው ፣ ሁሉን
ተናዬን ይቆረጥመኛል ፣ ሰሞኑን የያዘኝ ውጋት ቅስፍ
አድርጎ ይዞኝ በስቃይ ነው የከረምኩት ፣ ዛሬ ደሞ የያዘኝ
የራስ ምታት ይዞ ይፈልጠኛል ፣» በማለት ማማረራቸው አል
ቀረም ። አምናም ፣ ካቻምናም ፣ ከጥንትም ጀምሮ ስለህመ
ማቸው ሳያወሩ ጀምበር ወጥታ የጠለቀችበት ቀን የለም ።
በህመም ምክንያት ግን አልጋ ላይ ውለው አያውቁም—ለመ
ሀላ እንኳን ። ሀሞት መስሎ አንገታቸው ላይ ይታይ የነበ
ረው ንቅሳት የቀድሞውን ድምቀቱን አጥቷል ። የተወ
ማያያው ያንገት ቆዳቸው ግማሹን ሸፍኖታል ። ዱሮ ከስር
ኩል ጋር እንደፈርጥ ይንቦገቦጉ የነበሩት አይኖቻቸው በመ
ጠኑ መጨናበስ ጀምረዋል ። ቅሳታቸው ወደ መገርጣት
አዘነበለ እንጂ አልጠፉም ።

ምሳ ቀርቦ ትንሽ ከተበላ በኋላ ወይዘሮ ባፌና መብላታ
ቸውን ትተው ጣታቸውን እንጀራው ላይ ጠራረጉና ፣ «ፊታ
ውራሪ በነበሩበት ጊዜ በዛሬ ቀን ይህች ደጅ በስንት መኳ
ንንት ታሸበርቅ ነበር ፣ የበቅሎውና የጋሻጃግሬው ብዛት
ያንን ግዳ ሞልቶት ይተርፍ ነበር ። እኔም ፣ እነ እመቤቴንና
እነ ትርንጎን አስከትዬ ብቅ ባልኩ ቁጥር ነጠላው ከፊቴ
ኋ—ኋ እያለ ይጋረድልኝ ነበር ። እንደማይሆን የለም ፣
ያ ደጉ ዘመን አለፈ ። ፍሪዳው እዚያ ሲጣል ፣ ሙዳው
ሲቆረጥ ፣ አረቂ በያይነቱ ሲከፈት ፣ ጠጁ እንደዋዛ ሲቀዳ—
አይ ዘመን... እንደማይሆን የለም ። የጨዋ ልጅ አልቆ
ቀን ዘራሽ የበቀለበት ዘመን... አዲስ አበባ እንዲህ የዘረቢስ
ጎርኖ ሆና ትቅር !» እያሉ እንባቸውን በተጨማደዱት
ጉንጮቻቸው ላይ ያወርዱት ጀመር— እንደወትሮአቸው ።

ቤታቸው መጥቶ ስለዱር ኑሮአቸው በማድነቅ ያንሳባቸው ሰው ሳይበላና ሳይጠጣ አይወጣም ። ሲነሽጣቸው የቋጠሩት ገንዘብም ቢኖር አውጥተው ይሰጣሉ ። የመንደሩ ሰዎችም ሆኑ ከሩቅ ዝናቸውን የሰሙ መንገደኞች በተቻገሩ ቋጥር ጉራ ብለው ስለወይዘር ባሬና የቀድሞ እመቤትነት ማውራት ከጀመሩ የፈለጉትን ሳያገኙ አይሄዱም ። በዚህ የተነሳ ከቤታቸው እንግዳ አይጠፋም ።

አቶ አባተ ስላባታቸው ስለ ፊታውራሪ ወርቄ ባንት ይርጉ ሲሰሙ ልዩ ትምክህት ፊታቸው ላይ ይቀረጻል ። አበራ ግን ይሰለቸዋል ። ከመሰልቸትም የተነሳ ይቅበዘበዛል ። ስለበሽታ አይነትና ስላለፈው ዘመን መስማት አጉል ዘበት መስሎ ስለሚሰማው ፣ እናቱ ሲያወሩ በሙሉ ልቡ አያዳምጣቸውም ።

እልፍነሽ ፣ አንዳንዴ ተነስታ ለባሏ ጠላ ፣ ለአበራ ደግሞ እሱ ካመጣው ዉስኪ ትቀዳ ነበር ። ለአበራ እንዳንዴ የምታጕርሰው ጕርሻ ላንድ ሰው ቁርስ ሊሆን ይችላል ።

አቶ አባተ ከንፈራቸውን በመምጠጥ ራሳቸውንና እናታቸውን ካጽናኑ በኋላ ወደ አበራ መለስ ብለው ፣ «ያባትህ ክብርና ዝና ምን ያህል እንደነበረ ብታውቅና ቢገባህ ካንዱ መስሪያ ቤት ወደሌላ እያልክ ወደኋላ አትቀርም ነበር ። ገድሉ በቀብህ፣ የትምህርት ቤት ጓደኛህ፣ ዛሬ የትና የት ደርሷል ። ጓደኝነትህ ከሱ ጋር ቢሆን እንዴት በበጀህ ፣ ሰው ማለት እሱ ነው ። ያ ከይሲ ፣ ዘረቢስ ጓደኛህ እንደሆን ለምንም አይረባህም ፣ ሰው ትኩር ብሎ ሲመለከት ቡዳ ይመስላል ፣ አይን ሰበር ማድረግ እንኳን ያባት ነው ። ቢያደርግ

ትም እሺ ማለት የወጣ ልጅ ተግባር ነው ። እንዲል ምክር ከበድብ ይቆጠራል ይበለኝ ፤» እሉት እየተገረሙ ።

ለከባችሁ ባይገጥምና ባትጣጣሙ ነው እንጂ ፤ ሀይለማር ያም የኔና ያንተ ወንድምነት ተቀናቃኝ አይደለም…»

ሰው እንጂ ፤ በኔና ባንተ መካከል ያለው ጋኔን እሱ ነው ። የሚጋርመው ነገር ከኔ ይልቅ ለሱ ታደላለህ ። ካልጠፋ ጓደኛ ሰው እንዴት እንዲህ ያለውን ይመርጣል ባካችሁ — ስጋን ከሲጋ የሚያለያይ ።»

አበራ ዝምታውን አጸና ። ከወንድሙ ጋር መከራከር አይወድም ። ታዲያ ወንድሙን በጣም አበሳጭቶ የሚያ ስቆጣቸው ዝምታው ነው ። «ትእቢት ነው ፤ ትእቢት ነው ። የተማራችሁት ሁሉ ትእቢተኛነትን ነው ፤ ሌላ አይ ደለም ፤» ይሉታል ። አንዳንዴ ብሶበት ሲከራከራቸው ደግሞ ፤ «አዋቂዎች ! አዎን ፤ ከናንተ የበለጠ አዋቂ የለም ፤» በማለት ይሳለቁበታል ።

«አንደ ገድሉ ያለ ጓደኛ ብታገኝ ሰው ትሆን ነበር። »
«ጋሼ ፤ ብትተወኝ ምናለበት !»

«ምንነው ቢተውት እቴ…ባለንዳመት ምን ከርክር ያስፈልጋል !» አለች አልፍነሽ ። አበራን ለማጉረስ ኩርማን እንጀራ ቆርሳ ስትጠቀልል ነበር ። «ይቺን ብቻ በሞቴ ፤ ሁለተኛ አልመለስም፤» ካለች እምቢ ለማለት አይቻልም— መመለሷ አይቀርም ።

ወይዘሮ ባፈና የጐረሱት እንጀራ አልዋጥላቸው ብሎ ከጉሮሮአቸው ጋር ይታገል ነበር ። እንደምንም ታግለው የጡና ፤ «ልጄ ፤ አጥንቷ ጥሩ የሆነ ሚስት አግብተህ የልጅ

ልጀን ስሚ ፣ እያት ተብዬ እንድኖት ብታደርገኝ ምናለበት! አባተን እንደሆነ ተከልዬ ለልጅ አላደሉትም» አሉት፣ ለጆሮው እንግዳ ያልሆነ ጥያቄ ነበር ። እልፍነሽ ድንተኛ ጣር እንደያዘው ሰው ሲዘገንናትና ፊቷ ሲለወጥ ተመለከተ ። የጉረሰችውን ሳትውጥ እንባ እየተናነቃት ወደ ጓዳ ሮጠች ።

አበራ ተከትሏት ወደጓዳ ገባ ። ጉንጮቿን እያርጠበ እንደጐርፍ የሚወርደው እንባዋ ጸሀያማ ፊቷን በማጥቆሩ እያዘነ ፣ «ምን ነካሽ እልፍዬ? ለቅሶውን ተይና ንገሪኝ» አላት ።

የእናቱ አልጋ ቦታውን አልለቀቀም ። ከሰንት ዘመን ጀምሮ የተጠራቀመ እቃ መኝታ ቤቱን ሞልቶታል ። መኝታ ቤት ብቻ አይደለም ። ሌማቱም ፣ ገንቦውም ፣ ጋኑም ፣ በርሜሉም ፣ ስልቻውም ፣ ጆኒያውም ፣ ምኑም ፣ ምናምኑም ክፍሉን ሞልቶታል ። የውሻ ቡችላ የሚያካክሉ አይጦች በየስርቻው ይሯሯጣሉ ።

ጠጋ ብሎ አቀፋት ። እንባዋን በነጠላዋ ጫፍ ጠራረገችና ቀና ብላ እያየችው ፣ «አበርዬ ምን ባደርግ ይሻለኛል! እግዜርን ምን ብበድለው ነው እንዲህ ያለው ጣጣ ውስጥ የጨመረኝ ?» አለችው ፣ በተለመደው ልዝብ አንደበቷ ።

«ምንድነው እሱ ?»

«እዚህ በመጣሁ ቁጥር እማማ በሆነው ባልሆነው ነገር ኦስታከው ልጅ ባለመውለዴ ይጸጸቱብኛል ። ጥፋቱ ከኔ አይደለም ። ወልጄ ብስም እኔም ደስ ይለኛል ። ማህጸኔ ልጅ እንደሚያፈራ አውቃለሁ ። ብቻ ምንላድርግ ? ወርቄ

ሆቱ እንዳልሄድ መግቢያ የለኝም ፡፡ አልተማርኩም ፡፡ ድህ
ወዳጆቼ አልቀዋል ፡፡ የማገኘው ባርባ ቀን አድሌ ነው ፤
በለው አይደለም ፡፡ ግን እንዲህ እየተሰቃየሁ ከመኖር ብሄድ
ይሻለኛል ፤ እግዜር እንደሆን የከፈተውን ጉሮሮ ሳይዘጋ
አያድርም ፡፡»

«አይዞሽ እልፍዬ ፤ እማዬ እንደመጣላት ትናገራለች
እንጂ ለከፋት ብላ አይደለም ፤» ብሏት አገጯን ይዞ ፊቷን
ወደላይ ቀና አደረገና ስቆ ሊያስቃት ሞከረ ፡፡ ፊቷ ዝናብ
ካባራ በኋላ ጸሀይ ልትወጣ የቃጣችበት ሰማይ መምሰል
ጀመረ ፡፡

የእናቷን ድምጽ ሰማ ፡፡ ቀስ ብለው መናገር አይችሉም ፡፡
«ሰንቷን ብዬ ፡፡ እግሬ ከመሬት ተነስቶ ያብጣል ፤ ትንፋሼ
ያስኛል ፤ ሰሞኑን ብርድ ብርድ ይለኛል...» እያሉ የበሽ
ታውን አይነት ይዘረዝሩት ነበር ፡፡ ወዲያውኑ ደግሞ ስለ
የንት መኳንንቶች ማውራት ይጀምሩና ትንሽ ቆይተው
በዚያን ዘመን ስለነበራቸው ክብርና ድሎት፤ውበትና ጌጥ
ማውራት ይጀምራሉ ፡፡ ከፊታውራሪ ወርቄ በኋላ ያገቧቸ
ውን ሶስት ባሎች አበሳጭተውና ስካራም አድርገው ያባረ
ሯቸው ጥንት ፊታውራሪ ቤት በነበሩበት ዘመን ስለነበራ
ቸው ክብር ፤ ውበት ፤ ጌጥና ድሎት ወሬ ነበር ፡፡

«አንተ ብትረዳኝ ይህ ሁሉ አይደርስብኝም ነበር ፡፡
የእማማ ጸጸት ፤ የወንድምህ ንዝንዝና ብስጭት ሰውነቴን
አይጨርሰውም ነበር ፡፡»
«ምን አድርጌ ነው የምረዳሽ ?»

«ሚስት አግብተህ ። አንተ ልጅ ብታገኝልኝ እርይ ብዬ እንቅልፍ ይወስደኝ ነበር ። አበርዬ ተሰቃየሁልህኮ ።»

«ታዲያ ሚስት ፈልጊልኝ ብዬሽ መቼ ሆነልሽ ?» አላት ፣ የቀልዱን ነበር ፣ ሲያጽናናት ። ፊቷ ፣ አሻንጉሊት መሳይ ፊቷ እንደ ጧት ጸሀይ የሚሞቀውን ፈገግታ ተጐናጸፈ ፣

«ሁላገርሽስ ?» አለችው ፣ ከዚህ ቀደም ያስተዋወቀችውን ልጃገረድ በማስታወስ ።

«እሷ እንደስሟ ሁሉም ያምራታል ።»

«አበስኩ ጌታዬ ፣ ጌጤነሽስ ?»

«ፈገግታዋ ጌጥ የለውም ፣ በዚያ ላይ ጅል ነች ።»

«ያቶ ጥሩነህ ልጅስ ? ማንነው ስሟ እቴ ? እዎን ፣ ቱቱ ። እሷ ቆንጆ ልጃገረድ አይደለችም ?»

«ልጃገረድ አይደለችም ።»

«አበስኩ ገበርኩ ጌታዬ ! ታዲያ ምን ይሻላል ?»

«የሚሻለውን ማን ያውቃል ? ማን ያውቃል ?» አለ በትካዜ ። ልቡ እንደደንጊያ ከበደው ። አዘነላት ። የእልፍነሽ ስቃይ ተሰማው ። ለማንም እንዳላዘነ አድርጐ አዘነላት ። ሀሊናውን ፈተሸ ። ምን ባደርግላት እርይ ብላ ለመተኛት ትችል ይሆን ? በማለት ራሱን ጠየቀ ። መልስ አልነበረውም ።

ሁለት ወር ፣ ሁለት ወር ፣ ከዚያ በኋላ—

## ፭

አበራ ማክሰኞ ጧት ወደ አራት ሰአት ገደማ ወደቢሮ ሲገባ ሳየው ሰው ከቅዳሜ የፋሲካ ስኡር ጀምሮ እረፍት ላይ የቆየ አይመስልም ። እንቅልፍ አጥተው የከረሙት አይኖቹ ቀልተው በዙሪያቸው ያለው ቆዳ ጠቁሯል ። እር ምጃው ሁሉ ንቃት የለውም ። እያንዳንዷን እርምጃ እየተጠራጠረ የሚወስድ ይመስላል ። በራሱ ላይ የነበ ረው ትምክህት ፤ ንቃትና እምነት የት ሄዱ ? የስራ ጓደ ኞቹ መስኮት ከፍተው እሱ ነው ? ወይስ እሱ አይደለም ? በማለት እየተጠራጠሩ ይመለከቱት ነበር ።

ሁለት ቀን የቆየ ጢም የቀይ ዳማ ፊቱ ላይ ከሩቅ እንደ ሚታይ ሁሉ ፤ ዞማ ጠጉሩ ላይ ተርከፍክፎ ያልደረቀው ውሀ ጤዛ ይመስል ያንጸባርቃል ። ሁለት ወር...... ሁለት ወር..... ማንነታችንን ለማወቅ አስቀድመን በመጠኑ መሞት ያሻናል...... እና እያንዳንዷ እርምጃ ወደ ግቡ ፤ ወደ መጨ ረሻ ግቡ ፤ ወደ ማንነቱ ትመራዋለች ። ‘ግን እንዴት እር ግጠኛ ልሆን እችላለሁ ?...’

ቢሮው ውስጥ ያለው አየር ሻግቷል ። የበናይት አደራ ሽቱ እንኳን ሊለውጠው አልቻለም ። ጥቁር የእጅ ቦርሳዋ ከጽህፈት መኪናው ጐን ጠረጴዛ ላይ ተቀምጧል ።

አብጧል ። እሷ ግን የለችም ። ሰማያዊ እንደልማዱ ሆዱ የተሰጠፉት የጫማ ዱካዎች ጉልተው የወለል ምንጣፉ ላይ ከፋፍቶ ቁጭ ሳይል ጥቂር ይታያሉ ። ሁለቱን መስኮቶች የልብ አውቃ ገረዱ ገሸሽ ቡና አዘዘ ። ባለፉት ሁለት ቀኖች አውቋል ፤ ከዚህ ቀደም አድርጋዋለች ። ለምን እንደሆነ ነበር ። ግን ባለፉት ሁለት ሴት ቤቱ አሳድሮ አያውቅም ቀኖች ብቻውን ለማደር አልቻለም ። ሴት እጠገቡ መኖር ነበረባት ። ለመተኛት ፈጽሞ አልቻለም ነበር ። ሁለት ወር — ሁለት ወር ! የእንጀራ እባቱ እስከሬን እየመጣ ፤ «አንተ ወስላታ ፤ ተነስተህ በር አትከፍትም !» በማለት ከእንቅልፉ ያባንነው ነበር ።

«ከራሴ ጋር ፊትለፊት መጋተር አለብኝ ፤ ሌላ መውጫ መንገድ የለኝም ፤ » ብሎ የቀዘቀዘ ቡናውን ባንድ ትንፋሽ ጨለጠው ። ሲጃራውን አቀጣጠለና ከዚህ ቀደም በእርሳስ የነደፋቸውን ስእሎች ከጠረጴዛው መሳቢያ ውስጥ አውጥቶ እንደካርታ ፊቱ በመደርደር አንድባንድ በተቺ አይን ይመለከታቸው ጀመር ።

ያውራ ዶሮ ጥርስ የመሰለውን የስናይትን ረጅም አፍ ንጣ ፤ የልብ ቅርጽ ያለውን ከንፈሯን ፤ ረጅም ፊቷንና የብር እንክብል የሚያካክሉትን አይኖቿን በወረቀት ላይ በሚገባ ለመግረዝ ችሏል ። የሹራብ ስራ ይዛ የጽህፈት መኪና ጓላ እግሮቿን አጣምራ ቁጭ ብባለች ። ስእሉን «ስራ ብዙ» ሲል ሰይሞታል ። ሁለተኛው ስእል የሚያሳየው ዘመትር ቢሮው እየመጡ ቡና የሚጠጡትን ጓደኞቹን ሲሆን የሲጃራው ጢስ ፤ የቡና ሲኒዎች ፤ ጠረጴዛው ላይ ያለው ፋይል

ክምር በየእለቱ የሚደረገውን ሁኔታ ያሳያል ። «ትልቅ የሀላፊነት ስሜት» የሚል ስያሜ ሰጥቶታል ። ሶስተኛው ስእል «የተንቀሳቃሽ አእምሮ» የሚል ሲሆን ፤ የስእሉ አቀማመጥ ከላይ የሚታይ ሆኖ ጠረጴዛው ኋላ የተቀመጠው ሰው ጭንቅላቱ ብቻ ነው የሚታየው ፤ ትልቅ ጭንቅላት ። ራሰበራ ክብ አራት ማእዘን መስሎ የሚታየው ጠረጴዛ ላይ ብዙ የመስሪያ ቤት አርማ ያላቸው ወረቀቶች ተደርድረዋል ። የበላይ ፊርማ የሚጠባበቁ ይመስላሉ ። ወረቀቶቹ ላይ ተጽፈው የሚታዩት ግን እንደ ጠረጴዛው ክብ ፤ ሶስት ማእዘን ፤ አራት ማእዘን ሆነው የተጠላለፉ መስመሮች ናቸው ። ወንበሮቹም ሆኑ የስልክ መቀበያዎቹ ልዩ ልዩ ቅርጽ የያዙ ናቸው ። ይህ ሶስተኛው ስእል ፤ የተፈጥሮ ችሎታው ፤ የህይወቱ ጥሪ እንዴት እንደተቀሰቀሰበት አስታወሰው ። የእውነተኛ ችሎታውን ያገኘው ፤ ያወቀው ቢሮ ገብቶ ስራ በሌለው ቁጥር ትርጉም የሌላቸውን መስመሮች በሚሞነጫጭርበት ጊዜ ነበር ። ይህን ዘመን ሁሉ የት ነበርኩ? በማለት ሳምንት ሙሉ እየሰከረ ቤት ውስጥ ተዘግቶ የኖረበት ጊዜ ነበር ። የፈሰሰ ውሀ አይታፈስም በማለት ከቤት ወጣ ። ቢሆንም ከዚያ በኋላ ተመልሶ የዱሮው አበራ ለመሆን አልቻለም ። ትናንት አልነበረም ፤ ነገም የለም ፤ ከዛሬ ፤ ካሁን በስተቀር ..........

ሶስቱም ስእሎች የጐደላቸው ነገር አለ ። ምን እንደሆነ ግን አበራ ሊያውቅ አልቻለም ።

መስመሮቹ ህይወት የላቸውም ። አይነጋገሩም ። የት እንደሚሄዱ ፤ ወዴት እንደሚያመሩ የሚያውቁ አይመ

ስሉም ። በየስእሉ ላይ የሚታየው ጥላና ብርሃን አቀነባ
ውን ጊዜ ዝናብ እንዳረገዘ ጉም ስለሚከብድ ፣ ሌላው
ነገር ይጫንና ለብቻው እምባገነን ይሆናል ። ነገር ግን
በሰናይትና በጽህፈት መኪናው መካከል ሊኖር የሚገባው
ግንኙነት በስዕሉ ላይ አይታይም ። ከጽህፈት መኪና ኋላ
የተቀመጠች ማንም ሴት ልትሆን ትችላለች ። ሁለተኛውም
ስእል ተመሳሳይ ጉድለት አለው ። ስእሉ ስለሀላፊነትም ሆነ
ስለተጉለቆለ ህሊና የሚናገረው አንዳችም ነገር የለውም ፣
ሰዎቹን ከከባቢያቸው ጋር አወሳስቦና አዋህዶ አያሳይም ፣
የጊዜውንና የሁኔታውን መንፈስ አይማርከም ። ዋጋ የለ
ውም ። የስእሎቹ ጥልቀት ......«ወየጉድ ! ለምንድነው ሁል
ጊዜ ከሩቅ የምጀምረው ? እና ለምንድነው ሁል ጊዜ ፊት
ለፊት የሚያፈጡብኝ ? አፍጥጠው ሲመለከቱኝ ተወግረ
ህይወት የሚለምኑ ይመስላሉ ። የፈጠርኳቸው ሳይሆን
እንግዳ መሰዩ አታያቸዋለሁ ። ከኔ ምንም የላቸውም ፤
እኔም ከነሱ ምንም የለኝም ። በነሱ ውስጥ ራሴን አላይም ፣
ገና ባእዳን ነን!» በማለት በጣሚቅ ከቆሻሻ ማጠራቀሚያው
ውስጥ ጣላቸው ።

ከዚያ ፣ ስእሎቹን በጣሚቅ እንደጣላቸው ከአእምሮው
ጓዳ ውስጥ አንድ ነገር ፈልፍሎ በአይነ ህሊናው ይታየው
ጀመር ። ሸርተቴ ከሚጫወትባት ኮረብታ ላይ ቁጭ ብሏል ፣
የኔታን ከነጥምጥማቸው የወርቅ አለንጋቸውን እንደያዙ
ስእል ለመስራት ይታገላል ። ወንድሙ ፣ አቶ አባተ የ
ዡሰት አዲስ ደብተር በዚሁ ሙከራ ለማለቅ ደርሳለች ፣
«ምንድንነው የምትሰራው አንተ ?»

ወንድሙ ከበስተጀርባው ሲመጡ አልሰማም ። ልብ አላ ደረገም ። አእምሮው ፣ ስሜቱ ፣ ሀሳቡ በሙሉ በስራው ተመስጧል ።

«ምንም ።»

«እስቲ ወዲህ በለው ፣ በልኮ ! ወቸ ጉድ ፣ እንዲህ ልትማ ሪ ትበት ኖሯል ደብተር ፣ ደብተር ያልከው፣ አንተ ወስላታ፣ በል ሁለተኛ ያ-ለምድህል !»

ጉያው በቁንጥጫ ሲደብን ፣ የጆሮ ግንዱ በጥፊ ሲናጋ ይሰማዋል ። «ሁለተኛ አይለምደኝም …ጋሼዬ …አይለም ደኝም ! አይለምደኝም ! አይለምደኝም !»

በሁለተኛው ቀን ዱኔታ በወርቅ አሰንጋቸው ጀርባው ሰምበር እስኪያወጣ ድረስ ገረፉት ። ጥፋቱ ለሌሎቹም ምሳሌ ሆነ ። ዳግመኛ አልሞከረውም ።

ሀሳቡን ከራሱ ውስጥ አውጥቶ ሰናይትን ለመጥራት አሰበ ነበር ። «ምንድነው ብቻህን እንደእብድ እየለፈለፍክ እንዲህ በንዴት የምትበጣጭቀው ባክህ ?»

ተሰማ ደጃኔ ነበር ። አጭር ቁመናው ሳይሆን ወፍራም ሰውነቱ በሩን ሞልቶታል ። እንደዘይት የሚሳብ ፈገግታው ፣ በጣም የበሰለ ዱባ የሚመስለው ክብ ፊቱ ላይ እንደሙጫ ተጣብቋል ።

«ህይወቴን !» ብሎ መለሰለት ።

ተሰማ ፣ የቀኝ እጁ ላይ ያሰረውን በልብና ፣ በፈረስ ሉቱ ያጌጠውን ከወርቅ የተሰራ ሰንሰለት እያንቃጨለ ገብቶ ቁጭ አለ ።

«ምንነው ጃል ፤ እንኳን ጾመ ልጓሙን ፈታልህ እን ለኛም እንጂ ?!»

«ምነተ እፍ መቼ ታስሮ ያውቃልና !»

አበራ ከስናይት በስተቀር ሌላ ሰው ለማነጋገር ፈቃደኛ አልነበረም ። ተሰማ አንዴ ከገባ እንደማይወጣ ስለሚያውቅ ተስፋ ቆርጦ ቁጭ አለ ።

«እረ ጾሚአለሁ ፤ እማማ በኩዳዴ አታስበላኝም !»

ከወፍራም ፤ አጭር ሰው እንደዚያ ያለው ቀጭን ድምጽ እንዴት ሊወጣ እንደሚችል አበራ ሁል ጊዜ ይገርመዋል ፡ ተሰማ ሲጃራ አውጥቶ ክብሪት ይጠብቅ ነበር ። ክብሪት ፈጽሞ አይዝም ። ከቢሮ ቢሮ እየሄደ ክብሪት ሲለምን ይውላል ። ለምን ክብሪት አትይዝም ? ብለው ሲጠይቁት የሚሰጠው መልስ ፤ ለሲጃራ የማወጣውን ወጭ ለመቀነስ ይረዳኛል ብዬ ነው ይላል ። ታዲያ አንድ የክብሪት እንጨት ሰጥተውት አንድ ሲጃራ ስለሚወስዱበት ወጭው አልቀነሰም፡ ግን ክብሪት ለምን እንደማይዝ ሁሉም ያውቃሉ ፤ በክብሪት አስታኮ ከቢሮ ቢሮ እየዞረ አብዛኛውን ጊዜ ስለሰው ፤ በተለይ ደግሞ ስለሴቶቹ ማውራት አለበት ። ሳያወራ የዋለ እንደሆን ይፈነዳል ፤ «ይህ ወሬ እንዲዛመት ትፈልጋላችሁ ?» ሲባል ፤ አዎንታ የተጨመረበት እንደሆን ፤ መልሱ ፤ «ተሰማ ዘንድ ሂዱ» ነው ። በዚያ ላይ ባራት ግድግዳ ተከቦ ብቻውን ለመቀመጥ በጣም ያስፈራዋል ።

አበራ ክብሪት ጭሮ ሲጃራውን ለኮሰለት ። የማገውን የሲጃራ ጢስ ባፍንጫውም ባፉም እየተፋ ፤ «እማማ በቅርቡ

የን ለሀከምና ወደ እንግሊዝ አገር መሄዱ ነው ባከሀ ፤ እሱም እብሬእት ባልሄድ አልቀርም ፤» አለው ።

«እንግሊዞች ከጋዜጣ በቀር ስራ ፈተው ሰው ማነጋገር አይወዱም ፤ ታዲያ ክብሬት መግዛት ሊኖርብህ ነዋ ፤» እንዳለው ባልቻ ዋቆ እራት ማእዘን ቅርጽ ያለውን ጭንቅላቱን ወደፊት አስቀድሞ ዘው ብሎ ገባ ። የብብቱና የማጅራው ጠረን ቀደመው ። «ማንነው የቀደመኝ? ስርጥ የመጣው ለተሰማ ክብሬት ልስጥ ነበር ።» ድምጹን ሲሰሙ በተራው ጉሮር የሚናገር ይመስላል ። መጠጥ አቫከሮት ሳይሆን አይቀርም ። ጧት በማለዳ ሁለት ቀንዶ እግሬ መንገዱን ሳይነሳ ወደቢሮ አይመጣም—ለመሀሳ ።

አበራ ፤ «ጥፋተኛው እኔ ነኝ ፤» ብሎ ሲጃራ አውጥቶ ጋበዘው ። ባልቻ የሚኖረው በሰው ሲጃራ ነው ። የሰጠውን ሲጃራ ጠጋ ብሎ ሲያቀጣጥልለት እራት ማእዘን ቅርጽ ፊቴ ጉልቶ ታየው ።

አፍንጫው ድፍጥጥ ብሎ ወርዶ ከስር ሰፊ ይሆንና ወደላይ ስለሚገለበጥ ቀዳዳዎቹ ውስጥ የበቀሉት ጠጉሮች እንደራዲዮ አንቴና ቆመው ይታያሉ ። ከንፈሮቹ የቡሄ ሙልሙል ያካክላሉ ። እግሬ መንገዱን አንስቶ የመጣው ቀንጆ እንደ ስልጆ አፍንጫ ይሰንጋል ። የእጁ ላብ የያዘውን ሲጃራ ማራስ ጀምሯል ። ስላምታ የሰጠው ሁሉ እጁን በመሀረብ መጥረግ አለበት ።

ባልቻ ከቢሮ ቢሮ የሚዞርበት ሌላ ምክንያት አለው ። ሌጣ ነጋዴዎች ፤ ፖሊሶች ፤ ቤት አከራዮች ፤ መጠጥ የሚችና ገንዘብ ያበደሩት አያሌ ሰዎች ቢሮው አያስቀም

ሁሉ ልዩ ዘዴ ፈጥሯል ። ካንዱ ተበድሮ ሰነዚያ ሁሉ ልዩ ዘዴ ፈጥሯል ። ካንዱ ተበድሮ ሰሌላው ይከፍላል ። ታዲያ ምንጊዜም አዳርሶ ሳይጨርስ አልቀረም ። የአበራ ሀምሳ ብር ቀልጣ ቀርታለች ።

እጁ ውስጥ በላብ የወረዛችውን ሲጃራ በስመመግ እየሳበ ፣ «አበራ ፤ ምንነው ዛሬ የከፋህ ትመስላለህ ? ሀዘኑንና ብስጭቱን ለኔ ተውና ይልቅ ቡና በለን ፤ ተሰማ እንደሆን ዛሬ እማማ የኪስ ገንዘብ አልሰጡትም መሰለኝ...» ከማለቱ ፤ በቀለ ሮባ ረጅም ፣ ቀጭን ቁመናውን እንደ ሽመል እያውዘገዘገ መጥቶ ሲቀመጥ የተቀባው ሽቶ ክፍሉን በሙሉ አወደው ።

የባልቻ ብብትና ሜማ ጠረን ፤ የበቀለ ሽቶና የሲጃራው ጢስ ለቢሮው በዚህ አለም የሌለ ሽታ መስጠት ጀመሩ ። «ይህንን ልብስ በስንት ገዛሁት ? እስቲ ገምቱ ! አላማረብኝም ?»

በቀለ የሚናገረው በጥድፊያ ነው ። ሲናገር እንደቤት ይቅለሰለሳል ። ሲሄድም ይውዘገዘጋል ። የለበሰው ልብስ ዳለቻ ሆኖ ከሀር ጨርቅ የተሰራ ነው ። ቀይ ከራቫት አስሮአል ። የፈነዳ ጽጌ ረዳ ቅርጽ ያለው ከከራቫቱ ጋር ተመሳሳይ የሆን መሀረብ የደረት ኪሱ ላይ ሰክቷል ። ረጅም ፣ ዞማ ጠጉሩ በቅባት ወደኋላ ተለጥጦ ተኝቷል ። የሸሚዙ እጅጌ ቁልፎች ፤ የከራቫት መያዣው ፤ የእጅ ሰንሰለቱና የሰአት መያዣው ተመሳሳይ ናቸው ። ዘወትር ሙሽራ ፣ «ሽክ ታ» የሚል ቅጽል ስም ተሰጥቶታል ። «አምሮብሀል» አለው አበራ ፤ እንቅልፍ አጥቶው በቀሉት አይኖቹ እያማተረው ፤ «ሰሞኑን የፈጸምከው ሮብዱ የለም እንዴ ?»

የአበራ ጥያቄ ያስደሰተው መሆኑን ቢታ ቤት መልኩ
ላይ የሚወራጨው ስሜት ይገልጻል ። ረጃጅም እርጨ።
ላይ ጣቶቹን ተመለከተ ። «ፋሲካን ያሳለፍኩት ካንዲት
አገር አሸነፈች ከምትባል ኩረዳ ጋር ነበር ፣ ታዲያ ምን
ይሆናል ፣ እያስቀሰች ስቃዩዋ ደስታ ላይሆነኝ ።»

ሶስቱም ተያዩ ። የማያስለቅሳት ቤት የለችም ። ይህ
ን ጀብዱ ለማውራትና በየጊዜው የሚገዛውን ልብስ ለማ
ሳየት ከቢሮ ቢሮ መዞር ግዴታው ነው ። የበቀለ ተሳላኪ
ነው የተሰበሰበበትን ቢሮ ከመፈለግ በስተቀር ሌላ ስራ
ፈጽሞ የለውም ።

ቡናው ቀርቧል ። ቢሮው በሲጃራ ጢስ ታፍኗል ።
ሲጃራ ካፉ የማይለየው ባልቻ ዋቆ ብቻ ነው ። ባንድ የክ
ብረት እንጨት ሲጃራ ይመነገዘራል ። በቀለ እዩኝ ሲል ፣
ተሰማ ስለእናቱ ለማውራት ሲሞክር ወሬው እጅግ ደርቶ
አለ ። ቆይቶ ወደ ሀሜት ፣ ቀጥሎ ወደዚህ መንግስት አቋም
ተራመደ…ሶስቱም የሚናገሩት ስለዚህ መንግስት ጉድለት
በመሆኑ አበራ በመጨረሻ ትእግስቱን ጨረሰ ። ከዚህ ቀደም
የማያውቀው ንዴት በራሱ ላይ በድንገት ገነፈለበት ።

ጠረጴዛውን በቡጢ መትቶ ሲያፈጥባቸው ሶስቱም
ጸጥ ብለው ይመለከቱት ጀመር ። በረጅሙ ተነፈሰና እንዲህ
ሲል ተናገረ ፡—

«እነሱ ፣ እነሱ የምትሉት ፣ እነሱ እነማን ናቸው ?
እኛስ እነማን ነን ? እነሱ እነሱ ከማለት ራሳችንን ዞር ብለን
እንመልከት ። ወደኛ ዞር ብንል የምናየው ምንድን ነው ?
ባ ቢስ ፣ የምኞት አታሞዎች ሆነን እንገኛለን ። ከካስቴሊ

ወይም ከሎምባርዲያ ፤ ከራስ ወይም ከኢትዮጵያ ሆቴል ስን
ወጣ ፤ ለማኞች ላይ እያገሳን የምናልፈው እኛው ነን ። ወ
ናቻችን መሬት ቆፍረው ፤ ከመሬት ላይ ያገኙትን በሌተው
እጦት ካፍንጫቸው ስር ሳንድ ቀን ሳትርቅ እዚያው መሬት
ላይ ሞተው እንደሚቀበሩ እያወቅን ፤ በስምንትና በዘጠኝ
መቶ ብር ላይ ደመወዝ ይጨመርልን በማለት ጧት ማታ
ማመልከቻ የምናንጋጋው እኛው ነን…

«ለሀገር ልማት ይህን ያህል ከደሞዛችሁ ስጡ ብን
ባል መጀመሪያ የምናለቅሰው እኛው ነን ። መንግስት ጀርባ
ላይ እንደ ቋሀን ዘለአለም ተጣብቀን የምንኖረው እኛው ነን፣
ከምግዚት ጉያ ወጥተን ፤ በሁለት እግራችን መቆም ያስፈ
ራናል ። በራሳችን ላይ እምነት የለንም ። ማንነታችንን
አናውቅም …

«እንደኛ ያሉት ሰዎች በየትኛውም መንግስት፡ ስር
ያው ናቸው ፤ ከማማረር አያልፉም ። ታዲያ ይህ ሁሉ የጓደ
ወሬ ፤ ይህ ሁሉ አሉባልታ ፤ ይህ ሁሉ የትችት መአት ፤
የራሳችንን ጉድለት ለመደበቅ ፤ ወኔ ቢስነታችንን ለመሸፈ
ንና ያደፈውን ህሊናችንን ለመደለል ነው እንጂ ለሌላ አይ
ደለም ። ግን እስከመቼ ድረስ ? እስከመቼ ድረስ ?»

አበራ እንደጨረሰ ተስማ ቀደም ብሎ ፤ «እናጨብጭብ
እንጂ ! እንዴት ያለች ንግግር ናት ባካችሁ…እናቴ ትሙት
ግሩም ናት !» እለና ማጨብጨብ ጀመረ ።

«እርፈ ቢጃራ እንዳልቃርምበት ነው ይህ ሁሉ !
ደሞዝ ጭማሪ መጥታለች መሰለኝ !»

«ልብስ ነው እንጂ! ስላንዱ ቤት የሰባ ወሬ ነበረኝ ። ለሹመት ታጭተሀል እንዴ ?»

አበራ በዝምታ ሶስቱንም አንድባንድ ተመለከታቸው ። የሚሉትን አይሰማም ። የተናገረውን አእምሮው ውስጥ አንድ ባንድ እያገላበጠ ያሰላስል ነበር ። ዝግ ባለ ድምጽ ፤ «የኢትዮጵያ ተስፋዎች ፤» ካለ በኋላ ፤ «ግን ጥፋቱ የማን ነው ?» ሲል ራሱን በራሱ ጠየቀ ።

ሶስቱም እየተያዩ ጥለውት ወጡ ። አበራ የሀይለማርያምን ሀሳብ እንዳስተጋባ አወቀ ። ፊታችንን በመስተዋት ስንመለከት ምን ይታየናል ? እምን ፤ አበራ በገዛ አይኑ ራሱን ተመለከተ ። የተመለከተው ነገር አላስደሰተውም ። ራሱን በጣም ጠላው ። በፍጥነት ሰናይትን ካለችበት አስጠራት ።

የለበሰችው ያገር ልብስ ረጅም ቁመናዋን ደርበብ አድርጎታል ። ረጅም ሆኖ የተቆለመመው አፍንጫዋና እንደሳንቃ ሰጥ ያለው ግንባሯ ባለባበሷ ምክንያት እንደ ኣር ጎልተው አይታዩም ። ትላልቅ ውብ አይኖቿ ከሸማዋ ንጣት ጋር ይወዳደራሉ ።

«እስካሁን የት ነበርሽ ?»

«እነእያልነሽ ቡና ጋብዘውኝ ነው... የቡና እድር አለን ።»

በተለይ «ቡና» ስትል የላይኛው ከንፈሯ ደንበኛ የልብ ቅርጽ ይወስዳል ። «እናቶቻችን የተውትን በየመንደሩ ቡና የመቃረም ልማድ እናንተ እንደገና በየቢሮው መጀመራችሁ ይገርማል !»

«ወንዶቹም ቢሆኑኮ...» ብላ የጀመረችውን ሳትጨርስ የሹራብ መስሪያ ክሮቿን ነክሳ እንደመቅለስለስ አለች ።

«ትዳይ ነበረኝ ፤ በሩን ዝጊውና ነይ ፤» አላት ።

ሰናይት በር የመዝጋት ልማድ የላትም ። ጠረጴዛውን ዞሮ መጥቶ አንዱ እንግዳ መቀበያ ሶፋ ላይ ቁጭ ካለ በኋላ ፊት ለፊቱ እንድትቀመጥ በእጁ አሳያት ።

በመስኮት የሚመለከታቸው ሰው እንዳለ በማለት ትላልቅ አይኖቿ ይቃኛሉ ። የመርበትበት መልክ ሰፍ ኖባታል ። አበራ ሊጠይቃት የፈለገውን ሲያስብ የሰና ይትን መለወጥና መርበትበት አላስተዋለም ነበር ።

«ስለሉሊት ታደሰ የምታውቂው ነገር እንዳለ ልጠ ይቅሽ ነበር ።»

«ወንድ ሁሉ ስለሷ የሚጠይቀኝ ለምንድነው ? እኔ እላየ ለድኳት ! ወይስ አቃጣሪዋ ነኝ ?»

ድንገተኛ ንዴቷ አበራን አስደነገጠው ። ምን እንዳ ናደዳት ግን አልገባውም ። የት ገባ ሳይባል ፊቷ ላይ ያዙኝ ልቀቁኝ እያለ ይንቆራጠጥ የነበረው ደሟ ባንዳፍታ ቁል ቁል ወርዶ ጠፋ ። አበራ ከመገረም አልፎ ግራ ገባው ።

«ምናጠፋሁ ? አጥፍቼ እንደሆን ይቅርታ አርጊልኝ ፤» አላት ። ከዚህ በኋላ የጀመሩት ንግግር ወዴት ሊያመራ እንደሚችል ለመገመት አልቻለም ነበር ። በዝምታ ተው ጠና አቀርቅሮ ይጠባበቃት ጀመር ። አሁንም ቢሆን የተላ ሳተበት ቦታ ጨርሶ አልገባውም ። ምንነው ባልጀመርኩት ኖሮ በማለት ጸጸት አደረበት ።

«የለም ፤ አበራ አንተ ምንም አላጠፋህም ፤ ያጠፋሁት እኔ ነኝ ። ያናደደኝ የራሴ ምኝነት ነበር ።» ጥለቱ አይን የሚግ

ርበውን ቀሚቧን ከስሯ ሳብ ሳብ አድርጋ ወንበሯ ላይ ተመቻቸችና ፣ «ስለሉሊት ለማወቅ የምትፈልገው ነገር እንዳለ ልትጠይቀኝ ትችላለህ ። በደስታ የማውቀውን ያህል እመልስልሀለሁ ። ግን ፣ ስለሷ ሁሉን ነገር አውቃለሁ የሚል በዚህ አለም ያለ አይመስለኝም ። ኑሮዋ በምስጢር የተዋጠ ነው ።» አለችው ፣ በቀዘቀዘና እርጋታ ባለው መንፈስ ።

ይሄኛውን የጠባዩዋን ክፍል አበራ በሚገባ ያውቃል ። አንቱታውን ትታ አንተ እንድትለው ያስተማራት በስንት መከራ ነበር ። ሉሊት በዚያ ቀዝቃዛ በሆነውና ከሩቅ የሚሰማ በሚመስለው ድምጿ ፣ «ሴቶች ላይ ኩራትና ትእቢት ታበዛለህ ፣ በእምብርክክ መጥተው እስኪለምኑህ ድረስ ዞር ብለህ አታያቸውም አሉ ...» ስትል የነገረችው ነገር ትዝ አለው ። የስናይት ድንገተኛ ቁጣ ተገለጸለት ። ይህም ሆኖ ስናይት እንደማትዋሸው ያውቃል ። ስትዋሽ ይዟት አያውቅም ። ስሜቷን እንኳን አልደበቀችውም ።

ስለሷ ግራና ቀኝ የሚሰማው ፣ ሳያናግሯት የማታናግር ፣ ከተናገረች ደግሞ ስሜቷን የማትደብቅና ሀሜተኛ አለመሆን ሲሆን ፣ የምትታማበት ነገር ቢኖር በቁመቷ ከመጠን በላይ መርዘም ብቻ ነው ። በዚህ ላይ ታዲያ ጡቶቿ ከመጠን በላይ ትልቅ ሆነው ስለሚታዩ «ሱቅ በደረቴ» የሚል ቅጽል ስም ተሰጥቷታል ።

የስናይትና የሀይለማርያም ጠባይ ባንዳንድ በኩል ስለሚመሳሰል አንድ ቀን አስተዋወቃቸውና እሷ ከሄደች በኋላ ! «ታዲያስ ?» ቢለው «ሆሆ ! ተንጠራርቼም አልደርባት» ሲል አሹፎ በተራ ቀልድ መለሰለት ። ሀይለማርያም

ፊቶች ላይ እንከን አያጣም ።

አንድ ቀን ደግሞ ባሏቻ ዋቄ ሰናይት የጋበዘችውን ቡና ካጣጣመ በኋላ ፣ «ለመሆኑ ሰርግሽን መቼ ነው የምንበላው ?» ብሎ ሲጠይቃት ጊዜ ፣ «በድንኮች መሀል ተፈጥሬ ምን ተስፋ አለኝ ብለህ ነው ?» ስትል መለሰችለት ። «ስለሉሲት የምታውቂውን ያህል ብትነግሪኝ ይበቃል ።» አላት ፣ ወደሌላ እያየ ።

ስለሉሲት ለማወቅ ለምን እንደፈለገ አልጠየቀችውም ። ትጠይቀኛለች በማለት መልሱን ያዘጋጅ ነበር ። ምክንያቱን ታውቀዋለች ። ሉሲትን አይቶ የማይመኛት የለም ። እድሜ ስውነቷን ዝግንን አድርጎ ለጊዜው ቢያስቀናትም ፣ በግድ መንጭቃ ከአእምሮዋ ውስጥ አስወጣችው ። የልብ ቅርጽ ያለው ከንፈሯ ስለደረቀ በምላሷ ልሳ አራሰችው ።

«መቼም ፣» አለች ፣ «ስለሉሲት አውቃለሁ ማለት ዘበት ነው ። የሚያውቃት የለም ። ኑሮዋ ሁሉ በምስጢር የተዋጠ ፣ የተዘጋ መቃብር ናት ። ትዝ እንደሚለኝ ንግድ ትምህርት ቤት በነበርንበት ጊዜ አንድም የቤት ጓደኛ አልነበራትም...» «ለምን ይመስልሻል ?»

የምትለውን ለመስማት ጆሮዎቹን እንደጥንቼል ቀሰረ ። ትኩር ብሎ እየተመለከታት ጥፍሮቹን በጥርሱ ይከረክም ጀመር ።

«በውብቷ አልነበረም ። በቁንጅናም ቢሆን ከማንም አትበልጥም ነበር ። ግን ያያት ሁሉ ይመኛት ነበር ። ልመትልሽ

ይላት ነበር ። ለዚ ሲሉ እምዋቻቸውን እርግፍ አድርገው የተውም አይታጡም ።»

ሐሳብ ገባ

«በመጀመሪያ ወንዶችን ፊት አትንፍግም ። እንዲያውም እየሳቀች በማግባባት እንዲቀርቧት ታደርግ ነበር ። ወንዱ የልብ ልብ ተሰምቶት ሲጠጋት ከጀመረ በኋላ ግን ዞር ብላ አታየውም ። እርግፍ አድርጋ ትተውዋለች ። እሷን ወዶ ፍዳውን የጨረሰ አንድ የባንክ ሰራተኛ ትዝ ይለኛል ። የሚያዝኑለትም ፤ የሚስቁበትም ነበሩ ። እንዲያውም አን ዳንድ አይናውጣዎች እንጠራልሀለን እያሉት ከአውሮራ ቡና ቤት አይስክሬም በጅምላ ያስገዙት ነበር ። ከክፍል ስትወጣ አይኗን ለማየት ስራውን ትቶ የትምህርት ቤቱ ግንብ ስር ተለጥፎ ይውል ነበር ። በጣም ስላሳዘነኝ አንድ ቀን ከክፍል ለእረፍት ስንወጣ ያዝኳትና 'ሉልዬ ይህን ሰው ለምን እንዲህ ታሰቃይዋለሽ ? ባይሆን እንኳን ከስራው እንዲሆን ለምን አልፈልግህም ፤ አልወድህም አትይውም ፤ እንዲሆን ለምን አልፈልግህም ፤ ቁርጡን ያወቀ ሰው ምርጫ ይኖረዋልና' አልኳት ። የንን ቀዝቃዛ ፈገግታዋን አሳየችኝና 'ወንዶች ሲሰቃዩ ማየት ደስ ይለኛል ፤ ባይገባሽ ነው እንጂ እነሱም ክፉ ጨካኞች ናቸው—አረመኔዎች!' ብላኝ ጥላኝ ሄደች ። ሴቶቹ እንደሆኑ ኛ ለገና ወዳጆቻችንን ትቀማናለች በማለት ፈርተው ይጠሏት ነበር እንጂ እሷ ለነሱ ክፉ አታስብም ነበር…»

የሉሊትን ቅዝቃዜ እያስታወሰ ፤ ቅርብ ሆና ሩቅ ያለች መምሰሏን እያሰበ ፤ «ይገርማል ! እውነትም እንዳልሽው ነሩ ምስጢር ነው ፤» በማለት የበናይትን አስተያየት አብሰ

ለስለና ፤ «ለመሆኑ ስለወላጆቿ የምታውቂው ነገር አለ ?» ሲል ጠየቃት ።

«ምንም የማውቀው ነገር የለም ። የሚያውቅም ሰው እስካሁን አላጋጠመኝም ። ብቻ ፤ እቴጌ መነን ትምህርት ቤት የሚያውቋት ልጆች እውነተኛ ስሟ ሱሲት እይደለም ሲሉ ሰምቻለሁ ። ማን ነበር የሚሏት ልጄ ?... ረሳሁት...»

አንድ ነገር ሊጠይቃት ሲያስብ ከመስሪያ ቤቱ የሚኒስትር ቢሮ ጋር ተጣብቆ የቆዬ ነባር ተላላኪ በሩን ብርግድ አድርጐ ሲቆም ፤ ግዙፍ ሰውነቱ በሩን ሞላው ። ልዩ ስልጣን ያለው ስለሚመስለው በተላከ ቁጥር በር አያንኳኳም ። በዚያ ላይ ገንዘብ በአራጣ ስለሚያበድርና በየበአሉ ሰንጋ እያረደ ቅርጫ ስለሚያስገባ አብዛኛዎቹ የመስሪያ ቤቱ ባልደረቦች ፤ በተለይ ባልቻ ዋቆ ፤ ባለ እዳዎቹ ናቸው ።

«ሚኒስትሩ ባስቸኳይ ይፈልጉሀል ፤» ብሎት ፤ ሁለቱ እናፍ ላፍ ገጥመው ሲያወሩ በመድረሱ አፍሮ ፤ በሩን በፍጥነት ዘግቶ ወጣ ።

አበራ ሚኒስትሩ ቢሮ ሲደርስ ልዩ ጸሀፊው እንደሌላው ጊዜ አኩርፎና በበላይነት ስሜት ተኮፍሶ አላገኘውም ፣ ሰተት ብሎ ገባ ።

የቢሮው ስፋትና የጠረጴዛው ግዙፍነት ከውጭ የሚገባው ሰው ላይ የማነስ ስሜት ያሳድራል ። የቢሮውን አራት ማእዘን እየታከከ የሚዘረው ቀይ ፤ ወፍራም ምንጣፍ እግሮችን እርምጃ እየቆጠሩ እንዲወስዱ ያደርጋል ። ቢሮውን የሞላው ግርማ ሞገስ ስለሚጫን ሳይወዱ በግድ ያስደነግጋል ።

«ያገን ጥናት ምን አደረስከው ?» ብለው ጠየቁት ፤ በወፍ ራም ድምጽ ። ጥያቄአቸውን ከትእዛዝ ለይቶ ለማወቅ ያዳ ግታል ። ቀና ብለው ሰው አለማየት ልማድ አላቸው ። ዘሬ በፊት የቀረበውን ያርሩራጃዎች የውስጥ አስተዳደር ደንብ ተመልክቶ አስተያየቱን በሪፖርት መልክ እንዲያ ቀርብላቸው ጠይቀውት ነበር ።

«ጥናቱ የተሟላ ስታቲስቲክስ ከሌለው ...»

«የሕምቧይ ካብ ይሆናል ለማለት ነው ? ችግሩ ሳይገባህ አልቀረም ። ብቻ ያስጠራሁህ ለዚህ አልነበረም ። ያባተ ወንድም አይደለህም ? አዎን ፤ ትመሳሰላላችሁ ። ጥሩ ችሎታ እንዳለህ ስምቻለሁ ፤ እኔም ራሴ ደርሼበታለሁ ። ብቻ አንድ ቦታ ረግተህ ለመስራት አትችልም ። ስህተት ነው ። የረጋ ወተት ቅቤ ይወጣዋል ሲባል አልሰማህም ? ብቻ እናንተ ወጣቶች ሁሉንም ነገር ባንዴ ለማድረግ ትጣ ደፋላችሁ ። ሲሮጡ የታጠቁት ሱሪ ሲሮጡ ይፈታል የሚ ለውን ምሳሌስ አልሰማህም ? ብቻ ለማንኛውም ነገር ብዙ ታስቦልሀል ። ልጅ እንደሆኑ ዘለአለም አይኖርም ። ረጋ ብለህ ስራ ። ለመሆን ስንት አመትህ ነው ?»

ሰው የሚያስበውን አስቀድመው የማወቅ ችሎታ ያላ ቸው ስለሚመስላቸው የለም ማለቱ ቀርቶ አዎን ለማለት እንኳን ጊዜ አይሰጡም ። «ሰላሳ ሁለት !» አላቸው ፤ አቀር ቅር ። ሁለት እጆቹን ወደኋላ አጣምሮ ቆሞ ነበር ። ሰው ቢሮ አቸው ገብቶ አይቀመጥም ። ቁጭ በል ማለት አያውቁም ። «በጣም ልጅ ትመስላለህ ። ግን አርጅተሀል ። ለመሆን ሚስት አግብተሀል ?»

«አላገባውም ።»

«ታዲያ ምን ትጠብቃለህ ? ሁሉም በልጅነት ሲሆን ያ
ራል ። ለእድገትም ሆነ ለማንኛውም ነገር የቤተሰብ ሀ
ሬነት ጥሩ ዋስትና አለው ። አባትህ ስመ ጥር ጀግ
ነበሩ ። ታዲያ አስብበት እንጂ ፤ ችሎታ ብቻውን መ
ይበቃልና ፤» አሉት ።

እሳቸው ሲናገሩ አበራ አቀርቅሮ የባህል ቀጽእና እያ
ገደዳቸው ፤ የተጣላውን በማስታረቅ ፤ የተቸገረውን በ
ማለድ ፤ ለግል ጉዳዩ የመጣውን በማነጋገርና ከግባብ ው
የሆነ ደጅ ጥናት በመስማት ሚኒስትሮች ጊዜአቸውን ከጠ
ቀልጣፋ የሆነ ዘመናዊ አስተዳደር እንዴት ሊመ
ይቻላል ? እያለ ያስብ ነበር ። ዝም ካሉ ማሰናበታቸ
መሆኑን ስለሚያውቀው አበራ እጅ ነስቶ ወንድሙን በል
እየረገመ ወጣ ።

፮

ያን ቀን ማታ አበራ ሀይለማርያም ቤት ሲደርስ የቤቱ
መብራት በሙሉ እያይዘ ሲጽፍ አገኘው ።

መታጠቢያ ቤቱ ብቻ ሲቀር የተቀሩት ሁለት ክፍሎች
ተጣብበው የሚታዩት በመጽሀፍ ነው ። ከሳጠራ የተሰ

አራት መቀመጫዎችና አንድ መለስተኛ ጠረጴዛ ፤ ለእንግዳ መቀበያና ለምግብ ቤት የሚያገለግለውን ክፍል ሞልተውታል ። ወለሉ ላይ ያልጠፋ የሲጃራ ቁራጭ አራት ቦታ የበደሳት ዝንጉርጉር የደብረ ብርሀን ምንጣፍ ጣል ብላለች። በጣውላና በሸክላ ከተሰራ መደርደሪያ ላይ በደንብ ከተደረደሩት መጻህፍትና ውድ የሆኑ የግድግዳና የራስጌ መብራቶች በስተቀር ትርፍ ጌጥ በቤቱ ውስጥ አይታይም ።

ሀይለማርያም ባንድ ጊዜ ሶስት ወይም አራት መጻህፍት የማንበብ ልማድ ስላለው ፤ እንዱ ሲሰለቸው ወደሌላው ይዞራል ። ስለዚህ የተገለጡ መጻህፍት በየቦታው ይታያሉ ። በፍጥነት አንብቦ ለመጨረስ የፈለገውን መጽሀፍ ደግሞ በኪሱ ይዞ ይዞራል ።

ትንሽ የኮሬንቲ ምድጃ ላይ ከትንሽ ማንቁርቆሪያ ውስጥ የሚንተከተከው ቡና ፤ ቤቱ ውስጥ ያለውን አየር ባይበክለው ኖሮ ክፍሉ እና እና በሽተተ ነበር ፤ ወይም ሰው ያልኮበኘው ቤተ መጽሀፍ ሽታ በወሰደ ነበር ።

«ምን ሆነሀል .አበራ ? የደከምክ ትመስላለህ ። ለለውጥ ያህል ጢምህን አልተላጨህም ፤ ሸክ አላልክም ። ትንሽ መሞት እንደጀመርክ ይታየኛል።» አለውና ፈልቶ ሊገነፍል የደረሰውን ቡና ለማውጣት ሄደ ። ቡናው እስኪ.ሰክን ድረስ አልጠበቀም ። ሁለት ሲኒ ቡና ቀድቶ ሲያበቃ አንድ ለራሱ ፤ አንድ ለአበራ ሰጠና ቁጭ አለ ።

«ቡናዬ እንዴት ነው ?»

«ግሩም ነው ።»

ጥሩ አይደለም ያሉት እንደሆነ የቡናውን ጣእም ግ
ምነት ለማሳመን ሲል ጢት ድረስ ይከራከራል ። ሀይለ
ርያም በጣም የሚመጻደቅበት ነገር ቢኖር በሚያፈላው
ቡና ጣእም ነው ።

አበራ እንቅልፍ ያጡትን አይኖቹን አሻሸና አፉ
ከፍቶ አዛጋ ። የቀሉት ትላልቅ አይኖቹ እንባ አቀረሩ ።
አበራ መስልቸት ሲጀምር ምናልባት በደቂቃ ውስጥ አስር
ጊዜ ያዛጋዋል ።

«የመጣኸው ልታዛጋብኝ ነው እንዴ !»

«ሁሉም ነገር በድንገት ይማታብኝ ጀመር ። ባለፉት ሶስት
ቀኖች እንቅልፍ ባይኔ አልዞረም ። አንተ ፤ የወንድሜ
ሚስት ፤ ወንድሜ ፤ ናላዬን ልታዞሩት ነው ። ብሎ ብሎ
ዛሬ ወንድሜ ምን እንዳደረገኝ ታውቃለህ ?»

«ምናደረጉህ ?

«ትልቅ ወኔና ጅልነትን የሚጠይቅ ነገር ነው ያደረገኝ ።
ሚኒስትራችንን አማላጅ ላከብኝ - ስራዬን ተቆናጥጬ
እንድኖር ፤ ሚስት እንዳገባ ። ከራሱ ፍላጐት በስተቀር
የኔ ምንም አይታየውም ። የኔ ቀርቶ የሚስቱ ስቃይ አይገ
ባውም ። ችሎታዬን ለመሞከር በምዘጋጅበት ጊዜ እንዲህ
ያለው ጥቃቅን ጣጣ ሲገጥመኝ የማደርገው ነገር መላ
ቅጡ ይጠፋኛል ፤ ይማታብኛል...»

«የተማታው ነገር ሊገባኝ አልቻለም ። ምናልባት አታው
ቀውም እንጂ እንደሴት በደመ-ነፍስ ብቻ ነው የምታስ
በው ። አንዳንድ ጊዜ ጭንቅላትህን ተጠቀምበት ። ምር
ጫው ቀላል ነው— የወር ደሞዝህን ተቆናጥጠህ ፤ ሚስት

አግብተህ ፤ ልጅ መፈልፈል ፤ ወይም ችሎታህን አውቀህ ፈጣሪ መሆን… ?»

«እዎን ፤ ሁልጊዜ በአእምሮ የመጠቀም ችግሩ እዚህ ላይ ነው ። ማንኛውም ነገር ቀላል ሆኖ ይታያል ። ለወንድሜና ለምወዳት ሚስቱ ያለኝ ግዴታስ ? በኔ ምክንያት ሲሰቃዩ…» «ይህንን ነውኮ የምልው ። የምታስበው በልብህ ነው ። ያለህን ምርጫ አቀረብኩልህ እንጂ አንዱን ትተህ ሌላውን ምረጥ አላልኩህም !»

ሀይለማርያም ቡናውን ጨርሶ ሌላ ለመቅዳት ተነሳ ። አንድ ስኒ ከቀዳ በኋላ ከማንቆርቆሪያዋ ውስጥ ወሀና የቡና ፉቄት ጭምርባት እንደገና ጣዳት ። ቤት ከኖረ ማንቆርቆሪያዋ ከምድጃ አትወርድም ። የአበራ ቡና ቀዝቅዞ ነበር ። ሀይለማርያም ሳያየው ስኒውን አንስቶ ኩሶ እንደሚጠጣ ሰው ባንድ ትንፋሽ ጨለጠው ። ለለቡና ጣእም በመከራከር ምሽቱን ለማሳለፍ አልፈለገም ። ሀይለማርያም ቡናውን ቀድቶ ሲመለስ ወደ ጠረጴዛው ሄዶ ቅድም ሲጽፍ የነበረውን ነገር ላንዳፍታ ተመለከተውና እልፍ መጥቶ ከወንበሩ መቀመጫው ላይ ተመቻችቶ ተቀመጠ — ለመስማትም ሆነ ለመከራከር ዝግጁ መሆኑን እያሳየው ።

ምንነው እንደ ሀይለማርያም ብቸኛ ባደረገኝ ፤ በጥቃቅን የቤተሰብ ጣጣ ሳልቸገር …በሴን ግዴታ ሳልታሰር … ከዱኑት ኖሮኝ ፤ እያለ ያስብ ነበር ።

ሀይለማርያም የቤት አሽከር እንኳን የለውም ። ብቻውን ራሱን ችሎ ከራሱ ጋር መኖርን የቻለ ሰው ነው ። አሽከር ለመቅጠር አቅቶት ወይም ከሰው ጋር መኖሩን

ጠልቶ ሳይሆን ማንም ሲያስቸግረው እየጻፈ ከመጻፍቱ ጋር መናርጋ ስለመረጠ ብቻ ነው ። ከአበራ ሌላ ቤተሰቦቹም ፣ ዘመዶቹም ፣ ጓደኞቹም መጻህፍቱ ናቸው ። ዋሺ አበራ ፣ እንዳልኩህ ለሁሉም ምርጫው ያንተው ነው ። ጭንቅላትህን ተጠቀምበት ። ስላንተ የማውቀው አንድ ነገር አለ ፣ ይህም ከውስጥህ ወጥቶ ብርሀን ለማየት የሚፈልግ አንድ ነገር እንዳለ ይገባኛል ።»

በድንገት አበራ ከመቀመጫው ተነስቶ ፣ ጥፍሩን በጥርሱ እየከፈከመ ጥቂት ከተንጐራደደ በኋላ ቆም ብሎ ፣ «እንግዲህ ቅርጫስሁ ። ገና ለገና ወንድሜ ልጅ ይፈልጋል ብዬ የበሰበሰ ጉመን ሆኜ ለመቅረት አልችልም ፣» ሲል ለሀይለማርያም የሚናገር ሳይሆን ከራሱ ጋር ክርክር የያዘ መስሎ ፣ መድረክ ላይ ከወጣ በኋላ የሚናገረው ነገር እንደ ጠፋበት ተዋናይ እጆቹን በከንቱ ያወናጭፍ ነበር ።

«ይሆን ስትል በጭንቅላትህ እንደተጠቀምክ ትስፋ አደርጋለሁ ። ከልብህ መጥቶ እንደሆን ግን ዋጋ የለውም ፣ ቢሆንም ልገፋፋህ አልፈልግም ፣ የቤተሰብ ግዴታና ጣጣ ምን እንደሆን ከረሳሁ ዘመን የለኝም ። እኔ እንደሆንኩ ለወላጆቼ እንደ ክርስቶስ አንድ ነኝ ።»

«እድለኛ ነህ ።»

«አይመስለኝም ። ለሌላ ነገር እንኳን ባይሆን የወላጆችን ጣእምና የቤተሰብን ፍቅር ማወቅ ላንድ ደራሲ ይጠቅማል» አለና ማንቆርቆሪያዋ እንደገና መንተክተክ ስለጀመረች ተነስቶ ሄደ ።

አበረ ወደ ጠረጴዛው ጠጋ ብሎ ሀይለማርያም ሲጽፍ የነበረውን ማንበብ እንደጀመረ ፣ ተንደርድሮ መጥቶ እ

ጣለው ። ማንቆርቆሪያዋን ቸኩሎ በደንብ ሳያስቀምጣት ቆርቶ ናሮ ከምድጃዋ ላይ ተንሸራተተችና ተደፋች ።
ሰጋሩም ቡና አስደፋህኝ !» አለ እጆቹን አወናጭፎ ።

ሀይለማርያም ጽፎ ሳይጨርስ ድርሰቱን ለሰው ማሳየት አይወድም ። የሰው ሀሳብና ትችት ሳይጨምርበት መጀመሪያ ጽፎ መጨረስ አለበት ።

«አሁንስ ስለምንድንነው የምትጽፈው ?»

ሀይለማርያም ከዚያ ቀደም ስለአንድ ናላው በፍቅር የሰከረ ሰው ጽፎ ነበር ። ያ ሰው የሚወዳትን ለማግኘት ባለመቻሉ በእውነም ሆነ በእንቅልፉ ስለሷ ያልም ነበር ። ግን ባል አላት ፤ አንድ ቀን የፈለገው ነገር ሆነ ። በህልሙ ሲያገባት አየ ። ጧት ሲነቃ ካጠገቡ ስላጣት ፤ 'እንዴት ጥላኝ ትሄዳለች !' ብሎ በመናደድ ወደቤቷ ገስግሶ ሂዶ ፤ 'ለምንድንነው ጥለሽኝ የምትሄጂው ......ትናንት አግብቼሽ ዛሬ ... ሳታስጨርሽኝ...' እያለ ግራ የገባትን ሴት ሲተናነቃት ባሏ ደርሶ በጥይት ይመታዋል ። ጣር ሲተናነቀው ህልም መሆኑ ይገለጽለታል ። ግን ምን ይሆናል !»

«እስከመጨረሻው ድረስ ብትቆይ ምናለበት ። ሶስት ወይም አራት ወር ይፈጅብኛል ።»

ግን አበራ ለማድረግ ወይም ለማወቅ የፈለገውን ነገር ወዲያውኑ ካላደረገ ወይም ካላወቀ እንደማይለቀው ስለሚያውቅ ተስፋ ቆርጦ እጆቹን አወናጭፎ ሲያበቃ ፤ «ቡናውን ስላስደፋህኝ ገና ይቅርታ አላረኩልህም !» አለውና ስለሚጽፈው ድርሰት እንዲህ ብሎ አጫወተው ፦—

«ስለአንድ ሀብታም ገንዘብ ምልቶት የተረፈው ሰው ነው ። እድሜውን የፈጀው ገንዘብ በመሰብሰብ ነበር ። ሰው እያ

ይጠራጠራል ። በዚህ የተነሳ ብቸኛ ሆኖ ምንም ። ሁሉንም ይጠራጠራል ። ይህ ጓደኛው ፍጹም ሲኖር አንድ ቀን የልብ ጓደኛ ያገኛል ። ይህ ጓደኛው ፍጹም ሰው ነበር ። ታዲያ ሰዉዬው ጓደኛው የነገረውን ሁሉ ይሰማል ሆኖ ይቀበላል ፤ ይፈጽማል ። ቀንም ሆነ ማታ ፤ ሌሊትም ሆነ ጧት አይለያዩም ፤ ፍጹም አይለያዩም …

«ከጊዜ በኋላ ያ ሰው ገንዘቡ ያልቅበትና እጦት አፋፍ ላይ ይደርሳል። ጓደኛው የሚሰጠውን ምክር መስማት ፤ መቀበል ፤ መፈጸም ያቆማል ። ቀስ በቀስ እየተራራቁ ይሄዱና ከናካቴው ይረሳሳሉ ። ጓደኛው ጨርሶ ይጠፋል ። ያ ሰው ይጸጸታል ። ጸጸቱ ግን ሊመልሰው አልቻለም …

«ወይኔ ጓዴ ! ወይኔ ጓዴ ! ጓዴን ገደልኩት ! በገዛ እጄ ገደልኩት !» እያለ ሲጮህ ሄዶ ለፖሊሶች እጁን ይሰጣል…

«ፖሊሶቹ ተጣድፈው 'ሬሳውን አሳየን ፤ ወንጀሉን የፈጸምክበትን ቦታ አሳየን' ሲሉት ፤ ደጋግሞ ፤'ይሄውና' እያለ ራሱን ያሳያቸው ነበር ። ምርመራው ይቀጥላል ፤ ይፋፋማል ። በየቀኑ ያንኑ ጥያቄ ይጠይቁታል ። እሱም ይሄውና እያለ ይመልሳል ። ከስንት ምርመራ በኋላ በመጨረሻ ህሊናውን የሳተ መሆኑን ይገነዘቡና ወደ አማኑኤል ይልኩታል ። ከጓደኛው ጋር እንደተለያዩ ይቀራሉ ።»

አበራ የድርሰቱ ፍሬ ነገር እንደገባው ለማሳየት እሺ እንደሚል ሰው ራሱን ነቀነቀና «ጓደኛው የሰውዬው ህሊና መሆን ነው ፤ አይደለም !» ሲል ለማረጋገጥ ጠየቀው ።

«ነው ።»

«ህሊናና ሰው የተራራቁበት ዘመን መሆኑን ለማስታወስ ነው?»

«ይሆን ይሆናል !»

# ፮

አበራ ወርቁና ሉሲት ታደሰ በየቡና ቤቱ ደጅና በየዳንስ ቤቱ አብረው መታየት ከጀመሩ ሶስት ሳምንት አልፎአቸዋል ። ለአበራ ጊዜው በድንገት ተነስቶ ክንፍ ያወጣ ይመስለው ነበር ።

ይሂት ሂዶ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ቲያትር ፊትለፊት ካለው ሲዮን ቡና ቤት ፣ ወይም ንግድ ትምህርት ቤት ፊትለፊት ካለው አውሮራ ቡና ቤት ፣ ወይም ሜክሲኮ አደባባይ ነጋዴዎች ምክር ቤት ህንጻ አጠገብ ካለው ቡና ቤት ሲቆም ፣ ሎቅ በደረቴዎች ፣ ጋዜጣና ሎተሪ ቲኬት ሻጮች ፣ ማማጠራጊዎች ፣ ደላላዎችና ለማኞች የመኪናውን መስተዋት ስለሚተናነቁ እንዲያነጋግራት ፋታ አይሰጡትም ነበር ። ሎቅ በደረቴዎች ሴት ሲያዩማ ይብስባቸዋል ።

አበራ ከሉሲት ጋር ባመሸ ቁጥር ቤቷ ካደረሳት በኋላ የዱ ቤተኛ አዳሪዎች መንደር መሮጥ እንደልማድ ሆኖበት ነበር ። ቤተኛ አዳሪ አቅፎ ሲቃዩን ካስታገሰ በኋላ «ሁለተኛ አይኗን አላይም» ይላል ። በሁለተኛው ቀን ፣ «መጥተህ ሥራ አድርሰኝ !» ወይም «መጥተህ ቤት ውሰደኝ ፣» ወይም «ጠኮር ሰራ ቤት አድርሰኝ» ስትለው ግን አይቀርም ፣ ይሄዳል ። አይኗን ለማየት ሲቸኩል ትናንት ምን ብዬ ነበር ? ብሎ ለማስታወስ ራሱን ለመታዘብ ጊዜ የለውም ።

የትናንቷ ፃቻ ትገዛ የሚለው በሴተኛ አዳሪ ባብና ኸቶ ሰውነቷ ከራስ በኋላ ብመሆኑ ውስጥ አድሮ በራሱ ላይ የመሳቅ ልማድ አመጣ ። አልፎ አልፎ «ምን የሚያስቅ ነገር አገኘ ብኝ አንቱ !» የሚሉት ሴተኛ አዳሪዎች አልጠፉም ።

አንድ ቀን አንዷ «ሄደው መሳቂያዎን ይፈልጉ !» በማለት ከላዩዋ ላይ ገፍትራው ተነሳች ።

«እረ ባንቺ አይደለም ።»

«ታዲያ በማንነው ?»

«በራሴ ነው የምስቀው ።»

«ኡሁ ቱ ! እርስዎ ከማን በለጡና !» ስትል አንገቷን እንደ እስክስታ ወራጅ እንክት አደረገችው ።

በምን ምክንያት በራሱ ላይ እንደሚስቅ ሊያስረዳት አልሞከረም ። ሌላ ቦታ ሌላ ቤት ፍለጋ ሄደ...

ሉሲት እንደሆነች አንድ ቀን እንኳን ተሳስታ ቤት ለምን አትገባም ? በማለት ጠይቃው አታውቅም ። እሱም ቢሆን ቤትሽ ልግባ ፤ ወይም ቤቴን ላሳይሽ ብሏት አያውቅም። ቤቷ ካደረሳት በኋላ ያንን ቀዝቃዛ ፈገግታዋን አሳይታው ትሸኘዋለች ።

እሱም ምንም ሳይላት ስለሚሄድ እያደረ ይገርማት ነበር ። በተለያዩ ቁጥር «ቆይ አንተ ትእቢተኛ ! የማንበረ ከክህ ጊዜ ይመጣል ፤ ባራት እግርህ እንደውሻ ሳላስኬድህ የቀረሁ እንደሆን እኔ ሉሲት አይደለሁም !» እያለች በልቧ ሳትዝትበት አታድርም ። ታዲያ ይህን ባለች ቁጥር ልቧ ይፈልገዋል ። በእንቅልፍ ልቧ እበራን ለመዳሰስ ትን ጠራራለች ።

ቀዝቃዛ እቅፍ ውስጥ አስገብታው እየናቀችው ፣ እያስለ
ጣችው ፣ አዋርዳ ልታስቃየው ትመኛለች ። ምኞቷ ጣር
የሆነባት እንቅልፍ አጥታ የምታድርበት ሌሊት አለ ።
ከአበራ ጋር መውጣት ከጀመረችበት ቀን አንስታ ትራሷን
ተንተርሳ ያደረችበት ሌሊት የለም ።

መጀመሪያ ጉያዋ ውስጥ አግብታ ትራሱን ታቅፈዋ
ለች ። ትራሱ የሰውነቷን ሙቀት መውሰድ ሲጀምር አው
ጥታ ትጥለዋለች ። ይህን ስታደርግ አልጋን የተወጣች
ይመስል ውስጣዊ ደስታ ይሰማታል ።

ቤቷ የቱ እንደሆነ ለይቶ አያውቅም ። ኡራኤል ከአርሻ
ሚኒስቴር በስተጀርባ ሲያደርሳት ከመኪና ወርዳ ፣ በኮረ
ኮንች መንገድ ወደ መንደር ገብታ ትጠፋበታለች ። ተከት
ሏት የምትኖርበትን ቤት ለማየት ሞክሮም ፣ አስቦም አያ
ውቅም ። ጠይቋትም አያውቅም ። «ይህ የድብብቆሽ
ጨዋታ መጨረሻው ከምን ይሆን ?» እያለ ማሰቡ አልቀ
ረም ። እሷም በበኩሏ ከዛሬ ከነገ እንበረከከዋለሁ እያለች
መመኘቷ አላቋረጠም ።

አንድ ቀን ከእቴጌ ሆቴል በስተጀርባ ካለው ጠጉር
ስሪ ቤት ወስዷት በምሽት ከምትኖርበት ሰፈር አደረሳትና
እንደልማዱ ቀዝቃዛ ፈገግታዋን ሸልማኝ ትሄዳለች ብሎ
ሲጠብቃት ቁሜ ብላ ቀረች ። ያልታሰበ ነገር በመሆኑ የልቡ
ትርታ ጨመረ ። ወዲያውኑ ሰውነቱንና እጁን ያልበው
ጀመር ።

«አበራ ለምን ...» ብላ የጀመረችውን ሳትጨርስ ፣ ጉሮሮዋ
የታነቀ ይመስል ሀሳቧን ለጉመችና ከመኪናው ዘላ
ወረደች ።

በዚያ ጨለማና በዚያ ኮረኮንች መንገድ ሹል ጫማዋ እያደናቀፋት ስትሄድ ሁሉ «ሳላንበረክክህ የቀረሁ እንደሆን እኔ ሉሲት አይደለሁም ፤ አረመኔዎች ሁሉ መስገድ አለባቸው ፤ ያረመኔዎች ጣኦት መሆኔን ባታውቅ ነው ...» እያለች የቤቷን በር ከፍታ ስትገባ ገድሉ በዛብህ ቁጭ ብሎ ጠበቃት ። መጥረቢያ መሳይ ፊቱ በትካዜ ደንዟል ። ያ ከፊቱ ላይ የማይጠፋውን ፈገግታ አልተጐናጸፈም ፤ ከንፈሮቹ ስላል ተሳቀቁ ጥርሶቹ አይታዩም ። የእንግዳ ቤቱን ግድግዳ ባንድ በኩል ከዳር እስከ ዳር ያለበሱትን የሉሲትን ፎቶግራፎች አንድ ባንድ እየቆጠረ ሲመለከት ነበር የቆየው ።

እንዳለ አድርጋ አልቆጠረችውም ። በትላልቅ ውብ አይኖቿ ገርመም አድርጋው አለፈችና ከጠባብ እንግዳ ቤቱ ውስጥ ፤ ግድግዳ ላይ የተሰቀለውን ትልቅ የፊት መስተዋት እያየች ጠጉሯን ማስተካከል ስትጀምር «እስካሁን የት ነበርሽ ?» ሲል በስለታም ቀጭን ድምጽ ጠየቃት ።

ዞር ብላ እንኳን አላየችውም ። አዲስ የተሰራውን ጠጉሯን ካስተካከለች በኋላ ስስ ሰማያዊ ሻሽ ከእጅ ቦርሳዋ አውጥታ ዠርገድ አድርጋ አሰረች ።
«አንችን ነውኮ የማናግርሽ !»
«ሰምቻለሁ ። የት ብዬ ልንገርህ ?»
«የት እንደነበርሽ አውቃለሁ ። ከአበራ ጋር ነበርሽ !»
«ድምጽህን ዝቅ አድርገው ፤ ጆሮዬን ያመኛል ። ደግሞ ከአበራ ጋርም ሆነ ከማንም ፤ የትም ውዬ ባመሽ ልትቆጣጠረኝ አትችልም ። ሂድና ያቺ በቅናት እርር ድብን የምትልልህን እርጊት ሚስትህን ተቆጣጠራት ።»

«ልቆጣጠርሽ መብት አለኝ ። የቤቷን ኪራይ የሚከፍልልሽ ማን ሆነና ነው ? በቀን ሶስቴ የምትቀያይሪውን ልብስና ጣ የሚገዛልሽ ማን ሆነና ነው ? በየቡቲና በየጠጉር ሰሪ ዎች ቤት የምትበትኚው ገንዘብ የማን ሆነና ነው ? የአበራ አይደለም ! የኔ ነው ! የኔ !»

«የንተ አይደለም !»

«ታዲያ የማንነው?»

«ገንዘቡ እንደሆን የዛች ያሮጊት ሚስትህ ነው ። ታውቀዋ ለህ ! አውቀዋለሁ ። ስለዚህ የኔ ነው ብለህ አትፎክርብኝ ። ይልቅ ከቤት እንዳታስወጣህ በጊዜ ብትሄድ ይሻልሀል !» አለችውና ወደመኝታ ቤት ገባች ።

ተከትሏት ገባ ። የመኝታ ቤቷም ግድግዳ ከልዩ ልዩ አቅጣጫ በተነሳችው ፎቶግራፎች ተሸፍኗል ። ሉሲት ልብሷን ስታወልቅ የገድሉ አይኖች የሰውነቷን ቅርጽ ይቆጥሩ ነበር ። እሷ እንደሆነች ደንታ አልነበራትም ። እንደእውነቱ ከሆነ ወንዶች ፊት ልብሷን በምታወልቅበት ጊዜ እየጐመጁ በስቃይ ሲቃጠሉ ስታይ ልዩ ስሜት ይሰጣ ታል ። «ይሄውልህ የምትፈልገው ገላ ! ግን ፍቅር የማይ ሰጥህ ገላ ...ከስቃይ በስተቀር ...» የምትል ትመስል ነበር ። ገድሉ በዛብህ ያ ገላ ከሚሰጠው ስቃይ የበለጠ የሚፈልገው ነገር በዚህ አለም የለም ። ልብሷን በምታወልቅበት ጊዜ የረጠቡት ከንፈሮቹ ተላቀቁ ። ፊቷ አዲስ እንደተሳለ መጥ ረቢያ ያበራ ጀመር ። ከንፈሮቹ ብቻ ሳይሆኑ ጉሮሮ አይ የቹም እንባ አቅረው ረጠቡ ።

እንባ ባቀረሩት አይኖቿ ብዥ ብዥ ብላ ስትታየው [illegible] ጣኦት የተመለከተ ይመስል ፣ ከተቀመጠበት ወንበር ላይ [illegible] ተነስቶ እግሮቿ ስር ተንበረከከና ወደላይ ቀና ብሎ እያ[illegible] ያት ፣ «ሉሲትዬ ፣ ውደጂኝ አላልኩሽም ። ናቂኝ ፣ አዋር ጂኝ ፣ አሰቃይኝ ነው የምልሽ ። ባንቺ ገላ መሰቃየት ለኔ [illegible] ገነት ነው ። እኔን ብቻ አሰቃይኝ ነው የምልሽ ። ያንቺ ቅዝቃዜ ለኔ መንግስተ ሰማያቱ ነው ። ስትንቂኝና ስታዋር ጂኝ ሀሲናዬ ፋታ ታገኛለች ፤» ሲላት ፣ ሉሲት በድል አድራጊነት ስሜት ናላዋ ዞሮ ፣ እንደሰከረ ሰው ትወዛወዝ ነበር ። የድል አድራጊነት መንፈሷ የሚያይልበት ወቅት ነው ። ወንድ እግሯ ስር ተንበርክኮ ሲለምናት ፣ ሲማለዳት ፣ ሲያመልካት ከማየት የበለጠ ደስታ የሚሰጣት ነገር የለም ።

ፊቷን ጠቆር አድርጐ የለበሰችውን ቀይ ፣ ስስ የሌሊት ልብስ አጉልቶ ፣ የተራቆተውን ደረቷን ወለል አድርጐ የሚያሳየው የራስጌ መብራት ጠይም ጣኦት አስመስሏ ታል ። ገድሉ እንደተንበረከከ ፣ «አሰቃይኝ ፣ አዋርጂኝ ፣ ለህሲናዬ ንስህ የምትሰጭው አንቺ ነሽ ... ሉልዬ አንቺ ነሽ» እያለ እቀፋት ። ተጠጋት ። አልራቀችውም ። ልቧ በድል አድራጊነት ስሜት አብጦ በንቀት አይን ወደታች እየተመለከተችው ቀዝቃዛ ሰውነቷን ትመግበው ጀመር ...

በገድሉ ምትክ አበራ እግሯ ስር ተንበርክኮ ወደላይ አንጋጦ ሲማለዳት ፣ እንደጣኦት ሲያመልካት ላንዳፍታ ታያት ። የገድሉ ስሲታም ድምጽ አድሮባት የነበረውን ትምክህትና ኩራት አጠፋው ።

«ሉልዬ ፣ ካንቺ ተለይቼ ልኖር እንደማልችል ታውቂ የለም!»

ካርጊት ሚስትህም ተለይተህ ልትኖር እንደማትችል አውቃለሁ ።»

«አዎን ፣ ግን ለሁለታችንም ስል ነው ። ገንዘቧ ያስፈልገናል ። ገንዘብ አላት ። ግን ከሷ ገንዘብ ካንቺ የማገኘው ሲቃይ ይበልጥብኛል ። ስታሰቃይኝ የማገኘው የህሊና እረፍት እንዳይለየኝ ማናቸውንም ነገር ከማድረግ አልቆጠብም ። የተፈጠርሺው ለኔ ነው ። አበራ ቀርቶ ማንም ከኔ ሊለይሽ አይችልም - ከሞት በስተቀር ።»

አዲስ ወንድ እግኝታ ለማሰቃየት በኮበለለች ቁጥር ፣ «ማንም ከኔ ሊለይሽ አይችልም - ከሞት በስተቀር» ይላት ነበር ። ፉከራውና ዛቻው ይዞለት ሶስት አመት ሙሉ ሳትለየው ኖራለች ። ከገድሉ የምታመልጥበት መንገድ ጨርሶ አልነበራትም ።

እምልኩቱ ትምክህቷ ነው ። ውቃቢዋን ያረካል ። ካርጊት ሚስቱ ወስዶ እንደዋዛ የሚያፈስላት ገንዘብ ወጥመዷ ነው ። ፍላጎቷን ሁሉ ያረካል ። ግን ይህ ሁሉ ሰልችቷታል ። እጅ እጅ ብሏታል ። መግቢያ አሳጥቷታል ። ከሱ ለምልጣ የምትገባበት ጉድጓድ ግን አልነበራትም ።

ልታመልጠው በሞከረች ቁጥር እሷን መልሶ እጁ ውስጥ የሚያገባበት ዘዴ አለው … ዘዴው ምን እንደሆነ ሳታውቅም ። ብቻ የመጡላት ወንዶች ቶሎ ይሸሿታል ። ትገን አይሆኗትም ።

የተስፋ ጭላንጭል ታያት ። እና ቀዝቃዛ ፈገግታዋ ሙቀትና ድምቀት አገኘ ።

## ፰

ሆዱ ዝናም እንዳረገዘ ጉም እጉረመረመ ። የበላው ምግብም ሆነ የጠጣው ቡና አልተስማማውም ። የዱሮ ገረዱ ከተሰናበተች ሳምንት አልፎአታል ። ለሱዛን ሮበ ሲል የገዛው ራዲዮ ግራም አቧራ ለብሶ መልኩ ተለውጧል፡ ስለሱዛን ማሰብ ሲጀምር እናቱ ወይዘሮ ባፈና፤«እዩ ዛሬስ መሞቴ ነው ፤ ምንም ሰውነት የለኝም …» እያሉ ሲጉ ተቱ ገቡ ።

ልጃቸውን ለማየት በመጡ ቁጥር ድቁስ በርበሬ፤እዋዜና ድልህ ፤ ቃሪያ ፤ ምጥን ሽሮና ሽንኩርት በዘንቢል ሞልተው ሳይዙ አይመጡም ። አዲሷን ገረድ ጠርተው ያመጡትን ሁሉ ከምክር ጋር አስረከቧት ። ምንም መልስ ሳትሰጣቸው እቃውን ይዛ ወደጓዳ ገባች ።

እንደጥንቱ ቢሆንማ ተናግረው መልስ የማይሰጣቸው አልነበረም ። ብቅ ባሉ ቁጥር ከመቀመጫው ተነስቶ ፤ ከቆመበት ፈቀቅ ብሎ ፤ ነጠላውን አደግድጎ እጅ የማይነ ሳቸው አልነበረም ። የተሽሞነሞነች ሰጋር በቅሎ ላይ ሲወጡ ሲሉ እርካቡን ለመያዝ የሚሽቀዳደመውና ነጠላውን ከት ከሻው አውርዶ ለመጋረድ የሚጋፋው የሰው ቁጥር መጠን

አልነበረውም ። «የጨዋ ልጅ እንደከብት በእግሩ የሚተነበት ዘመን» ብለው ከንፈራቸውን መጠጡና ፤ «ሰምትን አንተን እያስታወስኩ ሳለቅስ ነበር የከረምኩት ፤» አሉት ።

«ለምን እማዬ ?»

«ምኑ ቅጡ ልጄ ፤ ስንቱን ነግሬህ እችላለሁ ። አንተ እንደ ሆንክ የነገሩህን አትሰማ ፤ የመከሩህን አትቀበል ። ምኑ ቅጡ ፤ ቤተክርስቲያን ከመሄድ በየመጠጥ ቤቱ ዳንኪራ መርገጥን ይመርጣሉ ፤ ጾም ጸሎትን ረስተዋል ፤ ፊታቸውን ወደገሀነብ ጀርባቸውን ወደ ቤተክርስቲያን መልሰዋል … በደረቅ ሰበብ እርጥብ እንደሚነድ ሁሉ ፤ ጠፍተው ሊያጠፉን ነው እያሉ … አባ … ማናቸው ወንድሜ ?… ሲናገሩ ስምቼ አንጀቴ ሲንገበገብ ነው የከረመው ። አይ ዘመን ! ምንነው ልጄ ፤ እና ያባትህ ማህተብ ጠንካራ ነበር እንጂ ። ምንነው ልጄ ፤ እር ጊቶች እንዲጠሩ ፤ ሀጸናቱ እንዲያድጉ ፊታችሁን ወደ አምላካችሁ ብትመልሱ …»

እበራ ከእናቱ ጋር ለመከራከር አልፈለገም ። የተሰማውን ሳይገልጽላቸው ፤ «አይ እማዬ …ባጉል ፍርሀት አትጨነቂ ፤» ብሎ ዝም አለ ።

አበራ የበላው ሽሮ ወጥ ነበር ። ሽሮ ወጥ ይወዳል ። ወይዘሮ ባፈና ቀርቦላቸው የነበረውን ምግብ እንዴነገሩ ነካኩና ፤ «እህል በእህል እንዴት ይበላል ?» ብለው ተውት ። ጥርሳቸውን ያዝ የሚያደርግ ነገር ካላገኙ ደስ አይላቸውም ። ትኩስ ቡና አል የቀረበላቸውንም ቡና ቀምሰው መለሱት ። የሰው ቤት ምግብና ቡና ምንም ቢሆን አይጥማቸውም ።

«አፎይ ! ተክልዬ እንዴት ታደርገኝ ነ» ካሉ በኋላ አበራን በእናት አይን ትኩር ብለው እየተመለከቱ ፤ «የመጣሁት ስላየሁት ህልም ልነግርህ ነበር ፤» አሉት ።

«ይህን ሁሉ መንገድ - በጠራራ ጸሀይ !»

«ተክልዬ ግልጽ አድርገው ያሳዩኛል ። እኔና አንተ ትልቅ ወንዝ ዳር የቆምን ይመስለኛል ። ወንዙን የሚያሻግረው ድልድይ ስላስፈራኝ እጄን ይዘህ ልታሻግረኝ ትመጣለህ ። አጠገቤ ስትደርስ ቄጠማ በጥስህ ትሰጠኛለህ ። ያቺን ቄጠማ ይዤ ስመለከት ወደ አባብ ትለወጥብኛለች ። ደንግጬ ብንን አልኩኝ ።»

«ታዲያ ትርጉሙ ምንድንነው እማዬ ?»

«ህልም እንደፈቺው ነው ልጄ ። ማለፊያ ህልም ነው ። ወንዝ መቸም ህይወት ነው ። ሳታሻግረኝ በመቅረትህ … አዬ … ተክልዬ ያውቃሉ ። የቄጠማዋም ወደአባብ መለወጥ … ተክልዬ ከክፉ ይሰውሩህ ልጄ ፤ ብትጠነቀቅ አይከፋም ። ባለፈው ሰሞን በህልሜ አባተና አልፍነሽ የሚበሉት እንጀራ ሻግቶ አይቼ ነበር ። የፈራሁት ነገር ደርሶ ይሄውና ሊፋቱ ነው …»

አበራ ደንግጦ ከተቀመጠበት ተወርውሮ ተነሳ ። ያን ቀን ከቀትር በኋላ ወንድሙንና አልፍነሽን ከአእምሮው ካንዳፍታ እንኳን ሊያወጣቸው አልቻለም ። «ምን ባደርግ ይሻለኛል ?» በማለት ራሱን ደጋግሞ ሲጠይቅ ዋለ ። መልስ አላገኘም ። መልስ በማጣቱ ህሊናው ከመጠን በላይ ተጨንቆ ዋለ ።

ካንድ ሁለት ጊዜ ሉሲ በደረቷ ዛለምንድነው ይህን ሰዎን ስራ እንደሚሊስቅ ሰው ጠረጴዛህን የምታጋዳው ?» ብላ ጠይቃው ነበር ፤ በጠየቀችው ቁጥር ፤ «እንዲያው ነው ፤» ብሎ ይመልስላት ነበር ። አእምሮው በወንድሙና በአልፍ ነሽ ነገር ሲጉላላ ፣ የአእምሮው ዓዳ ይግዋ ከሁለት ወር ውስጥ የቀረውን ጊዜ እየቆጠረ ይዘጋጅ ነበር ።

አበራ ከቢሮ ወጣ እንዳለ ሶስቱ ሰላሲዎች ፤ ማለት ተሰማ ደጀኔ ፣ ባልቻ ዋቆና በቀለ ሮባ ተያይዘው መጡ ።
«አበራ የለም እንዴ ?» ሲል ተሰማ ጠየቀ ።

«እሱ ለራሱ ይህን ሰሞን የመንፈስ እረፍት አጥቷልና ብትተውት መልካም ነበር ፤» ብላ ሉሲ በደረቷ የሶስቱን ወሬ ስለማትወድ የሹራብ ስራዋን ይዛ ወጣች ።

ባልቻ ለተሰማ ክብሪት ሲሰጠው ፣ ተሰማ ሲጃራ ጋበዘው ። በቀለ በመስኮቱ መስተዋት የከራቫት አስተሳሰሩንና የጠጉሩን አበጣጠር እያየ መመጻደቅ ላይ ሳለ ፣ ወዲያው ባልቻ ተጠርቶ ሄደ ። አንድ ፖሊስና ሶስት ሴቶች እሳት ጉርሰው ውጭ ይጠብቁት ነበር ።

«ጓናቴ ትመጣለች ፣ አበራ ለዓመን የመንፈስ እረፍት እንዳጣ አውቃለሁ ። ገድሉ በዛብህ አጫውቶኛል ። አንድ ሉሲት ታደሰ የምትባል ልጅ ወዶ ነው ፤» አለ ተሰማ ።
«ሉሲት ታደሰ ማን ናት ?»
«አላውቃትም ። ገድሉ እንደነገረኝ ከሆነ ግን አፍ ያለች ሽርሙጣ ናት ። በዚያ ላይ እልም ያለች ሌባ ናት ። ወንድ ከሷ ጋር አድሮ ሳይዘረፍ አይሄድም ። ሸርሙጣ የሆነችው በገንዘብ እጦት ሳይሆን ወንድ ስለማትጠግብ ብቻ ነው ።

ገድሉ ፤ አበራን በጣም ስለሚወደው ፤ በጣም አዝኖ እን
ስጠንቅቀው ነግሮኝ ነበር ።»

ወእንደኔ ያለው ወንድ ቢያጋጥማት ነው ። ግን ማንነው ያ
ከው ? አዎን ፤ ገድሉ የአበራ ጓደኛ ከሆነ እንተን ከመላክ
እሱ ራሱ ለምን አይነግረውም ?» ከማለቱ ባልቻ ቀ
እየርጠ መጥቶ ፤ «እንዲያው ስለእግዚአብሄር ብላችሁ
ሰላሳ ብር አበድሩኝ ?» ብሎ ይወተውታቸው ጀመር ።
ፖሊስ በር ላይ ቆሞ ይጠብቀው ነባር ።

አበራ ሲመለስ ፤ ቢሮው በሲጃራ ጢስ ታፍና አገኘው ።
የቢሮው ጠረን አነማን እዚያ እንደነበሩ አፍ አውጥቶ ይና
ራል ። ባልቻ በጣም እንዳልቆየ እንኳን ለማወቅ አላቃተውም ።
የበቀለ ሮባ ሽቶ ግን ክፍሉን አዳርሶታል ። የቢሮውን
ጠረን እየጠላ ፤ ስለወንድሙና ስለእልፍነሽ እያሰበ ፤ የጠረ
ጴዛውን መሳቢያዎች አንድባንድ እየከፈተና እያጸዳ ጥቂት
ከቆየ በኋላ ፤ ሉሲት ስልክ ደውላ መጥቶ እንዲወስዳት
ስታዝው የእጅ ሰአቱን ተመለከተ ። የቀኑ መምሸት ፈጽሞ
አልታወቀውም ።

ያለወትሮዋ ሰአቷን አክብራ መንገድ ቆማ ጠበቀችው ።
ሳያስገርመው አልቀረም ። በጣም ያስገረመው ግን ለመ
ጀመሪያ ጊዜ ባገር ልብስ አጊጣ ማየቱ ነው ። የልብሱ
ንጣት ጠይም ፊቷን ፈገግ አድርጎታል ። የማያስጠላ
ቅርጽ ይዞ ወደላይ የሚገሰበጠው አፍንጫዋ ሰው ላይ
ማሾፉን ባይተውም ፤ ትላልቅ ውብ አይኖቿና አጭር ፊቷ
ህይወት አግኝተዋል ። ፊቷ ላይ የሚታየው ህይወት ገላ
ሱም ላይ ነፍስ ዘራበት ።

ቀዝቃዛው አየር የተቀባችውን ሽቶ እየወሰደ ይበትናል ። አግረኞችም ሆኑ ባለመኪናዎች ባይመለከቷት አያልፉም ። ሴቶች በግልምጫ እንደሽንኩርት ሳይልጧት አይናቸውን አይሰብሩም ። የተመለከታት ሰው ሁሉ ይላሰማታል ። ከኋላዋ ውበቷን በሚያደንቁ ወንዶችና ሴቶች ከላይዋ በከዋክብትና በጨረቃ የታጀበች ጠይም የጣኦት ስእል መስላለች ። የመብራት ምሰሶ ስር በመቆሟ የኤሌክትሪክ ብርሀን በቀጥታ በላይዋ ላይ ይዘንባል ። «ሰርግ ነው ወይስ ከስራ ነው የምትመጪው ?» ብሎ ጠየቃት ፤ የተርከፈከፈችውን ሽቶ ወደሳንባው እየሳበ ። «ላወቀበት ኑሮ ዘወትር ሰርግ ነው ፤» አለችው ።

ድምጿ ልዩ የሙዚቃ ቃና አግኝቶአል ።
«ዛሬ ምን እንደነካሽ አላውቅም ። ብቻ ልዩ ሁነሻል ፤» አላት።
«ባታየኝ ነው እንጂ ሁሌም ልዩ ነኝ ፤» ስትል እንደበፊቱ አጭር መልስ ሰጠችው ። አእምሮዋ እንኳን ልዩ ስለት አግኝቶ ነበር ። እንደዚያ ሆና አይቷት ስለማያውቅ ግራ ገባው ። ቢሆንም በመካከላቸው የነበረው ርቀት ገና መልኩን አልለወጠም ።

ጠጋ ብሎ ጉንጯን ለመሳም ያደረበትን ብርቱ ፍላጐት እንደምንም ታግሎ ተቆጣጠረና እመቤቱ ወዴት ለመሄድ እንደተነሳች አስቀድሞ እንደሚያውቅ ሹፌር ይዟት ወደ አውሮራ ቡና ቤት ከነፈ ። እሷ ሳትጠይቀው በወሰዳት ቁጥር ፤ «አንተኮ የልብ አውቃ ነህ ፤» ትለዋለች ። እራቷ አንድ ቡና በወተትና ለስላሳ ኬክ ነው ። የቡና ቤቱ ልጅ

እነሱን [illegible] የተነሳ የሚፈልጉትን ነገር መጠየቅ [illegible] [illegible] [illegible] አለመቻሉ ። [illegible] የልብ ለውጥ [illegible] [illegible] ።

የልብ ለውጥ ያልሆኑት ፤ ሀጻን ልጅ ወይም ልጆች [illegible] ፤ ወይም ቁስላቸውንና ዱቄቻቸውን እያሳዩ [illegible] ምስኪኖች ፤ ወይም የያዘነውን ግብስብስ በት [illegible] እያሉ የሚተናነቁት ሱቅ በደረቴዎች ፤ [illegible] [illegible] ቤት ታትመው የወጡትን ከምር ጋዜ [illegible] [illegible] ብለው የሚሽቀዳደሙት ጋዜጣ ሻጮችና [illegible] [illegible] ነበሩ ።

[illegible] [illegible] —» ሲል አንዱ ምስኪን የእጁንና የፊ [illegible] [illegible] እያሳየው ለመነው ።
[illegible] [illegible] [illegible]

[illegible] የለማኙን ቁስል በማየቷ ቡና በወተቷን ለመ [illegible] [illegible] ። የተጉነጠቸው ልውጣ ልግባ እያለ [illegible] ።

[illegible] [illegible] ይስጥህ ትለኛለህ የኔ አበባ — ነስቶኝ እያየሁ ። [illegible] [illegible] መቼ የሰው ፊት እንደ እሳት ይጠብሰኝ [illegible] [illegible] ወደሌላ መኪና ለሌላ ልመና ሲያልፍ [illegible] ፤ [illegible] አምስት ሳንቲም አውጥቶ ሰጠው ። ሀይ [illegible] አንድ ቀን ላንድ ለማኝ አምስት ሳንቲም ከሰጠ [illegible] ፤ [illegible] ሁሉ አምስት ሳንቲም ከሰጠ በቀን [illegible] [illegible] ብር አይበቃም ፤ አይን እያየና ጆሮ እየሰማ [illegible] [illegible] [illegible] ያሻል ፤» ሲል የተናገረው ትዝ አለው ፣

«ሲያዩ ነው... አበሳ ። ይህንን እያዩ እንዴት ይቻላል ? ቁስላቸውንና ዱሻቸውን እያሳዩ ሲለምኑ ሰማር ብን ፈንታ ያቅለሸልሸኛል ፤ ያመኛል ። እየሸፈኑ ቢለምኑ በግ ምናለበት !» አለች ሉሊት እየተበሳጨች ።

«እንደ ሀሊናችን ቁስል ማለት !» አላት በድንገት ።

ምን ማለቱ እንደሆነ አልገባትም ። እንዲያብራራላትም አልጠየቀችውም ። አበራ ግን እነ ተሰማ ደጀኔ ባሉበት አንድ ቀን ቢሮው ውስጥ የተናገረውን ነበር የሚያስበው ። «ግሳት ! ግሳት ብቻ ! የፖቢታ ግሳት ! የማኪያቶ ግሳት !... የህሊና ቁስል ! የተሸፈነ የህሊና ቁስል !»

«ምንድነው እንዲህ አተኩረህ የምታስበው አበራ ?»

«ምንም ።»

የሙዚቃ ለዛ ባለው ድምፁ ስሙን ስትጠራ በመስማቱ ደስ አለው ። እስቲ ደግመሽ ስሜን ጥሪ ሊላት አሰበና ወኔው ስለከዳው ዝም ማለቱን መረጠ ።

«ለምን ዝምታ ታበዛለህ ?»

«አንቺ ለምን ኩራት ታበዢያለሽ ?»

«አንተ ነህ እንጂ የምትኩራው ። በዝምታህ ባህር ውስጥ ሰው የምታስምጠው ። የኩራትህ ብዛት አንድ ቀን እንኳን ቤቴን ላሳይሽ ብለህኝ አታውቅም ። ወይስ ቤት የለህም !»

አበራ ጆሮውን ለማመን አልቻለም ። ሉሊት መሆኗን ተጠራጥሮ ትኩር ብሎ ላንዳፍታ ተመለከታት ። ከዚህ ቀደም የሚያውቃት ሉሊት አልመሰለችውም ። አይኑን ለመ

ሸሽ ፊቷን ዘወር አደረገች ። ቀዝቃዛ ጠይም ጣእት መስላ አልታየችውም ።

ረጅም እንገቷን በትኩስ ከንፈሮቹ መዳሰስ ቢያስኝ ውም ቅሉ ወኔው እንደገና ከዳው ። ግን ጊዜውን አላጠፋም። ወደቤቱ ይዟት ከነፈ ። ወደቤቱ ይዟት ሲበር በሀሳቡ አሊጋ ውስጥ ገብተው ሲጫወቱ ፤ ሲስማት ፤ ስትስመው ፤ ሲያቅፋት ፤ ስታቅፈው ፤ ገላው የሷን ገላ ጠረን ወስዶ በደስታ ሲረካ ይታየው ስለነበር ፤ ሲኒማ አዱዋ አጠገብ ያለውን ቀይ መብራት ጥሶ ሲያልፍ ፖሊስ እያከታተለ ፊሽካ ሲነፋበት ጩርሶ አልሰማም ። የልቡን ትርታ ብቻ ነበር የሚያዳ ምጠው ፤ የሰውነቱ ትኩሳት ነበር የሚሰማው ። በፍላጐቱ እሳት ይነድ ነበር ።

የደረቁትን ከንፈሮቹን በምላሱ እየላሰ ሊያርሳቸው አልቻለም ። የውሀ ጥም አቃጠለው ። ቤት እንደደረሱ ፤ ቁጭ በይ ሳይላት ፤ ጭላጭ ዊስኪ እንዳለ ፍሊጋ ሮጠ ። እሷም ትፈልግ እንደሆን የጠየቃት ለራሱ አንዴ ከተጐነጨ በኋላ ነበር ። ምንም አልፈለገችም ። ቤቱን በአይኖቿ ታማትር ነበር ።

«ሚስት ለማግባት አስበሀል መሰለኝ ?»

«እንዴት ሊመስልሽ ቻለ ?»

«የቤትህን ድርጅት አይቼ ነው ።»

«የተሟላ ቤት ያለው ሁሉ ለማግባት አስቧል ማለት ነው ?»

ቀዝቃዛ ፈገግታዋን አሳየችው ። ሳይታወቀው ብብቱና ግንባሩ በላብ ረጠቡ ። እንግዳ ቤቱን ያጥለቀለቀው ብርሀን እጋልጦ ስለሰጠው [illegible]

ቀኝ ብርጭቆውን ጠበቅ አድርጎ ያዘው ። ሳንባውን እያቃ ጠለው የሚወርደው ዉስኪ ሊያዝናናው አልቻለም ። ሲጃራ ለማቀጣጠል አውጥቶ መለሰው ። አይኑን የጋረደው ፤ ናላውን ያዞረውና ብርክ ያስያዘው የሷ ሱስ ብቻ ነው ። ግን ፈራት ። በጣም ፈራት ። ቤት ሲፈራ በህይወቱ የመጀመሪያ ጊዜው ነው - እዚያ ቤት ባንድ ቀን ሁለት ሶስት ቤት እንዳላመላለስ ሁሉ !

ባንድ እጁ የዉስኪውን ብርጭቆ ወብጦ ፤ የሌላ እጁን ጥፍር በጥርሱ እየከረከመ ፤ እሱ እንደተለጐመ ሰው በምልክት ወደ መኝታ ቤቱ መራት - ሊያስጐበኛት ።
«ቤት ቤትህ ጋብዘህ መኝታ ቤቱን ላስጐብኝሽ ማለት ያረጀ ዘዴ። አይመስልህም ?» አላችው ፤ እየሳቀችበትና ከተቀመጠችበት እየተነሳች ።

ደንግጦ ቆም አለ። ቢሆንም አልቀረችም። ተከተለችው።

እንደማስጐብኘት ሂዶ አልጋው ጫፍ ላይ ቁጭ አለ ። ከውጭ በበሩ የሚገባው ቀዝቃዛ አየር የተቀባችውን ሽቶ እየወሰደ መኝታ ቤቱ ውስጥ ያሰራጨዋል ።

ብርድ ጃርባዋን መቷት ስላስነጠሳት ፤ በሩን መለሰ አደረገችና ከቦርሳዋ ውስጥ መሀረብ አውጥታ ሰው ላይ የሚያሾፈውን ትንሽ አፍንጫዋን እየጠራረገች ፤ በቁም ሳጥን መስተዋት ጠይም ፊቷን ፤ የብር እንክብል የሚመስሉትን አይኖቿን እያየች ፤ የጣእትንነት ስሜቷ በመምጣት ላይ ሳለ ፤ አበራ ምትሀት እንደ ያዘው ሰው በጭፍን እየተሳበ ፤ እየተጐተተ ፤ እያደባ መጥቶ ፤ እንደእሳት በሚንደድ ከንፈር ፤ ማጅራቷን በስሙሙን ይስም ጀመር ።

አልጋው ማዶ ላይ ቁጭ ብሉ ፣ እንደአገዳ ቀጥ ብለው የወጡትን እግሮቿንና ሳይወዱ የሚያናግረውን ዳሌዋን እያየ ፣ ልሂድ ልቅር እያለ ከራሱ ጋር ብዙ ተሟገቷል ። መመለሻ አልነበረውም ። ፊትለፊት ዞራ ፣ ጡቶቿ እንደ ሌባ ጣት እየጠቆሙት ፣ ከንፈሯን አላቅቃ ስጠችው ። የጽጌረዳ እምቡጥ የሚመስለውን ከንፈሯን ፈልቅቆ የትንፋሿን መአዛ ፣ የከንፈሯን ማር እንደንብ ቀሰመ ።

እንደረመጥ የሚፋጁትን ከንፈሮቹን ከከንፈሮቿ ላይ ሳያነሳ ፣ የጋለውን ሰውነቱን ከሰውነቷ ሳያርቅ ፣ እቅፉን ሳያላላ ፣ በመካከላቸው የተፈጠረውን የምትሀት ሀይል ሳይቀንስ ፣ የትንፋሿን ሽቶ እየጠጣ ፣ ከዐለሳም ሰገነቱ ላይ አብሮአት ወደቀ...

እድሯበት የነበረው ፍርሀት ሄደለት ። እንደተቀበ ለችው በማወቁ ባንድ በኩል ሲዝናና በሌላው በኩል ደግሞ ባላየው ድርጊት ትታዘበኝ ይሆን በማለት አፈረ ። ቢሆንም፣ ቢሆንም የኮራው ዳሌዋና እንደሌባ ጣት ሰው የሚጠቁ ሙት ጡቶቿ የትዝብቱን ጉዳይ አስረስተውት ፍላጐቱ ከመጠን በላይ ቀሰቀሱበት ። አይኖቹ የገላዋን ውበት እየ መገቡ ፣ ካንዱ የሰውነቷ ቅርጽ ወደሌላው እንደፈንጣ ይ ጥራሉ ። ሳይታወቀው አመለካት ። እንደጣእት ሰገደላት

ገላው ገላዋን ሲነካ ተፈጥሮ ትርጉሟን ለውጣ ስሜ ሆነች ። ህሉናዋ ስልት ብቻ ሆነ...ውጭ የሚነፍሰው ግ በመካከላቸው የተፈጠረውን ስልት አስተጋባ ።

አበራ ያረገዘውን ስሜት ሁሉ አራግፎ ስለሰጣት ፤
በድካም የተነሳ ከባድ እንቅልፍ ወስዶት ነበር ። ሉሊቱ
ስለገሰገሰ ሉሊት ከእንቅልፉ ቀሰቀሰችው ። ሌላ ስሜት
አርግዞ ፤ በፍላጐት ግሎ ነቃ ። ብብቷ ውስጥ ገብቶ ሳማት ።
ትከሻዋን ፤ አንገቷን ፤ ጉንጯን ፤ አፍንጫዋን ፤ ከንፈሯን ፤
አንድ ባንድ ፤ ተራ በተራ ሳማቸው ። በትኩስ ስሜት ተይዞ
ይቃትት ጀመር ።

«በቀላሉ ስላገኘሀኝ ጠላሀኝ ወይስ ወደድከኝ !»
«መቼ በቀላሉ ሆነና ። ...... ይህችን ስእት ብዙ ጊዜ
ተመኝቻታለሁ ፤» አላት ።

«እኔም ብዙ ሌሊት ናፍቄሀለሁ ። ግን እኔ ቤቷ ቤትህ ውስ
ደኝ ብዬ በልመና በመምጣቴ ይገርመኛል ። ሀለተኛ ግን
አይለምደኝም ። አንተው ትመጣታለህ !»

«ባራት እግሬ ፤» አላትና በስመመን ይስማት ጀመር ። ያበጠ
ውን ኩሩ ዳሌዋንና የተጋጠሙትን ጭኖቿን በኃለ እጁ
ይደባብስ ጀመር ።

«አይ ! እንግዲህ ይበቃል ፥ መሽቷል ። እናንተ ወንዶች
ፊት ከሰጧችሁ ሴቶችን አሻንጉሊት ለማድረግ ነው የምት
ፈልጉት ፤» ብላው ለመነሳት ስትሞክር ፤ በግድ ይተናነቃት
ጀመር ። «እንግዲህ እንስሳ አትሁን !» ፤ ስትል በቁጣ ተና
ነቿቸውና ገፍትራው ተነሳች ። አበራ የእፍረት ቡሉኮውን
ተከናንቦ ፤ በጀርባው ተንጋሎ አልጋው ላይ ብቻውን ቀረ ።

ልብሷን ለባብሳ ፤ የተንጨፈረረውን ጠጉሯን ካስተካከ
ለች በኋላ ፤ «ይልቅ ተነስ ፤ የምነግርህ ጉዳይ አለኝ ፤» አለችው ።
«ታማኝ ነኝ ፤» ብሎ ተነሳ ።

አንዳንድ ብርጭቆ የአንቦ ውሀ ጨለጡ ። ትዝታቸው ገርገብ አደረጋቸው ። የአበራ ላብ ግንባሩ ላይ መርጋት ከጀመረ ቆይቷል ። ከላቡ ጋር ተዋሀዶ ገላው ላይ የቀረው የሉሲት ሽቶ ልዩ መውደድ አሳደረበት ። ሉሲት የአበራን ፊት ትኩር ብላ እየተመለከተች ስታጠናው ነበር ። አንድ ሀሳብ አእምሮዋ ውስጥ እንደሚገባበጥ ፊቷ ይናገራል ። ከራሷ ጋር ሙግት ይዛለች ። አበራ ሳያውቅባት አልቀረም ። «ታዲያ እነግርሀለሁ ያልሺኝ ጉዳይ ምንድንነው?»

«ብንጋባ ምን ይመስልሀል ?» ስትል ያልታሰበ ጥያቄ አቀረበችለት ።

የሉሲት አጭር ጥያቄ እንቅ ያደረገው ይመስል ፤ ድንገተኛ ዝምታ ቤቱን ባንዳፍታ ዋጠው ። አበራም የዝምታው አዘቅት ውስጥ ገብቶ ሰመጠ ። ግን የሚያስበውን ለይቶ ለማወቅ አልቻለም ።

«ታዲያስ ምንነው ዝም አልክ?»

«እንዴት ሊሆን; ይችላል?»

«እንሰሀለሁ ?...»

«እንደሱ ማለቴ ሳይሆን ...»

«ወይስ ልጃገረድ ባለመሆኔ ነው ?»

አይኖቿ እንባ አቀረሩ ። የደም ስሮቿ እንደሽምቀ አጥር ተገተሩ ። የግንባሯ ቆዳ ተሸበሸበ ። የታችኛውን ከንፈሯን እየነከሰች ልታደማው ደርሳለች ። ጥርሶቿን አፋጨች ። ባንዳፍታ የቆሰለ የዱር አውሬ መሰለች ።

ጣር በተመሳበት ድምጽ ፤ «ልጃገረድ ባለመሆኔ ነው
እንጂ ! እናንተ አረመኔዎች ደም ካላፈሰሳችሁ መቼ ይሆ
ንላችኋል !» አለችው ። እንባዋ እንደበጋ ዝናብ በወፍራሙ
እየተንጠባጠበ ይወርድ ጀመር ።

«ለሱ አይደለም ። እንዴት ሊሆን ይችላል ? ያልኩት ገና
በቅጡ አልተዋወቅንም ለማለት ነበር ። ጋብቻ ጸጸትንና
ሀዘንን ማስከተል የለበትም ። በኋላ ላስቀይምሽ አልፈልግም ።
ይህ አንዱ ምክንያት ሲሆን ፤ ሌላው ደግሞ ፤ በቅርብ ጊዜ
ውስጥ ስራዬን ለመልቀቅና ያሰኘን ዝንባሌ ለመከተል
አስቤአለሁ ። ይህን ለማድረግ ብዙ ዘመን ስለሚፈጅብኝ ፤
እንኳን ሚስትና ራሴንም ችዬ ለማስተዳደር ይቸግረኝ
ይሆናል ...»

«ለመሆኑ ያለህ ዝንባሌ ምንድነው ?» ብላ እንባዋን እየጠ
ራረገች ጠየቀችው ።

«የሰአሊ ዝንባሌ ።»

«ብስተርጅና ?»

«ምንም ቢሆን እድሜ የተፈጥሮን ዝንባሌ አፍኖ ሊያስቀ
ረው አይችልም ። ቀብሬ ላስቀርህ ቢሉትም ራሱ በገዛ
እጁ ከውስጥ ገንፍሎ ለመውጣት ስለሚታገል ያንቀዠ
ቅዣል ። ቀኝ፣ቃገር ያደርጋል ። እረፍትና እላማ ያሳጣል ።
ኑታ አይሰጥም ። ይህንን ስል ለማለት የፈለግሁት በአ
ሰም ላይ ቦታውን ፤ መድረሻውንና ማንነቱን ገና ያላወቀ
ሰው ማግባት ትርፉ ጸጸት ፤ ሀዘንና ብስጭት ይሆናል ለሚ
ላት ነው ።» ሲል በግልጽ እንደበት ሊያስረዳት ሞክረ ።

አእምሮውን እየጨመቀ ፤ ስሜቷን በማይጎዳ መንገ
ብቻው ሊሆን ለምን እንደማይችል ሊያስረዳት በሚ
ሞክርበት ጊዜ ፤ እሷ እንደሆነች ጆሮዋ ቢያዳምጠውም ቅሉ ፤
በሀሳቧ እሩቅ ደርሳ ነበር ። ያንን ጊዜ ሁሉ ከገድሉ በባ
የምታመልጥበትን መንገድ ነበር የምታሰላስለው ። ያለኝ
እድል አበራ ብቻ ነው ፤ በማለት በሀሳቧ ቆረጠች ።

«ስአሊ ደስ ይለኛል ። ለሞዴል እንደሆን እኔ እሰሁልህ ።
አንተ በምትማርበት ጊዜ ደሞ እኔ እየሰራሁ ያለ ችግር
ልንኖር እንችላለን ። እራት መቶ ብር አይበቃንም ?» ብላ
ትንሽ ቆየችና ፈገግታ በተመላበት ፊት ፤ «ለመተዋወቁ
እንደሆን እንደ ሀገራችን ባህል እያደርን እንተዋወቃለን ።
ምሳሌነቱ የወንድ ፈንታ ነው ። ከዚህ የበለጠ ደሞ እንዴት
ልታውቀኝ ትችላለህ ? አንድ ሴት ከራሷ የበለጠ ም
ልትሰጥህ ትችላለች ? ወይስ ፍቅር ካለቀ በኋላ ስለጋብቻ
እናስብ ማለትህ ነው ?» አለችው ፤ ሁኔታውን እያጤነች ።

አበራም በተራው እሷ የምትለውን በጆሮው እያዳመጠ ፤
በልቡ የእልፍነሽን እንባና ምሬት ፤ የወንድሙን ሀዘንና
ብስጭት ፤ የእናቱን እድሜና ጉጉት ያስብ ነበር ። «ሀይለ
ማርያም ላይ ሸክም ሁኜ ከመኖር ፤ እሱን ከማስቸገር ...ግ
ሀይለማርያም ይህን ሲሰማ ምን ይለኝ ይሆን ? ለመሆ
ሉሊት ከሰማይ የተላከችልኝ ስጦታ ናት ? ወይስ የሰይጣ
ተንኮል ?»

«ታዲያ ምን ታስባለህ ?»

ከእንቅልፉ እንደባነነ ሰው ደነበረና ፤ «በውነቱ የ
ስበውን አላውቅም ። ሁሉም ነገር ለጊዜው ተወናብ
ቷል ።» አላት ።

# ክፍል ሁለት

## ፩

ከባድ ዝናብ ያረገዘው የሀምሌ ሰማይ አጣዳፊ ምጥ ይዞት በጣር ያጉረመርማል ። አዲስ አበባ ጥቁር የጉም ብርድ ልብስ ለብሳለች ። በጥፊ የሚማታ ቀዝቃዛ ፤ ስለታም ነፋስ እያፏጨ የሸምጥ ክንፍ አውጥቶ ይበራል ። ዛፎችና ቅጠሎች የዛር ዳንኪራ እየረገጡ ይወዛወዛሉ ።

ጠብ ያለህ በዳቦ እያለ ሲፎክር ከመጣው ፤ አህያ ከማይችለው ዝናብ ለማምለጥ እግረኞች ወደየቤታቸው ወይም መጠለያ ካለው ሱቅ ለመጠጋት ይሮጣሉ ፤ ወፎች ጫጫታቸውንና እልልታቸውን ትተው ወደየጎጆአቸው ይበራሉ ። ሁሉም ወደሰማይ እያየ ሲሮጥ ፤ ሽብር የመጣ ይመስል ነበር ።

ያለርህራሄ በጥፊ የሚማታው ነፋስ አቧራ አንስቶ በሰው አይን ውስጥ እየሞጀረ ፤ የቤቶችን ቀሚስ ወደላይ እየገለበና ጃንጥላቸውን ከእጃቸው ለመንጠቅ እየታገለ መንገደኞችን ይተናኮላል ። ነፋሱ ከራሱ ላይ የነጠቀውን ባርኔጣ የሚያባርር አንድ መላጣ ሰው አይቶ አበራ ፈገግ

አለ ። ከታች የሚመጣ አንድ ሰው ባርኔጣውን ባይዝለ
ኛር ሰውዬው መቆሚያ አልነበረውም ።

የንፋሱን ተንኮልና ሀይል ፣ የሰማዩን ጥቁረትና ጣር
መብረቁ ሰማዩን እንደደፈሬ ፍልጥ ሲተረከከውና ንፋ
ዛፎቹን የዛር ዳንኪራ ሲያስረግጣቸው ፣ የቤቶቹ ቀሚ
ተገልቦ ጃንጥላው ከንፋሱ ጋር ልብረር ሲል ፣ መላጣ
ሰው ቁልቁል እየሮጠ ባርኔጣውን ሲያባርር—ይህንና ይህ
ሁሉ አበራ ቤቱ በረንዳ ላይ ቆሞ እየተመለከተ በአእ
ሮው ሰሌዳ ቀረጻቸው ። ካፊያው መሬቱን ማራስ ስለ
መረ ፣ ትኩስ የአፈር ሽታ አፍንጫውን ወጋው ። በረጅ
ተንፍሶ የአፈሩን መአዛ በደስታ ወደ ውስጥ ሳበው ።

«ቡናማ አፈር ፣ ጣር የያዘው ጥቁር ሰማይ ፣ የማይታ
የንፋስ ሽውታ ... ምን አይነት ውበት ? ምን አይነት የ
ፈጥሮ ስልት ዳንኪራ ... አፈሩ በካፊያ ሽቶ ርሶ እየሩ
ያውዳል ፣ ይጣራል ። ተፈጥሮ ተፈጥሮን ሲያረካ...ግ
ለምን ? ሳር ቅጠሎቹ አንገታቸውን ደፍተው በሀዘን የሚ
ክዙት ? እንባ ይወርዳቸዋል !»

የውጭው በር ከመጠን በላይ ተንኳኳ ። ማን እንደመጣ
ያውቃል ። አበራ ወንድሙን ሲጠባበቅ ነበር የቆየው ።

አቶ አባተ ገብተው የዝናቡን ካፊያ ከጠጉራቸውና
ከቅንድባቸው ላይ በቆሸሸች ነጭ መሀረብ ጠራርገው ሲያ
በቁ ፣ እንግዳ ቤቱን በጉሪጥ አይኖቻቸው ዙሪያውን ገብ
ኙና ወደ አበራ መለስ ብለው ፣ «ሉሊት የለችም እንዴ»
አሉና ፈገግ ብለው ጠየቁት ።

እንግዳ ቤቱ የቤት ጠረን ደቷል ። ያለበታው የተቀመጠ እቃ አይታይም ። የወለሉ ሳንቃ እንደመበተዋት ያበራል ። ቤቱ ሁሉ ደመቅ ደመቅ ብሏል ። ህይወት አግኝቷል ። አይን የሚስበው እንደፈርጥ ከሚንቦገቦግ ትልቅ የአበባ ማስቀመጫ ውስጥ ተንጠራርቶ ወጥቶ በየአቅጣጫው ዘንፈል በማለት ፈክቶ የሚታየው ለጋ የጽጌ ረዳ አበባ ነው ።

«ጠጉር ስሪ ቤት ሄዳለች …»

«የናቴ ልጅ ፤ ሴት ያለችበት ቤት ምንም ቢሆን ህይወት አለው ። ልጆች እየተሯሯጡ ቢንጫጩበት ደግሞ ከዚህ የበለጠ ምንኛ በደመቀ ። ግን በአባትህ አጥንት ፤ በመካነ መቃብራቸውና በሚወዱት ታቦት ስም የምለምንህ ይህ መከላከያ የምትሉት ነገር ህሳብህ ውስጥ እንዳይገባ ነው ። የእግዚአብሄርን ፈቃድ ስለሚጻረር ፤ የክርስቲያን ልጅ እንዲህ ያለውን የአረመኔ ተግባር መፈጸም የለበትም ። የናቴ ልጅ ፤ ተስፋ አታስቆርጠኝ ።»

አበራ የወንድሙን ፊት ሳንጻፍታ ሰረቅ አ...ገ ። በነዚያ ተመለከተ ። የተመለከተው ነገር አስገረመው ። በነዚያ ጭላንጭል በደካከሙት ጉሬጥ አይኖች ውስጥ የተስፋ ጭላንጭል ይታያሉ ። በእድሜ ማረሻ ተሸርሽር ጠቁሮና ተጉሳቁሎ የነበረው ፊት አዲስ የህይወት ወዝ አግኝቷል ። የእልፍ ነሽም ፈገግታ እንደመስከረም ጮራ ክብ ፊቷ ላይ ከመ ግወቷም ሌላ ፤ የልጅነት ሰውነቷ እንደተቅምት ቡቃያ ማቤት ጀምሯል ። ከሁለት ሳምንት በፊት የነገረችውን አስታወሰ ።—

«አበርዬ ፣ እድሜ ላንተ ፣ ቤታችን እንደዱሩር የብስጭት ፣ የንትርክና የልቅሶ ጉሮኖ አይደለም ። አንተ ካገባህ ጊዜ ጀምሮ አባቴ በጊዜ ቤቱ ይገባል ፣ አይጠጣም ፣ አይበሳጭም ። ስምምነትና ተስፋ ያለበት ቤት ከመንግስተ ሰማያት ሳይበልጥ አይቀርም ...»

ለወንድሙ ደህንነትና ተስፋ ምክንያት በመሆኑ ፣ አበራ አንድ አይነት ደስታ በልቡ ተሰማው ። ግን እስከመቼ ድረስ የወንድሜን ፍላጐት እያሟላሁ እዘልቀዋለሁ ? መቼ ይሆን ነጻነት አግኝቼ የራሴን ፍላጐት ለመከተል የምጀምረው ? ሚስት ፣ ልጅ ስል ጐመን ሆኜ መቅረቴ አይደለም ? እያለ ሲያስብ ፣ የወንድሙ ሌላው መልክ በአይነ ህሊናው ታየው ።

ከጋብቻው በፊት ነበር ። አበራ ሉሲትን ለማግባት ስለ ቆረጠ ፣ ወንድሙን ለማስደሰት ሲል ማንን እንደሚያገባና መቼ ለማግባት እንዳሰበ አንድ ጠርሙስ ዉስኪ ይዞ ሂዶ ይነግራቸዋል ። «ወሬ መስሎኝ ነበር ፣ ለካስ እውነት ኖሯል ፤ እንግዲያውስ ስለሷ የሰማሁትም እውነት መሆን አለበት ። የናቴ ልጅ ፣ የጩዋ ልጅ መሳቂያ ፣ ያገር መሳለቂያ ለመሆን ካልፈለግህ በስተቀር ፣ ያባትህን አጽም ካረፈበት ቦታ በቁጣ ለመቀስቀስ ካላሰኘህ በስተቀር ፣ እሷን ማግባት የለብህም ። ባባትህ አጥንት ፣ በሚወዱት ታቦት ይዤሀለሁ ...» ይሉታል ።

«ለምን ? ህሳቤ ወደ ጋብቻ ቢመለስ ደስ የሚልህ መስሎኝ ነበር ...»

«እንዴታ ! ደስ ይለኛል እንጂ ። ግና ጋብቻ ደስ የሚለው ከእኩያ ጋር ሲሆን ነው ።»

«ላልገባኝም ...»

«በዘርም ሆነ ባስተዳደግ እኩያህ አይደለችም ። አጥንተ ሰባራ መሆኗን ስምቻለሁ ። በዚያ ላይ ደግሞ አገር ያሸነፈች ያማሪ ናት ። ስንቷ ጨዋ የጨዋ ልጅ ሞላታ ተርፋ ለለች ...እንዴት የአባቴ ዘር ከዚህ ላይ ይበቅላል?»

«እንዲህ አቀርቅረህ የምታስበው ምንድንነው ?» ብለው አቶ አባተ ሲጠይቁት ፤ አበራ እንደመባነን ብሎ ቀና አለ ። ቆርቆሮው የሚያስተጋባው የዝናብ እሩምታ ጆሮው ውስጥ ገባ ። ጠጠር ከሰማይ እየረገፈ ቆርቆሮ ላይ የሚያርፍ ያህል እንጂ ዝናብ ብቻ የሚወርድ አይመስልም ። የመስ ኮቱን መስተዋት የዝናብ ወጨፎ እየገረፈው ያለቅሳል ። የአበራ ልብ አብሮት አለቀሰ ።

«ምንም ፤ ምንም አይደለም ፤» አለ ጉሮሮውን እሳሳና ።

«ታዲያ እንዲያ ባስቸኳይ የፈለከኝ እያየሁኝ ለመተከዝ ኖሯል ?»

«አንድ ያልገባኝ ነገር አለ ። ከትናንት ወዲያ እማዬ ቤት ብሄድ ሰው ገብቶበት አገኘሁት ። ነገሩ እየከነከነኝ ቤትህ ስደርስ ፤ ያንንትንም ቤት የማላውቃቸው ሰዎች ገብተውበት ቆዩኝ ። ምክንያቱ ምንድንነው ?»

አቶ አባተ የማይወዱት ነገር ወይም ሊመልሱት ያልፈ ለጉት ጥያቄ ሲያጋጥማቸው ፊታቸውን ኮስተር አድርገው ትከሻቸውን ያስቀድማሉ ። ድምጹን ከረር አድርጐ ፤ «የለም ጋሼ ፤ ምክንያቱን ማወቅ አለብኝ ፤» አላቸው ።

«አንተን የሚመለከት ጉዳይ አይደለም ...»

«ባናቱ ጠጉሬ ከሸበተበት ቤት በማላውቀው ምክንያት

ድንገት ወጥታ ሳገኝ እንዴት አይመለከተኝም ?» የዝናቡ ዶፍ በድንገት ገለል በማለቱ ፣ አበራ ድምጹን ዝቅ አደረገና «ማወቅ ይገባኛል ?» ሲል ፊትለፊት ተጋተራቸው ።

አቶ አባተ የደቀኑትን ትከሻቸውን ከአበራ ፊት ገለል አደረጉና ጣራ ጣራውን እያዩ ፣ «አይ ነገሩ እስከዚህም አይደለም ። የኔን ቤት በሽህ አምስት መቶ ብር በወለድ አግድ ስላስያዝኩት ነው ። የእናታችንን ቤት ደግሞ በአ ርባ ብር አከራይቼዋለሁ ፣ ኪራዩ እዳችንን ቶሎ ለመክፈል ይረዳናል በማለት ...»

«ይህ ሁሉ ጣጣ ላንድ ቀን ድግስ ሲባል ነው ?»

«ምን ይደረግ ፣ እናንተ የዘመኑ ወጣቶች ለማንኛውም ነገር ጊዜና ፋታ አትሰጡም ። ሰው ቢመክራችሁ አትሰሙም ። ያንተ ችኩልነት ደሞ በተለይ ነው ። ሰው ዘመድ አዝማዱን ሳያማክር እንዴት ብሎ በሁለት ሳምንት ውስጥ ማግባቱ ነው ብሎ ይነሳል ? ...»

«ጋሼ ፣ ፍሬ ነገሩ ይህ አይደለም ። አስቀድሜ ሰርግና ድግስ የሚባል ነገር አልፈልግም ብዬ ነግሬህ ነበር ። እኔ በሀይ ወቴ እያለሁ ሉሲት የምትባለውን ሴት አታገባም ስትለኝ ከርመህ ፣ ቅርጨ መነሳቷን ስታውቅ ካልደገስኩ ሞቼ እገኛ ለሁ ፣ ሆድና ጀርባ ሆነን እንቀራለን ብለህ ገንዘብ እንዳለው ሰው ደገስክ ። ኩቶ አይገባኝም ፣ ጨርሶ አይገባኝም ...»

«ምን ይገባሀል የናቴ ልጅ ። አይገባህም ። ባህላችንንና አስ ተሳሰባችንን አታውቀውማ ። አንድ ታናሽ ወንድሜ ሲያገ እንዴት እንደ ባእድ ከዳር ቁሜ ብዬ ልመልከት ? ጉረቤት ምን ይለኛል ? የፊታውራሪ ወርቁ ልጅ ፣ የአባተ ወንድም ፣

በሙት ባሬና ባንትይርጉ ልጅ ያለሰርግ ፤ ያለድግስ እንዲሁ አገባ ቢባል ጕረቤት ፤ እድርተኛውና የሚያውቁን ሰዉ ሁሉ ምን አይነት ትዝብት ላይ ይጥለናል ፤ ምን አይነትስ ግምት ይወስድብናል ፤ አባታችን በንቀኝነት ተጠርተው ስማቸው በየመንደሩ የቡና ቁርስ ከሚሆን ሞቼ መቀበሬን እመርጣለሁ ። አባታችን በህይወታቸው ሳሉ በሰርግ ቀን ይቅርና በሌላውም ቀን ከሰው ተለይተው መብላትን አይወዱም ነበር ። እስከ እለተ ሞታቸው በክብር ጠብቀው ያቆዩት ስም እንዲህ በልጆቻቸው ምክንያት ይበላሽ ፤ እሳቸው ያቆዩን ትንሽ ቅርስ ባይኖር ኖሮ አንተስ አጋልጠህ ልትሰጠንና ሰዉ አፍ ውስጥ ልታስገባን ነበር ። እግዜር እንዳለ የልፋቱን ዋጋ ይቁጠረው ብቻ ! ሌላ የምለው የለኝም ።»

አበራ ፤ «ከእዳ ሌላ ምን ተረፈኝ ?» ከማለት ሌላ በተጨማሪ የሚናገረው ነገር አልነበረውም ። ዝናቡ አባርቶ የምሽት ጸሀይ ደመናውን በፈገግታዋ እያቀለመች ዝናብ ጠጥቶ ሰክሮ ቡናማ ፤ ቁጡና ችኩል ጕርፍ ከሚጋተነው መሬት ላይ ወርቅማ ጨረሯን መፈንጠቅ ጀምራለች ። በትኩስ የአፈር ሽታ ፈንታ ትንፋሹን ወደ ላይ እየሳበ በየሰንሰሉና በየዛፉ ውስጥ ያለውን ክርፋት ፤ በየቦታና በየግንቡ ስር ያለውን ቅርናት ላፍንጫ ያበስራል ።

ዛፎችና ቅጠሎች የዛር ዳንኪራቸውን አቁመው ዶሩታቸውን በጸጥታ ወደሰማይ መገልበጥ ጀምረዋል ። እየጠራ የሚሄደው ሰማይ የጸሀዩዋን ፈገግታ እየተቀበለ ይፈነጥቃል ። አበራ ግን በሀሳቡ ማእበል ውስጥ ሰጥሞ ባቅ ጥልቅ ሲል አመሸ ።

«እንዲህ እያቅበጠበጠ የሚያስተክዝህ ምን ነገር መጣ የወንደላጤነት ኑሮህ ትዝ አለህ እንዴ ? ሉሚ ነው አለችው ፤ የሚያንጸባርቅ ፈገግታ ፊቷ ላይ ፈንጥቃ ።

ሉሲት ገና ከማጉላ ቤት የወጣች ሙሽራ መስላለች ። ጠይምነቷ ወደወርቅማ ቀለም ተለውጧል ። ቀሚሷን የለ ወጠው የለበሰችው ብጫ ቀሚስ ላይሆን አይቀርም ። ኩ ዶረቷና ዳሌዋ አበጥ ብለው ኩራት ጨምረዋል ። ያ ቅርብ ሆና ሩቅ ያለች የሚያስመስላት ፤ ያለድምቀት ፊቷ ላይ የሚሰራጨው ውብ ፈገግታ በመጠኑም ቢሆን ህይወት ያለው ድምቀት አግኝቷል ።

«ምን ይዘጋሀል ልጄ ? ለምን አታናግረኝም ? ከመሬት ተነ ስቶ እንዲህ የሚጋግርህ ነገር ምን መጣ ? ያስቀየምኩህ ነገር አለ ?» ስትል ጥያቄዋን ደረደረች ።

«ሉሲት ፤ ባክሽን ተይኝ ። ሂጂና ተኚ ። ብቻዬን መሆን እፈልጋለሁ ።»

«ጊዮን ሆቴል እወስድሻለሁ ብለህ ቃል ስጥተህኝ አልነበ ረም ?»

«አልወስድሽም በቃ !» ብሎ በድንገት ጆሮዋ እስኪናጋ ድረስ ጮኸባት ። ደንግጣ እያለቀሰች ወደመኝታ ቤት ሮጠች ።

የከበበው የዝምታ አዘቅት እሱ ያሳያትን የጭካኔ መን ፈስ እንደመሰተዋት አጉልቶ አቀረበለት ። ልቡ በጸጸት እንዶ ደንገያ እየከበደው ሄዶ ከተኛችበት ሲገልጣት እያናዳ እንባ አቅረው ፤ ጉንጮቿና ትራሷ በእንባ ርሰው አገኛት ። የእንባዋ ጨው ከንፈሩ ላይ እየተሰማው አይኖቿን ፤ ጉንጮ

ታውቃለህ ፣ ግን አታውቅም ። ህይወቴን በሙሉ በዚህ ቃል ተጠቅሜ አላውቅም ። ካንደበቴ ወጥቶ አያውቅም ። አበርዬ ፈራሁ ። ለምን እንደሆነ አላውቅም — ፈራሁ ። እቀፈኝ ። እንገትህ ስር ሽጉጥ አርገኝ - ትንፋሽህ እንዲሞቀኝ ።»

ልብሱን እወላልቆ አቀፋት ። እንገቱ ስር ሸጉጣት ። ትንፋሹ ከትንፋሿ ፣ ሰውነቱ ከሰውነቷ ፣ ላቡ ከሷ ላብ ጋር ተዋሀዱ ። እስካሁን ያላወቀችውን የፍቅር ጣእም በሙሉ ለመውሰድ ፣ ተቆልፎ የኖረውን ልቧን ከፍታ ያላትን ፍቅር ምንም ሳትቆጥብ ፣ ስሜቷን በሙሉ አውጥታ አበራ ህይወት ውስጥ አንቆረቆረችለት ።

ለመጀመሪያ ጊዜ የጠይም ጣእትነት ስሜት አላደረባትም ። ፍቅር ሰጥታ መውሰድ የምትችል የሰው ፍጡር ፣ ሴት መሆኗ አእምሮዋ ውስጥ ተሰረጸ ። ስሜቷ በደም ስሮቿ እየተሰራጨ ሲሄድ የደስታ ጣር እያስለቀሳት የፍቅር እንባ እንድታነባ አደረጋት — እቅፉ ውስጥ እንዳለች ተንሰቅስቃ በደስታ አለቀሰች ።

የያዛት ሲቃ አልፎ አእምሮዋ ከተረጋጋ በኋላ ፣ «አበርዬ አንተ አረመኔ አይደለህም ፣» አለችው በደከመ ድምጽ ።

«የምን አረመኔ!» በማለት እንዳልገባው ገለጸላት ።

«አንተ አረመኔ አይደለህም ማለቴ ጨካኝ ስላልሆንክና ስለ ማምንህ…እና ስለምወድህ እንድታመልከኝ አልፈልግም ማለቴ ነው ። ከዛሬ ጀምሮ ጣእት — ጠይም ጣእት አይደለሁም ።»

አበራ የሉሲትን አእምሮ ጤንነት ለመጠራጠር ምንም አልቀረውም ። ትኩር ብሎ ተመለከታት ። ፍርሀት እየረበተ፡ ልንደ ክርስቶስ በምሳሌ መናገሩን ትተሽ ለማለት የፈለ ገሽውን ነገር በቀጥታ መንገድ ለምን አትነግሪኝም ክ ሲል መሳቅጡን ባጣ ድምጽ ጠየቃት ።

«በኋላ አትጠላኝም?»

«ለምን እጠላሻለሁ?»

«ታሪኩ ረጅም ነዋ ።»

«ግድ የለም ።»

አንዴ ወደሱ ፣ አንዴ ደግሞ ወደጣራው እሻቅባ ተመ ለከተች ። የፊቷ ቀለም ተለውጦ ደበብ አለ ። አበራ የሚጠ ብጠው ነገር ስለጠፋው ቶሉ ብሎ ሲጃራ ለኮሰ ። እይናሟ እየመነመነ የሚሄደውን የሲጃራ ጢስ ተከትለው ወደሩቅ ተጓዙ ። የህይወት ታሪኳን እንዲህ ስትል ጀመረች ፦

«የተወለድኩት እምቦ ፤ ጡሴ ከሚባል ፣ የአዋሽ ምንጭ ከሚፈልቅበት ተራራማ ቀበሌ ነበር ። ቀንንና ወሩን ባላው ቀውም ከእናቴ እንደሰማሁት አመተ ምህረቱ ትዝ ይለኛል ። ግን አልነግርህም ። እናቴ ስትልከኝ ሄጄ በማንቀርቀሪያ ወይም በቅል ውሀ የምቀዳበት ፣ ከዋርካ ስር የምትፈልቅ ምንጭና ፤ ያልተወሳሰበ ፤ ከተፈጥሮ ጋር እጅ ለእጅ ተያይዞ የሚራመድ ያገር ቤት ኑሮ ሁልጊዜ በአይኔ ይዞራል ። ነገድ ትምህርት ቤት ሳለሁ ያነበብኩት አንድ ልብወለድ ታሪክ ትዝ ይለኛል ። «አንዷን ልጅ ካገር ቤት ማውጣት ይቻላል ። የማይቻለው ግን አገር ቤቷን ከልቧ ውስጥ ማው ጣት ነው» ይላል ። የተወለድኩባት ሰፍራ ከልቤ ወጥታ

አያውቅም ። እናቴ ስትልከኝ ሄጄ ጉመሮን ቀንጥሼ የማመጣበት ጓሮ ፣ የተሰጣውን እህል ወፎችና ዶሮዎች እንዳይበሉት ስጠብቅ ፣ ጥላውን የሚያጠላልኝ የእህል ጉትሬዋ አረንጓዴ ሚዳዎቹን እየቀደዱ በጥዋ መቀነት መሰለው የሚገዙት ጠባብ የእግር መንገዶች ትዝ ይሉኛል ። እይኖቹ መንገዶቹን ተከትለው ሲሄዱ ዶሮዎቹ የተሰጣውን እህል ይጭሩብኝ ነበር ። ሆኖም እናቴ እጇን አሳርፋብኝ አታውቅም ...

«እናቴ ፣ እናቴ የምለው አባቴን ስለማላውቀው ነው ። አባቴ የሞተው ገና በህጻንነቴ ነበር ። ስለሆነም እኔና እናቴ በታላቅ ፍርሀት ተጠምደን እንኖር ነበር ። ከእንጀራ አባቴ በስተቀር ሌላ ፍርሀት አናውቅም ። ቤት በገባ ቁጥር እናቴን ከመደብደብ ሌላ ስራ አልነበረውም ። እያደግሁ ስሄድ የእኔና የናቴ ኑሮ ገሀነም መስሎ ይታየኝ ጀመር ። ወንዶችን መጥላት ጀመርኩኝ ።

«ያደረብኝ ጥላቻ አእምሮዬ ስር ነፍሶ ሲዘራ የዛ ሰው ግን አንድ ቀን ጤት ነበር ። እናቴ የገዛችልኝን ትንሽ እንስራ ተሸክሜ ወደ ምንጩ እሄዳለሁ ፣ ቢራቢሮዎች ካንዱ አበባ ወደሌላ እየበረሩ ይጫወታሉ ። አብሬአቸው ለመጫወት አስኘቶኝ ነበር — በድንገት ባልቀጠፍ ኖሮ ። የማላውቀው ሰው አፈን አፍኖ ወደ ጫካ ሲጎትተኝ ለምን እንደ ሆነ አልገባኝም ነበር ... እስከ ... እስከ — አረመኔ! አረመኔዎች ፣ አረመኔዎች!»

አበራ ይዟት ዝም ሊያሰኛት ሞከረ ። ግን የጀመረችውን ታሪክ እዚያ ላይ ለማቆም እቢ አልፈለገችም ። ሰ

ሆኖና ከንፈሮቿን ከሳሙ በኋላ ፤ «ሰሉሜ ይቅርታ አድርጊልኝ። እኔ እኔ አይደለሁም ። ትልቅ የሀሳብ ማካ ውስጥ ገብቼ ነበር ። ታስታውሺ እንደሆን ከመጋባታችን በፊት ማንነቱን ካላወቀ ሰው ጋር መኖር ጸጸትንና ሀዘንን ያስከትላል ብዬሽ ነበር ። ይሄውና ደረሰብሽ ፤ አዝናለሁ ።» በማለት ሊያጽናናት ሞከረ ።

እንባዋን ከፊቷ ላይ ጠራረገችና ፤ «ያዘንኩት ጊዮን ስላልወሰድከኝ አይደለም ። ስለመከነብኝም አይደለም ። ስትመሀብኝ ደስ ይለኛል ። ግን የሚያሳዝነኝ ብቻህን ተጐልተህ በሀሳብ ስትጉላላ ነው ። ሚስት ለመቼ ናት ! ግን አይገባህም ። እንዴት ብዬ ላስረዳህ ። እወድሀለሁ ...»

አፏ በድንገት ተከፈተ ። አይኖቿ ወደውጭ ተጐልጉለው ፈጠጡ ። ፊቷ ላይ ያለው ደም እንደ ቁልቁል ይወርዳል ፤ ወዲያውኑ ተመልሶ ትንፋሿ ውስጥ ይተራመሳል ። ከመቅጽበት ልዩ ፍጥረት ሆነች ። የታመመች መስሎት እንገቷን ከትራሱ ላይ ቀና አድርጎ ደገፋት ። ቀን የተሰራችው ጠጉር ተንጨፍርሮ ግንባሯ ላይ ዘንፈል ብሎአል ።

«ምን ሆንሻል ! ምን ነካሽ !» አላት ደንግጦ እየተርበደበደ ።

በቀስታ ቀና ብላ አይን አይኑን ትመለከተው ጀመር ። እንደጨለት መራ እየፈካ የሚሄድ ፈገግታ ፊቷን አጐናጸፈው ። ሆኖም ብርድ እንደ ያዘው ሰው ሰውነቷ ሲንቀጠቀጥ ተሰማው ።

«ምን እንዳልኩህ ሰምተሀል ?»

ግራ ገብቶት ምን እንዳለችው ለማስታወስ አልሞከረም ሲያተርፉምስ ቀደመችውና ፤ «እወድሀለሁ ነበር ያልኩህ ።

ጅም ዘመን እእምሮዋ ውስጥ ተቀብሮ የኖረውን ታሪክ
ለመተንፈስ የምትቃትት ትመስል ነበር ። በረጅሙ ተንፍሳ
ታሪኳን ቀጠለች ፡—

«ጫካ ውስጥ በጀርባዬ ተንጋልዬ በደም ተበውሼ
አገኙኝ ። እንስራዬም እዚያው ጐኔ ተሰብራ እንክትክቷ
ወጥቶ ነበር ። የእንጀራ አባቴ ካበላሸኝ ሰው ጋር በጐን
ታርቆ በትንሽ ገንዘብ ክብሬን በሸጠው በሳምንቱ እናቴ
ሞታ ተቀበረች ። የሙት አመቷ ሳይወጣ የእንጀራ አባቴ
ባንዱ ዳረኝ ። ያ የተዳርኩለትም ሰው ክብር የላትም በማ
ለት ጀርባዬ እስኪተላ ድረስ ገርፎኝ መሀሉ የተቆረሰ ዳቦ
አሸክሞኝና ሰደደኝ ...

«ለዚህ ሁሉ በደል ፤ ጭካኔና ውርደት ወንድ የተባለ
ውን ሁሉ በክብሩም ሆነ በስቃይና በመከራ እንድ ባንድ
ለማስከፈል የቆረጥኩት ያን ቀን ጀርባዬ እየደማ ያንን
ዳቦ ተሸክሜ ወደ እንጀራ አባቴ ቤት ስጓዝ ነበር ። ጠይም
ጓለት ሆንኩኝ ። ወዲያውኑ የተከተሉኝን ሰዎች በዘዴ
አታለልኩና ወደ ጫካ ጐራ ብዬ ጠፋሁ ።»

የምትነግረው የህይወቷ ታሪክ ያስቀናው ወይም ያናደ
ደው ወይም ያሳዘነው መሆኑን ወይም አለመሆኑን አበራ
ስሜቱን ለይቶ ለማወቅ አልቻለም ። ምንም አቅጣጫ ያል
ያዘና የተወሳሰበ ሀሳብ ውስጥ ገብቶ ታሪኳን እያዳመጠ
ይቆይ ነበር ። አይኖቹን ጨፍኖ በአይን ህሊናው እንስሳ
መሳይ ግዙፍ ሰው ከላዩዋ ላይ ቆሞ ወደታች ሲመለከታ
ትና እሷ ጫካ ውስጥ በጀርባዋ ተንጋላ ፤ በደም ተበውሳ
ባያት የቅናት ስሜት ሰውነቱን ዝግንን አደረገው ። ራሱን

ለመቆጣጠር ትንፋሹን ወደ ውስጥ ሳበ ። ሱሲት ቀና ብላ አየችው ።

«እሰማሻለሁ» አላት በጎረና ድምጽ ። ክንዷን ደገፍ አለችና ታሪኳን ቀጠለች ።

«ከቤቴ ርቄ ወይም ከመንደሬ ወጥቼ ሄጄ አላውቅም ፤ ቢሆንም ጠይም ጣእት ስለሆንኩኝ አልፈራሁም ። ከወንድ የበለጠ የሚያስፈራ ሌላ ምን አውሬ አለ ? ግን እሱን እግሬ ስር የማንበረክክበት መሳሪያና ልቡ በጣር እስኪ ደማ ድረስ የምገርፍበት አለንጋ እንዳለኝ ተረዳሁ ። ሴት ነቴ ። እንዲያውም ሴትነቴን እያሳየሁ እርቃን ስጋዬን መሄድ አሰኝቶኝ ነበር ። ግን ምሽት መጣ ...

«የት እንደምሄድ ፤ ምን ለማድረግ እንደኮበለልኩ አላውቅም ፡ የሚገፋፋኝ ያ ያደረብኝ ቂም በቀል ብቻ ነበር ። አምቦ ከተማ ስደርስ ልቤ እንደእሳት እራት ውል ውል እያለ ሲንሳፈፍ ተሰማኝ ። ጉልበቴ ዝሏል ። ሆዴ ተርቦ ይጮሀል ፤ አፌ ደርቋል ። ካንድ ትልቅ ግቢ ብዙ ጎረምሶች እየወጡ ሲገቡ አየሁና ሄጄ በር ላይ ቁጭ አልኩ ። ዘበኛው ለማኝ መስዬው ሲያባርረኝ ሞከረና ለቅሶዬን በመመልከት ማን እንደሆንኩ ፤ ምን እንደምሰራ ሲጠይቀኝ አይተው ከጥቂት ጊዜ በኋላ ብዙ ጎረምሶች ተሰብስበው ሲያበቁ ተመሳሳይ ጥያቄ ባስተርጓሚ ይጠይቁኝ ጀመር ። ከጋልኛ ሌላ ቋንቋ አላውቅም ነበር ። ምንም ሳልደብቅ ታሪኬን አጫወትኳቸው ። ከዚያ ምን ልበልህ ... አጅበው ይዘውኝ ገቡ ። ካምስት ከስድስት ቀን በኋላ ነበር አምቦ የእርሻ ትምህርት ቤት ውስጥ መሆኔ የገባኝ ...

«ተማሪዎቹ ገንዘብ ሲዋጥተው ሁለት ቀሚስና ማማ ገዙ ልኝ ። ለባብሼ ብቅ እንዳልኩ የሁሉም አይን ተወርውሮ ሲያርፍብኝ እየሁና አንድ አይነት ትምክህት ተሰማኝ ። ጣእትነቴ ታወቀኝ ። ካንድ ወር በኋላ ይመስለኛል ፣ አንድ ሽምግል ያለ ፈረንጅና ሁለት ተማሮች ወደ አዲስ አበባ ይዘውኝ መጥተው እቴጌ መነን ትምህርት ቤት ጨመሩኝ ። ለሶስት ዓመት ያህል ያ ፈረንጅ እየተመላለሰ ይጠይቀኝ ነበር ። አራት ወይም አምስት ዓመት ከቆየሁ በኋላ ነበር አባትና እናቴ ያወጡልኝን ስም ለውጬ ሉሲት የተባልኩት «ለምን ለወጥሽ ?» ብሎ ጠየቃት ።

«ማልቱ ቶሎሳ የሚባል ስም ለጠይም ጣእት ጥሩ ስም መስሎ ስላልታየኝ …»

«ከዚያስ?»

«ከዚያማ ምን ልበልህ - በትምህርቴ ሰነፍ አልነበርኩም ። አስተማሮቼ ቢለምኑኝም ከሰከንደሪ ይልቅ ንግድ ትምህርት ቤት ለመግባት የመረጥኩት ቶሎ ስራ ለመያዝና ለመሸቀር ቀር … እና ጣእትነቴን ለማስመስከር ስል ነበር …»

«ስንቱ መሰከረልሽ ታዲያ ?»

ጡንቻዎቹ ሲገታተሩ ተሰማት ።

«ያለፈው አለፈ ። ስለሱ አናውራ ። ወደኔ ዙርና እቀፈኝ!» አለችው ።

ወደቧ ዞሮ ርህራሄ በሌለቦት በእንሰሳ ስሜት አቀፋት። ግቀፍ ሳይሆን አነቃት ። ጥፍሮቹ ያንገቷ ቆዳ ውስጥ ስርስረው ገቡ ። ስላደረሰችበት ጉዳት ሁሉ ተበቀለባት …ቆጥቷን ተወጣባት…ፍቅር አይሉት ጥላቻ!

ክንዱ ላይ የሚንጠባጠበው ትኩስ እንባዋ ስሜቷን እየከለሰለት ራሱን ለመቆጣጠር ከቻለ በኋላ በሻከረ ድምጽ ፣ «ሱልዬ ይቅርታ ፣ እኔ አልነበርኩም ። ዛሬ የሆንኩትን አላውቅም ፣» አላት ።

ከተኛችበት ቀና ብላ ግንባሩን ሳመችው ። በስመመን አቅፎ ያዛት ። እሱም በተራው ትኩስ እንባ ወረደው ። ከረጅም ዝምታ በኋላ ነበር ለነሱ ሰርግ በተደረገው ድግስ ምክንያት ወንድሙ ቤታቸውን በወለድ አግድ አስይዘው ፣ የእናቱን ቤት አከራይተው ስለወጡ ፣ እዳውን እስከሚከፍልበት ቀን ድረስ ያለውን እቅድ ለማዘግየት እንዳሰበ የነገራት ።

«እሰም በሙሉ አድሞብኛል መሰለኝ ፣» አላት ።

ለጥቂት ጊዜ አሰበችና ፣ «ለዚህ ነው ችግሩ ፣ እንደ ጓደኛዬ ዘንድ አንድ ሺህ ሶስት መቶ ብር አለኝ። ጧት እምጥተን እንከፍላለን ። ቀሪውን ደግሞ በዚህ ወር መጨረሻ እናጣራለን ። ሰአሲ ከመሆን የሚያግድህ ነገር እንዲኖር አልፈልግም ። ህሊናውን ሸጦ በምኞት ከሚያኖረኝ ባል ጥሬውን ተከትሎ ማንነቱን ለማወቅ ከሚታገል ሰው ጋር ማቅቄ ብሞት ደስ ይለኛል ፣» አለችው ።

የተፈራረቀበት ደስታና ሀዘን ከአቅሙ በላይ ስለሆነ እንደግንድ ተጋድሞ ቀረ ። ሉሊት አይን አይኑን እያየች ለጥቂት ጊዜ ከተከዘች በኋላ የዛለውን ሰውነቷን ድካምና እንቅልፍ ወረሩት ። በአበራ ላይ ያላት ስሜት የመራራት ይሆን ወይም የመውደድ ፣ ልዩነቱ በግልጽ አልታያት ብሎ ሲያባንናት አደረ ።

## ፱

እንደሌላው ጊዜ ሁሉ ሰኞ የሚቀፍና የሚከብድ ቀን መስሎ አልታየውም ። ዱሮ ጢሙን ሲላጭ አንድ ቦታ ፊቱን ሳይቆርጥ አይቀርም ነበር ። አንድም ቦታ በምላጭ ያል ተቆረጠው ፊቱ የጸሀዩዋን ድምቀት በደስታ ያንጸባርቃል ።

አበራ እንደዚያን ቀን ፊቱ በደስታ ተሸልሞ አያውቅም ። ህይወቱ በተስፋ ተጥለቅልቆ ነበር ። ሉሲት በሰጠችው ገንዘብ የወንድሙን እዳ አብዛኛውን በመክፈሉ ተጭኖት የነበረው ሸክም ሲቀለው በሁለትና በሶስት ቀን ውስጥ እናቱ ወደቤታቸው መመለሳቸውን በማወቁ ልዩ የደስታ ስሜት አድሮበት ለዘፈንና ለፉጨት እንዲቃጣ ያደርገው ነበር ። ግን ልቡ የደስታ ክበሮ የሚመታበት ሌላ ምክን ያት ነበረው ። ናፍቆትና ፍርሀት በሚፈራረቅበት ስሜት ሲጠባበቀው የነበረው ቀን መዳረሱ ተሰማው ። እንደበፊቱ የነጻነቱ ቀን ሩቅና ደብዛዛ መስሎ አልታየውም ።

ቢሆንም እንደልማዱ በሰአት ቢሮው አልደረሰም ። ጊዜው ከጧቱ ለአራት ሰአት ሩብ ጉዳይ ሆኖአል ። ጧትም ገና ከሰአት በኋላ ሉሲት ግብገ/ እንደምትሄድ ሲት ከራስ ጠጉሩዋ እስከ እግር ጥፍሯ አዘወትራ የምትሽቀረቀርበት ምክንያት ከቶ ሊገባው አልቻለም ። ታዲያ ተኳኩላና ለባብሳ ለስክምትነሳበት ጊዜ ድረስ ሰአቱ ይሄዳል ። እነዚህ የቢሮ ሰቶች ደመወዝ የሚከፈላቸው ለስራቸው ሳይሆን ለመልክ

ቸው ቢሆን ነው እንጂ ቢሮ ለመሄድ ይህ ሁሉ ጌጥና ሽቶ ምን ያስፈልጋል ? ወቸ ጉድ ! ቀድሞውኑ የስልጣኔ ትርጉሙ ላይ ላዩን የሚታየው መልክ ብቻ ነው ብሎ ያስተማረ ቸውስ ማንነው ? እያለ ሲያስብ ፤ ቢሮው እንደደረሰ፣ ሀይለ ማርያም እንደልማዱ ባንድ እጁ ጢሙ ወደላይ የሚተገ ሲሻራ ፤ በሌላው እጁ ደግሞ የተዘረጋ መጽሀፍ ይዞ፣ ቁጭ ብሎ ቆየው ። ከሚያነበው መጽሀፍ ላይ ቀና አለና የእጅ ሰአቱን ተመለከተ ።

የሱቅ በደረቴ የእጅ ቦርሳ የጽህፈት መኪናው ከሚቀ መጥበት ጠረጴዛ ላይ ተንጠልጥሏል ። እዚያው ቅርብ መኖ ሯን ለሚፈልጋት ሰው የምታስታውቅበት ዘዴ ነው ። «ሰአት በማየት ለምን ትቸገራለህ ? ጊዜ ትርጉም የለውም ። በጧት መጥቼ ከዚህ ወንበር ላይ ስጐለት ራሴን የምመለ ከተው የበሰበሰ እንቁላል ላይ የተቀመጠች ዶሮ አድርጌ ነው ። የሚገርመው ነገር ግማቱ አይሰማኝም ...»

«ምናልባት ግማቱ ተዋህዶህ ይሆናል ፤» አለው ያነብ የነበ ረውን መጽሀፍ አጥፎ ኪሱ እየከተተ ። ሌላውም የኮት ኪሱ ወፍራም መጽሀፍ አጭቆ ይዟል ።

አበራ ወንበሩ ላይ ጉብ ብሎ ሁለቴ ተሽከረከረና ፤ «ይሆን ይሆናል ። ግን ...ግን የህይወቴ ጥሪ ግሩም መአዛ ከመቼውም ይልቅ ዛሬ በጣም እየቀረበኝ ሄዷል ። አሁን ጊዜው ሩቅ አይደለም ። ውስጤ ገንፍሎ ቀለም ቀለም ይሸ ተኛል ። ትንሽ ቀን ...ትንሽ ቀን... እና... ጉመን አለመ ሆኔን ሲሆን ለራሴ አረጋግጣለሁ ...»

«ሊሉን ተወው ባክህ ። በርካሽ ቅኔ አትመጻደቅብኝ ። ባዶ ነው ።»

«አታምነኝም?»

«ቀርቷል ። የሚያሳዝነኝ በስብሰና ደምህ ውስጥ ረግቶ የሚኖረው ችሎታህ ነው ። ወኔ የለህም ። ግን አልፈርድብህም ። ለምን ? ተራ ሰው ነህ ። ተራ ሰው ደግሞ ከካባቢው ጋር መመሳሰል አለበት ። ይህን እንተውና ደልቅ ሎሊት እንዴት ናት?»

«ለምን ቤት መጥተህ አትጠይቃትም ። አንተን ሳታነሳ ውላ አታውቅም ።»

«ባልና ሚስት ቤት መሄድ አልወድም ። በሽታቸው የሚተላለፍብኝ ይመስለኛል ። ግን እንደ እውነቱ ከሆነ ጭርስ ጊዜ የለኝም ። ከጊዜ ጋር መሽቀዳደም ጀምሬአለሁ ። ይህን ሰሞን ከመሬት ተነስቶ ጊዜ እያጠረብኝ የሚሄድ ይመስለኛል ።»

«ቀስ በል ።»

«ቀስ ለማለት አልችልም ። የሚገፋፋኝ አንድ ሀይል አለ ። በነገራችን ላይ ፤ ለመሆኑ አቶ አባተ እንዴት ናቸው ? ባንተ ማግባት ምን ያህል ደስታ እንደሚሰማቸው ይገባኛል ፤» ከማለቱ የቢሮ ተላላኪው ገባና ወደ አበራ እያየ እንግዳ ውጭ ቆሞ ለመግባት የሚጠባበቅ መሆኑን ነገረው ። ባለ ጉዳይ መሆኑን ስለተረዳ ፤ «ቢሮቴ ስራ ይዘዋል ብለህ ሸኘው ፤» በማለት አሰናበተውና እግረ መንገዱን ሁለት ትኩስ ቡና ይዞ በፍጥነት እንዲመጣ ካዘዘው በኋላ ህሊናው ስለከበደው በጸጸት ራሱን ነቅንቆ ጠረጴዛው ላይ በግንባሩ ተደፋ ። ሀይለማርያምም አለው ።—

«አትጨነቅ ። የግል ሠራ በማውራትና ቡና በመጠጣት ከፍተኛ ደሞዝ ፤ በተለይ ከገበሬ ላብ እየተጨመቀ የሚ

መጣ ደሞዝ ፤ የምታገኘው አንተ ብቻ አይደለህም ፡ ሁሉም ሲያደርገው ባህል ይሆናል …እና ልንኮራበት ደጋ ባናል ፡፡ ይብላኝ ብቻ ላገሬ !»

«ጥቂት ቀን ስጠኝና እሳይህለሁ ፡፡ ደም መጣጭ፤ ወፍራም፤ ሀሲና ቢስ ተባይ መሆን አስጠልቶኛል ፡፡»

«የቃላት ናዳ ቢሆንም ራስን መውቀስና መታዘብ ለመ ሻሻል የመጀመሪያ እርምጃ ነው ፡፡ እዚህ ላይ ነው ደካማ ነታችን ፤ ውድቀታችን— ሁልጊዜ ሌሎችን መውቀስ እለብን ፡፡»

«በደህና መንፈስ የጀመርኩትን ቀን አበላሸህብኝ ፡፡ ባል መጣህ ኖሮ፤ ስራዬን ለመልቀቅ ከሉሊት ጋር ተመካከ ረን ጨርሰናል ፡፡ ችግሬ ወንድሜ ብቻ ነው—ልጅ እንደን ወልድ ይፈልጋል ፡፡ ቅዳሜ ለት ስለመከላከያ መጥፎነት ሲያስረዳኝ ነበር የዋለው ፤» አለና ቢሮው እስኪያስተጋባ ድረስ ከት ብሎ ሳቀ ፡፡

«እኔና አቶ አባተን የሚያቀራርበን አንድ ነገር አለ ፡፡ በምን ፈልገው ነገር እንለያይ እንጂ ሁለታችንም አንድ ቅርስ በዚህ አለም ለማስቀረት እንጥራለን …እና የሁለታችንም ጥድፊያ ጊዜ እንደሌለን ያሳያል ፤» ካለ በኋላ ሀይለማ ርያም ቡናውን ቀምሶ እሬት እሬት ስላለው የተጉነጠ ውን እንደምንም ውጦ የተቀረውን ቁጭ አደረገ ፡

«የሳቸውን ፍላጐት ጠለቅ ብለን ብንመረምር፤ የሚፈልጉት ዝርያ ለማስቀረት ብቻ አይደለም ፡፡ እምነታቸው ፤ አስተ ያየታቸውና ፤ የኑሮ ህልውናቸው ሁሉ ከሳቸው በኋላ ቋሚ ሆኖ እንዲቀር ነው ፡፡ ይህን ራሳቸው እንዳያደርጉት መሆነ ናቸው ፡፡ ያላቸው ተስፋ አንተ ብቻ ነህ ፡፡ ይህ ፤ ለሳቸው

የሞትና የሽረት ጉዳይ ነው ። ነገር ግን ፤ የራሱን ማንነትና የኑሮ ህሉውና ገና ያላወቀ ሰው ፤ እንዲህ ያለው ተስፋ ሊጣልበት በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ ሳይሆንበት አይቀርም ። እንደነ አቶ አባተ ያሉት ሰዎች ፤ ይነስም ይብዛ ፤ ትርጉም ይኑረው አይኑረው ፤ የሚፈልጉትን ያውቃሉ ። ስለዚህ ጠንካሮች ናቸው ። ከሞኝነትና ካለማወቅ የሚመጣ ጥንካሬ አይደለም …እንደምናስበው ። እኛ ግን የምንፈልገውን አናውቅም …ፍሊጋ ላይ ነን ። የኑሮውን ህሉውና ባወቅና ባላወቀ ሰው መሀል መግባባት ሊኖር አይችልም … እኛ ግን በምንም ነገር አናምንም ። እምነት የለንም …ራሳችንን ፤ ማንነታችንን ስለማናውቅ ። በራሳችን ላይ እንኳን እምነት ቢኖረን ምናልበት ? ስለራሳችን የውነቱን ብናውቅ ! ለገዛ ራሳችን እንኳን ታማኝ ብንሆን …»

«ካንተ ቡና ሳይሻል ቀርቶ ነው እንዲህ ያንገፈገፈህ !» ሲል ጠየቀው ፤ አበራ እርእስተ ነገራቸውን ሲውጥ ።

«ስለቡና ጣእም ምን ታውቃለህና ! ይልቅ አንድ ነገር አስታወስከኝ ። ማንቆርቆሪያዬ ስለተበሳች ሌላ መግዛት አለብኝ ። ያቺን ማንቆርቆሪያ በጣም እወዳት ነበር…»

«እኔ ልግዛልህ ።»

«ገንዘቡን ለልጅህ ቆጥብለት !» አለውና ለመሄድ ከተነሳ በኋላ ፤ «ሌላ ጸሎት የለኝም ። ከጋብቻ ሰውረኝ ከማለት… ጋብቻ በጣም እንደተስማማህ ይታየኛል ። ለመሆኑ ሉሲ እንዴት ናት ?»

«ዘወትር ፤ የት ነበርክ? ለምን አመሸህ? የት ትሄዳለህ ? ምን ታስባለህ ? ምን ሆነሀል ? ይህ አንሷል … ያ የለም ። ለቅሶ ቤት ውሰደኝ ። ጠጉር ሰራ ቤት አድር

ሰኝ — ሰንት ጣጣ ! ያገባሁት ምናልባት ሰላም አገኝ እን ደሆን በማለት ነበር…ሆኖም ጀርባዬን አሽቶ የሚያጥባ ልኝ ሰው በማግኘቴ ባልደሰት አልቀረሁም ።»

«የሴቶች ጥረት ባሎቻቸውን በተቻላቸው መጠን የቤት ለማዳ ለማድረግ መሆኑን አትርሳ …»

«ከተቻላቸው ከዚያም አልፈው ትቃ ያደርጉታል…»

«ለሱሲት የከበረ ሰላምታ አቅርብልኝ !» ብሎት ሊወጣ ወደበሩ ሲራመድ ተሰማ ደጃፉ ወፍራም ሰውነቱን እንደኳስ እያንከባለለ ሀይለማርያምን ገፍትሮት ሲሮጥ ገባ። አበራ ሀይለማርያምን እንዲሰናበት ጊዜ አልሰጠውም ፤ «እንኳን ደስ ያለህ ልልህ ነው የመጣሁት!» አለው በሩጫ ምክንያት ትንፋሽ እያነሰው ።

«ለምን!?»

«መቶ ብር የደሞዝ ጭማሪ ማግኘትህን አልሰማህም እንዴ? እንግዲያውስ የምስራች ! እናት ትሙት ! አንድ ነገር ይገባኛል ። ዛሬስ በማኪያቶ አንሳቀቅም !» ብሎት በረጅሙ ተነፈሰና ወንበር ላይ ተዘረፈጠ ።

ተሰማ ቁጭ ከማለቱ አንድ የመዝገብ ቤት ሰራተኛ የእጅ ላብ ያጠቆራትን ትንሽ ሬኮማንዴና ማዘዣ ይዞ መጥቶ አበራ ፊት አስቀመጠለት ። ሬኮማንዴዋ ውስጥ በስሙ አቅጣጫ ፊርማውን አኖረና ማዘዣውን ተቀበለ ። መቶ ብር የደሞወዝ ጭማሪ ታዞለት ነበር ።

ተሰማ የጠበቀው ነገር ባለመሆኑ ተገርሞ መቀመጫው ላይ እየተቁነጠነጠ፡ «እንዲህ ፊት የሚያጠቁርና የሚያሳዝን ምን ነገር መጣ ? ከመቶ ብር በላይ አስበህ ኖሯል

እንዴ? እናቴ ትሙት፤ እኔ ይህን ያህል ባገኝ በደስታ ብዛት ጣራውን ቀድጄ እወጣ ነበር ፤» አለው ።

«የሰው ስሜት የተለያየ ነው ።»

«በገንዘብ ላይ ያለው የሰው ስሜት ሁሉ አንድ አይነት መሆኑን እናቴ ነግራኛለች ። ገንዘብ ማግኘቱን የሚጠላ የለም ። አንተ ግን ትገርማለህ ። ወይስ ኑደህ አፍ ተቀምቶ የመጣውን ምንም ሳልሰራ መብላት የለብኝም የምትለው ፈሊጥ ትዝ ብሎህ ነው ? ደሆን የፈጠረው እግዚአብሄር ነው እንጂ አንተ አይደለህም ። ወደሱ አንጋጠው ይጮሁ ። አንተ ምንቸገረህ?»

አበራ ለጊዜው ለሰው የሚያውሰው ጆሮ አልነበረውም። አይኖቹን ጨፍኖ በጥልቀት ወደውስጡ ተመለከተ ። ነገር ግን እርግጠኛ ዝንባሌውንና ስሜቱን ለመጨበጥ አልቻለም። ብቻውን እንደ እብድ ተንከትክቶ ሳቀ ። ተሰማም አብሮት እንዳይስቅ ቀልዱ ስላልገባው እንደሞኝ አፉን ከፍቶ ይመለከተው ጀመር ። አይኖቹ እንባ ዘርተውና ሆዱን ቁርጠት እስኪይዘው ድረስ ተንከትክቶ ከሳቀ በኋላ ፤ «የሚያስቅኝ ነገር ገብቶሀል ?» ሲል ጠየቀው ።

«አልገባኝም ።»

«እኔም ስላልገባኝ ነው የምስቀው ።»

«ምኑ ?»

«ምን ብዬ ልንገርህ ? እርሳው ።»

«አብደሀል መሰለኝ ?»

«እብድ ብሆን ኖሮ ይሻለኝ ነበር ። እኔን የሚያመኝ እብድ አለመሆኔ ነው ።»

ተሰማ አንድ ነገር ሲመናገር አስቦ አፉን ካሞጣሞጠ በኋላ ዝም አለ ። ልናገር ወይስ ልተው በማለት ከራሱ ጋር ሙግት መያዙን ፤ በወዝ የተንጨፈጨፈው ወፍራም ፤ ከባ ፊቱ ይናገራል ። መቼም የሰማውንና ያየውን ቋጥሮ ሰመ ያዝ ስለማይችል ፤ «ካልክስ ስላንተ የሚያሳብድ ነገር ሰምቻለሁ ። የሰማሁትም ሰላንተ በጣም አድርጐ ከሚቆረ ቆርና ከሚያስብ ፤ እጅግ ከሚያደንቅህ ሰው ነው ፤» አለው ፤ ለስባ ስጋ እንደሚዘጋጅ ቢላዋ ምላሱን ወፍራም ከንፈሩ ላይ በመሞረድ ስለት እያወጣለት ።

«ምን ሰማህ?»

«የሰማሁት ለጆሮ የሚቀፍ ነገር ነው ። እንኳን ባንተና በጠላቴም ላይ ቢደርስ አዝናለሁ ...»

«እኮ ምንድንነው ?»

አበራ በአእምሮው ውስጥ የሚጉላላውን ሀሳብ ለቀቅ አድርጐ ተሰማ የሚለውን ለማዳመጥ ወደሱ ዞረ— ከእንቅብ ገለባ ውስጥ አንድ ፍሬ አይጠፋምና በማለት አስቦ ። ተሰ ማም የአበራን ጆሮ በመማረኩ የልብ ልብ ስላገኘ ጉርድ በርሜል መሳይ አጭር፤ ወፍራም ሰውነቱ ተዝናና ። ላቡን ከከብ ቀይ ፊቱ ላይ በንጹህ ነጭ መሀረብ ጠረገና ፤ «ስለሴ ሊት ነው ፤» አለው ፤ «ታማኝና የባሏን ክብር የምትጠ ብቅ ሚስት አላገባህም ። ኮተቤ ከገጠር መናፈሻ ቡና ቤት ውስጥ ልትማግጥ ስትገባ አሁን ባለፈው ሰሞን በአይኑ ያያት ሰው ነግሮኛል ...»

«ቢቃህ! በቃህ ! ያገኘውን ጥሬ የሚሸረክት የወሬ ወፍሞ አትሁን ። ስራ ቢኖርህ የሰው ህይወት ውስጥ ገብተህ

አንዴህ አትፈተፍትም ነበር ፡፡ ውጣ !» ብሎ ሲጮህበት ጊዜ ጅራቷን የኋላዋ እግሮች መካከል እንደ ወሻ ኩስስ ፤ ሙሽሽ ብሎ ፤ ወፍራም ሰውነቷን እያን ከባለለ ወጣ ፡፡ የሆነ ሆኖ ፤ አበራ አእምሮ ውስጥ አንድ አይነት ነቀርሳ ሳይተክልና ትኩስ ቁስል ልቡ ላይ ሳይተው አልሄደም ፡፡ ጠረጴዛው ላይ በግንባሩ ተደፍቶ የጠረጴዛውን ወለል በቡጢ እየደበደበ ፤ «አሁንስ የት ልግባ ? የት ብደርስ ፤ ምን ብሆን ይሻለኛል ? ጭንቀቴንና ስቃዬን እንግዲህ ማን ይሰማኝ ? ቀና ብዬ ባየው ባዶው ሰማይ አፉን ከፍቶ ይስቅ ብኛል !» በማለት በታላቅ ጣር ሲጨነቅ ቆየና ወረቀትና ብእር አንስቶ ሲያበቃ ማር ማር ካደረገ በኋላ ፣ ጸሀፊውን ‘ሱቅ በደረቴን’ አስጠራት ፡፡

እያለቀሰች የስራ መልቀቂያ ደብዳቤውን ትመታ ጀመር.....

# ፫

አበራ የጐረሰውን እንጀራ ሳይሆን አእምሮው ውስጥ የሚንገዋለለውን ሀሳብ ነበር የሚያላምጠው ፡፡ ምግቡም ሆነ ሀሳቡ ምንም ጣእም ስላልሰጡት ገበታውን ትቶ ተነሳ ፡፡

ስራውን ለመልቀቅ እንደሚፈልግ ነግሮአት በመሰረቱ ቢስማሙም አሁን ሳያስጠነቅቃት ካደረገው ዘንድ ፤ ወንድ ፤ በዚያም ላይ የእለት እንጀራ አቅራቢ ባል በመሆኑ ፤ በቤት ጥላ ስር ወድቆና የሚስት ጥገኛ ሆኖ መኖሩን ሲቀበል አልቻለም ። የተፈጥሮን ድንጋጌ ያቃወሰ መስሎት ታየው ።

የሆነ ሆኗል በማለት ምንም ቢሞክር ወኔው እያመጻ አስቸገረው ። ከወኔው አመጽ ይበልጥ ግን ከሀሳብ አዘቅት ወስዶ የዶለው ሳይወድ በግድ አእምሮው ውስጥ ሰርጾ የገባው ጥርጣሬ ነው ።

ጣኦት ፤ ጠይም ጣኦት!

ከስራው ሰንብት የጠየቀበትን ደብዳቤ እያሰበ ፤ «ታዲያ ለምን በዚህ ሰአት አደረግሁት ?» ሲል ራሱን ጠየቀ። ወደ ውስጡ ዘልቆ ራሱን በመመርመር መልሱን ፍለጋ ላይ ሳለ ፤ «እንግዲህ ጀመርክ ›» አለችው ፤ ሶሊት ከፊት ለፊቱ ተቀምጣ ።

«ምኑን ?»

«ጋግርትህን»

ትኩር ብሎ እያያት አይኖቿን መረመረ ። ከራሱ ጥርጣሬ ሌላ ምንም ሊያይባት አልቻለም ። አይኖቹ እሷ ላይ ተተክለው እንደመቆየታቸው መጠን ፤ ከህይወት ይበልጥ ግዙፍነቷ በአይኑ ህሊናው ጐልቶ ታየው ። ወደ ጠይም ጣኦት ተለወጠችበት ። ኢመለካት ። ወደዳት ።

«የስራ መልቀቂያ ደብዳቤዩን አቅርቢ ነው የመጣሁት ›» ሲል ድንገተኛ ዱብ እዳ ጣለባት ።

ያልጠበቀችው ነገር በመሆኑ እንደመደንገጥ ብላ ፣ «ምን አስቸኮለህ ?» አለችው ።

«የመቸኮል ሳይሆን ምን ያህል እምነት ባንቺ ላይ እንዳለኝ ላሳውቅሽ ነው ፤» አላትና አእምሮው ውስጥ ስርጾ የገባውን ጥርጣሬ መንጭቆ ለማውጣት ሞከረ ። እንግዲህ በሆነ መንገድ ፣ «ከጥርጣሬ የሚመጣውን በሽታ ለማዳን ራስን መስዋእት ማድረግ ነው ፤» ሲል አሰበ ።

«አይ አበራ ፣ ለምን እንደሆነ እንጃ... ታሳዝነኛለህ...» ከማለቷ ፣ «እኔ የምፈልገው አፍቃሪ ሚስት ነው ። አዛኝ አላጣሁም፤» አላትና ወዲያውኑ ፣ ታዲያ ራሴን እግሯ ስር የጣልኩት ለምንድንነው? ሲል ራሱን ጠየቀ ። ራሱን ጠላ ። ምንም ሳይላት ተነስቶ ጥሏት ወጣ ።

ያን ቀን ማታ አምሽቶ ሲመለስ ጥምብዝ ብሎ ሰክሮ መጣ ። እየተንገዳገደ ሄዶ ፊቱን በመስተዋት ለማየት ሲሞክር በማግሳቱ ፣ «ግሳት ብቻ !» ብሎ ወደ ሉሲት ዞረ ።

«አዛኝቱ! ጣኦት ከመሆን አልፈሽ እንደ እምዬ ማርያም አዛኝ ለመሆን ነው ? በኔ ላይ አይደለም !»

«ታሳዝነኛለህ ማለት ነውር ሆኖ ነው ይህ ሁሉ ጣጣ !» ስትለው ሁሉ ከአፏ ከሚወጣው ቃል እንባዋ ይቀድም ነበር ።

«እኔ የሚታዘንልኝ ሰው አይደለሁም ። ወይስ የኔ ወንድነት ...ይህ ...እይው ይህ አልጠቅምም ብሎሽ ነው ? ...አዎን ፣ ዳሩ ምን ይሆናል ? ባንቺ አይፈረድም ። ወንዶችን ሞቶ ሀሞታችን ፈስሶ ሴት ሆነናል ። እዚያ ማካ ውስጥ እንጋሎ

እንደተጫወተብሽ አረመኔ ብሆን ኖሮ አፍሽን ሞልተኝ ታሳዝነኛለህ አትይኝም ነበር …»

ከተኛችበት እንደመብረቅ ተወርውራ ተነሳችና ፤ «እንግዲህ በቃህ !» አለችው በሚያንቀጠቅጥ ድምጽ ። ከንዴቷ የተነሳ የጋለው ፊቷ እንደተጠማ መሬት እንባዋን በንዳፍታ ምጥጥ አድርጎ አደረቀው ። «አንተው ካመጣኸው የእቅጩውን ልንገርህና ፤ ያገባሁህ ለፍቅር አልነበረም ። ሆኖም ደግነትህ እየሳበኝ ላፈቅርህና ጥሩ ሚስት ለመሆን ሞክሬ ነበር ። እድል አልሰጠህኝም ። እንዲህ ከሆንክ ደሞ ገደል ልትገባ ትችላለህ ! ሉሲት ደንታ የላትም ። ለማንም ወንድ ደንታ የላትም ። ምን አይነት አበሳ ነው ? እንዴት ያለ ስቃይ ? አንተም አረመኔ ነህ ! በቃ!»

የተናገረችው ሁሉ ምን አይነት ስሜት አድርሶበት እንደሆነ ለማወቅ ዞር ብላ አየችው ። ሚዛኑን ለመጠበቅ እግሮቹን አንፈራኮ ቆሟል ። እንደከረምት ኩሬ ደፍርሰው ወደ ውጭ የተጐለጐሉት አይኖቹ አርፈውባታል ። ግን አያዩዋትም ፤ በትክክል ። ወደታች የተንጠለጠለው መንጋጋው ቂል አስመስሎታል ። ማጅራቱ የራሱን ቅል ደግፎ ለመያዝ ስላልቻለ እንደወገሬ ማሽላ አንገቱን ዘልሶ ከመታየቱም በላይ ጉያውን እንደጨበጠ ቀርቷል ።

ለማስታወክ ፈለገ ። ወደመታጠቢያ ቤት ለመሄድ ግን በሩ በየት በኩል እንደሆነ ለማወቅ አልቻለም ። ችግሩ ስለገባት እጁን ይዛ ወደመታጠቢያ ቤት መራችው ። ሰገራው አፍ ላይ ተደፍቶ ጉንበስ ቀና እያለ ሲያስመልሰው ሁሉ ልቡን ደግፋ ይዛለት ነበር ።

ሁኩቱ ገለል ብሎለት ትንፋሽ ማግኘት ሲጀምር ፤ «ሆሞታችን ፈስሶ ያለቀው በዚህ አኳሆን ነው ፤ ስገራ ገብቶ አልጻል ?» አላትና ውሀ ለቀቀበት …

፲

እሑለ ቀን ሲሆን ወይም ወደዚያ ገደማ ከእንቅልፉ ባንኖ ነቃ ። ሉሊት አጠገቡ የለችም ። ምንም ቢሰክር አእምሮውን ባለመሳቱ ማታ በሉና በሉሊት መካከል የሆነ ውን ለማስታወስ ሞከረ ። እሱ እንቅልፍ ይዞት እሷ በመ ሄዷ ተቆጨ እንጂ አላማረራትም ። ይልቅ አእምሮው ውስጥ የገባው እንግዲህ ሰው ምን ይለኛል ? የሚል ጥያቄ ነበር ። መልሱም ቢሆን አልተሰወረውም ። ከስራም ሆነ ከሚስት የማይረጋ እብድ እንደሚሉኝ እውቃለሁ በማለት ሲያስብ ቆይቶ ምን እንደመራው ሳያውቅ ፤ ከኮሞዲኖው ውስጥ አንድ ትንሽ ሽጉጥ አወጣ ። አቶ አባተ ለስርጉ ያመ ጡለት ስጦታ ነበረች ።

«አንድ የጥይት እርሳስ … ዘለአለማዊ ሰላም … ባይ ርገውስ ? አሁን … አሁን …» ሰውነቱ በላብ ተደፍቋል ። ሆኖም የመኖር ፍላጎቱ አይሎ ከሚንቀጠቀጠው እጁ ጋር ይታገል ጀመር ። ነፍሱ ተለማመጠችው ።

ሲመኖር ብፈልግም ልኖር አልችልም ፤ ሲል ከራሱ ጋር ተከራከረ ። ያኔ ነበር ስለራሱ አንድ ነገር ያወቀው ይህን ህይወት ትቶ ለመሄድ የፈለገበትን ምክንያት የተረዳው።

«ሌላው የፈለገውን ቢለኝ ደንታ የለኝም …እፀም ከሄደች መንገዱን ጨርቅ ያድርግላት ። ብቻ ይቅርታ እንኳን ጠይቄአት ብትሄድ ኖሮ ምን ነበረበት ? ትሂድ ። እኔን የጨነቀኝ …»

የመኝታ ቤቱ በር በድንገት ብርግድ አለ ። ሶፊት ዘልቃ መስኮቱን ስትከፍት እጁ ውስጥ የነበረችውን ሽጉጥ ትራሱ ስር ደበቃት ።

«ነቅ፡ተሀል እንዴ ?»
«ሞቼ የምቀር መስሎሽ ኖሮዋል !»
«ማታ ላየህ ሰው ሳይመስለው አይቀርም !»

ስለማታው ጉዳይ እንደገና ለማንሳት አልፈለገም ። ዝም አለ ። ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት ብአይኑ ሲጋ ሁለተኛ የማይገናኙ መስሎት ስጋት አድሮበት ነበር ። ስጋቱ ጨርሶ ከልቡ ባይጠፋም አሁን ስሳያት መናደድ ጀመረና ፤ «ስራ ስትሄጂ ለምን ሳትቀሰቅሺኝ ወጣሽ ?» ብሎ በመጠየቅ አፈጠጠባት ።

«ስራ አልሄድኩም ።»
«ታዲያስ ?»

«ቤት ስፈልግ ነው የዋልኩት ።»

አጢው ዱብ ብሎ ፤ «የምን ቤት ! ?» አሳት ።
«የኪራይ ቤት ነዋ ። አነስተኛ ቤት መፈለግ አለብን ብለ

ሆኝ አልነበረም ? በስድሳ ብር እዚህ አፍንጮ በር አጠገብ ጥሩም ቤት አግኝቻለሁ ። ባለሶስት ክፍል ሆኖ ሰፊ ምድር ቤት አለው ። ምድር ቤቱ ከታደሰና ብርሀን እንዲያገኝ ከተደ ረገ ግሩም ስቱዲዮ ይወጣዋል ። እንዲታደስ ገንዘብ ከፍዬ ነው የመጣሁት — በአስር ቀን ውስጥ ይደርሳል ...»

ከተቀመጠበት ተነስቶ አቀፋት ። ለረጅም ጊዜ ተቃ ቅፈው ቆሙ ። የሚነጋገሩት በልባቸው ትርታ ብቻ ነበር ። «ያገባሺኝ ለፍቅር አለመሆኑን እያወቅሽ ይህን ሁሉ ምን አሳሰበሽ ?» ሲል ጠየቃት ፣ የፈለገው የተናገረችው ሁሉ ከልቧ አለመሆኑን እንድታረጋግጥለት ነበር ። ጥያቄውን ወደጐን አድርጋ ፤ «ይልቅ የስእል ስራህን ስትጀምር እኔን ወርሶ እንዳትረሳኝ ቃል ግባልኝ» አለችው ። ቃል መግባ ቱን በከንፈሩ ማህተም አረጋገጠላት ። ወዲያውኑ ለወደፊት ሱሊትን እንዴት አድርጐ ለመስራት እንደሚችል አንድ ሀሳብ መጣለት — ያ በአይን ህሊናው ከህይወት ይበልጥ ጐልቶ የሚታየው ርለምትህት ግዙፍነቷ ነበር ።

በተጨማሪ አስር ቀን ...በጉጉት በጭንቅ ተይዛ የነበ ረችው ነፍሱ ፋታ አገኘች ። አሁን አስር ቀን ቀርቶታል ።

## ፳

«ታውቃለህ !» አለው ሀይለማርያም ፤ «አስር ቀን … አስር ቀን ፤ አስሬ ስትል እንደ ፈራህ ያስታውቃል ። ያ ቀን እንዲመጣ አትፈልግም ። ለዚህ ነው ቆይ እዳዬን ልጨርስ ስትል ከርመህ ጊዜው ሲደርስ በድንገት ተነስተህ ያገባሽው፤ ከዚያ ደሞ ስራህን ለመልቀቅ ምቹ ጊዜ ስትጠብቅ ቆየህ ። ከዚህ በኋላስ ? ሚስትህ እርግዝ እስከምትወልድበት ቀን ድረስ መጠበቅ አለብህ ፤ አይደለም ? የእውነቱን ካልክ ያ ቀን እንዲደርስ ከቶ አትፈልግም !»

ሀይለማርያም ሉሊትን ለመጠየቅ ነበር የመጣው ። «አዎን ፤ ነው !» አለ አበራ በድንፋታ ፤— «ምክሬ ያልሆንልኝ እንደሆንስ ? እውነተኛ የተፈጥሮ ችሎታ መሆኑ ቀርቶ ባዶ የፈጠራ ስሜት ፤ ትንሽ አየር የሚያስተነፍሰው የሳሙና አረፋ ሆኖ ያገኘሁት እንደሆንስ ? ምን ለመሆን እችላለሁ ! ሀይወትን እንተውና ራሴንም ቢሆን ለማየት ድፍረት አይና ረኝም ። መሞት ይሻለኛል ። ይህ ለምን ሊገባህ አይችልም !» «ይገባኛል ። እውነተኛ ችሎታ አይናፋር ናት ። ገበያ መው ጣት ያስቸግራታል ። እኔን የማይገባኝ ግን በፍርሀት ጥይት ሰው በቁመናው ራሱን ሲገድል ነው ። አሊታወቀህም እንጂ ፈርተሀል ። የሻገተ ፤ የዛገና የደነዘ ኑእምሮ በድን ገት ተነስቶ ራሱን ለማዘዝ አይችልም ። ታፍና የኖረች ሀይወት ንጹህ አየር መተንፈስ ጭንቋ ነው ። ማስተጋባት

አገሺ መፍጠር ሲቃይ ይሆንብናል ። በሽተኞች ነን ። እአምሮአችን ታሟል ። ነፍሳችን ታማለች ። በሽተኞች ነን ። ፍርሀትህ ይገባኛል …» እንዳለው አቶ አባተ እሳት ጉርሰው ደረሱ ።

ሀይለማርያም ያንን ወፍራም ፈገግታውን እያሳያቸው ፤ «ምንነው ከናካቴው ሰላምታ እንኳን ነፈጉኝ ?» ሲላቸው ጊዜ ፤ «ተወኝ ብዮሀለሁ ። ባለጌን ካሳደገ የገደለ ይጸድቃል የተባለው ያለምክንያት አይደለም ። ደሞ እንደቡዳ አታፍጥብኝ !» አሉት ። ወደ መኝታ ቤት ሂዶ ሉሲትን ከተሰናበተ በኋላ ቅሬታ ሳይገባው እየሳቀ ወጣ ።

ሉሲት የአቶ አባተንና የወይዘሮ ባፈናን አይን ማየት ካስጠላት ጊዜ የላትም ። በመጡ ቁጥር ስለዘራቸው ጥራትና ትልቅነት ፤ ስላለፈው ክብራቸውና የኑሮ ድሎት በሰፊው ስለሚያወሯት መስማት ሰልችቷታል ። ከመሰልቸትም በላይ በዘር እቋም ከሷ እንደሚሻሉና ወገናቸውን በክብር መያዝ እንደሚገባት በዙሪያ መንገድ የሚነግሯት እየመሰላት መናደድ ጀምራለች ። ወይዘሮ ባፈና በመጡ ቁጥር ፤ «ምንነው ወላጆችሽን አላስተዋወቅሽን ? ዘመዶችም የሉሽ ? እንዴት ሰው ያለዘር ይፈጠራል ?» ሳይሏት አይሄዱም ።

ሀይለማርያም ከመውጣቱ አቶ አባተ እንደልማዳቸው ትከሻቸውን ወደፊት አስቀድመው ፤ «ደሞ ምን ነካህና ከስራህ ተፈናጠርክ ?» አሉት ።

«ምንም ።»

«እንዴት ምንም ? ሰው ያለምክንያት ከስራው ይወጣል ? ጤና አይደለም ። አንድ ቦታ ረግተህ ሰው እንዳትሆን የሚያዞር ፤ የሚያንከራትትና የሚያንቀዠቅዥ መድሀኒት

እንዳቀመሱህ ገብቶኛል ። የቀረህ ጨርቅህን ጥለህ መሄድ ነው ። ለዚህ ማርከሻው ጠበል ብቻ ነው — ሌላ አይደለም ።

የወንድሙ አስተያየት ከሌሎቹም እንደበት ይላ ማል ። ጥቂቶቹ ፤ አበራ የደረጃ እድገት ወይም የደመወዝ ጭማሪ ሲያገኝ ከሰራው የሚያፈናቅለው በሽታ አለው ፤ የደረጃ እድገትን የሚያስጠላ መድሀኒት አቅምሰውታል ሲሉ ፤ ሌሎች ደግሞ ፤ የለም ፤ እንዲያው ሞኝነትና ልጅነት ይዞት ከሀላፊነት ለመሸሽ ያለው ነው በማለት መካሪ በማጣቱ ሲያዝኑ ፤ የቀሩት ፤ መቼ እንዲህ ሆንና ፤ እሱ ከገንዘብ በስተቀር ሌላ ፍላጐት የለውም ፤ ለገንዘብ ይሞታል ፤ ለዚህ ነው ለትንሽ የደመወዝ ጭማሪ እንደገረድ ከአንዱ መስሪያ ቤት ወደሌላው እያለ የሚኖረው በማለት ሲጋው አልፎ አጥንቱ እስኪቀር ድረስ በጭቀው ያሙታል ። አበራ ለዚህ ሁሉ ደንታ የለውም ። እሱን የጨነቀው የእለቱ ቀን እየተገባደደ መሄድ ብቻ ነው ።

፳

ቀንገኮ የተወለድኩበት ቀን ነው ። እንዲጋጣሚ ሆኖ የመወረኛ ደሞዜንም የምቀበለው ነገ ነው ። ጥሩ አጋጣሚ አይደለም? አብረን ማክበር አለብን ፤ እሰና ለሁሊት ነገራት ። ወይ በምትኩት ! ለምን ቀደም ብለህ አልነገርከኝም አበርሽ ፤

«ትዝ ያለኝ አሁን የተፈጠርኩበትን ቀን ስራገም ነው ።»
«የተፈጠርክበትን ቀን የሚያስረግም ምን ነገር መጣ ?»
«አላውቅም ። ምናልባት ፈርቼ ይሆናል ።»

ባይሆን እንኳን ምንም ሳይፈራ በናፍቆት ነገን ቢጠብቅ ውሎ አደረ ። ከዚያ መከረኛ ቀን ሀሳቡን ወደሌላ የሚያመራ ማንኛውም ነገር ለጊዜውም ቢሆን ፋታ ስለሚሰጠው እንደትልቅ ቁም ነገር አድርጎት መመልከት ጀምሯል ። መጠጥ ብቻ ሳይሆን በግድም ሆነ በውድ ሉሲት ጋር ሳይታገልና ፍቅሩን ሳይገልጽ ያደረበት ሉሲት የለም— አብሮ አልፎ ቀንም ቢሆን ፤ ይህ አዲስና እንግዳ የሆነ ጠባይ ባይገባትም ስመመን ይሻናል በማለት ጠለቅ ብላ ለመመራመር አልሞከረችም ። ግን ለአበራ እንደሆን አድራጐቱ ጠለቅ ያለ ትርጉም ይሰጠዋል ። የሚታየው ጊዜውን ማሳለፉ ብቻ አይደለም ፤ የሚፈልገው በፍቅር ጦር ሲጎዳት ነው — ጣሩዋ ደስታ የሚሰጠው ይመስል ።

ያን ቀን ጧት ስንት ደቂቃ ጠብቋት ከቤት ሲወጡ እንዲያ እንደልማዷ ከእግር ጥፍሯ እስከራስ ጠጉሯ ተሸሞንሙና ስላያት ፤ «ቢሮ ለመሄድ አሁን ይህ ሁሉ ጌጥ ምን ያስፈልጋል ?» ሲል በአይኑ እያሽሟጠጠ ጠየቃት ።

«እኔ ከማን አንሳለሁ ?» ነበር መልሷ ።

የወጣችው ጸሀይ በሀይሏ የምትተማመን አይደለችም ። የሰማዩን አመድማ ቀለም ተቀብላ የምትወረውር ትመስላለች ። ማታ ዝናብ ዘንቦ ስለነበረ አየሩ ላይ የሚንሳፈፈው አቧራ በመታጠቡ ህይወትን የሚያድስ ንጹህና ቀዝቃዛ አየር ይነፍሳል ።

አበራ ሉሲትን መስሪያ ቤቷ ካደረሳት በኋላ ወደ መስ ሪያ ቤቱ ሄዶ የመጨረሻ ደመወዙን ለመቀበል ጊዜ አልወ ሰደበትም ። መቀበሉንና ቀሪውን የወንድሙን እዳ ለመ ክፈል መሄዱን ሊነግራት ወደሉሲት ስልክ ደወለ ። አልነበ ረችም ። ትንሽ ቆይቶ እንደገና ደወለ ። የሄደችበትን የሚ ያውቅ አልነበረም ። በምክንያት ሳይሆን እንዲያው በስ ሜት ተነስቶ ወደ መስሪያ ቤቷ ሄደ ።

የፖሊስ ቆመጥ የሚያክሉ አድማጪአቸው የገፋ ጥቁር የመስሪያ ቤቱ ዘበኛ አይተውት ፤ «የውሀዬ ጌታ» አሉት በቁልምጫ ። ሉሲትን ከተዋወቀበት ጊዜ ጀምሮ አልፎ አልፎ ኪሱ ውስጥ ያገኘውን ፍራንክ ለውሀ ጥምዎ እያለ ይጥልላቸው ስለነበረ ባዩት ቁጥር ጠብ እርግፍ ይሉስታል ።

«ምንነው ደህና ?»

«ሉሲትን ነበር የምፈልገው»

«አይ…አሁን እንዲያው ለጥቂት ። ወይዘሮ ሉሲት አሁን በቅርቡ ካንድ ሰው ጋር በጥቁር መኪና ሲወጡ ያየሁ መሰለኝ …»

«መኪናው ምን አይነት ነው ?…እ…ለብርቱ ጉዳይ ፈልጌ አት ነበር ።»

«እንዴት አይነት ልበልህ የኔ ጌታ ? አዎን ፤ የሄዱበት መኪና ቀለሙ ጥቁር ይሁን እንጂ ልክ የዚያ አይነት ነው ። ምን ነካህ ? ምንነው ደህና ?»

የ፲፱፻፺፱ አመተ ምህረት ሞዴል የሆነ ኦፔል መኪና ነው ። በዚያን ሰአት ተሰማ ደጀኔ ያሰማው ሹክሹክታ ከየትም መጥቶ ጆሮው ውስጥ ደወለ ። ጢት ሲያመጣት

የደረገችው ጌጥ ሁሉ ታየው ። የተርከፈከፈችው ሽቶ ሽተተው ። ለአይን ህሊናው ከህይወት በላይ ግዙፍ ሆነች ። መኪናውን እንደ አዙሪት አሽከርከሮ ወደኮተቤ የገጠር መናፈሻ ቡና ቤት እንደአውሎ ነፋስ በረረ ።

እውነትም በጓሮ በኩል ከቡና ቤቱና ከመኖቤቱ መካከል ባለው መተላለፊያ ላይ ጥቁር የ፲፱፻፶፱ አመተ ምህረት ሞዴል ኦፔል መኪና ቁማ በማየቱ ልቡ ከውስጡ ተበጥሶ የወደቀ መሰለው ። አእምሮው እንደድር ተወሳስበው ሊጨበጡ በማይችሉ ሀሳቦች ውስጥ ገብቶ ይዋኝ ጀመር ።

መኪናው ውስጥ እንዳለ አሻቅቦ በከፍተኛ ውሀ ልክ ላይ የተሰራውን ሰቀላ ቤት ተመለከተ ። በረንዳውን ከዳር እስከዳር የሸፈኑት መጋረጃዎች ክፍሎቹን ከልለው እያሳዩም ። ቁጭ ብለው በመጠባበቅ ሲወጡ ሲይዛቸው ልቡ ቢከጅልም በሀሳቡ ሉሊት ከሌላ ሰው ጋር ስትዳራ ፣ ስትደስትና ፣ ላቧ ከሌላ ሰው ላብ ጋር ተዋህዶ ፣ የሌላ ወንድ ጠረን ስትወስድ ማየቱ ሊያስቀምጠው አልቻለም ። ያ ግዙፍነቷ በአይነ ህሊናው መጣ ። ስሜቱን የሚገታበት ሉጋም ከዳው ። የመኪናውን ድምጽ አሰማ ። ወዲያውኑ እንደ እህል ቀምሶ የማያውቅ የሚመስል ጥቁር ረጅም የሆቴሉ ቤት እንግዳ ተቀባይ ሲሮጥ መጣና «አቤት» አለው ፤ በሻሽ ወይም በነጠላ ፉቲን የሸፈነች እስከሬን መሳይ ቤት መኪናው ውስጥ ባለማየቱ እየተገረመ ። ብቻውን እዚህ የሴት ቁራ ምን ያደርጋል ? የሚል ጥያቄ ፊቱ ላይ ይነበባል ። «የዚህ መኪና ጌታ ጓደኛዬ ነው ። በጣም ባስቸኳይ እፈልገው ነበር ። የተኛበትን ክፍል ታውቃለህ ?»

«እነሳቸው እራት ቁጥር ናቸው ።»

በፈጣን እርምጃ ወደ አራት ቁጥር አመራ ። ምን ሰማ ብሎ እርግጠኛ ሆኖ ለመናገር ግን አይችልም ። እእምሮው ፈርጅ ድረግ አስቦ እንደሆነ ግን አሳወቀም ። እእምሮው ፈርጅ ብሎ ዕረፍት ሊሆን አልቻለም ። በሌላቸው ሀሳቦች ውስጥ ሰጥሞ መዋኘቱን አልተወም ። በሌላ ወንድ እቅፍ ውስጥ እንደሂዋን እርቃን ሰጋዋን በደስታ ብትፈነድቅ የማግኘቱ ሀሳብ ስውነቱን ዘገነነው ።

በሩን አንኳኳ ። የመቃብር ዝምታ ። የሚሰማው የልቡ ትርታ ብቻ ነው ። እንደገና አንኳኳ ። «ማንነው ?» የሚል ወፍራም የወንድ ድምጽ ከውስጥ ሰማ ። አበራ መልስ አልሰጠም ። ለሶስተኛ ጊዜ አንኳኳ ። እንደገና የመቃብር ዝምታ ። በሩን ሰብሮ ለመግባት እንደተዋጊ በግ ወደኋላ አፈግፍጐ ወደፊት መንደርደር ባይ ሳለ ድንገተኛ ተኩስ ሰማ ። ወደ መኪናው ሮጦ ተመለሰና እቶ አባተ የሰጡትን ሽጉጥ አውጥቶ ካቀባበለ በኋላ በመጣበት ፍጥነት ተንደርድሮ በሩን ሲሰብር፤የሞት ጥላ ያረፈበት ይመስል በመቃብር ዝምታ ተውጦ የነበረው ሰፈር ሰላሙ ባንዳፍታ ተናጋ ። ጩኸትና ሩጫ ሆነ ።

በየክፍሉ ውስጥ የነበሩት ሴቶችና ወንዶች ከየጉሬአቸው እየተፈተለኩ እንደሚወጡ አይጦች ሹልክ ፣ ሹልክ እያሉ ሲጠፉ ይታያሉ ። አበራ ሽጉጡን በቀኝ እጁ ይዞ ፣ ሰብሮ ከገባበት ክፍል ሲወጣ በህልም ኣለም ውስጥ የሚንሳፈፍ አስከሬን እንጂ ሰው አይመስልም ነበር ።

ህይወት የሌላቸውን አይኖቹን ምእተ አለም ላይ አሳርፎ ኦረኛውን ሲወርድ ፣ ሲመጣ ያነጋገረው የቡና ቤት አስተናጋጅ ብቻ ሲቀር ፣ ሌሎች ደጅ ተሰብስበው የነበሩት

ሰዎች ገለል አሉለት ። አንዳንዶቹም እግሬ አውጭኝ እያሉ ወደጓሮ ዞሩ ።

ተላላኪው በሁለት እጆቹ ራሱን ይዞ ፣ «ምንነው ጌታው ! እንደአምላክ አምኜዎት… ምንነው እንዲህ ጉድ ሰሩኝ ! አወይ እንጀራዬ ! ሰርቼ እንዳልበላ ፤ እንዳያልፍልኝ ቀኑ……» እያለ እዬዬውን እንደዶፍ ሲያወርድ ፤ አበራ እንደ እብድ በሳቅ ፈነዳ ። የሳቅና የልቅሶ ልዩነት እስኪ ዘነጋው ድረስ ሳቀ ። በሳቅና በልቅሶ መሀል ተይዞ ፤ «እንዲህ ያለውን አጋጣሚ በፍጡሩ ላይ የሚያደርስ አምላክ ካለ ቀልደኛነቱ እንጂ አምላክነቱ አይታየኝም ፤» እያለ ያስብ ነበር ።

# ክፍል ሶስት

## ፩

ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ያ ሀሳብ ከአእምሮው አልተለየም ። የአምላክ ቸርነት ፣ ፍቅርና ርህራሄ የሚባለው ነገር የቱ ላይ እንደሆነ ሊገባው ስላልቻለ የደረሰበትን ፈተና ለመቋቋም ልቡን ወደ አምላኩ መልሶ በልቅሶና በጸሎት እንደመማለድ የእግዚአብሄርን መኖር ጨርሶ ከልቡ እስከማውጣት ደረሰ ። እግዚአብሄርን ሳጣ አለምና ምንም ምክንያት ለሌለው ከንቱ ህይወት አንዳች ጠብታ እንባ ሊያፈስ አልቻለም ። ውስጡ እንደኮረት ሻክሮ የእንባው ከረጢት ከመድረቁም በላይ ፤ ለሞትም ሆነ ለሽረት ደንታ አልነበረውም ። ብቻውን ቆሞ ቀረ — ያለፈጣሪ ።

ከመደንዘዙና ተስፋውን ቆርጦ የህይወትን ጣእም ከማጣቱ የተነሳ ፣ በወህኒ ቤቱ መኝታ ቤት ውስጥ ያለው ከሩቅ የሚገለማው የሰገራ ግማት ፣ የመኝታ ቦታ ጥበትና ሰው ሆኖ መፈጠርን የሚያስጠላው አሰቃቂ ትፍግፍግ ፣ ለረጅም ጊዜ ውሀ ነክቶት የማያውቀው የሰዉ ገላ ክርፋት ፣ የሽራና የዝናብ ማማዎች ጥምባት ፣ ከደረቅ ጥቁር ዳቦና ከረጋ ጥቁር የሽሮ ዶኬ ሴላ እህል ረስቶ የከረመ

የሰው ትንፋሽ ሽታ—አዎን ፣ እነዚህ ሁሉ እንኳን ምንም ስሜት አልሰጡትም ። ለምንም ነገር ስሜት አልነበረውም ።

ጸጸቱ ራሱን ሶስተኛ ፖሊስ ጣቢያ ድረስ እንደበግ እየጐተተ ሂዶ እጁን መስጠቱ ነበር ። መቶ ጊዜ ደጋግሞ ፣ «ለምን ራሴን ሳልገድል ቀረሁ?» በማለት ሳይጠይቅ አልቀረም ። ግን ያኔ አላደረገውም ። ነፍሱ ምስጢሯን ስላልገለጸችለት ለምን እንዳላደረገው ምክንያቱ ሊገባው አልቻለም ።

ዞሮ ዞሮ የሚመለሰው ግን እዚያው፣ «እግዜር እንዲህ ያለውን አጋጣሚ እንዴት በሰው ላይ ይፈርዳል ?» የሚለው ሀሳብ ላይ ነው ። ከሉሊት ጋር የተገናኘበትን ቀን ምርር ብሎ ረገመው ።

«ብቻህን ተክዘህ እስከመቼ ድረስ ትዘልቀዋለህ ወንድም?» የሚል ድምጽ ሰማ ። በመጀመሪያ ፣ ከዚህ አለም ውጭ የመጣ ድምጽ መስሎት ነበር ። ዞሬያውን ከነበሩት የሱብጤ እስረኞች አንዱ ሆኖ አገኘው ። ከሀሳቡ አለም ከመለየቱ በፊት የማይሰማው የእስረኞቹ ድምጽ አሁን እንደ ፈሳሽ ወንዝ እያጉረመረመ ጆሮዎቹ ውስጥ ገባ ። አንዳንዶቹ ሳያቸው ላይ ያረጁትን ነጠላዎቻቸውን ይቋጣሉ ። ጥቂቶቹ ድሪቶአቸውን በመርፌና በክር ቀውስውስ ይዘዋል ። ሌሎች ደግሞ ጸሀይ እየሞቁ ከየሸማቸው ላይ ተባይ ይለቅማሉ ። ከእስረኞቹ መካከል በጥርጣሬ መልክ የሚመለከቱትም አልጠፉም ። እንዲሁም ፣ ወጣትነቱንና ሁኔታውን እያዩ ከንፈራቸውን በመምጠጥ የሚያዝኑለት አልታጡም። አበራ ፣ አይኖቹን በደንብ ሲከፍት ከአብዛኞቹ እስረኞች

እፈንግጠው ባንድነት የሚያወሩ ጥቂት ሰዎች አየ ። አሳባ በሳቸውም ሆነ ሁኔታቸው የመጉሳቆል፣ መልክ አያሳዩም ። ከነዚህ መሀል አንዱ ከሸማቸው ላይ ተባይ ከሚለቅሙት እስረኞች ውስጥ አንዱን ጠርቶ እንዳሸከር ሲያዘው በማየቱ «እዚህም ?» በማለት ተገረመ ። ጆሮው ትእዛዙን አልሳተም ። «አስቲ ሂድና ሰገራውን አጥበህ ጥራኝ ፤» የሚል ነበር ።

ጆሮ አለና አጠገቡ ቆሞ የነበረውን እስረኛ፤ «ያ ሰው በምን ምክንያት ነው እንዲህ አሽቆጥቁጦ ሌላውን እስረኛ የሚያዘው ?» ሲል ጠየቀው ።

«አንተም የዳቦ ድርሻህን ወይም ሲጃራ ወይም ከውጭ የሚመጣልህን ምግብ ትርፍራፊ መስጠት ከቻልክ ብዙ እስረኞች እንዳሸከር ለማዘዝ ትችላለህ ። እኔም ስንቅ አቀባይ ዘመድ ፤ ቤሳ ብስቲን የሌለኝ ድሀ በመሆኔ ታዛዥህ ለመሆን ዝግጁ ነኝ ፤» ሲል ምንም ሳይዘገይ መለሰለት ።

አበራ ትኩር ብሎ ተመለከተው ። ሰውዬው ረጅም ፤ ድንደሳምና ጥቁር ሆኖ አይኖቹ በርበሬ ይመስላሉ ። የሚታየውን ሆዱን እያከከ ወደ ሀብታሞቹ ይመለከታል ። ታጥቦ የማያውቀው ጥቁር ቆዳው ላይ ጥፍሮቹ የሚተውት ነጭ መስመሮች ይታያሉ ። ጥቂቶቹ የሰውዬውን አይን ተከትለው ሄደዋል ። ሌሎች ደግሞ አበራ ላይ አፍጥጠው ቀርተዋል ።

አበራ ሳያስበው ሰውዬው ከጠገቡ በድንገት እንደ መቶ ሜትር ሯጭ ፈርጥጦ ሲሄድ፤ ሌሎችም ከያሉበት እንደ ወስፈንጥር ተወርውረው ተከተሉት ። ሁሉም ቦንድ ላይ ተደራርበው ወድቀው ለጥቂት ጊዜ ከተተረማመሱ በኋላ !

አበራ አጠገብ ቆሞ የነበረው ሰውዬ የተሸመበትን ነገር ይዞ ከላዩ ላይ ጥሏቸው ተነሳ ። ትንቅንቁ ለቁራጭ ሲጃራ ነበር ። ይህንን በማየቱ ሰው ስለመሆኑ አድሮበት የነበረው ጥላቻ በይበልጥ ነፍስ ዘርቶ አንጀቱ ውስጥ ሲገላበጥ ተሰማው ። ከህይወት መሰላል ስር መውደቅ የሰዉን ይሉኝታ፣ ክብርና ኩራት የጎን ያህል እንደሚገፍ ለመጀመሪያ ጊዜ የአይን ምስክር ሆኖ ስለተረዳው አዲስ አይነት ፍርሀት አደረበት ። መላ ሰውነቱ ተንቀጠቀጠ ።

«እኔም ከጊዜ በኋላ እንዲህ እሆን ይሆን ?» የሚል ጥያቄ ገባው ። ላመሞት ተመኘ ። በዚያኑ ጊዜ የሲጃራ ሱስ ተቀስቅሶበት ማጤስ በጣም አስፈልጎት ስለነበረ አቅበጠበጠው

«ጌታዬ ፣ ዘርጋው የሚልዎትን አይመኑ ፣ ለስራው እንደሆን እኔ አለሁልዎት!» አለው አንዱ ልጅ እግር እስረኛ ። የለበሰው ልብስ ላዩ ላይ ተቦጫጭቆ አልቋል ። ከመጎሳቆሉ የተነሳ መልኩ ጠይም ይሁን ጥቁር ለይቶ ለማወቅ አይቻልም ።

«ለምን አላምነውም?» ሲል የማወቅ ጉጉት አድሮበት ጠየቀው ።

«ሰባቂ ነው ። እርስዎ አዲስ ስለሆኑ ባያውቁት ነው እንጂ የዘርጋው ብጤ ብዙ ሰባቂዎች አሉ ...»

«ምንስ ለማንስ ያሳብቃሉ ?»

«ሲጃራ ያጤሳል ፤ የተከለከለ መጽሀፍ አስገብቶ ያነባል ፣ እስረኞችን ያሳድማል ፣ ወህኒ ቤቱን ሰብሮ ለመውጣት ያስባል ፣ እያሉ ለወህኒ ቤቱ አስተዳደር ክፍል ያሳብቃሉ ። እንደሚያዩት የምንጠብበቀው እርስ በርሳችን ነው እንጂ

«የታሰርኩትማ እናቴን ገድዬ ነው ።»
«ለምን?!»
«አባቴ በህይወቱ ሳለ ቀበኛው የነበረውንና መርዝ አጠጥቶ ገድሎታል ተብሎ አገር የሚጠረጥረውን ሰው ካባገባሁ ብላ ተነሳችና ብመክራት ፤ በጐረቤት ባስመክራት ፤ አሻፈረኝ ብላ ስላስቸገረችኝ አንድ ቀን ተናድጄ በዱላ ማጅራቷን መትቼ ገደልኳት ።» ብሎ ዝም አለ ። አበራ ሌላ ነገር ይጨምራል በማለት ሲጠባበቀው ከተቀመጠበት ጨርቁን ጥሎ ተነስቶ ራሱን በመያዝ እየተንጐራደደ «ወይ እምዬ...ማህጸንሽ ምንኛ ይረግመኝ ? ወይ እምዬ...እምዬ አንጂቷ... ጡቶችሽ ምን ይሉኝ...» እያለ እዩዩውን ሲያቀልጠው ከእስረኞቹ አንዳቸውም ዞር ብለው አላዩትም ። ቁም ነገር ብሎ የተመለከተውም አልነበረም—አንድ መንግና ፖሊስ ከውጭ ሲንደረደር መጥቶ በጥፊ ብሎ ዝም እስኪያሰኘው ድረስ ። ወዲያውኑ ወደ አበራ ተመልሶ ምንም እንዳልነ ካውና ምንም እንዳልሆነ ሰው ሆኖ ፤ «አደራምን እንግዲህ ያስጠጉኝ... ያለእርስዎና ያለፈጣሪ ረዳት የለኝም ። ዘርጋው እንደሆን አይሆንምትም ።» አለውና አግሩ ላይ ወደቀ ።

ሲጃራው እንዴት እንደሚገኝ በመጠየቅ ፈንታ ፤ «ከዘርጋው ጋር አትዋደዱም መሰለኝ?» በማለት ፍላጐቱንም ሆነ እረዳሀለሁ ብሎ ቃል መስጠቱን ለማዘግየት ሞከረ ።
«የጥላቻ ሳይሆን እሱ በስብቀትም ሆነ ከእስረኞቹ በመስረት እንደፖንም ይኖራል ። ቤቱ ነው ። ከወህኒ ቤት በወጣ በሳምንት ወይም በወር ተመልሶ ይመጣል ። አሁን ግን የመጨረሻው ሳዪሆን አይቀርም ። ሴሊት ካንድ ሽማግሌ ግሪክ ቤት ሰርስሮ ገብቶ ሲነቃበት ጊዜ ገድሎት ከኪሱ

አስራሁለት ብር ብቻ አግኝቶ እሷንም ሳይጠቀምባት ተያዘ…» ብሎ የጀመረውን ሳይጨርስ አበራ ስሙ ሲጠራ ሰምቶ ተነስቶ ሄደ ።

የጠራው ፖሊስ ወህኒ ቤቱ ጽህፈት ቤት ድረስ ባለ ስቶኪይ እንደሚፈለግ ነገረውና እያጀበ ወሰደው ። እንደ ደረሰ ሀይለማርያምን በማግኘቱ ባለፉት አስራ ሶስት ቀኖች ውስጥ ተሰምቶት የማያውቀው ደስታ ልቡን ወረረው ። «የት ጠፍተህ ከረምክ?» ብሎ ሲጠይቀው፣ ንዴቱንም ሆነ ደስታውን እንኳን ሊደብቀው አልቻለም ። ሆኖም ትርጉም ሊሰጠው ያልተቻለዉ አንድ አይነት ስሜት ሀይለማርያም ፊት ላይ ይነበብ ነበር ። ከአበራ ይልቅ ሀይለማርያም በይበልጥ ተጉሳቁሎ ነበር ።

«አልጠፋሁም ። ከተስፋዬ ጋር የመከላከያ ምስክሮች ስንሰበስብና ነገሩን ስናጠና የቀረበብህን ክስ ስንመረምር ፈጽሞ ጊዜ አላገኘሁም ።»

«ወንድሜስ? ካገር ቤት ተመልሷል?»

«አልተመለሱም ። ነገ ወይም ከነገ ወዲያ ይገባሉ ተብሎ ይጠበቃሉ ። የስሙለት ምን እንደሚሆን ለመገመት አልቻልም ። እጥፍ ሀዘን ይሆንባቸዋል ።»

«እናቴስ?»

መልስ ሳይሰጠው ሀይለማርያም ፊቱን አዞረ ። ትንሽ እንደቆየ ፤ «ፍርድ ቤቱ እንዳይህ የፈቀደልኝ ስለእናትህ ጉዳይ ነው ፤» አለው ሲቃ በያዘው ድምጽ ።

«ሞታለች፣ አይደለም ?»

«አዎን ።»

«መቼ?»

«ኪትናንት ወዲያ ። ኪታሰርኩ ቀን ጀምረው ካልጋ አልተነ ሱም ። ሆስፒታል ልወስዳቸው በጣም ጥሬ ነበር ። አል ታመምኩም ፣ እንዲያውም በጣም ጤና ይሰማኛል ብለው አሸነፉኝ ። እልፍኙ ነሽም መጥታ ልታይህ ያልቻለችው በዚህ ምክንያት ነው ።»

ከዚያ ለረጅም ጊዜ ሁለቱንም ከባድ ዝምታ ዋጣቸው ። አበራን ለመጠበቅ የቆመው ፖሊስ ብቻ ነገሩን ሰምቶ ሲያለቅስ ይሰማ ነበር ።

«እንባ የለኝም ። ለማልቀስ አልችልም ። በድን ሆኛለሁ ። ሞት እንኳ ካቅሙ ሸሸኝ ፤» በማለት ለሀይለማርያም ሳይ ሆን ለራሱ ሙክ ብሎ አወራ ። የድምጹ ባዶነት ተመልሶ ጆሮዎቹ ውስጥ አስተጋባ ። በዚያ ባዶ በሆነው ድምጽ ፣ «እናቴን ገደልኳት ፣ ልተብራትም አልቻልኩም ። በህይ ወቷም ሆነ በሞቷ ከዳኋት ። እግዜር ቢኖር ይህን አጋ ጣሚ በሰው ላይ ይፈርዳል?» አለ ።

ሀይለማርያም ፊቱን ወደ አበራ አዞረ ፣ «ይሆን ያህል ሆደ ባሻ አትሁን ። ራስህንም አታማር ... ባታውቀው ነው እንጂ ወደፈለገበት ሊመራህ እግዜር በጥበቡ አውቆ ያደረገው ነገር ይሆናል ፤» አለው ።

«ከዚህ የተሻለ ቀላል መንገድ አጥቶ ነው?»

«ሂቡ እይን ምን ክባድ ወይም ቀላል ነገር አለ? የሰዉ ደካማ ነት ነው...»

አበራ ሀይለማርያም የሚለውን ጠርሶ ለመስማት ትእግስት ስላጠረው ፣ «ከመቼ ወዲህ ነው ለእግዜር ጠበቃ የሆንከው!» ሲል ሞኸበት ።

«ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ...» እንዳለው ፖሊሱ ...«ሰአት ደርሷል» አላቸው ። የማስታወስ እንጂ የትእዛዝ ድምጽ አልነበረም ። «በሁለት ተቃራኒ አቅጣጫዎች ስንጓዝ ይታየኛል !» በማለት በመከራከር ፈንታ የእግዚአብሄርን ጉዳይ ደምድሞ ሲያበቃ አቀርቅሮ ለጥቂት ጊዜ ካሰበ በኋላ፣

«ሉሲትስ እንዴት ናት ?» ብሎ ጠየቀው ።

«አሁንም ይቅርታ አላደረገችልህም ። ሴቶች አንድ አይነት እምነት ካደረባቸው ሀሳባቸውን ለመለወጥ ተአምር ያስፈልጋል...»

«እሷ ደሞ በተለይ የባሰች ግትር ናት ። ለመሆኑ አሁን የት ነው ያለችው !»

«አዲሱ ቤት ነች ። ዛሬ እንኳን መጥታ እንድታይህ ላግባባት ሞክሬ ነበር ። አልሆነልኝም......»

«አያስፈልግም ነበር ። አሁን በአለም ላይ አጥብቄ የምፈልገው ነገር ቢኖር ሞትን ብቻ ነው...»

«ስለሱ አታስብ ። የሴትዮዋ ወገኖች ደምህ ጠምቶአቸዋል ። ከገመድ ጫፍ ተንጠልጥለህ ለማየት ሲሉ ማናቸውንም ነገር ከማድረግ የሚመለሱ አይደሉም ። አቅም አላቸው ። በዚህ ላይ ደሞ ያንተን ነገር የወሰደው አቃቤ ህግ በምን ምክንያት እንደሆነ እንጃ ሊያሰቅልህ ታጥቆ ተነስቷል ። ስለዚህ ምን አስቸከለህ ?»

ሀይለማርያም ትንሽ ቆይቶ በወሀኒ ቤቱ አስተዳደር ፈቃድ መሰረት ዳቦ ፣ የዳቦ ቅቤ ፣ ሰርዲንና ቶና ፣ ከፍራፍሬዎች ዘር ደግሞ ብርቱካን ፣ ሙዝና ፖም ፣ እንዲሁም በድስት ፓኮ ሲጋራ ፣ ገንዘብም ጭምር ትቶለት በአራት

ቀን ውስጥ ፍርድ ቤት እስከሚገናኙበት ድረስ ተሰናብቶት ሲወጣ የአበራ ልብ አብሮት ሄደ ። አንድ ሰሚት መጥቶ ሁለተኛ በአይኑ ስጋ እንደማይገናኙ ነገረው ። ለእናቱ መርዶ ልቡ ውስጥ ተቀርቅሮ የቀረው እንባ ወደላይ ገንፍሎ አይኖቹ ውስጥ አቀረረ ። ወደ በሩ ሮጦ፣ «ሀይለማርያም፣ ሀይለማርያም!» እያለ ተጣራ ። ሀይለማርያም ግን ርቆ ሂዶ ነበር ። «አንድ ነገር ሆኜ ነው እንጂ ይህ ለጤና አይደለም ። ወይም ከሱ መለየቴን ጠልቼ ይሆናል ፤» በማለት እያሰበ ወደወሀኒ ቤቱ ተመለሰ ። ገና ከመድረሱ ተሸክሞት የነበረውን ምግብ እንቀበልህ በማለት ብዙ እስረኞች እንደዝንብ ከበቡት ። አልለቀቀላቸውም!

፩

በእኩለ ሌሊት ነበር ንቃግነቱ የታወሰው ። ሁኔሬት ተማነው ። የእናቱ ሞትና ያለበት ሁኔታ ፤ ከጓደኛው የመለየትና ቀስ እያለ በእንቃቅቅ እየመጣበት የሚሄደው ከህይወት መሰላል ስር የመውደቅ ዝንባሌ እየከበዱት ሄዱ ። እንዳይገላበጥ ሰው በሰው ላይ ተደራርቦ ስለተኛ ቦታ አልነበረውም ። ግማት፤ ከርፋት ፤ ጥምባት፤ በዚያ ላይ መአት ቁንጫዎች ከሰርይፈተፍቱት ነበር ። በሰው ላይ እየሮጠ ሂዶ የበላውን አስመለሰ ። ለመጀመሪያ ጊዜ በዝምታ ስቅስቅ ብሎ አለቀሰ—በውድቅት ጨለማ፤ በእስረኞች ትንፋሽና ላብ በገለማ ሌሊት ።

ከዚያ በኋላ ለመቶኛትም ሆነ ለማሰብ ባላልቻለ እስረኞቹ የሚያወሩትን ያዳምጥ ጀመር ። አብዛኞቹ በሰላም ተኝተዋል ። አንዳንዶቹ ሲያኮርፉ የተኙበት በረት ያስተጋባል ። ጥቂቶቹ የሚያወሩት ወሬ ፤ «...ሲያምጽ ሲል ተያዘ... እኔ...ሲያምጹ ነው ይባላል...ተማሪዎች ሽብር አንሰተዋል...» የሚል ሲሆን ፤ ውይይታቸው ከሁከትና ከብጥብጥ አካባቢ ርቆ አይሄድም ። ቀንም የሚሠራው ይኸው ነበር ። አንድ እስረኛ ፍርድ ቤት ወይም ሀኪም ቤት ሂዶ ሲመለስ ሁሉም ተሰብስበው የሚጠይቁት ፤ «ከተማ ምን ይወራል?» የሚል የጸጥታን ጉዳይ የሚመለከት ወሬ ነው ። እስረኞች ሀወል የሚከተሉት የፖለቲካ እምነት ቢኖር ሁከትና ብጥብጥ መሆኑን አበራ ቀስ በቀስ እየገባው ሄደ ።

ጧት ከእስረኞቹ አንዱ የሆነ የመኝታ ቤቱ ካፖ ከእንቅልፉ ያለጊዜው ቀሰቀሰው ። እንቅልፍ አጥተው ያደሩትን አይኖቹን ለመክፈት ሲጣጣር ፤ «አንተ እጅህ አልፈታ ብሎ ነው እንጂ የተሻለ የመኝታ ቦታ እሰጥህ ነበር ?» አለው ። ምንም ሳይናገር አምስት ብር አውጥቶ ሰጠው ። ብዙ ገንዘብ የሰጠ ኦ አልመሰለውም ። የካፖው አይን ያየውን ለማመን አቅቶት ወደ ውጭ ተጉለጉለ ። ምግብም ሲጨምርለት ነበር — ካስቀመጠበት ባያጣው ኖሮ ። ከሁለት ብሩ ካንና ካንድ ፖም በስተቀር ሌላው ሁሉ ተሰርቋል ።

ያን ቀን ማታ አበራ ከስገራ ቤቱ የራቀ ሰፋ ያለ ቦታ በማግኘቱ እየተገላበጠ ቁንጫዎቹን ለመከላከል ችሎ አደረ ። ጧት የተቀሰቀሰውም በትህትና ነበር ። ተነስቶ ውጭ ሲወጣ እስረኞቹ ሁሉ በያሉበት እንገታቸውን ደፍተው ዝምታ ውጧቸው በማየቱ እንግዳ ነገር ሆነበት ። አካባ

ቢሮ እንደእና ቤት እሬጭ ከማለቱም ሌላ የአየሩ ክብደት ተጫነው ። ወዲያውኑ የወህኒ ቤት ፖሊሶች ፊሽካ እየነፉ እስረኞቹን ሁሉ ወደየመኝታ ቤታቸው መለሷቸው ። አበራ ወደ ፊጅ እግሩ እስረኛ ጠጋ ብሎ ፤ «ምንድንነው ? ምን መጣ?» ሲል ጠየቀው ።

«ከመካከላችን አንዱ በሞት ተቀጥቶ ነው ፤» አለው ።

አበራ በነገሩ እየተገረመ እንዳጋጣሚ ወደታች ሲመለከት ሰውዬው ኪስ ውስጥ ብርቱካን አየ ። ራሱ በማፈር ሳይነቃበት ቶሎ ብሎ አይኑን ወደሌላ አቅጣጫ አዞረ ። ብዙ አልቆየም ። ወደ ጽህፈት ቤቱ ተጠራ ። ሀይለማርያምን ለማየት የነበረው ጉጉት በጣም የጠነከረ ስለነበረ በሩጫ ደረሰ ። በሀይለማርያም ምትክ ጠበቃው ተስፋዬ ቁምላቸው የሀዘን መልክ ተጐናጽፎ ጠበቀው ።

አበራና ተስፋዬ በዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ የክፍል ጓደኞች ነበሩ ። የቅጽል ስሙ «ወስፌ» ነበር ። ምክንያቱም አፍንጫው ፤ ከቀኝ አይኑ ወደግራ አፉ ተወርውሮ እንደወስፌ ከመቆጋቱም ሌላ ፤ ትናንሽ አይኖቹ ደግሞ እንደእረቁ መርፌ ሰውን ስለሚጠቀጥቁና በተጨማሪ ፤ ስለታም ፊቱና ድምጹ ለፋሲካ እንደተሳለ ቢላዋ አየሩን ስለሚቆርጡ ነው ። ይኩራራበት የነበረው ጥቁር ሉጫ ጠጉሩ እንደመሳሳት ብሏል ። ጠጉሩ መሳሳት የጀመረውም የግል ጥብቅና ስራ ጽህፈት ቤት ከከፈተ ወዲህ ሳይሆን አይቀርም ።

እንዲያውም እንደእውነቱ ከሆነ የተከሳሽ ጠበቃ ሆኖ ሲቆም የመጀመሪያ ሙከራው በመሆኑ ዝናን ለማትረፍ በታላቅ ትጋት ጉዳዩን ይከታተላል ። ነገር ግን ይህን ትጋት አበራ ፤ ስለታም ፤ ጠይም ፊቱ ላይ አሁን ሊያይ አልቻለም ።

አበራ ጉሮሮውን አሳላና ፤ «ምን ችግር ገጠመህ ተስፋዬ?» ብሎ ጥርጣሬ በተመላበት ድምጽ ጠየቀው ።

ተስፋዬ ጽህፈት ቤቱ ውስጥ ተንጐራደደ ። ዝግ ብሎ የመሄድ ልምድ የለውም ። ሲሄድ እንደኳስ ይነጥራል ። እንደ ልማዱ እጆቹን አወናጨፈና ፤ «ልነግርህ የፈለግሁትን ነገር እያጠናሁ ነበር የመጣሁት ። ተበታተነብኝ ። እንዴት ብዬ እንደምነግርህ ግራ ገብቶኛል...» ብሎ ሳይጨርስ ፤ አበራ አቋረጠውና ፤ «አይዞህ ንገረኝ ፤ ማንኛውንም ነገር ለመስማት ዝግጁ ነኝ ።» አለው ።

«ስለወንድምህና ስለሀይለማርያም ነው ...»

«ምን ሆኑ ?»

«ወንድምህ ሀይለማርያምን ሉሲት ዘንድ አግኝተውት በጥይት ስለመቱት ዛሬ ጧት ሞተ ። ወንድምህም ወዲያውኑ በገዛ እጃቸው ህይወታቸውን አሳልፈዋል ።» አለውና እንደ በቁ ውስጥ ተቀርቅሮ ሲተናነቀው የነበረውን ትንፋሹ በረጅሙ ተንፍሶ ወደ ውጭ አወጣው ።

አበራ ፤ «ሀዘን ሲበዛ አስቂኝ ይሆናል !» ከማለት ሌላ ምንም ሲናገር አልቻለም ። ግን አይስቅም ነበር ።

«ከመሞቱ በፊት ላንተ አድርስልኝ ያለኝ መልእክት አለ ። 'ለኔ ስትል በርታ ፤ ስራህ ለወንድምህ ዝርያ ለኔ ሀውልት ይሁን ፤ በዚህ አለም ያለኝ ቅርስ መጽሀፎቹ ናቸውና በሚገባ አኑራቸው ። ጽንስ ጽሁፎቼን በተቻለህ ጊዜ ከንቱ ምኞት በሚል አርእስት አሳትማቸው ። የቤት ኪራይ አልከፈልኩምና ክፈልልኝ ። አዳው ወደ መቃብር አብሮኝ እንዲሄድ አልፈልግም ፤' ብሎሃል ።» እንዳለው አበራ አእምሮውን ስቶ ወደቀ ።

# ፫

አበራ ከወር በላይ ተኛ ። ለመሞት ጣረ ። ነፍሱ ግን ከስጋው ለመለየት ፈቃደኛ አልነበረችም ። ለመሞት የነበረው ምኞት እየገፋ ሲሄድ ነፍሱም በበኩሏ ትግሏን እያጠነከረች ትሄድ ነበር ። በመጨረሻ ብርታት ሰጥቶት ከአልጋ ያስነሳው የተስፋዬ ብስጭት ነበር ። በአበራ ከአልጋ ላይ መዋል ምክንያት የፍርድ ቤቱ ቀጠሮ እየተላለፈና ቀኑ ቀን እየወለደ በሄደ መጠን የተስፋዬም ብስጭትና የመንፈስ ቅዝቃዜ እየጨመረ ይሄድ ነበር ። ለገንዘብ ደንታ የለውም ። ሀይለማርያም የአበራን መኪና በአራት ሺህ ስስት መቶ ብር ሸጦ ከዚያ ውስጥ ሶስት ሺህ ያህል ቢሰጠው እንኳን አልተቀበለም ። ውጭውን ለመሸፈን ያህል ብቻ ስድስት መቶ ብር ወስዶ የተቀረውን መለሰለት ። የፈለገው የአበራን ነገር ከግቡ በማድረስ ዝናን ለማትረፍ ብቻ ነበር ።

ከብስጭቱ የተነሳ አንድ ቀን ምኒልክ ሆስፒታል ድረስ ሄዶ ፤ «እዚህ በጀርባህ ተኝተህ የምታንቀላፋው ከህግ ለመሸሽ አስበህ እንደሆነ ንገረኝ ፤ ለከንቱ ቀጠሮ ፍርድ ቤት መመላለሱ ሰልችቶኛል ። ብርትተህ መነሳት አለብህ!» ብሎ ሲጮህበት ፤ አበራ ከተኛበት አሻቅቦ አየው ። ተስፋዬ አልተለወጠም ። ያው በትምህርት ቤት የሚያውቀው ተስፋዬ

ነው ። ዝናን ለማትረፍ የማያደርገው ነገር አልነበረም ። ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ በነበሩበት ዘመን አብዛኛዎቹ ተማሪዎች ተስፋዬ ለዝና ሙት መሆኑን ስለሚያውቁ እንዲወክላቸው እሱን በመምረጥና ሆይ ሆይ በማለት እያነሳሱት ከጀዝዊቶ ችና ከባለስልጣኖች ጋር ያጋፍጡት እንደነበረ አስታወሰ ። ዛሬ ፍርድ ቤት መቅረብ ደስታ የሚሰጥህ ከሆነ ዝግጁ ነኝ ። ብሎት ሰላም የሰፈነበት እንቅልፍ አግኝቶ እንዳደረ ሰው ከተኛበት ዘሎ ተነሳ ። መቃብር በሚመስለው እሷም ሮው ውስጥ ታስራ ስትሟገት የከረመችው ነፍሱ ፈነደቀች ። እልፍነሽ ግን ደስ አላላትም ። ክብ ፊቷ ላይ እንደመሰከረም ሙራ ይጫወት የነበረው ፈገግታዋ ጠፍቶ ጥቁር ቱቢት ለብሳ ከሰውነት ወጥታለች ።

አበራ ከሆስፒታል በወጣ በአራተኛው ቀን ላይ ጧት ወደ አራት ሰአት ተኩል ገደማ አንደኛ የወንጀል ችሎት ቀረበ ። የውጭው አየር ጭፍግግ ብሎ ዝናብ ቢያካፋም ችሎቱ በሰው ተጨናንቆ ክፍሉ ውስጥ የነበረው ሙቀት ትንፋሽ ያሳጣል ። እዚያ የሚገኙት ሰዎች አብዛኛዎቹ ባለጉዳዮች ፤ ገሚሶቹ ደግሞ የፍርድ ቤት አየር ሱሰኞች ሲሆኑ ፤ ጥቂቶቹ የተስፋዬን ክርክር ለመስማት የመጡ ነበሩ ።

አበራ በግራ በኩል ካለው ከተከሳሽ ሳጥን ውስጥ ገብቶ ቆሞ ነበር ። አንድ ሰው በህግ ፊት ጥፋተኛነቱ ሳይረጋገጥ በግራ በኩል የሚውልበት ምክንያት ሊገባው አልቻለም ። ምስጢሩን ለመመራመር ሀሳቡን አላገፋበትም ። አይኖቹን ወደ ዳኞቹ አዞረ ። የመሀል ወይም ሰብሳቢው

ላኛ የአፍንጫቸው ቀዳዳዎች ላይ በወደቀው መነጽር ላይ ሆነ በምጠምጡት ትናንሽ አይናቻቸው አእምሮውን ዘልቀው ሲመለከቱት አገኛቸው...ለጥቂት ጊዜ እንደኑብ ርና እንደፍየል ተፋጠው ተያዩ ... የቀኝና የግራ ወንበር ተኞች አቀርቅረው ይጽፉ ነበር ። ሶስቱም ጠይም ፤ ሽበታምና ጥቁር ካባ የደረቡ በመሆናቸው ፤ ሁላቡን ምን ቢያረዝመው ፤ ከጊዜውና ከዘመናዊው የወንጀለኛ መቅጫ ህግና ስነ ስር ዐት ጋር እንርሱን ለማገናኘት አቃተው ። በነፍሱ በመጣ ጉዳይ ሊያምናቸው አልቻለም ።

አቃቤ ህጉ ወንጀሉንና በተከሳሽ ላይ የሚያቀርበውን ማስረጃ እንዲያስረዳ ተጠየቀ ። ጊዜ አልወሰደም ። ተጣድፎ አለ ። በአይኑ ህሊናው አበራ ከገመድ ጫፍ ተንጠልጥሎ እንደሚያይ በመጠን ሀይል የተጠበበ ጉበት የሚመስለው ራሱና የቦዘዙት ትላልቅ አይኖቹ ሊደበቁ አልቻሉም ።

«የተከበረው ፍርድ ቤት ሆይ በማለት ለዛ በሌለውና በተንዛዛ ድምጽ ከወረቀት በማንበብ ወንጀሉን ማስረዳት ጀመሩ — «ተከሳሽ ፤ ወይዘር አለምነሽ ጓዴ የተባሉትን ሴት በኔ ፲፰ ቀን ፲፱፻፷፪ እ፡ም፤ ሀሙስ ከጧቱ በአምስት ሰአት ካስር ደቂቃ ላይ በጊጠር መናፈሻ ቡና ቤት በሽጉጥ መግደሉን ራሱ በውዴታ በሰጠው ቃል ማመኑንም ፤ አምስት የአይን ምስክሮች ቀርበው ወንጀሉን ለመፈጸሙ በማያጠራጥር ሁኔታ ማረጋገጣቸውንና እንዲሁም ወይዘር አለምነሽ ጓዴን የገደለው ጥይት ከተከሳሹ ሽጉጥ መተኮሱን ኤክስፐርቶች የሰጡት ማረጋገጫ ያስረዳልኛል ። ወንጀሉ አስቀድሞ የታሰበበት ለመሆን አያጠራጥርም ። ብሎ ሲጨርስ በቀኝ

በኩል አሰፍስፈው ቆመው የነበሩት የሟቹ ወገኖች ዳኛው ተናደው ጠረጴዛቸውን እስኪደበድቡ ድረስ ጉልልታቸውን አቀለጡ ።

እንዲሞት የሚፈልጉ ሰዎች በመኖራቸው አበራ የመኖር ፍላጐት አደረበት ። ወደ ተስፋዬ ተመለከተ ። ተስፋዬ በራሱ ላይ ያለው መተማመን ብርታት ሰጠው ። ተስፋዬ ፣ እንደ ኳስ ከተቀመጠበት ነጥሮ ሲነሳ በስታም ፊቱ አየሩን ሰንጥቀው ። አዲስ የለበሳትን ጥቁር ካባ በፍቅር ስሜት ትከሻው ላይ አስተካከለ ። በስልታም ድምጹ የያንዳንዱን ሰው ጆሮ ይቀድ ጀመር ። «ሀተታ አላበዛም ። ደንበኛዬ ወንጀሉን የፈጸመው አስቀድሞ በማሰብ ሳይሆን ፣ ባልታሰበና በድንገተኛ አጋጣሚ ፣ እንዲሁም ከፍ ያለ አስገዳጅነት ባለው መንፈስን የሚለውጥ ስሜት ምክንያት መሆኑን በማቀርባቸው መከላከያ ምስክሮች አማካይነት እንዳስረዳ ይፈቀድልኝ ፤» ሲል ጥያቄውን አቀረበ ።

አቃቤ ህግም ሆነ ተስፋዬ ተቻኩለው ነበር — አንዱ ጥላቻቸውን ለመወጣት ፤ ሌላው ዝናን ለማትረፍ ።

ጥያቄውን የተቃወመ ሰው ባለመኖሩ ተስማ ደጀን ለምስክርነት ቀረበ ። ክብደት ጨምሮአል ። እንደምጣድ ክብ ፣ ወፍራም ፊቱ ላይ የሚጣበቀው ፈገግታው በተወ ማሪ ህፍረትን ቀላቅሎ ይታያል ። የፍርድ ቤቱን ስነ ስር አት ከፈጸመ በኋላ ፣ «ከአበራ ጋር ትተዋወቃላችሁ?» ሲል ተስፋዬ የመጀመሪያውን ጥያቄ አቀረበለት ።

«አዎን ።»

«እውቀታችሁ እንዴት ነበር ?»

«ጓደኞች ነበርን ።»

«ጓደኝነታችሁ የተቋረጠበት ጊዜ የለም?»

«ከመስሪያ ቤቱ ሲወጣ ገደማ ጓደኝነታችን ተቋርጦ ነበር ።»

«በምን ምክንያት?»

ወፍራም ፊቱን ላብ አስመጠጡ ። ነጭ መሀረብ አውጥቶ ላቡን ጠረገ ። እናቴ ትሙት ይል ይሆን ? እያለ አበራ ይጠባበቀው ነበር ። ጉሮሮውን እንደመጠራረግ ሲል ትን አለውና አሳለው ።

«ምክንያቱም …ምክንያቱማ…አዎን ፤ ባለቤትህ በገጠር መናፈሻ ቡና ቤት ከሰው ጋር ስትማግጥ ሰው አይቶ ነግሮኛልና ተጠንቀቅ ብዬ ስለነገርኩት ነው…»

«እንዴት አወቅህ?»

«በአይኔ አየሁ ብሎ ሰው ስለነገረኝ ነው የነገርኩት…»

«የነገረህን ሰው ታስታውሳለህ?»

«ገድሉ በዛብህ ይባላል ።»

የአበራ ልብ መምታቱን ባንዳፍታ ስላቆመ ትንፋሽ አጠረው ። አቃቤ ህጉ መስቀልኛ ጥያቄ እንዲጠይቅ ተፈቀደለት።

«ሁኔታውን ስታይ የነገርከውን ያመነህ አልመሰለህም?»

«ተቆጥቶ ከቢሮው አስወጣኝ ።»

«አላመነህም ማለት ነው ።»

አቃቤ ህጉ ሌላ ጥያቄ ስላልነበረው ተስፋዬ ሁለተኛ የመከላከያ ምስክሩን አስጠራ ። ሉሊት ነበረች ። የአበራ ልብ ስንጥቅ አለበት ። በሁለት ወር ውስጥ ሲያያት ያን ቀን የመጀመሪያ ጊዜው ነበር ። የሱንና የሷን ሁኔታ በመገመት ሀፍረት አደረበት ። በማቀርቀር አይኖቿን ሸሸ ።

ጥቁር በጥቁር ለብሳ ነበር ። ስሜቱ በፍቅርና በጥላቻ ተወ ሳሰበበት ። ያ አእምሮው ውስጥ ግዙፍ የሚሆነው ጣዕም ጣእትኑቷ መጣበት ።

«ገድሉ በዛብህ ከሚባለው ሰው ጋር ግንኙነታችሁ ምን ነበር?»

«አበራን ከማግባቴ በፊት ወዳጆች ነበርን ።»

«አልገባኝም ።»

«ፍቅረኞች ነበርን ማለቴ ነው ።»

«ፍቅረኞች ከሆናችሁ ለምን አበራን አገቡት?»

«ገድሉ እያስገደደኝና እያስፈራራኝ ነው እንጂ እኔ አልፈ ደውም ነበር ። ስለዚህ ከሱ ለማምለጥ ስል አበራን አገባ ሁት ። ካገባሁት በኋላ ግን ምንም ግንኙነት አልነበረንም...»

«ይበቃል ወይዘሮ ሉሊት ። ሰኔ ፲፰ ቀን ፲፱፻፷፫ እ፡ ም ሀሙስ ጧት ሲያደርጉ የዋሉትን ሁሉ ቢነግሩኝ ?»

«በተባለው ቀን ፤ አበራ ፤ ወደ ሶስት ሰአት ተኩል ገደማ ወስዶ ቢሮ ጣለኝ ። ቢሮ እንደገባሁ ለሀይለማርያም ስልክ ደወልኩለት ። የደወልኩበትም ምክንያት ፤ መጥቶ ከተማ እንዲወስደኝና አበራ የተወለደበት ቀን ስለነበር ስጦታ እንዲያጋዛኝ ነበር ። መጥቶ ከተመካከርን በኋላ ወደ ከተማ ወሰደኝ ። ግን ገንዘብ ስላልነበረኝ ወደ ወርቅ ሰሪ ቤት ሄድንና የነበረኝን ያንገትና የእጅ ጌጥ ከሸጥኩ በኋላ የተ ፈለገው ስጦታ ከሚገኝበት ሱቅ ገብተን ገዛንና ወደቤት ወሰደኝ...»

«ቀኑ ፤ አበራ የተወለደበት ቀን ነበር ። በተጨማሪ ስለቀኑ የሚያስታውሱት ነገር አለ?»

«አዎን ፤ አበራ ከስራ ወጥቶ ስለነበረ የመጨረሻ ደሞዙን የሚቀበልበት ቀን ነበር ።»

«ወይዘሮ ሉሲት ፤ አበራ ስራውን የለቀቀው በድንገት ነው?»

«ስራውን የሚለቅበትን ቀን አላማከረኝም እንጂ ያሰበበት ከመጋባታችን በፊት ነበር ።»

«ስራውን ለመልቀቅ የፈለገበትን ምክንያት ያውቃሉ?»

«ሰአሊ ለመሆን ነው?»

«የገዙለት ስጦታ ምን ነበር?»

«የሰአሊ መሳሪያዎች ።»

«ሀይለማርያም ወደ እርስዎ ዘንድ የመጣው በእርስዎ አሳሳቢነት ነበር? ወይስ በገዛ ራሱ?»

«በኔ አሳሳቢነት ነበር ።»

«ከሀይለማርያም ጋር ለመውጣት እንዳሰቡ ለአበራ አማክረውት ነበር?»

«አላማከርኩትም ።»

«እርስዎና ሀይለማርያም ተያይዛችሁ የሄዳችሁበት መኪና ምን አይነት ነበር?»

«የ፲፱፻፶፱ አ፣ ም ሞዴል ጥቁር ኦፔል መኪና ነበረች ።»

«ሌላ ጥያቄ የለኝም ፤» አለና ተከሳሹ ለመስቀልኛ ጥያቄ ሉሲትን ለአቃቤ ህጉ ለቀቀለት ።

አቃቤ ህጉ መስቀልኛ ጥያቄውን ለማቅረብ ተነሳ ።

«ካገባሽ ወዲህ ገድሉ በዛብህ አስፈራርቶሽ ያውቃል?»

«አያውቅም ። የት አግኝቶኝ?»

«ግጠር መናፈሻ ቡና ቤት ከወንድ ጋር ሂደሽ ታውቂያለሽ?»

«ሂጄ አላውቅም ።»

«የውነቱን ለመናገር የመሀላ ቃል እንደሰጠሽ ማስታወስ እለብሽ ። ከማግባትሽ በፊት ከልዩ ልዩ ወንዶች ጋር ወደቶ ባሰው ቡና ቤት በየጊዜው ትመላለሺ እንደ ነበረ በቂ ማስ ረጃ ሊቀርብ ይችላል...»ከማለቱ ተስፋዬ፤«ተቃውሞ አለኝ!» ሲል ስለታም ድምጹን አሰማ ።

ለመጀመሪያ ጊዜ የመሀል ዳኛው ካቀረቀሩበት ቀና ብለው ፤ «ተቃውሞህ ምንድንነው?» ብለው ጠየቁት ።

«የተከሰሱት ወይዘሮ ሉሊት አለመሆናቸውን አቃቤ ሕጉ እንዲረዱልኝ ያስፈልጋል ። ጥያቄው ከነገሩ ጋር ምንም አግባብ የለውም ...» ብሎ ሳይጨርስ ፤ አቃቤ ሕጉ ጠረጴ ዛውን እየደበደበ፤«ጥያቄው ከነገሩ ጋር ፍጹም የሆነ አግባብ አለው ። እንዳለው ሴትዮዋ ከምትሰጠው መልስ ለመረዳት ይቻላል ፤» ሲል ዳኛው የተስፋዬን ተቃውሞ ፤ «አልተቀበ ልንም» በማለት ውድቅ አድርገው አቃቤ ሕጉ ጥያቄውን እንዲቀጥል ፈቀዱለት ።

«ማስረጃውን ከማቅረባችን በፊት የውነቱን ብትናገሪ ይሻ ላል ። ሄደሽ ታውቂያለሽ፤ አታውቂም?»

«ብዙ ጊዜ ሄጃለሁ ። ግን ሁሉም ከማግባቴ በፊት ነው ።»

«ቅድም ቃለ መሀላሽን ረስተሽ ዋሽተሻል ማለት ነው ! የተናገርሽው ሁሉ ውሸት እንዳልሆነ በምን እናውቃለን ? ለመሆኑ ተከሳሹ የሰአሊነት ችሎታ እንዳለው እንዴት ለማ መን ቻልሽ ? የሰራውን ስእል ወይም ችሎታውን የሚመ ሰክር ስራ አሳይቶሽ ያውቃል?»

«አያውቅም» አለች ፤ ቅስሙ በተሰበረ ድምጽ ። እንባዋ ሳያቋርጥ ይወርድ ነበር ።

«አንቺ በዚያን ሰአት ከሀይለማርያም ጋር መውጣትሽን ተከሳሹ በሌላ መንገድ ከሌላ ሰው ለማወቅ አይችልም?»

«ይችል ይሆናል ።»

የሟቿ ወገኖች በቂም ጥርሶቻቸውን ሲያፋጩባት ሌሎቹ በሀዘን ከንፈራቸውን ይመጥጡ ነበር ።

ወዲያውኑ የሉሲት መስሪያ ቤት ዘበኛ የገዘናብ ማግና የተንዘረፈፈ ቅጠሊያ የወታደር ካቦርት እየጐተቱ ሶስተኛ የመከላከያ ምስክር በመሆን ቀረቡ...

በሉሲት በኩል ያላሰበውና ያልጠረጠረው ነገር በመ ፈጠሩ ተስፋዬ በራሱ ላይ የነበረው መተማመንና ትም ክህት በመጠኑም ቢሆን መቀነሱን የቀድሞውን ስለት ያጣው ድምጹ ይመሰክር ነበር ። ግን ተስፋዬ ተስፋ አል ቆረጠም ። ጥያቄውን መወርወር ጀመረ ።

«ሰኔ ፲፭ ቀን ፲፱፻፸፰ ዓ፡ ም ሀሙስ ጧት በእርስዎና በተከ ሳሹ መካከል የሆነውን ሊነግሩኝ ይችላሉ?»

«እንዴታ! አሳምሬ ነው እንጂ! ወደ አራት ሰአት ገደማ ይመስለኛል ፤ በመኪናው ሲገሰግስ መጥቶ ሉሲት የት እንዳ ለች ጠየቀኝ ። ለጥቂት በሌላ መኪና እንዳመለጠችው ነገርኩት ።»

«ይህን እንደነገሩት ዝም ብሎ ሄደ ወይስ ሌላ ሌላ የጠየቀ ዎት ጥያቄ ነበር?»

«በምን አይነት መኪና እንደሄደች ጠየቀኝና እሷ የሄደች በት መኪና ተመሳሳይ አጠገባችን ስለነበረች ያቺን በምት መስል መኪና ነው የሄደችው ብዬ አመለከትኩት ። ወዲያ ውኑ መኪናውን አዙሮ ሲከንፍ ሄደ።»

መኪና ሉሊት ከሄደችበት «አጠገባችሁ ቆማ የነበረችው መኪና ጋር በቀለም ወይስ በቅርጽ ነበር የምትመሳሰለው?» «የሚመሳሰሉት በቅርጻቸው ነበር እንጂ በቀለም አልነበረም ። ሉሊት የሄደችው በጥቁር መኪና ነበር ።»

ተስፋዬ አስር የሚሆኑ ቁመታቸውና ስፋታቸው ተመሳሳይ የሆኑ ፎቶግራፎች አምጥቶ ምንም ምልክት እንደሌላቸው ለመሀል ዳኛው ካሳያቸው በኋላ ሉሊት የሄደችበትን መኪና አይነት ዘበኛው መርጠው እንዲሰጡት ጠየቃቸው ። አገላብጠው አንድ ባንድ ከተመለከቱ በኋላ ፤ «ሉሊት የሄደችበት መኪና ጥቁር ነች እንጂ ልክ ይህችን ትመስላለች» ብለው የመረጡትን ፎቶግራፍ ሰጡት ። ተስፋዬ ተቀብሎ ለመሀል ዳኛው ሰጣቸው ። ቡላማ የ፲፱፻፶፱ እ·ም ኦፔል መኪና ነበረች ።

አቃቤ ሕጉ ዘበኛውን ተረከባቸውና ፤ «ተከሳሹን የምታስታውስበት ሌላ ምክንያት የለህም?» ሲል ጠየቃቸው ።

«ባለቤቱን ሲያመጣና ሲወስድ…»

«ይህ ብቻ ሳይሆን አልፎ አልፎ ውለታ አልዋለልህም?»

«የውሀ መጠጫ በየጊዜው ይሰጠኝ ነበር ።»

«ከዚህ የበለጠ ሰጥቶህ አያውቅም ?»

«አንድ ቀን አስር ብር ሰጥቶኛል ።»

«ለመሆኑ ደሞዝህ ስንት ነው?»

«ሀያ አምስት ብር ።»

ሰአቱ ስለደረሰ ቀጠሮው ለሌላ ቀን ተወሰና ችሎቱ ተበተነ ። አበራ ሉሊትን በአይኑ ይፈልግ ነበር ። እላገኛ

ቷም ። እልፍነሽ ብቻ እንባዋን እየረጨች የመሀኒ ቤቱ መኪና ድረስ ሸኘችው ። አንድ ፖሊስ ገፍትሮ ባይመልሳት ኖሮ ሊታነጋግረው በጣም ጓጉታ ነበር ።

የፍርዱ አካሄድ ምን ስሜት እንደሰጠው ለመገመት አበራ አልቻለም ። ተስፋ የሚሰጥ ወይም የሚያስቆርጥ ምና አላገኘውም ። የፈለገው ነገር ቢኖር በቀጠሮው ቀን ወደ ፍርድ ቤት ተመልሶ የሉሊትን አይን ማየት ነበር ። የሆነው ቢሆን ፣ ብታምነውም ባታምነውም ፣ እውነቱን ከሱ አፍ ሳትሰማ እንድትለየው አልፈለገም ። በሌላ በኩል እሱን ለማስደሰት ስትል ጌጣጌጧን የመሸጧ ነገር አንጀቷን ይበላው ነበር ።

፩

በቀጠሮው ቀን ወደ ፍርድ ቤት ሲመለስ ችሎቱ ካለፈው ጊዜ ይበልጥ በሰው ታጭቆ አገኘው ። የሰው ትርምስና ትንፋሽ ፣ የቦታ ጥበትና ትፍግፍግ ፣ ምንም አይደሉም ። ተለማምዷቸዋል ። ሉሊትም ሆነች እልፍነሽ በቦታው የሉም ። የችሎቱ ሙቀት ቢያፍንም ትዝታዜ ተሰማው — ከብቸኝነት የሚመጣ የመንፈስ ትዝታዜ — ያልፈጣሪ ፣ ያልዘመድ ።

«ከዚህ ቀደም የአቃቤ ህጉ ዋና ምስክር በፈለግሁት ጊዜ ለመስቀልኛ ጥያቄ እንዲቀርብልኝ በጠየቅሁትና ፍርድ ቤቱ በተስማማበት መሰረት አሁን እንዲቀርብልኝ የተከበረው ፍርድ ቤት ይፍቀድልኝ ፤» ሲል ተስፋዬ በትክክል ተስፉ አንስራራ ። ትናንሽ አይኖቹ ሁሉንም ፤ ዳኞቹንም ጭምር ፤ እንደመርፌ ከመጠቅጠቃቸውም በላይ ፤ ስለታም ፊቱ አየሩን ግራና ቀኝ ይቆርጥ ነበር ። እንደፈለገው የሰው አይን ሁሉ አረፈበት ። ውሀ እንዳገኘች እሳ ሆኖ ነበር ።

በጥያቄው መሰረት የገጠር መናፈሻ ቡና ቤት ተሳላኪ ቀርቦ ነበር ። አበራ የሰውዬውን ፊት ሊያስታውስ አልቻለም ።

«ከዚህ ቀደም ቃልህን ስትሰጥ ተከሳሹ ሽጉጥ ይዞ በሩን ሰብሮ ሲገባ አይቻለሁ ፤ ሲተኩስ ግን አላየሁም ብለህ መስክረሀል ። የፈለገውን ሰው በስም ጠርቶ እንዳልጠየቀ ህም ተናግረሀል ። 'የዚህ መኪና ባለቤት ስንት ቁጥር ነው የተኛው? ብሎ ጠይቆኝ ጓደኛዬ ነው በማለት ዋሽቶ ስላግባባኝ፤አራት ቁጥር ነው ያሉት ብዬ ነገርኩት' በማለት መመስከርህ ይታወሳል ። ነገር ግን የመጀመሪያው ጥይት የተተኮሰው ከውስጥ ወይስ ከውጭ ነበር?»

«ከውስጥ ይሁን ከውጭ አላውቅም ።»

«መልካም ። አስታውስ ፤ በቅጡ አስታውስ ። ውጭ ካንተ ሌላ ማንም ሰው አልነበረም ። የመጀመሪያውን ተኩስ ስትሰማ ምን አየህ?»

«ተከሳሹ ወደ መኪናው ሮጦ ሄደ ።»

«ከዚያስ?»

«ወደአራት ቁጥር ክፍል ሮጦ ተመለሰ ።»

«ምን አድርጉ ተመለስ?»

«ምን አውቄ!»

«የመጀመሪያው ጥይት ከተተኮሰ በኋላ ተከሳሹ ወደመኪናው የሮጠው የመኪናውን በር ለመቆለፍ ነው ? ፍሬን ለመያዝ ነው ? ወይስ መስተዋት ለመዝጋት? ወይስ እቃ ለመውሰድ? ምን አይነት እቃ? አታውቀውም ፣ አላየህም ። ደንግጠህ አይንህን ጨፍነህ ይሆናል ። ያየኸው ወደ መኪናው ሮጦ ከተመለሰ በኋላ በሩን ሰብሮ ሲገባ ብቻ ነው ፤ አይደለም?»

«አዎ።»

«ከዚህ ቀደም ቃልህን ስትሰጥ ተከሳሹ ከመጀመሪያው ተኩስ በኋላ ወደ መኪናው ሮጦ መመለሱን አልመሰከር ከም ነበር ፤ ለምን ?»

«የጠየቀኝ አልነበረም ።»

«ካልጠየቁህ ያየኸውን አትመሰክርም ማለት ነው?»

የሚሰጠው መልስ አልነበረውም ። አቃቤ ህጉ ተደና ግጦ ይንቆራጠጥ ነበር ። ከረጅም ዝምታ በኋላ ተስፋዬ አምስተኛውንና የመጨረሻ የመከላከያ ምስክሩን አስጠራ ።

ቀትረ ቀላል ሆኖ አንጀቱ ከጀርባው ጋር የተጣበቀ ሰው ነበር ። አበራ ሰውዬውን አይቶት አያውቅም ። መልኩ ቀይ ፤ ቁመናው መካከለኛ ሆኖ ፤ የግራና የቀኝ ጉንጮቹን ማዲያት ጠብሶት ነበር ።

ተስፋዬ ፤ ቀኑን ፤ ሰአቱንና ቦታውን ጠቅሶ በዚያን ጊዜ ሰውዬው የት እንደ ነበረ ጠየቀው ። አበራ የሰውዬውን መልክ በተለይ አይኖቹን ለማስታወስ ቻለ ። «ቡትባለው ቀንና ሰአት ከጓደኛዬ ከወይዘሮ አለምነሽ ጓዴ ጋር በገጠር

መናፈሻ ቡና ቤት አራት ቁጥር ክፍል ውስጥ ነበርን » ሲል በማያወላውልና ምንም ይሉኝታ በሌለበት ጆር ባሚስብ ወፍራም ድምጹ መለሰለት ።

«ምን ስታደርጉ እንደነበረ ለመጠየቅ አልፈልግም ። ሆኖም የርስዎና የሟቿ ፤ የወይዘሮ አለምነሽ ጓዴ እውቀት ምን እንደ ሆነና ከመቼ ጊዜ ጀምራችሁ እንደምትተዋወቁ ያስረዱኝ።»

«እኔና ወይዘሮ አለምነሽ የተዋወቅነው በአስተማሪነት ጐንደር ሄጄ በምሰራበት ጊዜ ነበር ። ካምስት አመት በፊት ይሆናል ። ከተማሪዎቼ አንዷ ነበረች ። በከንፈር ወዳጅነት ስንኖር በድንገት ወላጆቿ ዳሯት ። እኔም በንዴት ያስተማሪነቱን ስራ ተውኩና ወደ አዲስ አበባ መጥቼ ሚስት አገባሁ ። ቢሆንም አዲስ አበባ በመጣች ቁጥር እንገናኝ ነበር...»

«መልካም ። ወይዘሮ አልፍነሽ የሚኖሩት ጐንደር ነበር ማለት ነው ፤ አይደለም?»

«ነው ።»

«መልካም ። ሟቿ ወደ አዲስ አበባ የመጡት መቼ ነበር?»

«አደጋው ከመድረሱ ከሳምንት በፊት ይመስለኛል ።»

«ተከሳሹ መጥቶ የተኛችሁበትን ክፍል በር ሲያንኳኳ ምን አደረጉ?»

«መጀመሪያ ዝም አልኩ ። ለሁለተኛ ጊዜ ሲያንኳኳ ማን ነው ? ብዬ ብጠይቅ መልስ ባለማግኘቴ ልብሴን ለመልበስ ስነሳ በሩ በሀይል ስለተንኳኳ ለማስፈራራት ያህል የነበረችኝን አንድ ጥይት ተኮስኩ ። ከዚያ የሆነውን ለማስታወስ አልቻልም ።»

«ተከሳሹ በሩን ሰብሮ ሲገባ እርስዎ የት እንደነበሩና ምን

እንደሆን ለመጠየቅ አልፈልግም ። የመኪናዎን ቁጥርና አይነት ብቻ ቢነግሩኝ ይበቃል ።»

«መኪናዬ ጥቁር ፲፱፻፶፱ እ፡ም ኦፔል ናት ።»

ኢቃቤ ህግ ተነስቶ ፤ «ሟቿና ተከሳሹ እንተ የማታውቀው ግንኙነት ይኑራቸው አይኑራቸው ታውቃለህ?» ብሎ መስቀልኛ ጥያቄ ወረወረበት ።

«አላውቅም ።»

«ሟቿ ከጐንደር ስትመጣ ግንኙነት የምታደርገው ካንተ ጋር ብቻ ነው?»

«አይደለም ።»

«ለምሳሌ ከተከሳሹ ጋር ግንኙነት ሊኖራት ይችላል?»

«ተቃውሞ አለኝ!» ሲል ተሰፋዬ ድምጹን አሰማ ።

የመሀል ዳኛው ፤ «ተቃውሞህን አስረዳ !» አሉት ።

«መሪ ጥያቄ በመሆኑ ምስክሩ መመለስ የለበትም ።»

«ተቀብለናል ።»

ኢቃቤ ህግ ጀምሮት የነበረውን ጥያቄ ትቶ ወደ ሌላ ሄደ ። «እሺ ፤ ከዚህ በፊት በሰው ሚስት ላይ ተይዘህ ፍርድ ቤት ቀርበህ አታውቅም ?»

«ቀርቤአለሁ ።»

«ስንት ጊዜ?»

«ሁለት ጊዜ »

«የተከሳሹ ጠበቃ በሩ ከተሰበረ በኋላ የት እንደነበርክ አልጠይቅህም በማለት አልፎህ ነበር ። እኔ ግን እጠይቅሀለሁ ። የት ነበርክ?»

ሰውዬው ባብ አሰመጠው ። እየሟሸሸ ሄደ ።

«አልጋ ስር ነበርኩ ።»

ከአልጋው ስር ራቁቱን እየተጐተተ ብርክ ይዞት ሲወጣ አይኖቹ ላይ ይነበብ የነበረው ፍርሀት አበራን ትዝ አለው ። ሴትዮዋ ከዚያ ቀደም ፍጹም ኢጋጥመዋት የማታውቃቸውን የአበራን አይኖች እያየች ፤ እየመረመረች ፤ «ለምን? ለምን?» በማለት ትንፋሽ ባጠረው ድምጽ ስትጠይቀው ፤ «እኔም ለምን እንደሆነ አላውቅም ። እግዚአብሔርን ጠይቂው ፤» ብሏት መውጣቱን ጭምር አበራ አስታወሰ ።

ለጥቂት ጊዜ ችሎቱን ከባድ የሆነ ዝምታ ዋጠው ። ሶስቱ ዳኞች አፍ ለአፍ ገጥመው በሹክሹክታ መነጋገር ይዘዋል ። ባለጉዳዩም ፤ ለወሬ ምትኩ ባዩም ፤ አጫፋሪውም ሁሉ ችሎቱን ከአፍ እስከገደፉ ስለሞላው ክፍሉ ውስጥ ከታመቀው ከሰው ትንፋሽ በስተቀር ሌላ አየር የለም ። ሞትም ሆነ ሽረት መቃረቡ ለአበራ ተሰማው ። በመስኮት አሻግሮ ውጭ የምትጫወተውን ጸሀይ ተመለከተ ። የዳመናው ጥላ መሬቱን እያሽጐረጐረ በአረንጓዴ መስክና በዛፎች ላይ ሲሮጥ በማየቱ ለንጹህ ቀዝቃዛ አየር ጓጓ ። ህይወት ጠማው ። ነፍሱ የሙጥኝ አለችው ። ዋናው ጉጉቱ ግን ሉሊትን ለማነጋገር ባይችል እንኳን በአይኑ ላንዳፍታ አይቷት ሊሰናበታት ነበር ። ግን የለችም ።

አቃቤ ሁጉ የፍርድ ሀሳቡን ለመስጠት እንዲህ ሲል ጀመረ ፦— «...የቀረቡት የመከላከያ ምስክሮች ምራላቸው ከማጠራጠሩም በላይ ፤ ተከሳሹ በተንኮልና በወስላታነት አለመነሳቱን አላረጋገጡም ...የተማረ ሰው አንጐል በሁለ

ቆም በኩል የሚቆርጥ ስለት ያለው ቢላዋ እንደመሆኑ መጠን እንዲህ ያለውን ተንኮል አይፈጽምም ለማለት አንችልም ። በሟቿና በተከሳሹ መካከል የነበረውን ግንኙነትና ፤ በተከሳሹና በሀይለማርያም መካከል የነበረውን አግባብ እንዳና ውቅ ሁለቱም ዋና ምስክሮች በግፍ ተገድለዋል ። አጋጣሚ ላለመሆኑ የነገሩ አካባቢ ሁኔታ አይደግፍም …

«ተከሳሹ ፈቃድ የሌለው መሳሪያ ይዞ ለምን በተለይ በዚያን እለት ከቤቱ ወጣ? በተጨማሪ ፤ ተከሳሹ የፈጸመውን ወንጀል ሳይክድ ሟቿን ለመግደል የበቃሁት ባለቤቴ መስላኝ በመሳሳት ነው ሲል ቃሉን ሰጥቷል ። እርግጥ የተከሳሹ ባለቤት በዚያን ሰአት ሀይለማርያም ካሳ ከሚባል ከተከሳሹ የቅርብ ጓደኛ ጋር እንደነበረች ታውቋል ። ግን ፤ ሀይለማርያም በተከሳሹ ወንድም ተገድሏል ። ገዳዩም ወዲያውኑ በገዛ እጁ ህይወቱን አሳልፎአል ። በምን ምክንያት ? ምን ለመደበቅ ? ወይም ምን እንዳይገለጽ ለማድረግ? ይህ ሁሉ አጋጣሚ ሊሆን አይችልም …

«አጋጣሚ ነው ለማለት ካልቻልን ፤ አስቀድሞ የታሰበበት ፤ በወስላታነት ፤ በቂመኛነትና በግፍ የተፈጸመ ወንጀል መሆን አለበት ። ስለዚህ የተከበረውን ፍርድ ቤት የምጠይቀው በአንቀጽ ፭፻፳፪ ፤ ንኡስ ቁጥር ፩ (ሀ) መሰረት የጥፋተኛነት ውሳኔ እንዲሰጠኝ ነው ።»

ተሰፋዬ የፍርድ ሀሳቡን ለመስጠት ጊዜ አልወሰደበትም። ፊቱ ላይ የመገረም ሁኔታ ይታይ ነበር ። ስለታም ፊቱ የሚሸረድድ ፊገግታ ተጐናጽፎአል ። ቦታ የጠበባት ቀጭን

ራዙ ፤ ከቀኝ አይኑ ተወርውሮ ወደ ግራ ከንፈሩ የሚሄደውን አፍንጫውን ለመንካት ምንም አልቀራትም ።

«ሕቃቤ ህግ ፤ ደንበኛዬ ከስህተት የደረሰበትን ምክንያት ፤ በተለይም የስህተቱንና የነገሩን አካባቢ ሁኔታ በቅጡ ባይመረምሩ ፤ የማይሆንና አግባብ የሌለው የፈጠራ ጥርጣሬ በማምጣት ፤ በአንቀጽ ፭፻፳፱ ፤ ንኡስ ቁጥር ፩ (ሀ) መሰረት ውሳኔ እንዲሰጥ መጠየቃቸው ህጋዊ መንገድ አይደለም ። ተከሳሹ በትንክል ሳይሆን ወንጀሉን ሊፈጽም የቻለው በመሳሳት በሚት ፤ ባጋጣሚ ምክንያት መሆኑን የመከላከያ ምስክሮቼ አስረድተዋል ። አጋጣሚና አስገዳጅነት ያለው ፤ መንፈስን የሚሰውጥ ስሜት ለመሆኑ ለማንም ግልጽ ነው ። ከዚህም ሌላ ፤ መጀመሪያ ሄዶ በር ሲደበድብ ምንም መሳሪያ እንዳልነበረው ለማወቅ አያስቸግርም ። ከውስጥ ጥይት ከተተኮሰ በኋላ ወደ መኪናው ሮጦ የተመለሰው የመኪናውን በር ለመዝጋት ወይም ፍሬን ለመያዝ ሳይሆን ፤ መሳሪያ ለማምጣት እንደሆነ ግልጽ ነው ። ሽጉጢ በጣም አነስተኛ በመሆኗ ላትታይ ትችላለች ። በተጨማሪ ፤ የተከሳሹን የሰአሊነት ችሎታ የሚጠራጠር ካለ ችሎታውን ለፍርድ ቤቱ ለማሳየት ዝግጁ ነኝ ። ለማንኛውም ነገር ተከሳሹ በስህተትና ባጋጣሚ ምክንያት በፈጸመው ወንጀል ተጸጽቶ እጁን ለፍርድ ባለስልጣን መስጠቱ ይታወሳል ። የተከበረው ፍርድ ቤት ይህን ሁሉ ተመልክቶ ተከሳሹን በነጻ እንዲለቀው እመለከታለሁ ።»

ሌላ ዝምታ ችሎቱ ላይ ወደቀ ። ከፍሉ ውስጥ ያለው ክሩቅ እንደአባት ወላፈን የሰው ጉንጭ የሚልሰው አየር እንኳን እንደመቀዝቀዝ አለ ። የአበራ ነፍስ እንደገና

የሙጢኝ ብትል ተሰማው ። የሚሰማው ትዝታዉ ይሁን ሙቀት ለይቶ ለማወቅ አልቻለም ። ያለስሜትና ያለሀሳብ እንደድጥኝ ደንገጊያ ፈዝዞ ቀረ ። የአንጐሉ አንዱ ክፍል ብቻ ሉሊት! ሉሲት! እያለ ይጮሀል ።

የመሀል ዳኛው ተነስተው ቆሙ ። ከህይወት በላይ ግዙፍ መስለው ታዩት ። የአበራ ልብ እንደመቆም አለ ። የዳኛው ከንፈሮች በሚያደርጉት እያንዳንዷ ንቅናቄ ነበር የልቡ ትርታ የተመጠነው ። ዝግ ፤ በጣም ዝግ ያለ ድምጽ ነው ።

«ተከሳሹ ሟቿን ወይዘሮ አለምነሽ ጓዴን ለመግደሉ አምኗል ። በተጨማሪም ተመስክሮበታል ። ያገዳደሉን ሁኔታ ከመዝገቡ ስንመረምር ተከሳሽ ሟቿን ሚስቴ ከሴላ ወንድ ጋር በመባለግ ላይ ነች በሚል መሳሳት በተነሳ ስሜት ተገፋፍቶ የገደላት ለመሆኑ ተገንዝበናል ። ይህም በወንጀለኛ መቅጫ ህግ በቁጥር ፭፻፭ (፩) መሰረት ፤ ተከሳሽ ፤ አድራጎቱ ሊያስከትል የሚችለውን እርግጠኛ ነገር በተሳሳተ መንገድ በመገመት ስሜት ተነሳስቶ ወንጀል መስራቱን ያስረዳል ። ስለዚህ ተከሳሽ ከፍ ባለ ደም በሚያፈላ ምክንያት በስሜት የተነሳ ሟቿን ስለገደለ በወንጀለኛ መቅጫ ህግ በቁጥር ፭፻፳፬ (ለ) መሰረት በሶስት አመት እስራት እንዲቀጣ ፈርደናል ።»

የአበራ ነፍስ የሙጢኝ ብላ ከተደበቀችበት ማህደር ወጥታ በደስታ መፈንደቅ ጀመረች ። ንግግሩን ጨርሶ ጭብጨባ እንደሚጠብቅ ሰው ፤ ተሰፋፍ ወዲህና ወዲያ እያማተረ ችሎቱን ከአፍ እስከገደፉ የሞሉትን ሰዎች ይመለከት

ጀመር ። አበራ ሶስቱን አመታት እንዴት ለማሳለፍ እንደ
ሚችል ከማሰብ አልቦዘነም ። በዝምታ ፤ ሉሲት! ሉሲት!
እያለ መጮሁንም አልተወም ።

ወዲያውኑ ፤ ገድሉ በዛብህ በፖሊሶች ታጅቦ ገባ ። አበራ
ተከሳሾች የሚቆሙበትን ሳጥን ለቀቀለት ። የቀረበበት ክስ ፤
«ገድሉ በዛብህ ማህይም የሆኑትን አረጋዊ ሚስቱን ያለ
ኛን ቋሚና ተንቀሳቃሽ ሀብት ሁሉ በቁሜም ሆነ ከሞትኩም
በኋላ አውርሼሻለሁ የሚል ጽሁፍ በማጭበርበር ካስፈረ
ማቸው በኋላ ፤ መርዝ አጠጥቷቸው ሊገድላቸው ሲል መያዙ
ስለተረጋገጠበት በአጭበርባሪነትና በነፍስ መግደል ሙከራ
ለፍርድ ቀርቧል ፡» የሚል ነበር ።

አበራ ከተከሳሽ ሳጥን ሲወርድና ገድሉ በእግሩ ተተ
ክቶ ወደ ተከሳሽ ሳጥን ሲገባ ፤ ሳንዳፍታ ፤ እንዲያው ሳንዳፍታ
ተያዩ ። አንዱ የሌላውን አእምሮ ዘልቆ ለማየት ያህል
የሁለቱም አይኖች እንደጦር ተወረወሩ ። መሀል መንገድ
ላይ ተጋጩ ። ያንዱ አይን ሌላው ላይ ነጠረ — እንደመ
ብረቅ ኳስ ። እና... ከዚያ ግጭት በወጣው ብልጭታ ውስጥ
ሁለቱም ሉሲትን አዩዋት ።

## ፳

ከቀጠሮ ቤት ወደ ፍርደኞች መኝታ ቤት ተዛወረ ። እንደበፊቱ የቦታ ጥበት አላጋጠመውም ። በመኝታ ቤቱ አዳራሽ ከሚገኙት ቆጦች ውስጥ አንዱ ተሰጠው ። እዚ ህም ሆነ እዚያ የእስረኞቹ መንፈስ ምንም ያህል ልዩነት የለውም ። የሚወራው ስለብጥብጥና ሁከት ነው ። ልዩነት ቢኖር ቀጠሮ ቤት ከነበሩት እስረኞች ይበልጥ ፍርደኞቹ ስለቤትና ስለብቸኝነት ያለማቋረጥ ማውራታቸው ነው ።

በእስር ቤት የሚሰማው ብቸኝነት አበራን ደነቀው ። ዘመድና ወዳጅን ፤ በተለይ እንደልብ ከቦታ ቦታ የመዘዋወ ርን ነጻነት በሚያስብበት ጊዜ ፤ ብቸኝነት ልቡ ውስጥ ገብቶ ውርጭ ላይ እንዳደረ ብረት ይቀዘቅዘዋል ። በሌላ በኩል ደግሞ በወህኒ ቤቱ ውስጥ ከእስረኞች ብዛት የተነሳ ፋንዳ ፍታ እንኳን ብቻ የመሆን እድል ስለማይገኝ ሰው መሆንና ሰው ማየት እስኪያንገፈግፍውና እስኪያንገሸግሸው ድረስ እስጠልቶት ያሰቃየዋል ። እርስ በእርስ ከመጋፋት ሌላ ምርጫ የለም ።

ስለቤት ጉዳይ ሲያስብ አንድ ያጋጠመው ነገር ትዝ አለው ። ጢት በማለዳ ነበር ። እስረኞቹ ውጭ ወጥተው ጸሀይ ይሞቁ ነበር ። ወንዶቹ ከሚያድሩበት በረት በስተግራ

በኩል ከሚገኘው ሌላ ጉሮኖ የቤት እስረኞችም እንዲሁ ወጥተው ነበር ። ሴቶቹም ወንዶቹም ከሚለያያቸው የሽቦ አጥር ላይ ተንጠልጥለው ሩቅ ለሩቅ አይኖቻቸው እስኪፈዙ ድረስ መተያየት ላይ ሳሉ ፤ በሁለት የወንድ እስረኞች መካከል ግብ ግብ ተነሳ ። ሌሎች እስረኞች በግድ ባይገላግሏቸው ኖሮ ተያይዘው በሞቱ ነበር ።

ጠቡ ከበረደ በኋላ አበራ ወደ አንዱ እስረኛ ጠጋ ብሎ ፤ «ለምንድንነው የተጣሉት?» ሲል ጠየቀው ።

«የአይን ቁራኛውን ስላየበት ነው ።»

ነገሩ ውስጡ ድረስ ዘልቆ አንቀጠቀጠው ። ሆኖም ስለ ሉሊት ማሰቡን አልተወም ። ወደ ጽህፈት ቤቱ ተጠርቶ ሲሄድ ሁሉ ስለሉሊት ያስብ ነበር ። አይኑን ለማመን አልቻለም ። ሉሊት ነበረች ያስጠራችው ። አይኑ እሷ ላይ ስለተተከለ አልፍንሸንና ተስፋዬን ዞር ብሎ እንኳን አላያቸውም ። ብቻቸውን እንዲሆኑ በማለት ሁለቱም ትተዋቸው ወጡ ። የሚያደርገው ጠፋው ። እሷ ግን ሮጣ ተጠመጠመችበት ።

ለረጅም ጊዜ እንደተቃቀፉ ከቆዩ በኋላ ፤ «በሌላ ሴት የለወጥከኝ መስሎኝ ነበር ፤ እምነት እየጣልኩብህ በምሄድበት ጊዜ ፤ በቤት ላይ ተጋደለ የሚል ወሬ ስለሰማሁ ግራ ገባኝ ።» አለችው ።

«ነገሩ ሳይገባሽ ቀርቶ ይቅርታ ሳታደርጊልኝ ብሞት ነፍሴ የሰላም እረፍት አይኖራትም ነበር ። ከእንግዲህ ምን ይቀረኛል?»

«ሊገባኝ አልቻለም እንጂ ህይለማርያም ሊያስረዳኝ ሞክሮ ነበር ። አላመንኩትም ። ሳላምነው ህይወቴ ብግለኝ ሀዘኑ

ከልቤ ሰዘሑአለም አይወጣም ፣ የምተው ለኛ ሲል ነው ።»

«አውቃለሁ ፣ ለኛ ሲል ነው—እንደክርስቶስ ። እንዴት ነበር አሟሟቱ?»

«ለምን እንደሆነ እንጃ ፣ ወንድምህ አዲሷ ቤት ድረስ ሲገሰግሱ መጡ ። እንደሚመስለኝ አመጣጣቸው ሰኔ ነበር ። ያን ቀን እኔና ሀይለማርያም አብረን እንደነበርን አውቀዋል ። ሲያዩት ደማቸው ተለወጠ ። 'አንተ ጋኔን !' አሉት ። ሲያ ስረዳቸው ሞከረ ። 'አጥፊዬ አንተ መሆንክን ድሮውን አውቄ ነበር !' ብለው ሽጉጣቸውን ሲመዙ እሮጬ ጠጣሁ… በጀርባው ተንጋሎ ወደጣራ እያየ ፣ የሚያምነኝ ሰው አጣሁ ሲል ትዝ ይለኛል…»

እንደገና ሁለቱንም ረጅም ዝምታ ዋጣቸው ። የመረረ እንባ በዝምታ ሁለቱም አነቡ ። ከዚያ በኋላ ፣ «ይቅርታ ካደረግሽልኝ ዘንድ የምልሽን ስሚኝ …እኔ እስር ቤት ሆኜ አንቺ ውጭ ሆነሽ …እንዴት ልበልሽ? …እምን ፣ አብረን ሳለን በቅናት ተሰቃይቼ የማሰቃይሽ ሰው አሁን ምን ይሰማኛል ? ለሆነው ሁሉ እወድሻለሁ ። ጸጸት የለኝም ። ግን ነጻነት ልሰጥሽ እፈልጋለሁ…»

«ለምን አበርዬ ? ለሶስት አመት ይቅርና እስከ አለም ፍጻሜም ድረስ ቢሆን እጠብቅሀለሁ …»

«አውቃለሁ ። ግን ፣ ተሰቃይቼ ባሰቃይሽ አልፈልግም ። የወህኒ ቤት ኑሮ ሰዉን ምን ያህል እንደሚለውጥ ባስረዳሽ አልችልም ። በከፉ ቅዥት አለም ውስጥ ስለምንኖር ሰው ጭው ያለ እንጓጓለን ። ጉጉቱ ስለማይሟላና ሩቅ ስለሚሆነብን ያስቀናናል ። ከጊዜ በኋላ ስሜቱ በሽታ ይሆናል ።

እና ተመልሰን እንደቀድሞአችን ለመሆን አንችልም ። በንጹህ መንፈስና በቅን ልቦና አሁኑኑ ብንለያይ ይሻላል ።» «እጠብቅሀለሁ ። አንተ የሌለህበት ህይወት ጣእም አይሰጠኝም ። አንተን በታማኝነት በመጠበቅ ያለፈውን ጥፋቴን ሁሉ እግዜር ይቅር እንዲለኝ እድል ስጠኝ ። አንተም ሳትለወጥ ትወጣለህ ብዬ አይደለም ። ማንነቱን ያወቀ ሰው ሆነህ እንደምትወጣ ተስፋ አለኝ ። ይልቅ የተወለድክበትን ቀን ምክንያት በማድረግ የገዛሁልህን ስጦታ ተቀበለኝ ።»

አሻቅቦ ጣራውን ተመለከተ ። አቀርቅሮ የማማውን ጫፍ እንደ አዲስ ፍጡር አየው ። ቀና ሲል ፊትለፊት አይን ለአይን ተጋጩ ። እሱ ከታሰረ በኋላ ገደሉ በዛብህን አነጋግራው እንደሆን ሊጠይቃት ቃጣውና ፤ ብጠይቃት ምን ያደርጋል ? አንድ አይነት ተስፋ ባትሰጠው መቼ እንደዚህ ያለውን እርምጃ ይወስድ ነበር ? በማለት ጥያቄውን መልሶ ዋጠው ። ቢሆንም የተናገረችው ሁሉ ከልቧ መሆኑ ቢሰማውም የወደፊት እድላቸው ያልተጣመረ መስሎ ስለታየው ፤ «ሉሉዬ አትቀየሚኝ ፤ እኔም ሆንኩ አንቺ አዲስ ህይወት ፤ አዲስ ተስፋ መሻት አለብን ። አዲስ ህይወት መቀበል የጀግኖች ሙያ ነው ። ሸክም ልሆንብሽ አልፈልግም ። ደህና ሁኚ ፤» አላትና ፊቱን አዞረ...

የያዘችውን ስጦታ በቀስታ ቁጭ አድርጋ እንባዋን እያረገፈች ወደ በሩ ስትራመድ ፤ አላስችለው ብሎት ወደኋ ዞሮ በአይን ሊሸኛት ፈለገ ። ዞር ሲል የለችም ። «ይቅናሽ የኔ ጠይም ጣኦት ።» ሲል ባዶው ክፍል ድምጹን ወስዶ አስተጋባ ።

፮

ወደ ወሀኒ ቤት የተመለሰው የዱሮው አበራ ሳይሆን ሌላ ከወሀኒ ቤቱ አድማስ ባሻገር የሚመለከት አበራ ነው ። ምክንያቱም ፣ አዲስ ህይወትና የመኖር አላማ ይዞ ነበር የተመለሰው ። ሉሲት ያመጣችለትን የስእል መሳሪያ ዎች ስጦታ ከፍቶ እጁ እየተንቀጠቀጠ አንድ ባንድ ተመ ለከታቸው ።

መሳሪያዎቹን ይዞ ወደ ውጭ ወጣ ። አሁን ፣ አድማሱ የተወሰነ ነው ። በየኪያ ተመድበው በየቦታው ስራ ላይ የሚገኙት እስረኞች ህልም ወይም በህልም አለም ውስጥ ያሉ መስለው ታዩት ።

በአካል እዚያ ናቸው ። በሀሳብ ግን ከተወሰነው አድ ማስ አልፈው ሄደዋል ። ከውጭው አለም በወል ያላቸው ነገር ቢኖር የፍም አሎሎ መሰላ ከአድማስ መከዳ ላይ የተ ኛችው ጸሀይ ብቻ ነች ።

እስረኞቹ የሚሰሩት ስራ ምንም ጠብ የሚል ነገር የለውም ። ምክንያቱም ፣ የሚቆፍሩት መሬት ማህጸኗን ነፍጋ ቸው ፣ እነሱም ህይላቸውንና ልባቸውን ስላልሰጧት ነው ። እሷ የነርሱ ፣ እነርሱ የሷ አካል አይደሉም ። ሁኔታው ሁሉ እንደህልም ነው ። ከህልም አለም ውጭ ሆና

በእውን የሚታየው ፤ አካባቢውን የሚማነው የወህኒ ቤቱ ሰገነት ብቻ ነው ።

የህይለማርያም ድምጽ ፤ ዐለኔ ስትል በርታ ፤ ስራህ ለወንድምህ ዝርያ ፤ ለኔ ሀውልት ይሁን ፤» አለው ፤ ከአድማስ ባሻገር መጥቶ ። ከፊት ለፊቱ በስሌዳ ላይ ተወጥሮ የነበረው ባዶ ነጭ ሸራ ህይወት አርግዞ ነፍስ ይዘራ ዘንድ ሙሉ ህይሉን ፤ ስሜቱንና ሀሳቡን አሳርፎበት ይጉተጉተው ጀመር... ጸሀዩም ጠልቃ ቀኑ እስኪመሸም ድረስ ። 'ነገም ሌላ ቀን ነው...'